www.abyssinialaw.com

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት
# የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራተጅዎቻችን

## በማስኖወቂያ ሚኒሰቴር የፕሬስና ኦዲዮቪዥዋል መምሪያ

ኅዳር 1994 ዓ.ም.
አዲስ አበባ


ማስኖወቂያ ሚኒስቴር

www.abyssinialaw.com

# ማ ው ጫ

## ክፍል አንድ

መቅድም ....................................................................1
መግቢያ ....................................................................8

1. ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ልማት ፈጣን እድገት ለማረጋገጥ ያስችላል..........................................................10
2. ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገ ልማት ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ እንዲጠቀም ያደርጋል ......... 16
3. ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ልማት አገራችንን ከተመፅዋችነት ማዳን ያስችላል:: ..............23
4. ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ልማት በአገራችን የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መፍጠር ያስችላል:: .......27

## ክፍል ሁለት

## የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራተጅዎቻችን

1. የግብርና ልማት መሰረታዊ አቅጣጫዎች .......30
1.1. የሰው ጉልበትን በሰፊው የመጠቀም አቅጣጫ ..30
1.2. የእርሻ መሬታችንን በአግባቡ የመጠቀም አቅጣጫ ...........................................................33
1.3. አንድ እግር በመሬት ......................................35
1.4. ከተለያዩ የአግሮ-ኢኮሎጂ ዞኖች ጋር የተጣጣመ አቅጣጫ ...........................................37
1.5. የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ .............................38



2. የሰው ሃይላችንን ብቃት ማጎልበትና በሰፊው መጠቀም .................................................40
2.1. ታታሪነትና የስራ ዝግጁነትን ማረጋገጥ ....... 40
2.2. የግብርና ሙያ ብቃትን ማሻሻል .......................45
2.3. የአርሶ አደሩን ጤንነት ማረጋገጥ ....................50
2.4. የቴክኖሎጅ አቅርቦት፣ ብዜትና ስርጭትን ማሻሻል ...........................................................61
3. መሬትን በአግባቡ መጠቀም ................... 72
3.1. በሕገ መንግሥቱ ላይ የሠፈረውን የመሬት ይዞና ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ.......................72
3.2. የተስተካከለ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ መከተል ........................................96
3.3. የውሃ አጠቃቀማችንን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል ................................................100
4. ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የልማት ፖኬጅ ማዘጋጀት ..........................110
4.1. ዳይቨርሲፊኬሽንና ስፔሻላይዜሽንን ማጣመር ... 111
4.2. በድርቅ አካባቢዎች የሚሰራ ስራ .................... 117
(ሀ) ሰፈራን እንደመፍትሄው አካል መውሰድ ..........121
(ለ) የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና የእንስሳት ሃብት ልማት ..............................128
(ሐ) የውሃ ሃብት አጠቃቀምን ማሻሻል ............. 133
4.3. በቂ ዝናብ ባላቸው የአርሶ አደር አካባቢዎች የሚሰራ ስራ .................................................137
4.4. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚሰራ ስራ ............. 141
4.5. ያልታረሰ ሰፊ መሬት ባላቸው አካባቢዎች የሚሰራ ስራ ...................................................151

www.abyssinialaw.com

5. በገበያ የሚመራ የግብርና ልማት እንዲኖር ማድረግ ....................................155
5.1. በገበያ ያልተመራ የግብርና ልማት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ሊሆን አይችልም......................155
5.2. በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን የሚያመርት የግብርና ዘርፍ መገንባት አለብን .....................159
5.3. የግብርና የግብይት ስርአትን በቀጣይነት ማሻሻል ........................................................166
(ሀ) የደረጃ ምደባ ስርአት መፍጠር .......................166
(ለ) የገበያ መረጃ አቅርቦትን ማሻሻል ...................171
(ሐ) የህብረት ስራ ማህበራትን ማስፋፋት፣ ማጠናከር ........................................................175
(መ) የግል ባለሃብቶች በግብርና ግብይት ስርአት ያላቸውን ተሳትፎ ማሻሻልና ማጠናከር .................184
6. የገጠር የፋይናንስ ስርአትን ማሻሻል .............189
6.1. ባንኮችና የገጠር የፋይናንስ ስርአት ............... 192
6.2. የገጠር ባንኮች ............................................... 198
6.3. የህብረት ስራ ማህበራት ................................ 202
7. የግል ባለሃብቶች በግብርና ልማት ዘርፍ በሰፊው እንዲሳተፉ ማበረታታት .............................204
7.1. የውጭ ኢንቨስተሮችን ወደ ግብርና ዘርፍ መሳብ .................................206
7.2. የግብርና ሙያ ስልጠናና የግል ባለሃብቶች ተሳትፎ ....................................209
7.3. የግል ባለሃብቶችና የአርሶ አደሩ የግብርና ምርት ትስስር ............................................213
8. የገጠር መሰረተ-ልማትን ማስፋፋት ............218
8.1. የትምህርትና የጤና ጥበቃ አገልግሎትን ማስፋፋት ..........................................................219
8.2. የገጠር መንገድና ትራንስፖርት አገልግሎትን ማጠናከር ...............................222
8.3. የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻል ................ 227
8.4. ሌሎች የመሰረተ-ልማት አገልግሎቶችን ደረጃ በደረጃ ማስፋፋት ................................231
9. ከግብርና ውጭ ያሉ የገጠር ልማት እንቅስቃሴዎችን ማጠናከር .......................236
9.1. ከግብርና ውጪ የሚኖር ልማት አስፈላጊነት...237
9.2. የግብርና ልማት የሚፈጥረውን እድል አሟጦ መጠቀም ...........................................240
9.3. የገጠርና ከተሞች ትስስርን ማጠናከር ............242

## ክፍል ሶስት
## የገጠር ልማት አመራር

1. የህዝብ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎና የገጠር ልማት ....244
1.1. የህዝብ ተሳትፎ አስፈላጊነት .......................... 244
1.2. የህዝብን የተሳትፎ መድረኮች በአግባቡ መጠቀም .........................................265
2. ቁልፍ የገጠር ልማት ተቋሞችን ማጠናከርና በአግባቡ መጠቀም ..........................................270
3. በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላትን ሚና መለየት ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ.............272
4. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚኖር አመራር ...........279

www.abyssinialaw.com

## መቅድም፣

አገራችን በዝቅተኛ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የእድገት ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ኢኮኖሚያችን የተመሰረተው በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ፣ ለዚያውም ከእጅ ወደአፍ በሆነ ኋላቀር አመራረት ነው፡፡ ለዘመናት በቆየ መዋቅራዊ ችግር የተተበተበው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ለሌሎች ክፍላተ ኢኮኖሚዎቻችን እድገት መፋጠን መነሻ ሊሆን የሚችል ሀብት የሚፈጠርበት ሆኖ አልቆየም፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ መድረሱ ቀርቶ የህዝባችንን የምግብ ፍላጎት ለማርካት የሚያስችል ምርት የሚታፈስበት ደረጃ ላይ መድረስም ተስኖት ኖሯል፡፡

ለአጠቃላዩ ኢኮኖሚያችንም ሆነ ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ በመዋቅራዊ ችግር መተብተብ መሰረታዊ ምክንያቱ ለዘመናት የተስተካከለ የልማት ፖሊሲ፣ ስትራተጅና ስልት ሳይኖረን መኳዛችን ነው፡፡ ቀደምት መንግስታት አንድም የተስተካከለ የልማት ፖሊሲ ባለመንደፍ አሊያም ደግሞ እድገትን ከማፋጠን ይልቅ የማደናቀፍ ሚና የሚጫወቱ የተሳሳቱ ፖሊሲዎችን ቀይሶ በስራ ላይ በማዋል ኢኮኖሚያችንን ለመሰረታዊ መዋቅራዊ ችግር አጋልጠውት ቆይተዋል፡፡ ትክክለኛ የልማት ፖሊሲዎች ባልተነደፉበት ሁኔታ የአገራችን ልማት ፈጣን እድገት ሊያሳይም ሆነ ህዝቡ የሚጠቀምበት ሁኔታ ሊፈጠር አይችልም፡፡ በመሆኑም በምግብ እህል እንኳ ራሳችንን መቻል አቅቶን በየአመቱ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ወገኖቻችን የምግብ ርዳታ ለመጠየቅ ተገደን ቆይተናል፡፡



ይህን ከመሰለው መሰረታዊ ችግር ለመላቀቅ የሚቻለው አገራችን የምትመራበት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ልማትን ለማፋጠንና ከዚህም የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ በአለም አቀፉ የስራ ክፍፍል ውስጥ እያደር የሚጎለብት ነፃነት ያለው የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል ሲሆን ነው፡፡ ፖሊሲው፣ ስትራተጅውና ስልቱ በተመጋጋቢነት እነዚህን መሰረታዊ አላማዎች ሊያሳኩ የሚችሉ ሆነው ከተነደፉ በርግጥም ፈጣንና ህዝባችን የሚጠቀምበት የዳበረ የነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ስርአት መገንባት ይችላል፡፡ ይህም ሆኖ የኢኮኖሚ ልማትን ለማፋጠን ትክክለኛ ፖሊሊዎች፣ ስትራተጅና ስልቶች መንደፍ ብቻ በቂ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ፈጣን እድገት ያመጡና ከዚህም ህዝባቸውን ተጠቃሚ ያደረጉ የምስራቅ እስያ አገሮችን የእድገት ርምጃ ስንመለከት የምንገነዘበው መሰረታዊ ጉዳይ ትክክለኛ ፖሊሲ ስትራተጅና ስልት መንደፍ የመጀመሪያው ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ በተነደፉት ትክክለኛ አቅጣጫዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ መያዝና ለተግባራዊነቱ በሰፊው መነሳሳት ደግሞ ለፈጣን እድገት ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ከዚህ መሰረታዊ ግንዛቤ በመነሳት አገራችን የምትመራበትን ትክክለኛ የኢኮኖሚ ፕሮግራም ነድፏል፡፡ ይህን ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መሰረታዊ ስትራተጅዎችና ስልቶችንም ቀይሷል፡፡ የኢኮኖሚ ልማታችንን ለማፋጠን እያንዳንዱ ሴክተር በየደረጃው የሚጫወተውን ሚና በትክክል ለይቶ ሁሉም ሴክተሮች ትክክለኛና ተደጋጋፊ አቅጣጫዎች ይዘው እንዲኳዙ ለማድረግም ሲረባረብ ቆይቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

እነሆ አሁን ደግሞ ባለፉት አስር አመታት የኢኮኖሚ ልማታችንን ለማፋጠን ከተከተልናቸው ፖሊሲዎችና በተግባር ካገኘናቸው ልምዶች በመነሳት፣ እንዲሁም ለፈጣን ልማት የበቁ አገሮችን ተመክሮ በማገናዘብ ለአጠቃላዩ የኢኮኖሚ እድገታችን ወሳኝ የሆነውን የገጠርና የግብርና ልማት የሚመራበት ፖሊሲ፣ ስትራተጅና ስልቶች ቀምሯል:: እነዚህን መሰረታዊ አቅጣጫዎች በተግባር ለመተርጎምም ተዘጋጅቷል::

በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲያችን በተለይ ደግሞ የገጠርና የግብርና ልማት ፖሊሲያችን በተግባር ላይ ሊውል የሚችለው መላው ህብረተሰብና በየደረጃው የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በዝርዝር ተገንዝበውት ከተጨባጭ ልምዶቻቸው እየተነሱ ሲያዳብሩትና ለተግባራዊነቱ ሲረባረቡ ነው:: በመሆኑም መንግስት ያዘጋጀው የገጠር ልማት ፖሊሲ፣ ስትራተጅና ስልቶቻችን የተቀመሩበት ይህ ፅሁፍ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት አካላት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በሲቪል አደረጃጀቶችና በአጠቃላይ በመላው ህብረተሰብ ዘንድ ውይይት ሊካሂድበትና የጋራ ግንዛቤ ተይዞ ሰፊ ርብርብ ሊካሄድበት ይገባል:: በሚካሄደው ውይይት ላይ የሚቀርቡ ገንቢና ልማታችንን የሚያፋጥኑ ሃሳቦች ይህን መሰረታዊ ሰነድ ይበልጥ እንደሚያዳብሩት ይታመንበታል:: በመሆኑም የአገራችን የልማት ጥያቄ የሚያሳስባቸው ወገኖች ሁሉ ፖሊሲ፣ ስትራተጅና ስልቶቹን በውይይት ለማዳበርና በተግባር ላይ ለማዋል የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚገባቸው ለማሳሰብ እንወዳለን::



# ክፍል አንድ

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የገጠር ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራጂዎችና ስልቶች፣

www.abyssinialaw.com

## መግቢያ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የኢኮኖሚ ልማትን በተመለከተ አንድ መሰረታዊ አላማ አስቀምጧል፡፡ ይህም ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት፣ አገራችንን ከተመፅዋችነት የሚያላቅቅ ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት በማረጋገጥ በአገራችን የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርአት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ ይህ መሰረታዊ አላማ አራት ገፅታዎች ያሉት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥን በመሰረታዊ አላማነትና መነሻነት የያዘ ነው፡፡ የዚህ ኢኮኖሚያዊ አላማ ሁለተኛው ገፅታ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ከማረጋገጥ በሻገር ህዝቡ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ እውን ለማድረግ ማስቻል ነው፡፡ ሶስተኛው ኢኮኖሚያዊ አላማ አገራችንን ከተመፅዋችነት ማላቀቅና በአለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ውስጥ ደረጃዋ በቀጣይነት እየተሻሻለ እንዲሄድ ማድረግ ነው፡፡ በአራተኛ ደረጃ ደግሞ ከላይ የተጠቀሰው ባህሪ ያለው ፈጣን እድገት በአገራችን የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚን በመገንባት እውን እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

ይህን መሰረታዊ የኢኮኖሚያዊ ልማት አላማ ተግባራዊ ለማድረግ የተሟላ የገጠር ልማት ራዕይና ይህንኑ የማስፈፀም እንቅስቃሴ መኖር ይኖርበታል፡፡ በገጠር በአሁኑ ሰአት የሚካሄደውና መካሄድም የሚገባው የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴ በዋነኛነት የግብርና ልማት እንቅስቃሴ ነው፡፡ ይሁንና በገጠር ከግብርና ስራ ውጪ ሌላ የልማት እንቅስቃሴ አይኖርም ማለት አይደለም፡፡ ራሱን የግብርና እንቅስቃሴውን ለማሳካት ሰፊ



የመሰረተ-ልማትና የማህበራዊ ልማት እንቅስቃሴ መካሄድ አለበት፡፡ በግብርና ልማት ላይ ተመስርቶ ሰፊ የንግድና የኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴም ሊካሄድ ይችላል፣ ይገባልም፡፡ በመሆኑም የገጠር ልማት ስራ ማእከሉን ግብርና ያደረገ ነገር ግን በግብርና ስራ ላይ ብቻ ያልታጠረ የልማት እንቅስቃሴ መሆን ይገባዋል፡፡

ማዕከሉን ግብርና ያደረገ የገጠር ልማት እንቅስቃሴ፣ የነደፍነውን የኢኮኖሚ ልማት መሰረታዊ አላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አንድ የስራ መስክ ነው፡፡ መሰረታዊ የኢኮኖሚ ልማት አላማችንን ተግባራዊ ለማድረግ በሌሎች የስራ መስኮችም ከፍተኛ ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ ይሁንና የገጠር ልማት ስራችን አንድ የልማት ስራችን መስክ ነው ተብሎ ብቻ የሚታለፍ አይደለም፡፡ የኢኮኖሚ ልማት መሰረታዊ አላማችንን ለማሳካት የሚያስችለን ዋነኛ መሳርያ እንደሆነም ሊሰመርበት ይገባል፡፡ የምንከተለው የልማት አቅጣጫ ማዕከሉን ግብርናና ገጠር ያደረገ ነው፣ ግብርና-መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጅ ነው ወዘተ. እየተባለ የሚገለፀውም ገጠርና ግብርናን ማዕከል ያደረገ የልማት እንቅስቃሴ የልማት አላማችን ዋነኛ ማስፈፀሚያ መሳሪያና የልማት እንቅስቃሴያችን መሪ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው፡፡ ግብርናን ማዕከል ያደረገ የገጠር ልማት ስትራተጅ ዋነኛ የልማት አቅጣጫችን የሚሆነው መሰረታዊ የኢኮኖሚ ልማት አላማችን የሆኑትንና የሚከተሉትን አራት ጉዳዮች በተሟላ አኳኋን ለማስፈፀም የሚያስችለን የላቀ አቅጣጫ በመሆኑ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

# ክፍል አንድ

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የገጠር ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራተጅዎችና ስልቶች፣

### 1. ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ልማት ፈጣን እድገት ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

የመሰረታዊ የኢኮኖሚ አላማችን አንዱ ገፅታና ለስኬታማነቱም መሰረት የሚሆነው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትን ማረጋገጥ ነው፡፡ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ ሲባል የሚቆራረጥና ተከታታይነት የሌለው እድገት ማለት አይደለም፡፡ ተከታታይነት የሌለው ፈጣን እድገት ከረጅምና መካከለኛ ጊዜ አኳያ ሲታይ ፈጣን እድገት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም ያስቀመጥነውን መሰረታዊ የኢኮኖሚያዊ ልማት አላማ ለማሳካት ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ቀጣይነት ያለው ፈጣን እድገት ሊያረጋግጥልን የሚያስችለንን ዋነኛ መንገድ ለይቶ ማስቀመጥና ይህንኑ በጥብቅና በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል፡፡

ማንኛውንም አይነት የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴ ለማካሄድ ካፒታል፣ ሰራተኛ የሰው ሃይል፣ መሬትና እነዚህን ይበልጥ ውጤታማ በሆነ አኳኋን አቀናጅቶ ሊያንቀሳቅስ የሚችል አመራር ያስፈልጋል፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለልማት



ከሚያስፈልገው ካፒታል አኳያ ከፍተኛ እጥረት ይታያል፡፡ ይህ ከፍተኛ የካፒታል እጥረት በአጭር ጊዜ የሚወገድም አይደለም፡፡ በአንፃሩ ታታሪና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰራተኛ ህዝብና በቂ መሬት አለን፡፡ ፈጣን እድገት ለማረጋገጥ የምንችለው እጥረት የሚታይበትን ካፒታል በቁጠባ፣ በበቂ መጠን አለን የምንለውን የሰው ጉልበትና መሬት ደግሞ በሰፊው የሚጠቀም የልማት አቅጣጫ የተከተልን እንደሆነ ነው፡፡ ካፒታልን በሰፊውና በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀም የልማት አቅጣጫ የተከተልን እንደሆነ ያለንና ሊኖረን የሚችለው ካፒታል ውሱን በመሆኑ፣ በዚህ ላይ የተንጠለጠለ አቅጣጫ የሚያስገኘው እድገትም በዚያው መጠን ውሱን ይሆናል፡፡ የሰው ጉልበትና መሬትን በሰፊው በመጠቀም ላይ ያልተመሰረተ የልማት አቅጣጫ ከተከተልን ከፍተኛ የልማት አስተዋፅኦ ሊኖረው የሚችል የሰውና የመሬት አቅማችን በተሟላ መልኩ ጥቅም ላይ ሳይውል ቀርቶ ልማታችን መሆን በሚችለው ደረጃ ሳይፋጠን ይቀራል፡፡ በመሆኑም በአገራችን ፈጣን እድገትን ለማረጋገጥ የሚቻለው ካፒታልን በከፍተኛ ደረጃ የሚቆጥብ፣ መሬትና ጉልበትን፣ በተለይም ጉልበትን በሰፊውና በላቀ ደረጃ የሚጠቀም የልማት አቅጣጫ የተከተልን እንደሆነ ነው፡፡

ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ በአንድ በኩል ካፒታልን በቁጠባ ለመጠቀም፣ በሌላ በኩል ደግሞ መሬትንና የሰው ጉልበትን በሰፊውና በላቀ ደረጃ የሚጠቀም የልማት ስትራተጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡ ከአገራችን ህዝብ ውስጥ ከ 85% የማያንሰው የሚኖረው በገጠር ነው፡፡ አብዛኛው መሬት ያለውም በገጠር ነው፡፡ ከፍተኛ ካፒታል የማይጠይቀውና ጉልበትንና መሬትን በሰፊውና በላቀ ደረጃ መጠቀም የሚቻለው በግብርና ዘርፍ ህዝቡና መሬቱ ባለበት በገጠር ላይ ያነጣጠረ የልማት ስትራተጅ የተከተልን

www.abyssinialaw.com

እንደሆነ ነው፡፡ የግብርና ስራ፣ በገጠሩ አካባቢ የሚካሄደው የግብርና ልማት እንቅስቃሴ ያለብዙ ካፒታል ጉልበትንና መሬትን በሰፊውና በላቀ ደረጃ መጠቀም የሚቻልበት ዘርፍ ነው፡፡ ባለን የልማት አቅም በላቀ ደረጃ ተጠቅመን፣ የሌለንን በቁጠባ በመጠቀም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥ የሚያስችለን ዘርፍ ነው፡፡

ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራተጅ የግብርናው ዘርፍ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲያረጋግጥ በማድረግ፣ ከአገራችን አጠቃላይ ምርት ከግማሽ በላይ የሆነውን የሚያመርተውን ዘርፍ ፈጣን እድገት እንዲያመጣ በማድረግ ኢኮኖሚያችን በአጠቃላይ በፍጥነትና ቀጣይነት ባለው አኳኋን እንዲያድግ ያደርጋል፡፡ የዚህ የልማት ስትራተጅ ፋይዳ ግን በዚህ ብቻ የታጠረ አይደለም፡፡ ፈጣን የግብርናና የገጠር ልማት ንግድና ኢንዱስትሪም ቀጣይነት ያለው ፈጣን እድገት እንዲያስመዘግቡ የሚያደርግ ነው፡፡ በነዚህ ሁለት መልኮች ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ ግብርና ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይም ኢኮኖሚያችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲያስመዘግብ የሚያደርግ ነው፡፡

ግብርና ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ሲያስመዘግብ በሂደት የካፒታል ክምችታችን እየጎለበተ ስለሚሄድ ከዚሁ በሚገኘው የካፒታል ክምችት ንግድና ኢንዱስትሪ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲያረጋግጡ በር ይከፍትላቸዋል፡፡ ግብርና ፈጣን እድገት ሲያሳይ ለአገር ውስጥ የካፒታል ክምችት መዳበር ከፍተኛ ሚና የሚጫወት አዲስ ሃብት ይፈጥራል፡፡ በከፍተኛ ደረጃ የሚጨምረው



ምርታማነት በአገር ውስጥ የካፒታል ክምችትን ብቻ ሳይሆን ለኤክስፖርት የሚሆኑ ምርቶች በተሻለ ጥራትና መጠን እንዲቀርቡ በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ክምችታችንንም በፍጥነት ያሳድጋል፡፡ ይህም ለኢንዱስትሪያዊ ልማታችን መፋጠን ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ የግብርና ምርታማነት እየተሻሻለ ፈጣን እድገት በሚያረጋግጥበት ወቅት፣ የምግብ ሸቀጦች በሰፊው ለገበያ እንዲቀርቡና ዋጋቸውም ዝቅ እንዲልና በመለስተኛ ደሞዝ በቂ ምግብ አግኝቶ ሊሰራ የሚችል ሰራተኛ እንዲኖር በማድረግ ለንግድና ኢንዱስትሪ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ በተጨማሪም በግብርና እድገት ሂደት ምርታማነት አድጎ በግብርና ስራ ላይ ተፈላጊ ያልሆነ ጉልበት እንዲበረክትና ይህም በንግድና ኢንዱስትሪ መስክ ተቀጥሮ ለነዚህ ዘርፎች ፈጣን እድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርግ ዘንድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

የግብርና ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እውን ሲሆን በኢንዱስትሪ ጥሬ እቃነት ተፈላጊ የሆኑ የግብርና ምርቶች በሚፈለገው ጥራትና መጠን በርካሽ ዋጋ እንዲመረቱ ያደርጋል፡፡ ይህም ለንግድና ኢንዱስትሪ ፈጣን እድገት በር ይከፍታል፡፡ ግብርና ፈጣን እድገት ሲያረጋግጥና የአርሶ አደሩ የኑሮ ሁኔታ በዚሁ መጠን ሲሻሻል አርሶ አደሩ የሚፈልጋቸው የፍጆታ ሸቀጦችና አገልግሎቶች በዚያው መጠን ይጨምራሉ፡፡ ይህም ንግድና ኢንዱስትሪ በጣም ሰፊ የአገር ውስጥ ገበያ አግኝተው ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲያመጡ ያስችላቸዋል፡፡ በግብርና ፈጣን እድገት ሂደት አርሶ አደሩ የሚጠቀምበት የግብርና ቴክኖሎጂ እየተሻሻለ በዚሁ ልክ በግብርና ዘርፍ የሚፈለጉ ግብአቶችና የማምረቻ መሳሪያዎች እየጨመሩ ይሄዳሉ፡፡ ይህም ተጨማሪ ሰፊ የአገር ውስጥ ገበያን በመፍጠር

ለኢንዱስትሪ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት መሰረት ይሆናል፡፡

ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ባለባት አገራችን ያለብዙ ካፒታል የሰው ጉልበትን በሰፊው በሚጠቀመው የግብርና ዘርፍ ላይ በመረባረብ የኢኮኖሚያችን ወሳኝ ክፍል የሆነው ግብርና ፈጣን እድገት እንዲያስመዘግብና በዚሁ መጠን ደግሞ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገታችን እንዲፋጠን ከማድረግ ባሻገር ይኸው እድገት ኢንዱስትሪንና ንግድን መርቶ ፈጣን እድገት እንዲያስመዘግቡ የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ለንግድና ኢንዱስትሪ የሚሆን የካፒታል ክምችትና የሰራተኛ ጉልበት ከማቅረብ ባሻገር ንግድና ኢንዱስትሪ በቂ ጥሬ ዕቃ በተመጣጣኝ ዋጋ አግኝተው፣ ለግብርና የሚሆኑ ግብአቶችና የማምረቻ እቃዎች፣ ኑሮው ለሚሻሻለው አርሶ አደር የሚሆን ሰፊ የፍጆታ እቃዎችና አገልግሎቶች ገበያ ተፈጥሮላቸው የግብርና ልማት እየመራቸው እነሱም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲያረጋግጡ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸዋል፡፡ ሰፊና እርስ በርሱ የሚመጋገብ የአገር ውስጥ ገበያን ለመፍጠር ያስችላል፡፡

በመሆኑም ግብርና መር የልማት ስትራተጅ ነው የሚኖረን ስንል፣ ግብርናን በማሳደግ ወሳኙን የኢኮኖሚያችን ዘርፍ እያሳደግን ነው ማለታችን ብቻ አይደለም፡፡ ንግድና ኢንዱስትሪ ይህን ፈጣን የግብርና እድገት ተከትለውና እሱኑ አጅበው ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲያረጋግጡ የሚያስችላቸው ሁኔታ ይፈጠራል ማለታችን ጭምር እንጂ፡፡ ይልቁንም ገጠርንና ግብርናን ማእከል ያደረገው የልማት ስትራተጅ እጅግ ተፈላጊ የሚሆንበት አንዱ ዋነኛ ምክንያት ለንግድና ኢንዱስትሪ ፈጣን እድገት የተመቻቸ ሁኔታ የሚፈጥር



በመሆኑ ነው፡፡ ይህ የንግድና ኢንዱስትሪ ፈጣን እድገት በበኩሉ ለግብርናው እድገት ቀጣይነት ዋስትና ይሆናል፡፡ በመሆኑም ዘርፎቹ ገና ከመጀመሪያው ተደጋግፈው ማደግ ይኖርባቸዋል፡፡ የግብርና እድገት መሪነቱን ካልያዘና ኢንዱስትሪና ንግድ ከወዲሁ ከዚሁ ጋር ተቀናጅተው የሚያድጉበት አቅጣጫ ካልተቀመጠ የአገራችን ፈጣን እድገት ሊረጋገጥ አይችልም፡፡

የግብርናና የገጠር ልማት በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴያችን ውስጥ የመሪነት ሚናውን ሲይዝ ነው ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ማረጋገጥ የምንችለው ስንል ይህ ስትራተጅ ለዘልአለሙ የሚኖር ነው ማለታችን አይደለም፡፡ በሂደት የካፒታል ክምችታችን እያደገ፣ የኢንዱስትሪ ዘርፋችን እየሰፋና ጥልቀት እያገኘ መሄዱ አይቀርም፡፡ በዚህ ሂደት አንድ ወቅት ላይ ኢንዱስትሪ ወሳኙ የኢኮኖሚ ዘርፍና በልማት እንቅስቃሴያችን ውስጥ የመሪነት ሚና የሚጫወተው ዘርፍ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ኢንዱስትሪ እዚህ ደረጃ ላይ ሊደርስ የሚችለው ከወዲሁ በግብርና ልማት ውጤታችን ላይ የተመሰረተና ተመልሶም የግብርና ልማታችንን የሚያጠናክር የተስተካከለ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጅ ስንቀይስና ተግባራዊ ስናደርግ ነው፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ ከመድረሳችን በፊት በሚኖረው ሂደት ውስጥ ፈጣን እድገትን ልናረጋግጥ የምንችለው ግብርና መር ስትራተጅ በመከተል ብቻ ነው፡፡ ኢኮኖሚያችን በፍጥነት አድጎ ኢንዱስትሪ የመሪነት ቦታውን የሚጨብጥበት ደረጃ ላይ ልንደርስ የምንችለው ግብርና መር የልማት ስትራተጅን በመከተል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

## 2. ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገ ልማት ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ እንዲጠቀም ያደርጋል፡፡

በኢኮኖሚያዊ ልማት ሂደት ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንጂ የበይ ተመልካች እንዳይሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ማድረግ የሚያስፈልገው ልማት ከፍትሃዊነትና ህዝቡን ከድህነትና ድንቁርና ከማላቀቅ አኳያ መታየት ስለሚገባው ነው፡፡ ህዝቡ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ተፈላጊ የሚሆነው ግን ከፍትሃዊነት በመነሳት ብቻ አይደለም፡፡ በተለይም እንደኛ አይነት ሰፊና እጅግ አስከፊ የሆነ ድህነት ባለበት አገር ልማት እውን ሆኖ ህዝቡ ተጨባጭ የኑሮ መሻሻልና የለውጥ ተስፋ ካላገኘ በስተቀር፣ የበይ ተመልካች ሆኖ ከቀጠለ በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ሊኖር አይችልም፡፡ በድህነት መከራ የሚገረፈው ህዝብ በአንድ ወቅት በአስከፊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀውስ መናወጡ፣ መፍትሄ ወደሌለው ብጥብጥና ደም መፋሰስ መግባቱ የማይቀር ነው፡፡ ይህ በንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ የሚደረስበት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በበርካታ የአፍሪካ አገሮች በተጨባጭ የታየ ክስተት ነው፡፡ ቀውስና ደም መፋሰስ በነገሰበት አገር ደግሞ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ብሎ ነገር ሊታሰብ አይችልም፡፡ በመሆኑም ነው ህዝቡ በላቀ ደረጃ የሚጠቀምበት የኢኮኖሚ እድገት የማረጋገጥ ጉዳይ መሰረታዊ የኢኮኖሚ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ወሳኝ የሰላምና መረጋጋት፣ የብሄራዊ ደህንነት ጥያቄም የሚሆነው፡፡

ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ እንዲጠቀም ከማድረግ አኳያ እንደ አንድ አማራጭ ሊቀርብ የሚችለው፣ ከፍተኛ ካፒታልና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ልማትን ማረጋገጥ፣ በዚህ የልማት ሂደት ተጠቃሚ የሚሆነው ይጠቀማል፣ ተጠቃሚ የማይሆነውን ደግሞ መንግስት በተለያዩ መንገዶች እየደጎመ



በረሃብና በድንቁርና ከመርገፍ እንዲድን ያደርገዋል፣ በዚሁ መልክ ሰላምና መረጋጋትን አረጋግጦ ልማቱን ማስቀጠል ይገባል የሚለው አማራጭ ነው፡፡

ይህ አማራጭ በርካታ ጉድለቶች ያሉት አማራጭ ነው ተብሎ በብዙዎች የተተቸ አማራጭ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ነው የሚባል ስራና የልማት አስተዋፅኦ ሳያደርግ በድጎማ የሚኖር ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሰው እንዲኖርና የተመፅዋችነት አመለካከት እንዲሰፋ፣ ምንም ስራ ሳይኖር በድጎማ የሚኖረው ክፍል በተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች ውስጥ እንዲዘፈቅ የሚያደርግ አማራጭ ነው ተብሎ ይተቻል፡፡ ለድጎማ የሚውለው ከፍተኛ ወጪ በልማት ተግባር ላይ ቢውል ሊገኝ የነበረውን ከፍተኛ እድገት በማስቀረት አጠቃላይ እድገትን ያቀጭጫል ተብሎም ተተችቷል፡፡ እነዚህ ጉድለቶች የአማራጩ መሰረታዊ ችግሮች እንደሆኑ መቀመጡም ተገቢ ነው፡፡ ይህን አማራጭ የሚደግፉ ወገኖችም እነዚህን ጉድለቶች አይክዱም፡፡ ይህን አማራጭ የሚደግፉት በልማቱ ያልተጠቀመ ሰው የፈለገው ይሁን ማለት የባሰ ጉዳት ያስከትላል በሚል ነው፡፡

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ይህ የድጎማ አማራጭ ቢፈለግም ባይፈለግም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም፡፡ ቀድሞ ነገር ከፍተኛ ካፒታልና ቴክኖሎጂ ስለሌለን በነዚህ ላይ የተመሰረተውን የልማት ስትራተጅ ብንፈልገውና ብንመኘውም ተግባራዊ ልናደርገው አንችልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ሰርቶ የማይበላውን ህዝብ በድጎማ ለማኖር ቢፈለግም ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ገንዘብ የለም፡፡ ስለሆነም በድጎማ ህዝብን ከልማት ተጠቃሚ እንዲሆን የማድረግ አማራጭ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ቢፈለግም ባይፈለግም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል

አማራጭ አይደለም፡፡ ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆንበት፣ ሰላምና መረጋጋትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ልማት ከተፈለገ ከድኅግ አማራጭ የተለየ አማራጭ መቅረብ አለበት፡፡

ከድኅግ አማራጭ ውጪ ፈጣን ልማትን እያረጋገጡ ከዚሁ ልማት ህዝቡ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ያስችላል ተብሎ የሚታሰበውና በተግባርም በአንዳንድ የምስራቅ እስያ አገሮች ተሞክሮ አጥጋቢ ውጤት ያስገኘው አማራጭ የህዝቡን የማምረት አቅም የማጎልበትና ይህንኑ በሰፊው ለልማት የመጠቀም አማራጭ ነው፡፡

ህዝቡ ሌላው ቢቀር በስራ ላይ እንዲሰማራ የሚያስችለው ጉልበት አለው፡፡ የዚህን ጉልበት ጤንነት፣ የስራ ተነሳሽነትና የስራ ችሎታ ከፍ በማድረግ የህዝቡን የማምረት አቅም ማጎልበት ይቻላል፡፡ እንደኛ ባለው አገር ህዝቡ ከጉልበት በተጨማሪ አርሶ ለመኖር የሚፈልግ ሰው መሬት የማግኘት መብት አለው፡፡ እየዳበረ የሚሄደውን የማምረት አቅሙንና (ጉልበቱን) መሬቱን በአግባቡ ተጠቅሞ ማምረት ይችላል፡፡ የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበት (የሰው ጉልበት መሬት ወዘተ.) ይህን የህዝቡን የማምረት አቅም በሰፊው ለመጠቀም የሚያስችል የልማት ስትራቴጂ ተግባራዊ ከሆነ ህዝቡ ከሚገኘው ልማት በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ በዋነኛነት የኢኮኖሚ እድገት የሚያመጣው ህዝቡ በጉልበቱና በመሬቱ በመጠቀም የሚያመርተው ምርት ነው፡፡ ህዝቡ በጉልበቱና በመሬቱ በመጠቀም ከሚያመርተው ምርት ከፍተኛው ድርሻ የራሱ የአምራቹ ስለሚሆን ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ይህ አማራጭ ድኅግን በማይጠይቅ መልኩ ፈጣን እድገት ለማረጋገጥና ከሚገኘው ልማት ህዝቡ በላቀ



ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ይሆናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራተጅ በአገራችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችለው ብቸኛው አማራጭ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር የድኅግ አማራጭ ዝግ በሆነባት ድሃ አገራችን ህዝቡ ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ብቸኛው አማራጭም ነው፡፡ ይህ የሚሆንበት በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡

ከድኅግ አማራጭ ውጭ ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ የሚቻለው የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበትና ይህንኑ በሰፊው የሚጠቀም የልማት አቅጣጫ ነው፡፡ የህዝቡ የማምረት አቅም በዋነኛነት ጉልበቱ ሲሆን መሬትም ተጨማሪ የማምረት አቅም ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሁኔታ ከ85 በመቶ የማያንሰው ህዝብ ያለው በገጠር ነው፡፡ የህዝቡን የማምረት አቅም አጎልብተን በሰፊው እንጠቀምበት ከተባለ በገጠር ላይ ከማተኮር ሌላ አማራጭ የለም፡፡ የካፒታል እጥረት ባለባት አገራችን ይህን ሰፊ የሰው ጉልበት በሰፊው እንጠቀምበት ከተባለ በግብርና ስራ ላይ እንዲሰማራ ከማድረግ ውጭ ሌላ አማራጭ የለም፡፡

የህዝቡን የማምረት አቅም ለማጎልበት ጤንነቱ የተጠበቀ፣ የስራ ችሎታውና ዝግጁነቱ በትምህርትና ስልጠና የዳበረ የሰው ሃይል እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንኑ ስራ ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ በማይጠይቅ አኳኋን መፈፀም ይቻላል፡፡ በመለስተኛ የመንግስት ወጪ በዋነኛነት በህዝቡ

በራሱ ጥረት ጤንነቱ የተጠበቀ፣ የስራ ችሎታውና ዝግጁነቱ የተረጋገጠ ዜጋ መፍጠር ይቻላል።

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ማንኛውም ዜጋ ሰርቶ ለመኖር የሚያስችለው የእርሻ መሬት የማግኘት መብት አለው። የማምረት አቅሙ የጎለበተው ዜጋ በመሬት በመጠቀም በምርት ስራ ላይ በሰፊው ሊሳተፍ የሚችልበት ሁኔታ አለ። ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ስላለብን ያለንን መሬት ከፍተኛ ካፒታል በማፍሰስ ለግብርና ልማት ልናውለው አንችልም። ያለን አማራጭ የማምረት አቅሙ የጎለበተውን የሰው ሃይላችንን በሰፊው የሚጠቀም የግብርና ልማት ስትራተጅ መከተል ብቻ ነው። በመሆኑም ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራተጅ የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበት ይህን አቅም በሰፊው ለመጠቀም የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥርልናል። በአገራችን ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ያስችለናል።

በአገራችን ከተሞችም አስከፊ ድህነት መኖሩ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ነገር ግን የከፋ ድህነት መናኸሪያ የሆነው ገጠር ነው። እጅግ የሚበዛው የአገራችን ድሃ የሚገኘው በገጠር ነው። የድህነቱ መጠን እጅግ አስከፊ በሆነ ደረጃ ላይ የሚገኘው በገጠር ነው። እጅግ የሚበዛው የአገራችን ድሃ ባለበትና፣ የባሰው ድህነት በሚገኝበት በገጠር ፈጣን ልማት ማረጋገጥ ካልተቻለ በስተቀር በአገራችን ድህነትን ከመቅረፍ አኳያ መሰረታዊ ትርጉም ያለው ስራ መስራት አይቻልም። ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትረተጅ የድህነት መናኸሪያ በሆነው ገጠር ፈጣን ልማትን በማረጋገጥ ህዝቡ ከዚሁ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ያስችላል።



ግብርናንና ገጠርን ማዕከል ያደረገው የገጠር ልማት ስትራተጅ የሚያስገኘው ጠቀሜታ ከአገራችን ህዝብ ከ85% የማያንሰውን የገጠር ህዝብ ከድህነት ማላቀቅና ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ላይ ብቻ የተወሰነ ቢሆንም እጅግ ተመራጩ መንገድ መሆኑ ባልቀረ ነበር። ይሁንና ይህ የልማት አቅጣጫ ድህነትን በገጠር በመቅረፍና የገጠሩ ህዝብ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ደረጃ የተወሰነ ጠቀሜታ ብቻ ያለው አይደለም። የከተማውን ህዝብ ከድህነት በማላቀቅና ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግም ረገድ እጅግ ተመራጭ የሆነው የልማት አቅጣጫ ነው።

ግብርና በከፍተኛ ደረጃ በሚያድግበት ወቅት ልዩ ልዩ የግብርና ምርቶች በሰፊውና በሚፈለገው ጥራት ስለሚመረቱ የገበያ ዋጋቸው መቀነሱ የማይቀር ነው። አምራቹ ከፍተኛ ምርት ስለሚያገኝ የምርቱ ገበያ ዋጋ ቢቀንስም በድምር ከፍተኛ ገቢ ማግኘቱ አይቀርም። የከተማውም ህዝብ ከዚህ በቀጥታ ተጠቃሚ ይሆናል። ከከተማው ህዝብ የዕለት ተዕለት የኑሮ ወጪ ውስጥ ከ50% የማያንሰው የምግብ ወጪ ነው። የግብርና ውጤቶች ዋጋ በሚቀንስበትና በሚረጋጋበት ወቅት የከተማው ህዝብ የኑሮ ሁኔታ ቀጣይነት ባለው መንገድና በቀጥታ ይሻሻላል። ነገር ግን የገጠርና ግብርና ልማት ለከተማው ህዝብ ያለው ጠቀሜታ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም።

ቀደም ሲል እንዳየነው የግብርና ልማት ለንግድና ኢንዱስትሪ እድገት እጅግ የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል። ለኢንዱስትሪ የሚሆኑ ጥሬ እቃዎችን፣ የካፒታል ክምችትንና የሰራተኛ ጉልበትን እንዲሁም፣ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሰፊ የአገር

www.abyssinialaw.com

ውስጥ ገበያን በመፍጠር የንግድና ኢንዱስትሪ ልማትን ያፋጥናል፡፡ የንግድና ኢንዱስትሪ እድገት ሲፋጠን ደግሞ የከተማውም ህዝብ ሰፊ የስራ እድል አግኝቶ የማምረት አቅሙን አሳልብቶ በዚሁ በሰፊው በመጠቀም ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

የገጠርና የግብርና ልማት ንግድና ኢንዱስትሪም በዋነኛነት የሰው ጉልበት በሰፊው የመጠቀም አቅጣጫ ተከትለው እንዲያድጉ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ተፅእኖ ያሳርፋል፡፡ ምንም እንኳ በልማቱ ሂደት የካፒታል ክምችታችን እየጨመረ የሚሄድ ቢሆንም ለረጅም ጊዜ የካፒታል እጥረት ማጋጠሙ ግን አይቀርም፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ ራሱ የንግድና ኢንዱስትሪ ልማታችን የሰው ጉልበትን በሰፊው የመጠቀም አቅጣጫ እንዲከተል ተፅእኖ የሚያሳርፍ ይሆናል፡፡ ከዚህም በላይ ኢንዱስትሪ የግብርና ምርቶችን በፋብሪካዎች ወደተለያዩ ሸቀጦች በመለወጥ ስራ ማለትም በአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ላይ ያተኮረ መሆኑ አይቀርም፡፡ ይህ በሚሆንበት ወቅት የኢንዱስትሪው ባህሪ ራሱ ጉልበትን በሰፊው መጠቀም የሚጠይቅ በመሆኑ የኢንዱስትሪ ልማታችን የህዝቡ ዋነኛ የማምረት አቅም የሆነውን የሰው ጉልበት በሰፊው የሚጠቀም እንዲሆን ይገደዳል፡፡ የኢንዱስትሪው ሰፊ የአገር ውስጥ ገበያ የአርሶ አደሩ የፍጆታና የማምረቻ እቃ ፍላጎት ይሆናል፡፡ እነዚህም በአብዛኛው ጉልበት በሰፊው በሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች የሚመረቱ ናቸው፡፡

ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራተጂ የግብርና ምርቶች ዋጋ ቀንሶ የከተማው ሸማች እንዲጠቀም፣ የንግድና ኢንዱስትሪ እድገት ተፋጥኖ የከተማው ህዝብ የስራ



እድል እንዲያገኝ ከማድረግ ባሻገር የሚካሄደው የኢንዱስትሪ እድገት የሰው ጉልበትን በሰፊው የመጠቀም ባህሪ ባለው የኢንዱስትሪ አይነት ላይ ያተኮረ እንዲሆን በማድረግ የሚፈጠረው የስራ ዕድል በሌላ አማራጭ ሊኖር ከሚችለው ሁሉ እጅግ የሰፋ እንዲሆን፣ በመሆኑም የኢንዱስትሪ ልማቱም የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበትና ይህንኑ በሰፊው በመጠቀም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን፣ ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ለመጠቀም የሚያስችለው እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የገጠሩም ሆነ የከተማው ህዝብ ከልማቱ በላቀ ደረጃ እንዲጠቀም ለማድረግ የሚቻለው በግብርናና በገጠር ላይ ያተኮረ የልማት ስትራተጅን በመከተል ነው፡፡

## 3. ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ልማት አገራችንን ከተመፅዋችነት ለማዳን ያስችላል፣

ያለንበት አለም አገሮች በተለያዩ የኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ሰንሰለቶች በቅርብ የተቆራኙበትና የተሳሰሩበት አለም ነው፡፡ ማንኛውም አገር ቢሆን ከዚህ ትስስር ውጪ ሊሆን አይችልም፡፡ አንድም በሻጭና ገዥነት፣ አሊያም በተመፅዋችነትና በተስፈኝነት ከዚሁ አለም አቀፋዊ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ጋር ያልተቆራኘ አገር የለም፡፡ አገሮች ከተመፅዋችነት ተላቀው ራሳቸውን የመቻላቸው ጉዳይ፣ ኢኮኖሚያዊ ነፃነታቸውን የማጎልበታቸው ጉዳይ በዚሁ አለም አቀፋዊ ትስስር ውስጥ ሆኖ የሚፈፀም እንጂ ከዚህ ትስስር ውጪ ሆኖ ሊታሰብ የሚችል አይደለም፡፡

በዚህ አለም አቀፋዊ ትስስር ውስጥ አገሮች የተለያየ

www.abyssinialaw.com

የስራ ድርሻ አላቸው፡፡ አንዳንዶቹ እርስ በርሱ የሚመጋገብ ሰፊ የአገር ውስጥ ገበያን የሚፈጥር የዳበረ ኢኮኖሚ ገንብተው ከሌላው አገር ጋር በጠንካራ የአገር ውስጥ ገበያ ላይ ተመስርተው ይተሳሰራሉ፡፡ ሌሎቹ ይህ ነው የሚባል ስፋትና የእርስ በርስ ትስስር የሌለው ኢኮኖሚ ይዘው በአለም ገበያ ላይ የሚነፍስ ማንኛውም መለስተኛ ነፋስ ክፉኛ እያንገዳገዳቸው ይንፏቀቃሉ፡፡ አንዳንዶቹ በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ቴክኖሎጂና ካፒታል ኑሯቸው በትስስሩ ውስጥ የላቀ ቦታና ጥቅም ያገኛሉ፡፡ ሌሎቹ የቴክኖሎጅ እድገትና የካፒታል ክምችት ማምጣት ተስኗቸው ያዘግማሉ፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንደኛ ያለው አገር ከተመፅዋችነት ለመዳን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት በማረጋገጥ ያለማቋረጥ የቴክኖሎጂ ደረጃውንና የካፒታል ክምችቱን ማሳደግ፣ በዚህም አማካኝነት በአለም አቀፋዊ ትስስሩ ውስጥ የሚኖረውን ድርሻና ጥቅም በቀጣይነት ማሻሻል አለበት፡፡ በሂደት የአገር ውስጥ ኢኮኖሚው እርስ በርሱ የተቆላለፈና የሚመጋገብ ሰፊ የአገር ውስጥ ገበያ እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል፣ ስለሆነም ደግሞ በአለም ገበያ ውስጥ የሚነፍስ ማንኛውም መለስተኛ ንፋስ ከጫፍ ጫፍ የማያላጋው መሆን አለበት፡፡ ግብርናንና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ ይህንኑ ለማድረግና ከተመፅዋችነት ተላቀን የኢኮኖሚ ነፃነታችን እንዲጎለብት ለማድረግ የሚያስችለን መተኪያ የሌለው አማራጭ ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራተጅ በአገራችን ቀጣይነት ያለው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ የሚያስችለን ብቸኛ አማራጭ ነው፡፡ ይህ



ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት የቴክኖሎጂ ደረጃችን ያለማቋረጥ የሚያድግበት፣ የካፒታል ክምችታችን በቀጣይነት የሚዳብርበት የልማት አማራጭ ነው፡፡ በመሆኑም በአለም አቀፋዊ ትስስሩ ውስጥ የሚኖረን ድርሻ በአፋጣኝ የሚሻሻልበት፣ ከዚሁ የምናገኘው ጥቅም በቀጣይነት የሚሻሻልበት ሁኔታ ይፈጥርልናል፡፡ ከተመፅዋችነት ተላቀን ኢኮኖሚያዊ ነፃነታችን እየጎለበተ እንዲሄድ ለማድረግ የሚያስችለን ምርጥ የልማት ስትራተጅ ነው፡፡

ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ የሰፊው አርሶ አደር ምርት በፍጥነትና በቀጣይነት እንዲያድግ ያደርጋል፡፡ ከህዝባችን ከ85% የማያንሰው ክፍል ምርቱ በፍጥነትና በቀጣይነት በሚያድግበት ወቅት ከየትኛውም አማራጭ በበለጠ አኳኋን ሰፊ የአገር ውስጥ ገበያን ለመፍጠር ያስችላል፡፡ የጥቂቶችን የመግዛት አቅም ብቻ ሳይሆን የመላውን ህዝብ የመግዛት አቅም በፍጥነትና በቀጣይነት ስለሚያሳድግ በጣም ሰፊ መሰረት ያለው የአገር ውስጥ ገበያን ይፈጥራል፡፡

የአርሶ አደሩ የመግዛት አቅም በፍጥነትና በቀጣይነት ሲያድግ እርስ በርሱ በጥብቅ የተሳሰረና የተቆራኘ አገራዊ ኢኮኖሚ እንዲኖር ለማድረግም ያስችላል፡፡ አርሶ አደሩ ሰፊ የመግዛት አቅም ሲኖረውና ንግድና ኢንዱስትሪም ይህንኑ የአርሶ አደሩ የማምረቻና የፍጆታ እቃዎች ፍላጎት ለማርካት ሲንቀሳቀሱ ነው ሊስፋፉና ሊዳብሩ የሚችሉት፡፡ እነዚህ የአርሶ አደሩ ፍላጎቶች ደግሞ የተራቀቀ ቴክኖሎጂና ሰፊ የካፒታል ክምችት በማይጠይቅ፣ በአገራችን በቀላሉ ሊስፋፉ በሚችል ንግድና ኢንዱስትሪ ሊረኩ የሚችሉ ናቸው፡፡ የአርሶ አደሩ የግብርና ምርት በመጠንም በአይነትም እየተሻሻለ ሲሄድ ንግድና

ኢንዱስትሪ ሊሰፋፉ የሚችሉት ግብርና ባመረተው በዚህ ጥሬ ዕቃ በመጠቀም ላይ አተኩረው ነው። ይህንን የሚጠቀም ንግድና ኢንዱስትሪ የተራቀቀ ቴክኖሎጂና ከፍተኛ የካፒታል ክምችት የማይጠይቅ በመሆኑ በአገራችን የመስፋፋት ዕድሉ የላቀ ነው። በመሆኑም ግብርናንና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ በጥብቅ የተሳሰረ እርስ በርሱ በቀጣይነት የሚመጋገብ ኢኮኖሚ እንዲኖር በማድረግ እድገታችን ተመጋጋቢ እንዲሆንና ቀጣይነትና ፍጥነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እንዲኖረን ያደርጋል። እድገቱና ተመጋጋቢነቱ በተረጋገጠ መጠን የአገር ውስጥ ገበያችን ስፋትም በዚሁ መጠን ይጨምራል።

በመሆኑም ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ልማት በማረጋገጥ በአለም አቀፋዊው ኢኮኖሚያዊ ትስስር አገራችን ያላት ድርሻና ጥቅም ያለማቋረጥ እንዲሻሻል ከተመፅዋችነት እንድንድንና ኢኮኖሚያዊ ነፃነታችን እንዲጎለብት ያደርጋል። ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ እርስ በርሱ የተሳሰረና ተመጋጋቢ የሆነ ኢኮኖሚን በመፍጠር ህዝቡን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ የሚያደርግና የህዝቡን የመግዛት አቅም በከፍተኛ ደረጃ የሚያሳድግ በመሆኑ ሰፊ የአገር ውስጥ ገበያና በአለም ገበያ በሚነፍስ በማንኛውም መለስተኛ ነፋስ በቀላሉ የማይናወጥ ኢኮኖሚ እንዲኖረን ያደርጋል። በመሆኑም ከተመፅዋችነት ተላቀን ኢኮኖሚያዊ ነፃነታችን እየተሻሻለ እንዲሄድ ያደርጋል።



## 4. ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ልማት በአገራችን የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መፍጠር ያስችላል፣

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ የሚቻለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መርሆዎችን በመከተል ነው። እነዚህን መርሆዎች ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ከማድረግ ውጪ በአገራችን ቀጣይነት ያለውና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማምጣትም ሆነ ከዚሁ እድገት ህዝቡ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ድህነትን ማስወገድ አይቻልም። ስለሆነም የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ የልማት መርሆም የልማቱ ግብም ሆኖ ያገለግላል። እነዚህን መርሆዎች በመጠቀም የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መፍጠር የኢኮኖሚያዊ ልማታችን መሰረታዊ አላማ አንድ ገፅታ ይሆናል።

በአገራችን የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚን ለመፍጠር የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መርሆዎችን በመከተል ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥን ያስፈልጋል። ይህን የመሰለውን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የእድገት ለማረጋገጥ የሚያስችለን ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ መከተል ብቻ ነው። ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት በሌለበት የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ብሎ ነገር በአገራችን ሊኖር ስለማይችል ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራተጅ ከዚህ አኳያም እጅግ ተፈላጊ ይሆናል።

ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራተጅ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠረው አርሶአደር የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መርሆዎችን በመከተል በምርት ተግባር ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ

ለማድረግ የሚያስችል ነው:: የነፃ ገበያ ኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በጥቂቶች ብቻ የተንጠለጠለ ሳይሆን ሰፊውን አርሶ አደር ያሳተፈ በጣም ሰፊ መሰረት ያለው እንዲሆን የሚያደርግ ነው:: ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራተጅ ህዝቡ የበይ ተመልካች መሆኑ ቀርቶ ከነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ግንባታው ሂደት በላቀ ደረጃ እንዲጠቀም የሚያደርግ ነው:: በመሆኑም የአገራችን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ እንቅስቃሴ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችን በዋነኛ ተዋናይነት የሚያሳትፍና መላው ህዝብ ከእንቅስቃሴው በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ በአገራችን አስተማማኝና ሰፊ መሰረት እንዲኖረው ያደርጋል:: በመሆኑም ለዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል::

በማጠቃለል ሲታይ ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ መከተል በአገራችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲኖር፣ ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን፣ አገራችን ከተመፅዋችነት ተላቃ ኢኮኖሚያዊ ነፃነታችን እንዲጎለብትና በአገራችን የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ እንዲገነባ ለማድረግ የሚያስችለን የተሻለውና ብቸኛው የልማት አማራጭ ነው:: ይህ የልማት አቅጣጫ ያስቀመጥነውን መሰረታዊ የኢኮኖሚያዊ ልማት አላማ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለን ዋነኛ መሳሪያ ነው::

ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ እንከተላለን ማለት ብቻውን የተሳካ የግብርናና የገጠር ልማት ስራ ለመስራት የሚያስችል አይሆንም:: ፈጣንና ቀጣይነት



ያለው የገጠርና የግብርና ልማት ለማረጋገጥ ይህንኑ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ስትራተጅዎች ፖሊሲዎች ወዘተ. መቀየስ በየጊዜው መከለስና ማሻሻል ይጠይቃል:: የሚቀየሱት ፖሊሲዎችና ስትራተጅዎች የመሰረታዊ ኢኮኖሚያዊ አላማችንን አራት ገፅታዎች በተሟላ ሁኔታ ለማሳካት የሚያስችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥና በየጊዜው ማሻሻል ይጠይቃል:: ይልቁንም ያስቀመጥናቸው ግቦችና አላማዎች መሳካት አለመሳካታቸውን ከመወሰን አኳያ ግቦችን ከማስቀመጥ በላይ ፋይዳ የሚኖረው ግቦቹን ለማሳካት የሚያስችሉ የተስተካከሉ ስትራተጅዎችና ፖሊሲዎች የመንደፍና እነዚህን በቀጣይነት የማሻሻል ጉዳይ ነው:: በመሆኑም በሚቀጥለው ክፍል የገጠርና የግብርና ልማት ስትራተጅዎቻችንና ፖሊሲዎቻችን እየዘረዘርን እናብራራለን::

www.abyssinialaw.com

# ክፍል ሁለት

# የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራተጅዎቻችን፣

## 1. የግብርና ልማት መሰረታዊ አቅጣጫዎች፣

የገጠር ልማት ስንል ተደጋግሞ እንደተገለፀው በግብርና ልማት ላይ የታጠረ ነገር ማለታችን አይደለም፡፡ ከግብርና ልማት ውጪ በገጠር ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ መካተት ያለባቸው በርካታ ስራዎች ይኖራሉ፡፡ ይሁንና በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የገጠር ልማት እንቅስቃሴያችን ማዕከል የግብርና ልማት መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በመሆኑም የገጠር ልማት ፖሊሲዎቻችንንና ስትራተጅዎቻችንን በምንተነትንበት ወቅት ከሁሉም በላይ ለግብርና ልማት ፖሊሲዎችና ስትራተጅዎች ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ የግብርና ልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራተጅዎቻችን የሚመሩባቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች አስቀድሞ መተንተንም ከዚህ አኳያ እጅግ ተፈላጊና ጠቃሚ ይሆናል፡፡ እነዚህ መሰረታዊ አቅጣጫዎች የግብርና ልማት ስትራተጅዎቻችንና ፖሊሲዎቻችንን በሙሉ የሚመሩና የሚገዙ በመሆናቸው በነዚህ ላይ ግልፅነት ሳይኖር በግብርና ልማት እንቅስቃሴያችን ላይ ግልፅነት ሊኖር አይችልምና፡፡

### 1.1. የሰው ጉልበትን በሰፊው የመጠቀም አቅጣጫ፣

በመግቢያው ላይ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በአገራችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥ የሚቻለው ካፒታልን



በሰፊው የመጠቀም አቅጣጫ በመከተል ሳይሆን የሰው ጉልበትን በሰፊው የመጠቀም አቅጣጫ በመከተል ነው፡፡ ይህ ከሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍም በላቀ ደረጃ በግብርናው ዘርፍ ተፈላጊነት ያለው ጉዳይ ነው፡፡ የሰው ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም የግብርና ልማት አቅጣጫ እንከተል ሲባል ከሚፈለገው ሰው በላይ በየማሳው አሰማርተን በኋላቀር የግብርና ቴክኖሎጅዎች በመጠቀም መንቀሳቀስ አለብን ማለታችን አይደለም፡፡ በአንድ ማሳ ላይ ተፈላጊ ከሆነው የሰው ሃይል በላይ በማሰማራት የሚፈለገውን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ በፍፁም የሚታሰብ አይደለም፡፡ በግብርና ዘርፍም ቢሆን ኋላቀር ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ቀጣይነት ያለው ፈጣን እድገት ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

የሰው ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም የግብርና ልማት ስትራተጅ እንከተላለን ስንል በእርሻ ማሳ ላይ ከሚፈለገው የሰው ሃይል በላይ ይሰማራ ማለታችን ሳይሆን ተፈላጊ በሆነው መጠን አሰማርተን የሰው ሃይሉን የማምረት አቅም አሟጠን ለመጠቀም የሚያስችለን አቅጣጫ እንከተል ማለታችን ነው፡፡ የሰው ጉልበት በሰፊው እንጠቀም ስንል ኋላቀር ቴክኖሎጅና የግብርና ዘይቤ እንከተል ማለታችን ሳይሆን የሰው ጉልበትን በመተካት ላይ ያላተኮረ የላቀ ቴክኖሎጅና የአስተራረስ ዘይቤ እንጠቀም ማለታችን ነው፡፡

የሰው ሃይልን በሰፊው በመጠቀም ዘመናዊ የግብርና ዘይቤዎችን በስራ ላይ ለማዋል ከሚያስችሉ ዋነኛ ስልቶች አንዱ ግብርናው የሰው ሃይሉን በማስተማርና በግብርና ሙያ በማሰልጠን የስራ ተነሳሽነቱን በማሳደግ የሚከናወን እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ዘመናዊ ማሽነሪ በሰፊው በመጠቀም በግብርና

www.abyssinialaw.com

ሙያ ሰፊ ስልጠና የሌለውን ጥቂት ሰው ብቻ በማሰማራት ሊመጣ የሚችል የግብርና ልማት አለ፡፡ እንደዚህ አይነቱ የግብርና ልማት በሰፊ መሬት ላይ ጥቂት ሰው በማሰማራት ሊመረቱ በሚችሉ የግብርና ምርቶች ላይ ያተኮረ የሰፋፊ እርሻዎች ግብርና (ኤክስቴንሲቭ ፋርሚንግ ሜተድ) ዘይቤ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በግብርና ሞያ በብቃት ያልሰለጠነ የሰው ጉልበትን የማይተኩ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም በአንድ ውሱን ማሳ ሊገኝ የሚችለውን ምርት በከፍተኛ ደረጃ በመጨመርና ከፍተኛ ዋጋ የሚያስገኙ የግብርና ምርቶችን በማምረት ላይ ያተኮረ የግብርና ዘይቤ (ኢንቴንሲቭ ፋርሚንግ ሜተድ) ይኖራል፡፡ የኛ ዋነኛ የግብርና ልማት አቅጣጫ የሰው ጉልበትን በሰፊው ለመጠቀም የሚያስችለው የግብርና ዘይቤ ላይ ይሆናል፡፡

ሁለቱም የግብርና ዘይቤዎች ቀጣይ የሆነ የግብርና ምርታማነትና የቴክኖሎጅ እድገትን ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡ የቴክኖሎጅና የምርታማነት እድገት አቅጣጫቸው ግን በጣም የተለያየ ነው፡፡ ጉልበትን በሰፊው በመጠቀም ላይ ያተኮረው የግብርና ዘይቤ የሰራተኛውን የግብርና ሞያና የስራ ተነሳሽነት በቀጣይነት በማሻሻልና በማዳበር ላይ ያተኩራል፡፡ ካፒታልን በሰፊው የመጠቀሙ ዘይቤ ጉልበትን የሚተኩ የተራቀቁ ማሽነሪዎች በሰፊው በመጠቀምና በማሻሻል ላይ ያተኩራል፡፡ ጉልበትን በሰፊው የመጠቀም ዘይቤ የሙያተኛ ገበሬ ከፍተኛ እንክብካቤና ክትትል የሚፈልጉ የግብርና ምርቶችን በማምረትና የነዚህን ምርቶች መጠንና አይነት በማሻሻል ላይ ያተኩራል፡፡ ካፒታልን በሰፊው የሚጠቀመው ዘይቤ እንደዚህ አይነት ክትትልና እንክብካቤ በማይጠይቁ ምርቶችና የግብርና ስልቶች ላይ ያተኩራል፡፡ ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀመው ዘይቤ አንድን ውሱን የእርሻ ማሳ በከፍተኛ ደረጃ በመጠቀም (በመስኖ፣ የተለያዩ ምርቶችን በማምረት፣ወዘተ.) ምርትና ምርታማነትን



በማሳደግ ላይ ያተኩራል፡፡ ካፒታልን በሰፊው የሚጠቀመው ሰፊ መሬትን በጥቂት ሰው ለማልማት በሚያስችሉ ስልቶች ላይ ያተኩራል፡፡

በመሆኑም የምንከተለው የሰው ጉልበትን በሰፊው የመጠቀም የልማት አቅጣጫ በኋላ ቀር ቴክኖሎጅና የግብርና ዘዴ ከሚፈለገው በላይ የሰው ሃይል በማከማቸት የግብርና ምርትን ማምረት አይደለም፡፡ በእያንዳንዱ ማሳ ላይ ተፈላጊው የሰው ሃይል ብቻ ተሰማርቶ የሚያመርትበት አቅጣጫ ነው፡፡ የሰው ሃይልን በሰፊውና በላቀ ደረጃ ለመጠቀም የሚያስችሉ የግብርና ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ምርታችንና የግብርና ቴክኖሎጅ ደረጃችን በቀጣይነት እንዲያድግ የሚያደርግ አቅጣጫ ነው፡፡ በመሆኑም በግብርና ስራ ላይ የተሰማራውን የሰው ሃይል በትምህርትና ስልጠና የላቀ ደረጃ ላይ በማድረስ፣ ይህ የግብርና ሞያው የዳበረ የሰው ሃይል የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጅዎችንና ስልቶችን እንዲጠቀም በማድረግ ላይ ያተኮረ አቅጣጫ ነው፡፡ የመስኖ-ልማትን፣ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው የግብርና ምርቶችን፣ በውሱን መሬት የላቀ የግብርና ምርት ለማስገኘት የሚችሉ አማራጮችን ሁሉ አሟጦ የመጠቀም አቅጣጫ ነው፡፡ የሰለጠነ የሰው ሃይልን ማዕከል ያደረገ የምርታማነትና የቴክኖሎጅ እድገት አቅጣጫን የመከተል ጉዳይ ነው፡፡ የግብርና ልማት ስትራተጅዎቻችንና ፖሊሲዎቻችን በዚህ መሰረታዊ አቅጣጫ የሚመሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 1.2. የእርሻ መሬታችንን በአግባቡ የመጠቀም አቅጣጫ፣

በግብርና ልማት እንቅስቃሴያችን ውስጥ የመሬት አቅርቦትና አጠቃቀም ጉዳይ ወሳኝ ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ መሬታችንን በአግባቡ መጠቀም ካልቻልን በሚፈለገው

www.abyssinialaw.com

መጠን ፍጥነትና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት ማረጋገጥ የሚቻል አይሆንም፡፡ ከዚህ አኳያ አርሶ ለመኖር የሚፈልግ ሰው የእርሻ መሬት ማግኘቱን የማረጋገጥ ጉዳይ አንድ መሰረታዊ የመሬት አጠቃቀም ጉዳይ ይሆናል፡፡ የተፈጥሮ ሃብታችንን በጥንቃቄና በእንክብካቤ የመያዝ ጉዳይ የግብርና ምርታማነታችን ለማሳደግና ቀጣይነት ያለው የግብርና ዘርፍ እንዲኖረን ከማድረግ አኳያ የጎላ አስተዋፅኦ ያለው ጉዳይ ይሆናል፡፡ መሬታችንን በላቀ ደረጃና ከዚሁ ሊገኝ የሚችለውን ምርት ሁሉ አሟልቶ ለማስገኘት በሚያስችል ደረጃ በመጠቀም አቅጣጫ ከዚህ ጋር በተያያዘም የመስኖ ልማትን በማስፋት መሬቱን አመቱን ሙሉ ለመጠቀም የመቻል፣ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን በውሱን ማሳ ላይ የማምረት ጉዳዮች ወዘተ. ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ይሆናሉ፡፡ መሬታችን ለተለያዩ ስራዎች ሊያገለግል የሚችል በመሆኑ የትኛው መሬት ለምን አይነት ስራ ቢውል እንደሚሻል ለይቶ በማወቅ በዚሁ መሰረት ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ጉዳይም ቁልፍ የመሬት አጠቃቀም ጉዳይ ነው፡፡ በአገራችን ብዙ ህዝብና ውሱን መሬት ያለበት አካባቢና ሰፊ መሬትና አነስተኛ ቁጥር ያለበት አካባቢ እንዳለም ይታወቃል፡፡ የመሬት አጠቃቀማችን ይህንኑ ግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ማድረግም ያስፈልጋል፡፡

በአጭሩ መሬታችንን በጥንቃቄ፣ የላቀ ልማታዊ አስተዋፅኦ ለማበርከት በሚያስችል አኳኋን የመጠቀም ጉዳይ የግብርና ስትራቴጅዎቻችንና ፖሊሲዎቻችን የሚመሩበት መሰረታዊ አቅጣጫ መሆን ይኖርበታል፡፡ መሬታችንን በአግባቡና የላቀ ልማታዊ አስተዋፅኦ ለማበርከት በሚያስችል አኳኋን ለመጠቀም የማያስችለንና ከዚህ መሰረታዊ አቅጣጫ ውጪ የሆነ የግብርና ልማት ስትራቴጅ፣ ፖሊሲ ወዘተ. የግብርና



ልማታችንን ከማቀጨጭ አልፎ ሊያፋጥነውም ሆነ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል አይሆንም፡፡

## 1.3. አንድ እግርን በመሬት፣

ማንኛውም በፍጥነት ለመጓዝ የሚፈልግ ሰው እፈጥናለሁ ብሎ ሁለቱን እግሮቹን በአንድ ጊዜ በማንቀሳቀስ ልራመድ ቢል ለአጭር ጊዜ መዝለል ይችል ይሆናል እንጅ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ጉዞ ሊኖረው አይችልም፡፡ በፍጥነት መጓዝ የሚቻለው አንድ እግርን መሬት ላይ በማድረግ ብቻ ነው፡፡ አንደኛው እግር መሬትን አደላድሎ ከረገጠ በኋላ ሌላው ወደሚቀጥለው ለመሸጋገር በአየር ላይ ሲሆን፣ በአየር ላይ የነበረው አልፎ ሄዶ መሬት ሲረግጥ፣ መሬት ረግጦ የነበረው እየተነሳ ነው ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የእግር ጉዞ ማድረግ የሚቻለው፡፡ የግብርና ልማት እንቅስቃሴያችንም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ጉዞ ሊኖረው የሚችለው ተመሳሳይ አቅጣጫን በመከተል ብቻ ነው፡፡ ይህንኑ አቅጣጫ አንድ ምሳሌ በመጠቀም በይበልጥ መረዳት ይቻላል፡፡

በአሁኑ ወቅት ያለን አርሶ አደር በአብዛኛው ያልተማረና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ በመጣ የግብርና ቴክኖሎጅ በመጠቀም የሚኖር ነው፡፡ ይህንኑ አቅም በማጣጣል ተንጠራርተን የተማረ አርሶ አደርና የላቀ ቴክኖሎጅ የመጠቀም አቅጣጫ እንከተል ብንል ከሁሉም ሳንሆን እንቀራለን፡፡ መራመድ የምንችለው አንድ እግራችንን በመሬት ላይ በማድረግ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ያልተማረ አርሶ አደር ሊደርስ የሚችልበት የላቀ የምርታማነት ደረጃ ላይ ለማድረስ፣ በልምድ ከተገኘው የግብርና ዘይቤ የበለጠውን በመምረጥና ይህንኑ

www.abyssinialaw.com

በመጠኑ በማሻሻል በምርታማነታችን ላይ በጣም ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል:: በመሆኑም ያለንን ጠቃሚ አገር በቀል እውቀት በአግባቡ አሰባስበን መያዝና ልማትን ከማፋጠን አኳያ ይህንኑ መሰረት አድርጎ መንቀሳቀስ፣ ለልማታችን አስፈላጊ የሆነውን እውቀት ለአዲሱ ትውልድ ማሳለፍና በአግባቡ መዝግቦ መያዝ ያስፈልጋል:: ያለን ይህ የሰው ሃይልና ቴክኖሎጅ ሊያስገኝ የሚችለውን የላቀ እድገት አሟጠን ለማምጣት በሚያስችል አኳኋን በሰፊው መረባረብ ይኖርብናል::

ነገር ግን ይህ ብቻ ቀጣይነት ያለው ፈጣን የግብርና እድገት ሊያስገኝልን አይችልም:: ባለን የሰው ሃይልና ቴክኖሎጅ ሊመጣ የሚችለው እድገት ሄዶ ሄዶ መሟጠጡ አይቀርም:: ተሟጦ ከማለቁ በፊት ፈጣን እድገታችን እንዲቀጥል ለማድረግ መሰረት የሚሆን ስራ ከወዲሁ  መስራት አለብን:: በመሆኑም በአንድ በኩል ያለንን የማምረት አቅም አሟጠን እየተጠቀምን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ያልነበረንን የልማት አቅም ለመፍጠር መረባረብ ይኖርብናል:: የተማረ አርሶ አደር ለመፍጠርና አዳዲስ ቴክኖሎጅ ተግባራዊ ለማድረግ መስራት ይኖርብናል:: በዚህ አኳኋን ነባሩ የማምረት አቅም ሲሟጠጥ አዲሱ አቅም ተዘጋጅቶ፣ ተጀምሮና እየተስፋፋ ስለሚጠብቅ እድገታችን ፈጣንና ቀጣይነት ይኖረዋል::

ስለሆነም የግብርናና የገጠር ልማት ስራችን በአንድ ጊዜ ሁለት ነገሮችን መስራትን መሰረት ያደረገ አቅጣጫ መከተል ይገባዋል:: በመጀመሪያ ደረጃ በተጨባጭ በእጃችን ያለው የማምረት አቅም ሊያስገኝ የሚችለውን የላቀ ምርት ለማምጣት የሚያስችለንን አማራጭ በሙሉ የመዳሰስና ጥቅም ላይ የማዋል ስራ መስራት አለብን:: ይህን ሳናደርግ ወደሌላ



ርምጃ ለመሸጋገር መሞከር እድገታችን ፈጣን እንዳይሆን ያደርጋል:: ይህንኑ እየሰራን እያለን ወደሚቀጥለው የምርታማነትና የቴክኖሎጅ ደረጃ የሚያሸጋግረንን ስራ ጎን ለጎን እናከናውናለን:: በመጀመሪያ የነበረን የማምረት አቅም የእድገት አድማሱ ተሟጦ ከማለቁ በፊት ጎን ለጎን በተሰራው ስራ ለቀጣይ እመርታ ዝግጁ እንሆናለን:: በዚህ መልክ አንድ እግር በመሬት በማድረግ ቀጣይነት ያለው ፈጣን የግብርና እድገት ማረጋገጥ እንችላለን:: በመሆኑም የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጅዎቻችን ሁሉ የሚመሩበት አንድ መሰረታዊ አቅጣጫ አንድ እግርን መሬት ላይ የማድረግ አቅጣጫ መሆን ይኖርበታል::

## 1.4. ከተለያዩ የአግሮ-ኢኮሎጂ ዞኖች ጋር የተጣጣመ አቅጣጫ፣

በአገራችን ውስጥ በዝናብ መጠን፣ በመሬቱ አይነትና በአካባቢው ከፍታና በመሳሰሉት መስፈርቶች የሚለያዩ በርካታ የአግሮ-ኢኮሎጂ ዞኖች አሉ:: ከዚህ ጋር ተያይዞም በዋነኛነት በከብት ርቢ የሚኖሩ ዜጎች የሚኖሩባቸው የምስራቁና በተወሰነ ደረጃም የደቡብ ቆላዎች፣ ሰፊ ያልታረሰ መሬትና ጥቂት ህዝብ የሚኖርባቸው ለእርሻ ስራ በጣም ምቹ የሆኑ የምዕራባዊ ክፍል ቆላዎች፣ እና ብዙ ህዝብና ጠበብ ያለ የእርሻ መሬት ያላቸው ደጋማ አካባቢዎች አሉን:: በነዚህ የተለያዩ የአግሮ-ኢኮሎጂ ዞኖች ውስጥ ሊካሄድ የሚችለው የግብርና ስራ በጣም የተለያየ እንደሚሆን ለመገመት አያስቸግርም:: በሁሉም አካባቢዎች አንድ አይነት የግብርና ልማት ስራ እንስራ ብንል በሚፈለገው ደረጃና ፍጥነት ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት ስራ መስራት አይቻለንም::

www.abyssinialaw.com

የአገራችን የግብርና ልማት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ሊሆን የሚችለው በየአግሮ-ኢኮሎጂ ዞኑ ያለውን ተጨባጭ የልማት ዕድል ከለየን በኋላ፣ እነዚህን የልማት ዕድሎች አሟጠን ለመጠቀም የሚያስችለን መንገድ የቱ እንደሆነ በዝርዝር ለይተን ተግባራዊ ማድረግ ስንችል ነው:: በዚህ መልክ ለእያንዳንዱ አካባቢ የሚሆን ዝርዝር የልማት እቅድ ማዘጋጀት፣ እያንዳንዱ ሊያስመዘግብ የሚችለውን የላቀ እድገት እንዲያመጣ በማድረግ አጠቃላይ የአገራችን የግብርና ልማት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን የማድረግ አቅጣጫን መከተል አለብን:: የግብርና ልማት ስትራተጅያችንና ፖሊሲዎቻችን ይህንን አቅጣጫ የተከተሉና ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉም መሆን አለባቸው::

## 1.5. የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ፣

ማንኛውም የልማት እንቅስቃሴ የተለያዩ ስራዎችን አስተባብሮና አቀናጅቶ መምራትን ይጠይቃል:: የግብርና ልማት እንቅስቃሴያችንም በርካታ ስራዎችን አቀናጅቶ መስራት የሚጠይቅ ይሆናል:: በመጀመሪያ የግብርና ስራውን ራሱን በተናጠል በምናይበት ወቅት በዚሁ ርእስ ስር የሚካተቱ በጣም በርካታ የተለያዩ ምርቶችንና እንቅስቃሴዎችን ያቀፈ ነው:: እነዚህን ስራዎች በዝርዝር መርምሮና በነሱ መካከል ያለው ትስስር ምን እንደሆነ ለይቶ፣ እነዚህን አስተሳስሮና አቀናጅቶ ለመስራት ያለው ዕድልና በዚህ አኳኋን በመንቀሳቀስ የሚገኘው ጥቅም ምን እንደሆነ አስቀምጦ በዚሁ መሰረት መንቀሳቀስ የሚገኘው ልማት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል:: ስለሆነም የግብርና ልማት እንቅስቃሴያችን የተቀናጀ የልማት አቅጣጫን የሚከተል መሆን አለበት::



ቅንጅት የሚጠይቀው ግን በግብርና ስራ በራሱ ላይ ባሉ ስራዎችና ምርቶች መካከል ብቻ አይደለም:: የግብርና ልማት እንደ ትምህርትና ጤና ከመሰሉ የማህበራዊ ልማት ስራዎችና መንገድን ከመሰሉ የመሰረተ-ልማት ስራዎች ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው:: አንዱ በሌለበት ሌላው ፈጣንና ቀጣይ እድገት ሊኖረው አይችልም:: ከዚህ በተጨማሪ የግብርና ልማት ስራ ከንግድና ፋይናንስ፣ ከኢንዱስትሪና ከመሳሰሉት ዘርፎች ጋር በቀጥታ የተሳሰረ ነው:: እነዚህን አቀናጅቶና አስተሳስሮ መምራት ማለት የአንደኛው ስራ ለሌላው የሚፈጥረውን ምቹ ሁኔታ አውቆ ይህንኑ በላቀ ደረጃ ለመጠቀም የሚያስችል አሰራር መከተል ማለት ነው:: በቅንጅት መስራት ማለት በተጨማሪም ጎን ለጎንና በጋራ ካልተሰሩ በስተቀር ልማታዊ አስተዋፅኦዎቻቸው የሚቀጭጩ ነገሮችን ለይቶ ጎን ለጎንና በጋራ እንዲሰሩ ማድረግ ነው:: የግብርና ልማት ስራችን በዚሁ መልክ የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ መከተል ስላለበት የምንነድፋቸው ፖሊሲዎችና ስትራተጅዎች ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው::

የግብርና ልማት ስራችን የሚመራባቸውን መሰረታዊ አቅጣጫዎች በዚህ መልክ ለይቶ ማስቀመጥ ዝርዝር ስትራተጅዎችንና ፖሊሲዎችን የሚተካ አይሆንም:: ዝርዝር ፖሊሲዎቹና ስትራተጅዎቹ የሚመሩበትን ቅኝት ብቻ ነው ሊያስቀምጥ የሚችለው:: ይህንኑ ተገንዝቦ ዝርዝር ፖሊሲዎችና ስትራተጅዎችን ወደማየት መሸጋገሩ አስፈላጊ ይሆናል::

## 2. የሰው ሃይላችንን ብቃት ማጎልበትና በሰፊው መጠቀም፣

በመግቢያው ላይ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት ስትራተጅያችን በተለይ ደግሞ የግብርና ልማት ስትራተጅያችን የሰው ሃይላችንን የማምረት አቅም በቀጣይነት በማጎልበትና ይህንኑ በሰፊው በልማት ስራ ላይ በማሳተፍ ላይ የተመሰረተ ነው:: የሰው ሃይላችንን የማምረት አቅም ማጎልበት ሲባል በአራት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ያተኮረ ስራ መስራትን የሚጠይቅ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ የሰው ሃይላችንን የስራ ዝግጁነትና ታታሪነት ማረጋገጥ ይጠይቃል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሰው ሃይላችንን የግብርና ስራ ችሎታና ሙያውን ማበልፀግና በቀጣይነት ማሻሻል፣ በዚህ ላይ የተመሰረተ ቀጣይ የግብርና ቴክኖሎጅ እድገት ማረጋገጥ ይጠይቃል:: በሶስተኛ ደረጃ ሰው በትጋትና ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ጤንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል:: በአራተኛ ደረጃ ደግሞ የቴክኖሎጅ አቅርቦት፣ ብዜትና ስርጭትን ማሻሻል ያስፈልጋል:: እነዚህን የሰው ሃይላችንን የማምረት አቅም የማጎልበት ዋነኛ ስራዎች ዘርዘር አድርጎ መመልከት ጠቃሚ ነው::

### 2.1. ታታሪነትና የስራ ዝግጁነትን ማረጋገጥ፣

በአሁኑ ወቅት በግብርና ስራ ላይ የተሰማራው ዜጋ በመሰረቱ ከግብርና ስራ ውጪ ሌላ የስራ አማራጭ አለኝ ብሎ የማያስብ፣ በመሰረቱ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ በመጣ የግብርና ዘይቤ የሚሰራ ነው:: በግብርና ስራ ላይ ለመስራት



የተሚላ ዝግጁነት ያለው ነው:: ይህ በግብርና ሞያ የመሰማራት ዝግጁነት ሌላ አማራጭ ስለሌለ ብቻ የመጣም አይደለም:: ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር የመጣ የስራውና የሞያው ፍቅርም ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም:: ስለሆነም በግብርና ሞያ በሰፊው የመሰማራት ፍላጎት መፍጠርን በተመለከተ ነባሩ የአርሶ አደራችን ትውልድ ብዙ የሚጎድለው ነገር የለውም:: ዝግጁነቱ በመሰረቱ የተረጋገጠ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል::

ዝግጁነቱ ኖሮ ታታሪነቱ ከጎደለ የሰው ጉልበት በግብርና ስራ ላይ አመቱን ሙሉ እንዲሰማራ በስራ ላይ በሚሆንበት ወቅትም ያለመታከትና በትጋት እንዲሰራ ማድረግ ስለማይቻል የግብርና እድገታችን በሚፈለገው መጠን ሊሆን አይችልም:: ምንም እንኳ የህዝባችንን ታታሪነት የሚፈታተኑ በርካታ ጎጅ ባህሎችና ልምዶች ያሉና የስራ ታታሪነት ባህል ከቦታ ቦታ የሚለያይ ቢሆንም በመሰረቱ አርሶ አደር ህዝባችን ታታሪ ሰራተኛ ነው ሊባል ይቻላል:: የጉልበት ስራን የማይጠየፍና ጥሮ ግሮ ኑሮውን ለማሸነፍ የሚጣጣር ነው:: በስራ ባህላችን ላይ የሚታዩ ጉድለቶችንና ከባህልና ልምድ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በአሳማኝና ዴሞክራሲያዊ የአስተሳሰብ ትግል እያስተካከሉ፣ ያለውን የስራ ትጋትና ታታሪነት መጠበቅና በይበልጥ ማጠናከር የሰው ሃይላችንን የማምረት አቅም ለማጎልበት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ጉዳይ ነው:: በዚህ ስራ ላይ የተሰማራውን ነባሩን የአርሶ አደር ትውልድ በይበልጥ ለማትጋት የሚቻለው በግብርና ስራ ላይ ተግቶ በመሰማራት ኑሮውን ያለማቋረጥ ለማሻሻል እንደሚችል በማረጋገጥ ነው:: ምርቱን ለማሳደግ እንዲችል፣ ከሚያመርተው ምርት ዋነኛ ተጠቃሚ እንዲሆን፣ ከዚህም በሚያገኘው ገቢ የኑሮ ደረጃው እንዲሻሻልና ለዚህ የሚያስፈልጉትን ሸቀጦችና አገልግሎቶች

በየጊዜው እየጨመረ በሚሄድ መጠንና አይነት እንዲያገኝ ማድረግም ያስፈልጋል::

ከዚህ አኳያ ዋናው ችግር በተማረውና በወጣቱ ትውልድ አካባቢ ነው:: በርግጥ ተምረው ሌላ የስራ ዕድል ባለማግኘታቸውም ሆነ በሌላ ምክንያት በግብርና ስራ ላይ ተሰማርተው ያልተማረው አርሶ አደር ካለው ዝግጁነትና ታታሪነት ባልተናነሰ ሁኔታ በግብርና ስራ ላይ የተሰማሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች እንዳሉ ይታወቃል:: ይልቁንም ብዙውን ጊዜ እነዚህ ወጣቶች ይህ ነው የሚባል የግብርና ሞያ ስልጠና ባይሰጣቸውም ባገኙት አጠቃላይ ትምህርት ምክንያት ከሌላው በተሻለ አዳዲስ አሰራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ የሆኑና ምርታማነታቸው የላቀ ሆኖ ይገኛል:: ይሁንና በትምህርት ገበታ ላይ ተሰማርቶ የሚገኘው ወጣት በአብዛኛው ከነዚህ የተለየ አመለካከት ያለው ነው::

በገጠርም ሆነ በከተማ በትምህርት ቤት የሚገኘው ወጣት ተምሮ አርሶ አደር ለመሆን፣ በግብርና ሞያ ሰልጥኖ በዚህ መስክ ለመሰማራት ፍላጎት አይታይበትም:: የግብርና ስራን የድህነትና የኋላቀርነት መገለጫ አድርጎ የሚወስደው ወጣት ተማሪ ብዙ ነው:: የጉልበት ስራን የሚጠየፍ፣ ተምሮ እንደግብርና ባሉ የጉልበት ስራን በሚጠይቁ የስራ መስኮች ለመሰማራት የማይፈልገው በርካታው ክፍል ነው:: በትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ትምህርትና የሚያሳድገው ባህል፣ የጉልበትን ስራን ጨምሮ የስራን ክቡርነት የሚያሳምንና የግብርና ሞያም እንደሌላው ክቡር መሆኑን የሚያስገነዝብ አለመሆኑ አንዱ መሰረታዊ ምክንያት ነው:: በግብርና ስራ ላይ ተሰማርቶ የሚያየው ህዝብ በድህነትና በኋላቀርነት የሚገረፍ መሆኑ፣



ተጨባጭ ልምዱና ተመክሮው የሚያረጋግጥለት ነገር በግብርና ስራ መተዳደር ለድህነትና ኋላቀርነት የሚያጋልጥ እንደሆነ ነው::

ወጣቱ ትውልድ በግብርና ሞያ የመሰማራት ዝግጁነትና ይህን ስራ በታታሪነት የመስራት ፍላጎት እንዲያድርበት ካልተደረገ በስተቀር ቀጣይነት ያለው ፈጣን የግብርና እድገት ሊታሰብ አይችልም:: ከዚህ አኳያ ወጣቱ ትውልድ ያሉበትን ችግሮች ከምንጫቸው ማድረቅ መቻል ይኖርብናል:: ትምህርት ቤቶች የስራ ክቡርነትን የሚያሳምኑ፣ ለስራ፣ በግብርናም ሆነ በሌላ መስክ ለሚካሄድ የጉልበት ስራ የሚያዘጋጁ፣ የስራ ታታሪነት ባህልን የሚያዳብሩ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል:: ትምህርት ቤቶቻችን አሁን እንዳለው በአጠቃላይ የጉልበት ስራን በተለይ ደግሞ ግብርናን የሚጠየፍ ወጣት በመፍጠር እስከተሰማሩ ድረስ ፋይዳ ያለው የገጠርም ሆነ ሌላ የልማት ስራ መስራት ሊታሰብ አይችልም:: ከዚህ አኳያ የትምህርት ቤቶቻችን በተለይም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቻችን አሰራር፣ የትምህርት አሰጣጥና የሚያሰርፁት ባህል ተፈትሾ መስተካከል ይገባዋል::

ትምህርት ቤቶች አምራች ታታሪ ዜጋን፣ በግብርና ሞያ ለመሰማራት ፍላጎቱና ዝግጁነቱ ያለው ዜጋን ከመፍጠር አኳያ መጫወት የሚገባቸው ቁልፍ ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ብቻ የሚፈለገው ውጤት ሊረጋገጥ አይችልም:: የግብርና ስራ የኋላቀርነትና የድህነት መናኸሪያ እስከሆነ ድረስ፣ ተጨባጭ ልምዱ የሚያረጋግጥለት ይኸው እስከሆነ ድረስ አማራጭ ጠፍቶ ካልሆነ በስተቀር የሰው ሃይላችንን በፍላጎቱ በግብርና ስራ ላይ እንዲሰማራ ማድረግ አስቸጋሪ ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ነው::

በመሆኑም ተምሮ በግብርና ስራ ላይ የሚሰማራው ወጣት ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ኑሯቸው ከግብርና ውጪ በሆነ ስራ ላይ የተሰማሩ ወጣቶች ከሚያገኙት ያልተናነሰ ገቢ የሚያገኝበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ የግብርና ሙያ ስልጠና አግኝቶ ይህንኑ በመጠቀም ካልተማረው አርሶ አደር እጅግ የተሻለ ምርታማነትና ገቢ የሚያገኝበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡

በማጠቃለል የሰው ሃይላችንን የማምረት አቅም ለማጎልበት በግብርና ስራ ላይ ለመሰማራት ዝግጁነት ያለው ታታሪ ሰራተኛ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከቦታ ቦታ ቢለያይም በነባሩ የአርሶ አደር ትውልድ አካባቢ ከዚህ አኳያ ከፍተኛ ችግር አለ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ አርሶ አደሩ በግብርና ስራ ላይ ተሰማርቶ ኑሮውን በቀጣይነት የሚያሻሽልበትና ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ በመፍጠር የግብርና ስራ ዝግጁነቱንና ተነሳሽነቱን መጠበቅና ማሻሻል የሚገባ ቢሆንም ከዚህ አኳያ ልዩ ትኩረት የሚጠይቀው የወጣቱ ትውልድ ጉዳይ ነው፡፡ ወጣቱ ትውልድ በግብርና ስራ ላይ የመሰማራት ፍላጎትና በትጋት የመስራት ዝግጁነት እንዲኖረው ለማድረግ ትምህርት ቤቶች ታታሪ አምራች ዜጋን የሚያፈሩ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የተማረውና በግብርና ስራ ላይ የሚሰማራው ወጣት ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ይዞ በሌላ የስራ መስክ ከሚሰማራው የማይተናነስ ገቢ የሚያገኝበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡



## 2.2. የግብርና ሙያ ብቃትን ማሻሻል፣

አሁን በግብርና ስራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኘው አርሶ አደር በመሰረቱ የትምህርት እድል ያላገኘ ነው፡፡ በግብርና ስራ ላይ ያለው እውቀትና ሙያም በልምድ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ ነው፡፡ ይሁንና ይኸው እውቀት በቀላሉ የማይገመት ነው፡፡ በልምድ የሚታወቁ የግብርና ዘይቤዎች ተመርጠው መላው አርሶ አደር እነዚህን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው በማስቻል ከፍተኛ የምርት እድገት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከዚህም በላይ በሰርቶ ማሳያዎች ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በማስፋፋት ያልተማረው አርሶ አደር የግብርና ሙያውንና ምርቱን እንዲያሻሻል ማድረግ ይቻላል፡፡ እነዚህን ስልቶች በማጣመር የአርሶ አደሩን የግብርና ሙያ በቀላሉ በማይገመት ደረጃ ማሳደግና ከፍተኛ የግብርና ምርት እድገት ማምጣት እንደሚቻል የራሳችንን ሆነ የሌሎች አገሮችን ልምድ በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

በመሆኑም የአርሶ አደሩን የግብርና ሙያ በማሻሻል ረገድ በመጀመሪያ ደረጃ ሊሰራና ሊተኮርበትም የሚገባው ከላይ በተጠቀሱት ስልቶች አማካኝነት የመላውን ያልተማረ አርሶ አደራችንን የግብርና ስራ ሙያ ማሻሻልና የግብርና ምርትን ማሳደግ ነው፡፡ ይሁንና በዚህ ላይ ተመስርቶ ሊሰራው የሚችለው ስራ የራሱ ውሱንነት አለው፡፡ ያልተማረው አርሶ አደር የአጠቃላይ ትምህርት አቅሙ ደካማ በመሆኑ ምክንያት ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን የመረዳትና የመተግበር አቅሙ ደካማ ነው፡፡ ከሚለዋወጡት ቴክኖሎጂዎች ጋር አብሮ መራመድና ቶሎ ቶሎ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መቀበል

ያስቸግረዋል፡፡ በሰርቶ ማሳያ መልክና በልምድ ካልሆነ በስተቀር በፅሁፍ የሚያገኘው ትምህርት ስለማይኖር አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ለመቅሰምና እነዚህን ማስታወሻውን እያየ ለመተግበር አይችልም፡፡ በአጭሩ ፈጣንና ቀጣይ የግብርና ቴክኖሎጂና የግብርና ዘይቤ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል አቅም ይጎድለዋል፡፡ ይህን የመሰለውን ለውጥ ማረጋገጥ የሚቻለው በተማረ ትውልድ ላይ በመመስረት ብቻ ነው፡፡

በመሆኑም ያልተማረው አርሶ አደር ሊያስገኝ የሚችለውን የላቀ የግብርና እድገት አሟጠን ለመጠቀም ከመረባረብ ጎን ለጎን በተማረ የአርሶ አደር ትውልድ ለመተካት መስራት ይኖርብናል፡፡ እንዲህ አይነቱ የተማረ የአርሶ አደር ትውልድ ሊፈጠር የሚችለው አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጅዎችን በቀጣይነት ለመማርና ለመተግበር የሚያስችለው፣ አንብቦ ለመረዳትና በማስታወሻው ላይ ተመስርቶ የግብርና ስራውን በሳይንሳዊ አኳኋን ለመፈፀም የሚያስችለው አጠቃላይ ትምህርት የተማረ መሆን ይገባዋል፡፡ ቢያንስ በአሁኑ ወቅት እየተሰጠ ያለውን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማረ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ ብቻም በቂ አይሆንም፡፡ የግብርና ስራውን በብቃት ለመፈፀም የሚያስችለው የግብርና ሞያ ስልጠና ያገኘ መሆንም ይኖርበታል፡፡

ይህን የመሰለውን የአርሶ አደር ትውልድ ለመፍጠር በአሁኑ ወቅት በገጠር በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ ያለው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በጣም የተመቻቸ ሁኔታን



ይፈጥርልናል፡፡ በያዝነው አመት መጀመሪያ በአንደኛ ደረጃ መማር ከሚገባው ዜጋ ውስጥ ከ57% የማያንሰው በትምህርት ገበታ ላይ ነው፡፡ እስካሁን የተገኘው ውጤት በተያዘው የአምስት አመት እቅድ የተቀመጠው የ65% ግብ እንደሚሳካ ያረጋግጣል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እየተስፋፋ ያለው በከተማ ቢሆንም አብዛኛው እድገት እየተመዘገበ ያለው በገጠር ነው፡፡ እጅግ የሚበዛው የገጠር ወጣት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚማርበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ይህ ወጣት በሙሉ ከግብርና ስራ ውጪ ስራ ይያዝ ቢባል በፍፁም ሊሆን አይችልም፡፡ ከአጭር ጊዜ አኳያ መላውን የገጠር ወጣት ሊሸከም የሚችል የከተማ እድገትና የስራ ዕድል በምንም ተአምር ሊፈጠር የሚችል አይደለም፡፡ አብዛኛው የገጠር ተማሪ ከግብርና ስራ ውጪ የስራ ዕድል ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም በገጠር ከሚማረው ወጣት ውስጥ ከ70% የማያንሰው በግብርና ስራ መሰማራት ይኖርበታል፡፡ ይህ ወጣት በግብርና ሙያ ላይ መሰማራት ያለበት ግን ሌላ የስራ አማራጭ አይገኝለትም በሚል ሂሳብ ብቻ አይደለም፣ መሆንም አይገባውም፡፡

ይህ ወጣት በግብርና ስራ ላይ መሰማራት ያለበት በአገራችን ፈጣን ልማት ለማምጣት ያለን ብቸኛ አማራጭ ግብርናን ማዕከል በማድረግ የሚካሄድ ልማት በመሆኑና ይህንኑ ቀጣይነት ባለውና ፈጣን በሆነ አኳኋን ለማረጋገጥ የሚቻለው አሁን ከምንጠቀምበት የግብርና ቴክኖሎጂና የአመራረት ዘይቤ እጅግ የላቀ የአመራረት ዘይቤ

የሚጠቀም፣ ይህንኑ በቀጣይነት ለማሻሻል የሚችል የአርሶ አደር ትውልድ ሲኖር ብቻ በመሆኑም ጭምር ነው:: ይህ የተማረ ወጣት ለአገራችን ልማት የላቀ አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችለው በዚሁ መስክ ሲሰማራ ብቻ በመሆኑም ጭምር ነው:: ይህ ወጣት የግብርና ሙያ ስልጠና አግኝቶና ሌሎችም አስፈላጊ ድጋፎች ተሟልተውለት ከተሰማራ ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ጋር የማይተናነስ ገቢ ማግኘት ስለሚችልና በዚህም ኑሮውን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል ስለሚችል ነው:: በአጭሩ የተማረው የገጠር ወጣት በዋነኛነት በግብርና ስራ ላይ መሰማራት የሚኖርበት አገሪቱን ጠቅሞ ራሱን ለመጥቀም የሚችልበት የተሻለውና ብቸኛውም አማራጭ ይኸው ስለሆነ ጭምር ነው::

አሁን በገጠርም በከተማም እየተሰጠ ያለው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አጠቃላይ እውቀትን በማስጨበጥ ረገድ በቂ ሊባል የሚችል ነው:: ከዚህ አኳያ በተለይም ጥራቱን በሚመለከት መሻሻል የሚገባው ነገር የለም ባይባልም እንደዋነኛ ጉድለትና ችግር ሊቆጠር የሚችለውና የሚገባው ከስነ-ዜጋ ትምህርት አኳያ ያለበት ችግር ነው:: በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚገባው ችግር የስራ ክቡርነትን ከማስረፅ፣ በግብርና ስራ በታታሪነት ለመሰማራት የተሟላ ዝግጁነት ያለው ወጣት አንፆ ከማውጣት አኳያ ያለው ችግር ነው በአሁኑ ሰአት ትምህርት ቤቶቻችን እየፈጠሩ ያሉት በአጠቃላይ የጉልበት ስራን በተለይ ደግሞ የግብርና ስራን የሚጠየፍ ወጣት ነው:: የተሟላ የስነ-ዜጋ ትምህርት በመስጠት ላይ ከፍተኛ ችግር አለ:: ይህ ችግር በተቻለ ፍጥነት መስተካከል ይገባዋል:: በፍጥነት ካልተስተካከለ



በስተቀር የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በከፍተኛ ደረጃ በማስፋፋት ያገኘነውን ታላቅ የልማት ድል፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ልማትን ለማረጋገጥና ህዝቡ ከዚህ ልማት በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ልንጠቀምበት አንችልም:: ያ ድል ፋይዳ የሌለው ድል ሆኖ ሊቀርና ከፍተኛ ማህበራዊ ችግር ሊፈጥርም ይችላል::

በዚህ አኳኋን የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ተምሮ በግብርና ስራ ለመሰማራት ዝግጁ የሆነው ወጣት በቀጥታ ወደ ግብርና ስራ ይግባ ቢባል የሚያስገኘው የምርታማነት እድገት ይህን ያህል የሚያረካ አይሆንም:: የተሻለ ውጤት ሊኖር የሚችለው ይህን ወጣት በአጫጭር የግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋሞች አስገብቶ በአጭር ጊዜ (ከ3 ወር እስከ 6 ወር) በማሰልጠን አስተማማኝ የግብርና ሞያ ችሎታ እንዲኖረው በማድረግ ነው:: በመሆኑም በየቀበሌው የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማስፋፋት የተረባረብነውን ያህል በየቀበሌው የግብርና ሞያ ስልጠና ተቋማትን ለማደራጀትም መስራት ይኖርብናል::

በአሁኑ ጊዜ ይህን በተመለከተ የተቀመጠው ስትራቴጅ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ወጣቶችን መልምሎ በግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች የሶስት አመት የግብርና ስልጠና መስጠት ነው:: በዚህ አኳኋን ከሰለጠኑት ውስጥ ቢያንስ ሶስት (አንድ በአዝርእት፣ አንድ በእንስሳት ሃብት አንድ በተፈጥሮ ሃብትና መስኖ ልማት የሰለጠኑ) ሰዎችን በየቀበሌው መመደብ ነው:: በየቀበሌው የሚመደቡት እነዚህ ሙያተኞች ሁለት ስራዎችን ደርበው ይሰራሉ:: በመጀመሪያ ደረጃ በቀበሌው ላሉ አርሶ አደሮች ሁሉ፣

www.abyssinialaw.com

ለተማሩትም ላልተማሩትም ከግብርና ሞያ እውቀታቸው ጋር የሚመጥን የግብርና ኤክስቴንሽንና የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ። በዚህም ምክንያት የግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ይሆናሉ። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ በየቀበሌው በሚሰራው የሰርቶ ማሳያ ጣቢያ፣ የተማሩ ወጣቶችን እየተቀበሉ የግብርና ሞያ ስልጠና ይሰጣሉ። በዚህም የግብርና ሙያ አሰልጣኞችና መምህራን ይሆናሉ።

በዚህ አኳኋን በአንድ በኩል ያልተማረው አርሶ አደር ባለው አቅም በላቀ ደረጃ እንዲያመርት ለማድረግ የተሟላ የግብርና ኤክስቴንሽንና የምክር አገልግሎት በመስጠት፣ የማምረት አቅሙን እያጎለበትን፣ በሌላ በኩልና ከዚሁ ጎን ለጎን ለግብርና ቴክኖሎጂ ቀጣይ እድገትና ለግብርና ልማታችን መፋጠን መሰረት የሚሆን የተማረና የሰለጠነ የአርሶ አደር ትውልድ እንዲፈጠርና ይህም ሃይል ከደረጃው ጋር የሚመጥን የተሟላ የግብርና ኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት እንዲያገኝ እናደርጋለን። አንድ እግር በመሬት አድርገን በመረማመድ የአርሶ አደር ህዝባችንን የማምረት አቅም በትምህርትና ስልጠና በቀጣይነት እናጎለብታለን።

## 2.3. የአርሶ አደሩን ጤንነት ማረጋገጥ፣

አርሶ አደሩ ቢማርም ባይማርም ጤንነቱ እስካልተጠበቀ ድረስ በምርት ተግባር ላይ ሊሰማራ አይችልም። አማራጭ አጥቶ እየወደቀ እየተነሳ በምርት ተግባር ላይ እንዲሰማራ ቢደረግም የሚያመረቃ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም። ስለሆነም የአርሶ አደሩ ጤንነት፣ እንዲረጋገጥ ማድረግ የአርሶ አደሩን የማምረት አቅም የማጎልበት ስራ



እንደ ቁልፍ አካል ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል። ጤንነቱ የተጠበቀ አምራች ዜጋ ከመፍጠር ውጪ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት በገጠርም በከተማም ሊታሰብ የሚችል አይሆንምና።

የአርሶ አደሩን ጤንነት ለመጠበቅ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በሽታን በመከላከል ላይ ያተኮረና በመሰረተ-ጤና አገልግሎት ላይ ያተኮረ የጤና አገልግሎት ስርአት መዘርጋት ይኖርብናል። በሽታን አክሞ የማዳን ስራም መሰራት ያለበት ቢሆንም ይህ አማራጭ በኛ አገር ሁኔታ ቢፈለግም ባይፈለግም ዋነኛው አማራጭ ሊሆን ከቶ አይችልም።

በሽታን መከላከል ለመድሃኒት፣ ለህክምና ቁሳቁስና ለሞያተኞች ከፍተኛ ወጪ ማውጣት በማይጠይቅ አኳኋን የአንድን ዜጋ ጤንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው። ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት ባለባት አገራችን በሽታን አክሞ በመፈወስ ላይ ያተኮረ የጤና አገልግሎት እንስጥ ብንል በፍፁም የሚሆን አይደለም። በምንም ተአምር ለሁሉም ዜጋ ሊዳረስ አይችልም። በፊትም እንደነበረው ድሃውና የገጠሩ ህዝብ ከህክምናውም ከመከላከሉም ሳይሆን እንዲቀር የሚያደርግ ነው።

በጤና እንክብካቤ ረገድ ዋናው ነገር ዜጋው ከበሽታ ነፃ ሆኖ ሰርቶ መኖር እንዲችል ማድረግ ነው። ይህን ሁኔታ መከላከሉንና የመሰረተ ጤና አገልግሎቱን በሁለተኛ ደረጃ አስቀምጦ የህክምና አገልግሎት በመስጠት ለማቋቋም ቢፈለግ ከሚያስከትለው ቀጥተኛ ወጪ በተጨማሪ ከፍተኛ

www.abyssinialaw.com

ጉዳትን የሚያስከትል ይሆናል፡፡ ሰው ታሞ ታክሞ እስኪድን ድረስ ከስራ ውጪ ይሆናል፡፡ ታክሞ ድኗል በሚባልበትም ወቅት ከፍተኛ የአካል መጎሳቆል ደርሶበት ለማገገም ረጅም ጊዜ ሊጠይቀው ይችላል፡፡ ሙሉ በሙሉ ሳይድን ሊቀርም ይችላል፡፡ ይህ በምርት እንቅስቃሴው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው፡፡ በዚህ ላይ አነሰም በዛም ለህክምና አገልግሎት የሚያወጣው ወጪ መኖሩ አይቀርም፡፡ ስለሆነም ታሞ መታከምን እንደዋነኛ አማራጭ መውሰድ የልማት እንቅስቃሴያችንን ክፉኛ የሚያቀጭጭ በዜጎች ላይ ከፍተኛ የአካል፣ የአእምሮና የኢኮኖሚ ደረጃ መጎሳቆልን ማስከተሉ የማይቀርን አማራጭ እንደዋነኛ አማራጭ መውሰድ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በመከላከልና በመሰረተ-ጤና አገልግሎት ላይ ያተኮረ የጤና አገልግሎት ከመዘርጋት ውጪ አማራጭ ሊኖረን አይችልም፣ አይገባምም፡፡

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ህዝቡን ከሚያጎሳቁሉት በሽታዎች ውስጥ ከ80% የማያንሱት ብቃት ባለው በሽታን የመከላከል እንቅስቃሴ ሊወገዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህን በሽታዎች በህክምና ለማስወገድ መሞከር ቀዳዳ በርሜልን የመሙላት ያህል የማይሆን ነገር ነው፡፡ የበሽታዎቹ መንስኤዎች በመከላከል መወገድ ሲገባቸውና ሲችሉ በዚህ አማካኝነት ሳይወገዱ ቀርተው በህክምና ቢፈወሱም ምንጫቸው እስካልደረቀ ድረስ እንደገና እያገረሹ ታክሞ የዳነውን ሰው መበከላቸው አይቀርም፡፡

በመሆኑም የተሻለው አማራጭ በመከላከልና በመሰረተ-ጤና አገልግሎት ላይ ያተኮረው የጤና



አገልግሎት ነው፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከዚህ ውጪ በህክምና ላይ ያተኮረ የጤና አገልግሎት ይኑር ቢባልም ተግባራዊ ሊሆንና ሊፈፀም የሚችል አይደለም፡፡ ህብረተሰቡ በሽታን የመከላከል የተወሰኑ ስራዎች በመስራት ጤንነቱን ማረጋገጥ ሲችል ይህን ሳያደርግ በመቅረቱ ለበሽታ የሚጋለጥበትን ምክንያት እየለዩ በዚህ ላይ የተመሰረተ የጤና አገልግሎት ስራ መስፋፋት ይኖርበታል፡፡

ህዝቡ የግልና የአካባቢ ንፅህናን በመጠበቅ፣ የአካባቢ ንፅህናን በማሻሻል፣ አመጋገቡን በማሻሻልና የክትባት አገልግሎትን በማግኘት እጅግ የሚበዙትን በሽታዎች ማስወገድ ሲችል ይህን ሳያደርግ የሚቀርበት አንዱ ምክንያት ድህነት ነው፡፡ በተለይም አመጋገቡን ከማሻሻል አኳያ ድህነት ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያሳድርበት ይታወቃል፡፡ የአካባቢና የግል ንፅህናን በመጠበቅ፣ የክትባት አገልግሎትን በሚፈለገው ደረጃ ከማስፋፋት አኳያም ቢሆን ድህነት የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ማሳረፉ አልቀረም፡፡ ዋናው ችግር ግን ድህነት አይደለም፡፡ ዋናው ችግር የአስተሳሰብና የባህል ችግር፣ የእውቀት ችግር ነው፡፡

ህዝቡን ለተለያዩ በሽታዎች የሚያጋልጡት በርካታ ኋላቀር ባህሎችና አስተሳሰቦች ያሉት መሆኑ ሊካድ አይችልም፡፡ የግል ንፅህናንና የአካባቢ ንፅህናን በመጠበቅ ረገድ ዋናው ችግርም ይህ ነው፡፡ አመጋገቡን በማሻሻል ጉዳይም ላይ ኋላቀር ባህሎችና አስተሳሰቦች ቀላል ያልሆነ ተፅእኖ አላቸው፡፡ ህዝቡ ጤንነቱን መጠበቅ የሚፈልግ ቢሆንም ወሳኙ የጤንነቱ መጠበቂያ መሳሪያ የህክምና መሳሪያ ሳይሆን የራሱ የአኗኗር ዘይቤ፣ የራሱና የአካባቢው ንፅህና መሆኑን በሚገባ

አይገነዘብም። የጤና አገልግሎትን በሚመለከት ያለው አመለካከትም በአብዛኛው ሲታመም መርምሮ ክኒን የሚሰጠውን ወይም መርፌ የሚወጋውን እንጂ በሽታን እንዴት መከላከል እንዳለበት የሚያስተምረውን የሚያስመኘው አይደለም። በመሆኑም በህዝቡ አካባቢ ያለው አስተሳሰብና ባህል መከላከልን ማዕከል ያደረገ የጤና አገልግሎት ተግባራዊ እንዳይሆን ከፍተኛ እንቅፋት ነው።

በጤና አገልግሎት ሙያተኞች አካባቢ ያለው አስተሳሰብም ቢሆን ለዚሁ አቅጣጫ ተግባራዊነት የተመቻቸ አይደለም። በርግጥ ሞያተኞቹ በህክምና ላይ ያተኮረ አገልግሎት ከመስጠት ይልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ለመከላከል እንደሆነ የሚቀበሉት አባባል ነው። መከላከልን ማዕከል ያደረገ የጤና ፖሊሲ ሊኖረን ይገባል ሲባል የሚቃወም ሞያተኛም ቁጥሩ በጣም አነስተኛ ነው። ለማለቱ ያህል ሁሉም የሚለው ነው። ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ የነበሩት መንግስታት ሁሉ ይህንን ፖሊሲ እንከተላለን ብለውም ለፍፈዋል። በተጨባጭ በተግባር ሲታይ ግን የመከላከል ስራ የጤና አገልግሎት ስራችን ማዕከል ሆኖ አጥጋቢ ውጤት በሚያስገኝ አኳኋን አልተፈፀመም። ሙያተኛውም ለዚህ ስራ እንዲበቃ ተብሎ ለስልጠና ሲመደብ ይህንን ትቶ መማር የሚፈልገው ማከምን ነው። ማከምን ካልተማረ በስተቀር የጤና አገልግሎት ሞያተኛ ያልሆነ የሚመስለውም ጥቂት አይደለም።

መከላከልን ማዕከል ያደረገ ፖሊሲ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ድህነት የሚፈጥረው ተፅእኖ በሂደት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት በማረጋገጥ ብቻ የሚፈታ ይሆናል። ከዚህ አኳያ ዋነኛው ችግር የአስተሳሰብና የባህል ችግር በመሆኑ



በህዝቡም ሆነ በሙያተኞች አካባቢ ያለውን ያልተስተካከለ አመለካከትና ባህል በማስወገድ ችግሩ በወሳኝነቱ ሊወገድ ይችላል። በመሆኑም ጤናማና አምራች ዜጋን ከመፍጠር አኳያ የመጀመሪያውና ወሳኙ ርምጃ የመከላከልንና የመሰረተ-ጤና አገልግሎትን ወሳኝነት የማይቀበሉ አስተሳሰቦችና ባህሎችን በቀጣይ የማስተማርና የማሳመን እንቅስቃሴ ማስተካከል ነው። ይህ ወሳኝ ስራ በተሳካ ሁኔታ ካልተፈፀመ በስተቀር መከላከልንና የመሰረተ ጤና አገልግሎትን ማዕከል ያደረገ የጤና አገልግሎት ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግም ሆነ ጤናማ አምራች ዜጋ መፍጠር በፍፁም የሚቻል አይሆንም።

አስተሳሰብን ለመቀየር ከመረባረብ ውጪ የሚሳካ የዜጎችን ጤንነት የመጠበቅ ስራ ባይኖርም፣ ስራው አስተሳስብን በመቀየር ብቻ ይጠናቀቃል ብሎ ማሰብ አይቻልም። መከላከልንና የመሰረተ-ጤና አገልግሎትን ማዕከል ያደረገውን የጤና ፖሊሲ በተሟላና በተሳካ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስችል ዝርዝር እቅድና አስፈፃሚ አካል ያስፈልጋል። በገጠሩ አካባቢ ይህን ስራ የሚያስፈፅመው የመጀመሪያው ረድፍ ተዋጊ ጤና ኬላ ነው።

በፖሊሲ ደረጃ አምስት ሺ የሚሆን ህዝብ ባለበት አካባቢ ሁሉ አንድ የጤና ኬላ መቋቋም ይኖርበታል። ከሞላ ጎደል ሁሉም ቀበሌዎች በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ በመሆናቸው በየቀበሌው የጤና ኬላ መመስረት ይኖርበታል ማለት ነው። የጤና ኬላዎችን ለማስፋፋት ሲፈለግ በአንድ በኩል የገንዘብ አቅም ችግር በመኖሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአመለካከት መዛባት ምክንያት ከማንኛውም ሌላ የጤና

www.abyssinialaw.com

አገልግሎት ተቋም ቀድሞ የጤና ኬላዎችን በየቀበሌው ከመገንባት ይልቅ ውድ የሆኑ ሆስፒታሎች በመገንባት ስራ ላይ የማተኮር አጋጣሚዎች በመከሰታቸው ብዙ ቀበሌዎች የጤና ኬላ የላቸውም፡፡ በዚህ ረገድ የነበረውን የባጀት አመዳደብ መዛነፍና ለዚህም መንስኤ የሆነውን የአስተሳሰብ መዛባት አስተካክለን፣ ህዝቡ የጤና ኬላዎችን በመገንባት ስራ ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ በማነሳሳት ረጅም ባልሆነ ጊዜ ውስጥ ሁሉም ቀበሌዎቻችን የጤና ኬላ እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል፣ ይገባልም፡፡

የጤና ኬላዎች ስራ በሽተኛን ማከም አይደለም፡፡ ከህክምና አኳያ የሚሰጧቸው እጅግ ቀላል የሆኑ አገልግሎቶች ቢኖሩም ስራቸው በመሰረቱ የመከላከል ስራውን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ህዝቡን በማስተማር የግልና የቤት ንፅህናውን እንዲጠብቅ፣ አመጋገቡን እንዲያሻሽል ማድረግ ነው፡፡ ህዝቡን በማስተባበር የአካባቢ ንፅህናን በመጠበቅ ጤናማ የኑሮ አካባቢን መፍጠር ነው፡፡ ለህዝቡ የተሟላ የክትባት አገልግሎት በመስጠት በሽታን መከላከል ነው፡፡ የተሟላ የእናቶችና የህፃናት እንክብካቤ፣ የወለድ አገልግሎት ወዘተ. በመስጠት የህዝቡን ጤንነት ማረጋገጥ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ ይህን አገልግሎት በመስጠት ረገድ በርካታ ችግሮች አጋጥመዋል፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሰው የጤና ኬላዎች በሚፈለገው መጠን አለመስፋፋት አንድ ችግር ነው፡፡ በተቋቋሙት ኬላዎች የተመደበው የሰው ሃይል የመካለከል አገልግሎትን በመስጠት ስራ በቂ ስልጠና ያልተሰጠውና አብዛኛውም በህክምና አገልግሎት ካልተሰማራ በስተቀር ቀጣይ እድገት ያለው ሞያተኛ መሆን የማይችል የሚመስለው፣



በመከላከል ስራው ላይ የተሟላ እምነትና ተነሳሽነት የሌለው ነው፡፡ የተሟላ የክትባት፣ የእናቶችና ህፃናት እንክብካቤ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ስርአት በሚገባ አለማሟላቱና ብዙዎቹ ተቋሞች ይህንኑ ለማስፈፀም የሚያስችል ቁሳቁስ የሚጎድላቸው መሆኑም ሌላው ችግር ነው፡፡ የመከላከል ስራውን በፕሮግራም መልክ ቀርፆ ህዝቡን በዚህ ዙሪያ ለማስተማርና በተጨባጭ ተግባራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ብቃት ያለው ስልት አለመቀመጡም ሌላው ችግር ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች ሳንፈታ በሽታን የመከላከል እንቅስቃሴያችንን አጥጋቢ በሆነ መንገድ መፈፀም አይቻልም፡፡

ከማንኛውም የጤና አገልግሎት ተቋም በላይና ከሁሉም በፊት ለጤና ኬላዎች ቅድሚያ የመስጠት አመለካከት በሁሉም አስፈፃሚ አካላት በተለይም በክልልና በወረዳ መሪዎች እንዲጨበጥ በማድረግ ህዝቡ በጤና ኬላዎች ግንባታ ላይ በሰፊው እንዲሳተፍና ጤና ኬላዎቹ የተሟላ ቁሳቁስ እንዲኖራቸው በማድረግ በዚህ ረገድ ያለውን ችግር በአፋጣኝ መቅረፍ ያስፈልጋል፡፡ የጤና ኬላዎች በሁሉም ቀበሌዎች የሚቋቋሙበትን ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ማፋጠን ይችላል፣ ይገባልም፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የክትባት አገልግሎት ስርአታችን እስከቀበሌ ድረስ የሚዘረጋበትና የሚጠናከርበት ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

በጤና ኬላዎች ተመድበው የሚሰሩ ሞያተኞች ስራቸው በመሰረቱ ተለይተው የተቀመጡ የመከላከል ስራዎችን መፈፀም እንደሆነ ጠንቅቀው የሚያውቁ በስራው ላይ የተሟላ እምነት ያላቸው፣ የመከላከል ስራውን በብቃት ለማስፈፀም፣ ህዝቡን ለማስተማር ለማሳመንና በሽታን በመከላከል ዙሪያ ለማነሳሳት የሚችሉ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ስልጠና ማግኘት አለባቸው፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህ ደረጃ በቂ የአስተሳሰብና የሞያ ብቃት ያላቸውን ሞያተኞች መፍጠርና በየቀበሌውም ማሰማራት የጤና ፖሊሲዎቻችንን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ከሁሉም ስራዎች በላይ ወሳኙ ይኸው መሆኑ ታውቆ ለዚህ ስራ በቂ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የመከላከል ስራን በተሟላ መልክ ለማስፈፀም በህዝቡ ውስጥ የባህልና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣትን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የላቀ ሚና ያላቸውን እናቶች አደራጅቶና አሳምኖ የግል የቤት ንፅህናንና አመጋገብን በሚመለከት ተጨባጭ የለውጥ ርምጃዎች እንዲወስዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚከናወኑትን ስራዎች በየጊዜው እየገመገሙ ማጠናከርን ይጠይቃል፡፡ ስራው የእናቶች ብቻ ሳይሆን የመላው ቤተሰብ ስራ ጭምርም ስለሆነ በትምህርት ቤትም፣ በየስራና ስብሰባ ቦታውም ህዝቡ በሽታን ለመከላከል መወሰድ በሚገባቸው ርምጃዎች ላይ የተሟላ ግንዛቤ እንዲይዝ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የቀበሌ አመራሮች በዚህ ጉዳይ ላይ የተስተካከለ ግንዛቤ ይዘው ህዝቡን እንዲያነሳሱና የአካባቢ ንፅህናን በመጠበቅ ረገድ በህዝቡ ተሳትፎ ተጨባጭ ርምጃዎችን እንዲወስዱ ማድረግም ያስፈልጋል፡፡ በሌላ አነጋገር የህዝቡን አስተሳሰብና አኗኗር በመቀየር የመከላከል ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሽታን ለመከላከል መወሰድ ስላለባቸው አንዳንድ ርምጃዎች ህጎችና መመሪያዎች ወጥተው ተግባራዊ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ስራ በተሟላ ሁኔታ ሊያግዝ ይችላል ተብሎ የተገመተውን በያዝነው አመት በተለያዩ አካባቢዎች እየተሞከረ ያለው የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ነው፡፡ ይህ ስልት ከግብርና ኤክስቴንሽን ስልት ጋር በብዙ መልኩ



የሚመሳሰል ነው፡፡ በየሰርቶ ማሳያ ጣቢያው የሚመደብ የግብርና ሞያተኛ የሚሰራው መሆኑ ቀርቶ በየጤና ኬላው የሚመደብ የመከላከል አገልግሎት ሞያተኛ የሚያስፈፅመው ይሆናል፡፡ እንደግብርናው ሁሉ የመከላከል አገልግሎት ፖኬጅ ተዘጋጅቶ የሚመለከታቸው ሁሉ ፖኬጁን አውቀውና አምነውበት በየቤታቸውና በጋራ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ይደረጋል፡፡ የጤና ኬላ ሞያተኛውም አፈፃፀሙን በቅርብ እየተከታተለና እየገመገመ ያጠናክራል፡፡ በዚህ መልክ አንድ -ኬጅ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ተጨማሪ ሌላ -ኬጅ በተመሳሳይ መልኩ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ይህን አሰራር በተጀመረው መልኩ በተወሰኑ አካባቢዎች ሞክሮ ከዚሁ በሚገኝ ልምድ አሻሽሎና አስተካክሎ በሁሉም ቀበሌዎች በሰፊውና በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ለመካለከል ስራችን ስኬታማነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው መገመት ይቻላል፡፡

በሽታን ለማስወገድና ጤናማና አምራች ዜጋ ለመፍጠር በሚካሄደው ትግል፣ ወሳኙ መድረክ የጤና ኬላ፣ ወሳኙ አንቀሳቃሽ ሃይል የጤና ኬላ ሞያተኛ ዋናው ፈፃሚ ህዝቡና በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ያሉ መሪዎች፣ ወሳኙ የትግል መልክ አስተሳሰብና ባህልን በመለወጥ የህዝቡ አኗኗር በሽታን ለመከላከል የሚያስችል እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህ ትግል በአግባቡ ካልተከናወነና በተሳካ አኳኋን ካልተፈፀመ በስተቀር ኤች አይ ቪ ኤይድስ በገጠር እንዳይስፋፋ መከላከልን ጨምሮ የትኛውንም በሽታን የመከላከል ስራ በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀም አይቻልም፡፡ ይህ ብቻውን ግን በቂ አይሆንም፡፡ በየጤና ኬላው የሚደረገውን የመከላከል ስራ በቅርብ የሚደግፍና የሚያስተባብር፣ ከመከላከል ስራው ጋር የተያያዙ መስረታዊ የሆኑ የመሰረተ ጤና አገልግሎቶችን የሚሰጥ በጤና ኬላ ከሚሰማራው ሞያተኛ የላቀ

ሞያ ያላቸው ሰዎችን ያቀፈ የጤና ጣቢያ ማቋቋምና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

በእቅድ ደረጃ ለ25ሺ ሰዎች አንድ የጤና ጣቢያ እንዲኖር ነው የሚፈለገው። የጤና ጣቢያ መስፋፋትን በሚመለከትም በጤና ኬላ መስፋፋት ላይ የታዩት ችግሮች ታይተዋል፣ መፈታትም ይኖርባቸዋል። መጀመሪያ ላይ አንድ የጤና ጣቢያ ከአምስት በላይ የጤና ኬላዎችን እንዲደግፍና እንዲያስተባብር በማድረግም መስራት ይቻላል። ይህ በሂደት በይበልጥ እየተሟላ መሆን ወደሚገባው ደረጃ ሊደርስ ይችላል። እዚህም ላይ ለጤና ኬላዎች በተቀመጠው መልኩ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል።

ከጤና ጣቢያ በላይ በጤና ጣቢያው ከሚሰጠው መሰረታዊ የህክምና አገልግሎት የላቀና የተሟላ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ሆስፒታሎች መኖር ይገባቸዋል። የገጠሩን ህዝብ ጤንነት ከመጠበቅ አኳያ ወሳኞቹ ግን የጤና ኬላና የጤና ጣቢያ ናቸው። በመሆኑም በባጀት አመዳደብም ሆነ በሌላው ነገር ሁሉ ቅድሚያ ለጤና ኬላ ከዚያ ቀጥሎ ለጤና ጣቢያ መስጠት ያስፈልጋል። መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጤና ኬላዎችና ጤና ጣቢያዎች ለማስፋፋት የሚያደርጉት ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ የግል ባለሃብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሆስፒታል ግንባታ ረገድ በሰፊው እንዲሳተፉ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ህዝቡም በጉልበቱና በንብረቱ ሆስፒታሎችን በመገንባት ስራ ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ጥረት መደረግ አለበት። መንግስትም ዋነኛውን ትኩረቱን ሳይስት በዚህ ስራ ላይ የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይኖርበታል።



## 2.4. የቴክኖሎጅ አቅርቦት፣ ብዜትና ስርጭትን ማሻሻል፣

ጤንነቱ የተጠበቀ የስራ ፍላጎቱና ታታሪነቱ የተረጋገጠና በቂ ትምህርትና ስልጠና ያለው አርሶ አደር መፍጠር ለግብርና ልማታችን ወሳኙ መሰረት ቢሆንም ይህም ሃይል ሆነ ያልተማገረው አርሶ አደር ምርታማነቱን ለማሳደግ የሚያስችለው የቴክኖሎጂ አቅርቦት ካላገኘ፣ ቴክኖሎጂው በሚፈለገው መጠን ካልተባዛና በአግባቡ ወደ አምራቹ ካልተሰራጨ የሚፈለገው እድገት ሊገኝ አይችልም። በመሆኑም የቴክኖሎጅ አቅርቦት፣ ብዜትና ስርጭትን የማሻሻል ጉዳይ የህዝቡን የማምረት አቅም ከማጎልበት ተግባር ተነጥሎ የማይታይ ጉዳይ ይሆናል።

የሚመረጠውና የሚቀርበው ቴክኖሎጂ የግብርና ምርታማነታችንንና የዚህን የእድገት አቅጣጫ የሚወስን ነው። በመሆኑም በቀጣይነት የሚቀርብና ያለማቋረጥ የሚሻሻል ብቻ ሳይሆን በጥንቃቄ የሚመረጥም ይሆናል። የተገኘውን ቴክኖሎጂ በማግበስበስ የምንፈልገውን የግብርና ልማት ማረጋገጥ አንችልም። የግብርና ቴክኖሎጂያችን የግብርና ልማት አላማችንን ማሳካት ይችል ዘንድ የሚከተሉት ባህሪያት ሊኖሩት ይገባል።

የግብርና ልማት ስትራተጅያችን የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበት ይህንኑ በላቀ ደረጃ የመጠቀም ስትራተጅ ነው። ይህን ስትራተጅ በተሳካ አኳኋን ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው የምንመርጠው ቴክኖሎጅ የሰው ሃይልን በካፒታልና በተራቀቀ ማሽነሪ የሚተካ ሳይሆን ይህን የሰለጠነ የሰው ሃይል በሰፊው በመጠቀም ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። ጉልበትን

www.abyssinialaw.com

በሰፊው በመጠቀም በውሱን መሬት የላቀ መጠንና ዋጋ ያላቸውን ምርቶች ለማምረት የሚያስችለን ቴክኖሎጅ ነው መሆን ያለበት፡፡ ምንም እንኳ ሰፋፊ መሬት ባላቸው የአገራችን አካባቢዎች በሰፋፊ እርሻዎች የግብርና ዘይቤ (Extensive Farming Method) የምንጠቀምበት ዕድል ሊኖርና በዚህም ምክንያት ከዚሁ ጋር አብሮ የሚሄድ ቴክኖሎጂ መጠቀማችን ባይቀርም እጅግ የሚበዛው ህዝባችን በተሰማራበት አካባቢ የምንመርጠው ቴክኖሎጂ በውሱን መሬት የላቀ ጉልበት በመጠቀም የበለጠ ምርት የማግኘት ዘይቤ (Intensive Farming Method) ነው፡፡ የምንመድበው ቴክኖሎጂም ከዚሁ ጋር አብሮ የሚሄድ መሆን አለበት፡፡

ካስቀመጥነው መሰረታዊ የኢኮኖሚ አላማ ገፅታዎች አንዱ የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚን መገንባት ነው፡፡ የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ ይህንን አላማ የሚያሳኩና በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ መርሆዎች የሚመሩ መሆን አለባቸው፡፡ የግብርና ልማታችንም ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም፡፡ የግብርና ቴክኖሎጂያችን አርሶ አደሮች በገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በማምረት በተፈላጊው ጥራትና ተወዳዳሪ በሆን ዋጋ ሸጠው ለመጠቀምና በዚህም ሂደት ገበያቸው በቀጣይነት እንዲያድግ የሚያስችላቸው መሆን አለበት፡፡ በገበያ ተፈላጊነት የሌላቸው ምርቶች ቴክኖሎጂው ስለተገኘ ወይም ልናመርታቸው ስለቻልን ብቻ ብናመርት ለቀጣይ እድገታችን መሰረት ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በገበያ ተፈላጊነት ኖሮትም ቢሆን ያለን ቴክኖሎጂ ምርቱን በተፈላጊው ጥራትና ዋጋ አምርተን ለመሸጥ የማያስችለን እስከሆነ ድረስ የማያቋርጥ እድገት መሰረት ሊሆነን አይችልም፡፡ በመሆኑም በገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በተፈላጊው ጥራትና ተወዳዳሪ ዋጋ ለመሸጥ የሚያስችለንና በዚህ ሂደት



የአርሶ አደሩ ገቢ በቀጣይነት እንዲሻሻል ለማድረግ የሚያስችል የግብርና ቴክኖሎጂን ብቻ እየመረጥን መጠቀም ይኖርብናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተለገፀው በአገራችን እጅግ በርካታ የተለያዩ የአግሮ-ኢኮሎጂ ዞኖች አሉ፡፡ በሁሉም አካባቢዎች አንድ አይነት ቴክኖሎጂ መጠቀም አይገባም፡፡ በአንድ አካባቢ የሚሰራ ቴክኖሎጂ (ለምሳሌ በቂ ዝናብ ባላቸው አካባቢዎች) በሌላ አካባቢ (ለምሳሌ በቂ ዝናብ በሌላቸው አካባቢዎች) ፈፅሞ አይሰራም፣ ወይም ቢሰራም ተፈላጊውን ውጤት ሊያስገኝ የሚችል አይሆንም፡፡ እያንዳንዱ አካባቢ በግብርና ልማት ረገድ ሊያስገኝ የሚችለውን የላቀ እድገት እንዲያስገኝ ለማድረግ ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ቴክኖሎጂ መቅረብ አለበት፡፡ በመሆኑም ለተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚሰማሙ መላውን የአገራችንን የአግሮ ኢኮሎጂ ዞኖች ፍላጎት የሚያረኩ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብና ይህንኑ በቀጣይነት ማሻሻል ይኖርብናል፡፡ የግብርና ቴክኖሎጂ አቅርቦታችን ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ባህሪ ሊኖረው ይገባል፡፡

የሚቀርበው የግብርና ቴክኖሎጂ አርሶ አደሩ በማምረት እንቅስቃሴው ሂደት የሚያጋጥሙትን ምርታማነቱንና ገቢውን የሚጎዱ ችግሮችን በመፍታት የግብርና ልማታችንን ለማፋጠንና የአርሶ አደሩን ኑሮ ለመለወጥ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ስለሆነም የሚካሄደው የግብርና ምርምርና የሚቀርበው የግብርና ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግር የሚነሳ መሆን አለበት፡፡ አርሶ አደሩ የማምረት ስራ ከሚጀምርበት አምርቶ እስከሚሸጥበት ድረስ ያሉትን እጅግ በርካታ ስራዎች በሚገባና በዝርዝር በማጥናት፣ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ የሚቀርበው

መፍትሄም ዋና ዋና ችግሮችን ለይቶ እነሱን በመፍታት ላይ ማተኮር ያለበት ቢሆንም የምርትና ሽያጭ ኡደቱን በአጠቃላይ በመዳሰስ በድምሩ የአርሶ አደሩን ገቢ ከፍ የማድረግና የግብርና ልማታችንን የማፋጠን አላማ የሚያሳካ መሆን አለበት፡፡ ከአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግሮች ውጪ የሚካሄድ ምርምርና የሚቀርብ ቴክኖሎጂ የምንፈልገውን ልማት ሊያረጋግጥልን አይችልም፡፡

የግብርና ቴክኖሎጂ አቅርቦት አንድ ጊዜ ተፈፅሞ የሚያበቃ ነገር አይደለም፡፡ ቀጣይነት ያለው ፈጣን የግብርና ልማት ማረጋገጥ ከተፈለገ የማያቋርጥ የተሻሻለ ቴክኖሎጂ አቅርቦት መኖር አለበት፡፡ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ የምርምርና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ስርአት መኖር አለበት፡፡ በግብርና ምርምር ዘርፍ ቀላል ግምት የማይሰጠው አቅም አለን፡፡ ይሁንና በመጠንም መላውን የአገሪቱ የአግሮ ኢኮሎጂ ዞኖች የማይሸፍንና ቁጥሩ አነስተኛ የሆነ ነው፡፡ በአይነትም ፈጣንና ቀጣይ እድገትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን የተፋጠነ አቅርቦት ለማረጋገጥ የማይችል ነው፡፡ በጣም ዘገምተኛ የሆነ የተሻሻለ ቴክኖሎጂ አቅርቦት ከያዝነው የግብርና ልማት አላማ ጋር አብሮ የሚሄድ አይሆንም፡፡ በመሆኑም የምርምር አቅማችንን በመጠንም ሆነ በአይነት በከፍተኛ ደረጃ መጨመር አለብን፡፡

የራሳችንን የምርምር አቅም በከፍተኛ ደረጃ ማጎልበት በፍፁም የማይታለፍ ስራ ቢሆንም የግብርና ልማታችንን በሚፈለገው መጠን ለማፋጠን በራሳችን የምርምር ግኝቶች ላይ ብቻ ልንመሰረት አንችልም፣ አይገባምም፡፡ በመጀመሪያ እኛ ያለን የግብርና ቴክኖሎጂ ደረጃ ከሌላው አለም ጋር ሲነፃፀር እጅግ ኋላ ቀር በመሆኑ፣ በሌላው አለም ተግባራዊ የሆኑ



ቴክኖሎጂዎች ለኛ አዲስ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ከኛ ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ በጣም በርካታ እንደሚሆኑም አያጠራጥርም፡፡ እነዚህን በመውረስና ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመን ተግባራዊ በማድረግ ከፍተኛ እድገት ማስመዝገብ ስንችል በዚህ ሳንጠቀም ቀርተን የምንንቀራፈፍበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም፡፡

የራሳችንን የምርምር አቅም በተቻለ ፍጥነትና በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ያለብን ቢሆንም ተመራማሪዎችን የማሰልጠንና የማብቃት ስራ ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ ነው፡፡ በምርምር አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን የመፍጠር ስራም እንደዚሁ የራሱን ጊዜ የሚጠይቅ ነው፡፡ የምርምር አቅማችንን ለመገንባትና በዚሁ አማካኝነት አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን ለመገንባት በሚወስደው ጊዜና በዚሁ ስራ ፍጥነት ላይ የተመሰረተ የግብርና ልማት ይኑረን ከተባለ ፈጣን እድገት ብሎ ነገር ህልም ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡ በዚህ ምክንያት የቴክኖሎጂ አቅርቦታችን ዋነኛው መሰረት በራሳችን ምርምር የሚገኝ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ሳይሆን ከሌሎች አገሮች መርጠን የምንዋሰው ቴክኖሎጂ መሆን አለበት፡፡

የምርምር ተቋሞቻችን ለግብርና ልማታችን መፋጠን ተፈላጊውን አስተዋፀኦ ማበርከት የሚችሉት ይህን ሲገነዘቡ ነው፡፡ የራሳችንን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ለማፍለቅ የምናደርገው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጭርና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ ግን ዋናው ትኩረታችን የውጭ ቴክኖሎጂዎችን የማፈላለግ የመምረጥና ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይ እንደሆነ ሊታመንበት ይገባል፡፡ ይህን መሰረታዊ ጉዳይ በተመለከተ ከዚህ በፊት የነበሩት የተዛቡ አመለካከቶች

www.abyssinialaw.com

ካልተስተካከሉ በስተቀር በግብርና ልማት እንቅስቃሴያችን ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ አደጋ ሊያንዣብብ ይችላል፡፡ በአለም ደረጃ ያሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን መዳሰስ፣ ከነዚህ ውስጥ ለኛ ሊሆኑ የሚችሉትን መምረጥ፣ የተመረጡትን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣሙ የማድረግ ስራ ራሱ ከፍተኛ ሞያና የምርምር አቅም የሚጠይቅ ነው፡፡ ተመራማሪዎቻችን ዋነኛ ስራቸው ይህ እንደሆነ ተገንዝበው እስከተረባረቡ ድረስ ከሁኔታችን ጋር የሚሄድ ያለማቋረጥ የሚሻሻል መላውን የአገራችንን አግሮ-ኢኮሎጂ ዞኖች የሚሸፍን የቴክኖሎጂ አቅርቦት ማረጋገጥ እንደሚቻል አያጠራጥርም፡፡ ዋነኛው የቴክኖሎጅ ምንጭ የራሳችን አዲስ ግኝት አይደለም ሲባል የራሳችን አዲስ ቴክኖሎጅ ለመፍጠር የምንሰራው ስራ መዳከም ወይም መቋረጥ አለበት ማለታችን አይደለም፡፡ ይልቁንም የውጭ ቴክኖሎጂዎችን ለመዋስና የራሳችንንም ለመፍጠር የምርምር አቅማችንን በከፍተኛ ደረጃ በማሻሻል አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በማፍለቅ እስካሁን ከነበረውም በተሻለ ሁኔታ መስራት እንደሚገባን ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ቴክኖሎጂዎች ተመርጠውና በ-ኬጅ ተዘጋጅተው መቅረባቸው የስራው ቁልፍና ነገር ግን ደግሞ የመጀመሪያ ርምጃ ከመሆን የማይዘል ስራ ነው፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ ወደ አምራቹ መድረስና መሰራጨት አለበት፡፡ ይህም ሊፈፀም የሚችለው በተለያዩ ስልቶች (በፅሁፍ፣ በሴሚናሮች ወዘተ.) ሲሆን በኛ ሁኔታ ዋናው ስልት የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ነው፡፡ በመሆኑም ጠንካራ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ስርአት መፍጠር የማይታለፍ ተግባር ነው፡፡ ተግባራዊ መሆን በጀመረው እቅድ መሰረት በየቀበሌው ከሶስት ያላነሱ በመለስተኛ ኮሌጅ የሰለጠኑ የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ይመደባሉ፡፡ ይህ



እቅድ ሲፈፀም በኤክስቴንሽን አገልግሎት ስርአታችን ውስጥ እጅግ በጣም መሰረታዊ የሆነ እመርታ ይመዘገባል፡፡ ይህ ብቻውን ግን በቂ አይሆንም፡፡ በየቀበሌው የሚመደቡ ሞያተኞችን የሚደግፉ የሚመሩና የሚያስተባብሩ ከፍተኛ የግብርና ኤክስቴንሽን ሞያተኞችም መኖር ይገባቸዋል፡፡ ከዚያም ባሻገር በምርምር ስርአቱና በኤክስቴንሽን ስርአቱ መካከል የቅርብ ትስስርና ቁርኝት ሊኖር ይገባል፡፡ የኤክስቴንሽን አገልግሎታችንን በየጊዜው እየተፈተሹ ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ነገሮች በማረጋገጥ ብቻ ነው የቴክኖሎጂው ስርጭት አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ የሚቻለው፡፡

የግብርና ዘይቤዎችን በሚመለከቱ የሚገኙት አዳዲስ እውቀቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በምክርና ኤክስቴንሽን፣ እንዲሁም በአጫጭር ስልጠናዎች ወደአምራቹ ማስተላለፍ እንደሚቻል እሙን ነው፡፡ የተሻሻሉ ዘሮችና የግብርና መሳሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ በተመሳሳይ አኳኋን ወደ አምራቹ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ቴክኖሎጅዎች በዚህ መልኩ ሊሰራጩ አይችሉም፡፡ ለምሳሌ የተሻሻሉ ዘሮችና የግብርና መሳሪያዎች ከመሰራጨታቸው በፊት መባዛት ይኖርባቸዋል፡፡ ከቴክኖሎጂ ሽግግር አኳያ የስርጭት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የብዜትም ጉዳይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ጉዳይ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ከምንፈልገው ፈጣን የግብርና እድገት ጋር የሚሄድ የቴክኖሎጂ ብዜት ስርአት፣ አዳዲስ ቴክኖጂዎችን ቶሎ ቶሎ እያበዛ ለአርሶ አደሩ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡ አንድን ቴክኖሎጂ አባዝቶ ለማድረስ አመታት የሚጠይቅ ከሆነ በሚፈለገው መጠን ፍጥነትና ቀጣይነት ያለው እድገት ሊኖር

አይችልም። የሚባዛው ቴክኖሎጂ ጥራቱ የተጠበቀና በዋጋም አርሶ አደሩ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል መሆን አለበት። ይህንኑ ለማሟላት የሚቻለው መንግስት፣ የግል ባለሃብቶች፣ አርሶ አደሮች የበኩላቸውን ድርሻ የሚወጡበት ወጥነት ያለው ቀልጣፋ የቴክኖሎጂ ብዜት ስርአት ሲኖር ነው።

በዚህ መሰረት ለምሳሌ ምርጥ ዘሮችንና የእርሻ መሳሪያዎችን ብንወስድ ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ፣ የመፈተሽና በሙከራ ደረጃ ለአርሶ አደሮች የማስተዋወቅ ስራ በዋነኛነት የመንግስት መሆን አለበት። መንግስት ይህን ስራ በተከታታይና ቀልጣፋነትን በሚያረጋግጥ አኳኋን የሚሰራበት ስርአት መፈጠርና ያለማቋረጥ መሻሻል አለበት። ይህ ስርአት ቴክኖሎጂውን ለማባዛት ከተፈለገ በአፋጣኝና በሰፊው ለማባዛት የሚያስችል እንዲሆን ተደርጎ መሰራት አለበት። እዚህ ደረጃ ላይ ከተደረሰ በኋላ የማባዛቱ ጉዳይ በአብዛኛው በግል ባለሃብቶችና በተመረጡ አርሶ አደሮች የሚፈፀም መሆን አለበት። ምርጥ ዘር በማባዛት ስራ ላይ የተመረጡ አርሶ አደሮች በሰፊው ሊሳተፉ ይችላሉ። በዚህ ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶችም ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። የግብርና መሳሪያዎችን በሚመለከት የግል ባለሀብቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።

መንግስት ቴክኖሎጂዎችን በአፋጣኝ ሊባዙ በሚችሉበት ደረጃ ላይ ካደረሰ በኋላ እንካችሁ ብሎ ለተመረጡ አርሶ አደሮችና ለግል ባላሃብቶች መተው አለበት ማለት ግን አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ የብዜት ተቋሞች ተለይተው የስርአቱ አንድ አካል ተደርገውና ተመዝግበው መያዝ



ያለባቸው ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞም ተቋሞቹ ቴክኖሎጂዎቹን በተፈለገው ጥራት ማባዛት እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ድጋፍና የተሟላ የጥራት ቁጥጥር ስርአት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል። ዋናው ነገር የብዜት ስርአቱ ልክ እንደምርምርና ስርጭት ስርአቱ በአግባቡ የተደራጀ ስርአት መሆኑን የማረጋገጥ ቀልጣፋነቱን በቀጣይነት የማሻሻል ስራ ነው። እንደዚህ አይነቱ ስርአት ከሌለ የቴክኖሎጅ አቅርቦቱ የፈለገውን ያህል ብቃት ቢኖረውም የስርጭቱና የብዜቱ ስርአት ማነቆ እየሆነ ፈጣን እድገትና የቴክኖሎጅ ሽግግር እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል። በመሆኑም ነው ብዙ የተሻሻሉ ቴክኖሎጅዎችን ያለማቋረጥ የሚያቀርብ፣ የሚያሰራጭና የሚያባዛ ስርአት የመፍጠር፣ ይህንኑ በቀጣይነት የማሻሻል ስራ ቁልፍ የግብርና ልማት ስራችን አካል የሚሆነው።

የቴክኖሎጅ አቅርቦት ብዜትና ስርጭት ስርአት ተፈጥሮና ቀልጣፋነቱም ተረጋግጦ ቢሆን ዞሮ ዞሮ ይህንኑ ተቀብሎ ተግባራዊ የሚያደርገው አምራቹ አርሶ አደር ነው። ስለሆነም የሚቀርበው ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ አቅም ጋር እንዲመጥን ተደርጎ መቅረብ አለበት። አርሶ አደሩ ሊጠቀምበት የማይችል የተሻሻለ ቴክኖሎጂ እድገታችንን ከማፋጠን አንፃር ምንም ፋይዳ አይኖረውም። በሌላ በኩል ደገሞ አዳዲስ ቴክኖሎጂ በስንት አመት አንዴ ብቅ የሚል ነገር ከሆነ፣ በተከታታይና ያለማቋረጥ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች የማይቀርቡ ከሆነ የምንፈልገውን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ሊያረጋግጥልን አይችልም።

ቴክኖሎጂው ከተጠቃሚው አቅም ጋር መመጣጠን አለበት ሲባል ከኤክስቴንሽን አገልግሎታችን ተጠቃሚ መሆን የሚችሉና የሚገባቸው ሶስት የተለያየ አቅም ያላቸው አምራቾች

እንደሚኖሩ ታሳቢ መደረግ አለበት። በመጀመሪያ ደረጃና በዋነኛነት ያልተማረው አርሶ አደር አለ። በሂደት እየጨመረና ዋናው ክፍል እየሆነ የሚሄድ የተማረና የሰለጠነ አርሶ አደርም አለ። ሁለቱ አንድ አይነት ቴክኖሎጂ መጠቀም አይችሉም። ስለዚህም ካልተማረው አርሶ አደር አቅም ጋር የሚመጣጠን የዝቅተኛ ቴክኖሎጂ ፖኬጅ እየተዘጋጀ መሰራጨት ይኖርበታል። አሁን ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ሲታይም ዋናው ጉዳይ ይህ ነው። ከዚህ ጎን ለጎንና በሂደት በከፍተኛ ፍጥነት ይጨምራል ተብሎ ለሚገመተው የተማረ አርሶ አደር የሚቀርበው ቴክኖሎጂ የላቀና ላልተማረው ከሚቀርበው የተለየ መሆን አለበት። ሁሉም እንደየአቅማቸው የሚመጥናቸውን የቴክኖሎጂ አቅርቦት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ልዩ ግምት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ክብደት ያላቸው ናቸው ባይባሉም፣ በሰፋፊ እርሻዎችም ሆነ በውሱን መሬት በላቀ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በግብርና ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች አሉ። ወደፊት ቁጥራቸውና በግብርናው ኢኮኖሚ የሚኖራቸው ድርሻ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ እንደሚሄድም ይገመታል። እነዚህ የሚፈልጉት የምክርና የቴክኖሎጂ አቅርቦት አርሶ አደሩ ከሚፈልገው በጣም የተለየ ነው። የግብርና የቴክኖሎጂ አቅርቦት ስርአቱም ለአርሶ አደሩ አገልግሎት ተብሎ ከሚቀረፀው የተለየ መሆን አለበት። እንደዚህ አይነት አገልግሎት በአሁኑ ወቅት የሚሰጥበት ስርአት የለም። ምንም እንኳ ዋናው ትኩረት በአርሶ አደሩ ላይ ሆኖ መቀጠሉ ተገቢ ቢሆንም በግብርና ስራ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች አገልግሎት የሚውል ስርአት መፍጠርና ከእድገታቸው ጋር ተያይዞ እያደገ እንዲሄድ ማድረግ በጣም ተፈላጊ ነው።



የቴክኖሎጂው አቅርቦት ከአምራቾች አቅምና ሁኔታ ጋር የሚመጥን የተማረውንም ሆነ ያልተማረውን አርሶ አደር እንዲሁም የግል ባለሃብቱን በተሟላ ሁኔታ የሚያገለግል እንዲሆን ለማድረግ የአቅርቦቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የአዳዲስ ቴክኖሎጂ አቅርቦት በስንት አመት አንድ ጊዜ የሚፈፀም ሳይሆን ተከታታይነት ያለውና የማያቋርጥ መሆን ይኖርበታል። በመሆኑም አንድ አዲስ ቴክኖሎጂ ከመሰራጨቱም በፊት የተሻሻለ ተኪ ቴክኖሎጂ የማፈላለግ ስራ መከናወን አለበት። የአርሶ አደሩ የምርትና የግብይት ስራ ችግሮች ያለማቋረጥ መጠናት አለባቸው። ለችግሮቹ መፍትሄ የሚሆን ነገር በቀጣይነት መቅረብ አለበት። ለዚህም ነው የምርምር ስራችን በአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግሮች ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፣ በምርምር ስርአቱና በኤክስቴንሽን ስርአቱ መካከል ጥብቅ ትስስር ተፈጥሮ በአንድ በኩል የአርሶ አደሩ ችግሮች በሚገባና በአፋጣኝ ተለይተው ለተመራማሪዎች የሚቀርቡበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተገኙ መፍትሄዎች በአፋጣኝና በአግባቡ ወደ አርሶ አደሩ የሚሸጋገሩበት ስርአት መፈጠር አለበት የምንለው።

የአርሶ አደራችንን የስራ ፍላጎትና ተነሳሽነት ከጠበቅንና ካሻሻልን፣ ጤንነቱን ካረጋገጥን፣ የትምህርትና ስልጠና ደረጃውን ካሻሻልን፣ ከዚሁ ጎን ለጎን አምራቹ ምርቱን እንዲያሳድግ የሚያስችለው ከአቅሙ ጋር የሚመጥን የቴክኖሎጂ አቅርቦ በቀጣይነት እንዲኖር ካደረግን፣ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል ቀልጣፋ የቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ ብዜትና ስርጭት ስርአት ከፈጠርን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት ለማረጋገጥ የሚያስፈልገንን ወሳኝ ስራ ሰርተናል ማለት ነው። ነገር ግን የግብርና ልማት በዚህ ብቻ የታጠረ አይደለም። የሰው ሃይልን

ብቻ ሳይሆን መሬትንም በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል:: ቀጥሎ የምንመለከተው ጉዳይም የመሬት አጠቃቀም ጉዳይ ይሆናል::

## 3. መሬትን በአግባቡ መጠቀም፣

የሰው ሃይላችንን የማምረት አቅም በማጎልበት ይህን በላቀ ደረጃ መጠቀም የግብርና ልማት መሰረታዊ አቅጣጫዎችን ነው:: የሰው ሃይላችንን የማምረት አቅም ማጎልበት የግብርና ልማት ስራችን የሚዋቀርበት አንድ መሰረታዊ ምሰሶ ነው:: መሬታችንን የግብርና ልማታችንን በሚያፋጥንና የዚህን ልማት ቀጣይነት በሚያረጋግጥ አኳኋን መጠቀምም የግብርና ልማት ስራችን የተዋቀረበት ሌላው ምሰሶ ነው::

### 3.1. በህገ-መንግስቱ ላይ የሰፈረውን የመሬት ይዞታ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ፣

በህገ-መንግስታችን የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲ ምን መሆን እንዳለበት ተመልሷል:: የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ በአብዛኞቹ አገሮች እንደአንድ ህገ-መንግስታዊ ጉዳይ ተደርጎ የማይወሰድ ቢሆንም ጉዳዩ በአገራችን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ህይወት ውስጥ ከሚጫወተው ልዩ ሚና አኳያ ታይቶ በአገራችን ህገ-መንግስት እንዲሰፍር ተደርጓል:: በህገ-መንግስቱ የሰፈረው ፖሊሲ መሬት የግል በመሆኑ ወይም የመንግስት በመሆኑ ጉዳይ ላይ ያስቀመጠው መልስ ብቻ ተቆንፅሎ የሚወሰድበት ሁኔታም አለ:: በህገ-መንግስታችን የሰፈረውና በዚህ ላይ ተመስርቶ ተግባራዊ እየሆነ ያለው ፖሊሲ ግን ከዚህም ዘርዘር ያለ ነው:: የፖሊሲውን አንድ ገፅታ ብቻ ቆንፅሎ በመውሰድ የፖሊሲውን ፋይዳ በተሟላ መልኩ መረዳት አይቻልም::



ፖሊሲው መሬት የህዝብ እንደሚሆን፣ በህዝቡ ስም መንግስት በተለይም የክልል መንግስታት እንደሚያስ ተዳድሩትና ፌዴራል መንግስትም ከዚህ አኳያ ምን ድርሻ እንደሚኖረው ያስቀምጣል:: መሬት በመንግስት የሚተዳደር የህዝብ ንብረት ይሆናል የሚለው ነገር ሲዘረዘር በተጨባጭ ምን ማለት ነው? አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ የሚኖረውና የማይኖረው መብት ምንድነው ብሎ ዘርዝሮ ማየት ያስፈልጋል::

ፖሊሲው መሬት የመንግስት በመሆኑ ማንኛውም አርሶ አደር አርሶ ለመኖር የሚያስፈልገውን መሬት በነፃ የማግኘት መብት እንዳለው ያስቀምጣል:: በዚህ መሰረት መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መሬት እንደገና ሊያከፋፍል የሚያስችለው መብት ይኖረዋል:: አርሶ አደሩ የማይጠቀምበት መሬት ሲኖር መንግስት በባለቤትነት ይዞ ለተለያዩ ጥቅሞች እንዲውል ያደርገዋል፣ የግል ባለሃብቶች በግብርና ለመሰማራት ሲፈልጉ በረጅም ጊዜ ሊዝ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ይገልፃል:: አርሶ አደሩ በምንም ምክንያት መሬቱ በመንግስት ከተወሰደ በመሬቱ ላይ ላፈሰሰው ካፒታልና ላደረገው መሻሻል ካሳ ይከፈለዋል:: የመሬት ባለቤትነቱ የመንግስት መሆኑ የሚገለፅበት አንዱ መልክ ከላይ የተዘረዘረው ነው::

ፖሊሲው መሬት የመንግስት በመሆኑ ሊሸጥ ሊለወጥ በወለድ አግድ ሊያዝ አይችልም ይላል:: በመሆኑም አርሶ አደሩ በግብርና ስራ ለመሰማራት እጠቀምበታለሁ ብሎ የተቀበለውን መሬት ልሸጥ ቢል አይችልም፣ ይህንን መሬት እንደግል ንብረት ቆጥሮ መሬቱን በወለድ አገድ ላስይዝ፣ መሬቱን አስይዤ ልበደር ካለም አይችልም::

በሌላ በኩል ግን መሬት የመንግስት ነው ቢባልም በመሬቱ አርሶ ለመጠቀም የተቀበለው ሰው ለዘልአለሙ በነፃ ሊጠቀምበት ይችላል፣ ራሱ በመሬቱ በነፃ ከመጠቀምም አልፎ በመሬቱ የመጠቀም መብቱን ለወራሾቹ ማስተላለፍ ይችላል:: መንግስት መሬቱን በሆነ ምክንያት ቢወስደው አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ ላፈሰሰው ካፒታልና ላደረገው መሻሻል በቂ ካሳ ይከፍላል:: ይህ ብቻ ሳይሆን አርሶ አደሩ የተቀበለውን መሬት ራሱም ሊያርሰው ይችላል፣ ለሌላ ሰው ሊያከራየውና ይችላል:: የራሱንና የቤተሰቡን ጉልበት በመጠቀምም ሊያርሰው ይችላል:: የፈለገውን ያህል ጉልበት በፈለገው ጊዜ ቀጥሮም ሊያሰማራበት ይችላል:: እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ ያሉት መብቶች እጅግ በጣም መሰረታዊ ትርጉም ያላቸውና ከመንግስት የመሬት ባለቤትነት ይልቅ ከመሬት የግል ባለቤትነት ጋር የሚመሳሰል ባህሪ ያላቸው ናቸው::

ፖሊሲው ተዘርዝሮ ሲታይ ይህ ሆኖ ሳለ ፖሊሲውን በሚገባ በመገንዘብም ሆነ ባለመገንዘብ የሚቀርቡ በርካታ የተሳሳቱ ትችቶች አሉ:: መንግስት እነዚህን የተሳሳቱ ትችቶች የማይቀበለው በህገ-መንግስት የሰፈረውን ፖሊሲ የማስፈፀም ህገ-መንግስታዊ ግዴታ ስላለበት ብቻም አይደለም:: ፖሊሲው ትክክለኛ ነው፣ በዚህ ላይ የሚቀርቡት ብዙዎቹ ትችቶች የተሳሳቱ ናቸው ብሎ ስለሚያምንም ጭምር ነው::

አንዳንድ ሰዎች የመሬት ባለቤትነት ከላይ በተዘረዘረው መልኩ የመንግስት መሆኑ በግብርና ልማት እንቅስቃሴያችን ላይ ምን አይነት ትርጉም ይኖረዋል የሚለውን ጉዳይ ሳይመረምሩ ከርዕዮተ-አለማቸው ብቻ በመነሳት መሬት የግል እንጂ የመንግስት መሆን የለበትም ብለው ይከራከራሉ:: የመሬት





ባለቤትነት ጉዳይ በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ካለው ፋይዳ አኳያ እንጂ ከጭፍን ርዕዮተ-አለማዊ መነሻ አኳያ አቋም ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ አይደለም:: መሬት እንደካፒታል፣ እንደሰው ጉልበት ሁሉ አንድ የምርት መሳሪያ ነው:: ይህ የምርት መሳሪያ ምርትን ለማሳደግ፣ ህዝቡ ከሚገኘው ምርት በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የሚሆነው ባለቤትነቱ ምን ቢሆን ነው ተብሎ በተጨባጭ ከተመረመረ በኋላ ነው:: እንደዚህ አይነቱ ተጨባጭ ትንተና ከቀረበ በኋላ የመንግስት ይሁን የግል ይሁን ቢባል ቢያንስ ፋይዳ ያለው ውይይት ለማድረግ በር ይከፍታል:: ከእንደዚህ አይነቱ ትንተና ውጭ መሬት የመንግሰት ይሁን ወይም የግል ይሁን ብሎ መከራከር መሬትን የህዝቡን የልማትና የኑሮ መሻሻል ፍላጎት ለማሳካት እንደሚያገለግል እንደአንድ የልማት መሳሪያ ከማየት ይልቅ እንደ ጣኦት ማምለክን ወይም የግል ባለቤትነትን እንደጣኦት ማምለክን ያመለክታል:: በመሆኑም በዚህ መልኩ የሚቀርበው ትችት ክብደት ሊሰጠው የሚችልና የሚገባው አይሆንም::

መሬት አይሸጥም አይለወጥም ተብሎ ተበጣጥሶ ለአርሶ አደሩ ተከፋፍሏል፣ ይህም ሰፋ ያለ መሬት ይዘው በዘመናዊ መንገድ ለማረስ የሚፈልጉ ባለሃብቶች መሬት ገዝተው ዘመናዊ እርሻ ማቋቋም እንዳይችሉ ይገድባቸዋል:: በዚህ መልኩም ዘመናዊ እርሻ በአገራችን እንዳይስፋፋና የግብርና ልማት እንዳይፋጠን እንቅፋት ይሆናል ብለው የሚተቹም አሉ:: ይህ ትችት ቢያንስ የመሬት ባለቤትነትን ከልማት አስተዋፅኦው አኳያ የሚመዝን መሆኑ አንድ ቁምነገር ነው:: ይሁንና ይህም ቢሆን ትችቱን በፍፁም የተሳሳተ ከመሆን የሚያድነው አይደለም::

ስለግብርና ልማት ብሎም ስለመሬት ባለቤትነትና

www.abyssinialaw.com

የመሬት ባለቤትነት በግብርና ልማታችን ላይ ስለሚኖረው ተፅእኖ ስንወያይ ከአገራችን ተጨባጥ ሁኔታ መነሳት አለብን፡፡ አብዛኛው የአገራችን አርሶ አደር የሰፈረው በአገሪቱ ደጋማ አካባቢ ነው፡፡ ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት ውስጥ ውሱን በሆነው አካባቢ እጅግ የሚበዛው አርሶ አደር የሰፈረ በመሆኑ የመሬት ጥበቱ መጠን ቢለያይም በደጋማው አካባቢ ከፍተኛ የመሬት ጥበትና ከፍተኛ የሰው ሃይል ክምችት ይታይበታል፡፡ ከአገራችን የቆዳ ስፋት ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቆላማ አካባቢ በተለይም ከሰሜን ጫፍ እስከደቡብ ጫፍ በተዘረጋው የምዕራቡ ቆላማ አካባቢ በዝናብና በመስኖ ሊለማ የሚችል ሰው ያልሰፈረበትና የማይጠቀምበት ሰፊ መሬት አለ፡፡ ይህ መሬት በመንግስት የሚተዳደርና በረጅም ጊዜ ሊዝ ሰፋፊ እርሻዎችን ለማቋቋም ለሚፈልጉ የግል ባለሃብቶችም የሚሰጥ መሬት ነው፡፡ ስለሆነም መሬት አለመሸጥ አለመለወጡ ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች እንዳይቋቋሙ እንቅፋት ሆኗል የሚል ጉዳይም ሊነሳ የሚችለው የአገሪቱን አጠቃላይ የመሬት አጠቃቀም በመመልከት ሳይሆን ከፍተኛ የመሬት ጥበትና የሰው ሃይል ክምችት ባለበት በደጋማው አካባቢ ያለውን ሁኔታ በመመልከት ብቻ ነው የሚሆነው፡፡

እዚህ ላይ መነሳት የሚገባው ከፍተኛ የመሬት ጥበትና የሰው ሃይል ክምችት ባለበት ደጋማ አካባቢ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችለን ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎችን መመስረት ነውን? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ መሬት የሚሸጥ ቢሆንና የግል ባለሃብቶች መሬቱን ገዝተው አስፋፍተው የሚይዙት ቢሆን ይህን የገዙትን መሬት በሁለት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡



አንደኛው አማራጭ መሬቱን አስፋፍቶ በመያዝ ዘመናዊ ማሽነሪዎችን ገዝቶ አርሶ አደሩን አፈናቅሎ በከፍተኛ ካፒታል ጥቂት የሰው ሃይል ቀጥሮ መሬቱን የማልማት አማራጭ ነው፡፡ ይህ አማራጭ ጉልበትንና ካፒታልን በከፍተኛ ደረጃ ያባክናል፡፡ ሰርቶ ማምረት የሚችለውንና ሌላ አማራጭ ስራ የሌለውን የሰው ሃይል አፈናቅሎ ስራ ፈት ማድረግ ይህ ከፍተኛ የማምረት አቅም እንዲባክን ማድረግን ያስከትላል፡፡ በተለይም በአገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ሰፊ ያልታረሰ መሬት ባለበት ሁኔታ በምርት ተግባር ላይ የተሰማራውን ሃይል አፈናቅሎ ከልማት ተግባር ውጪ እንዲሆን ማድረግ የልማት አቅማችንን በከፍተኛ ደረጃ ማባከን ይሆናል፡፡

ይህ አሰራር ካፒታልንም በከፍተኛ ደረጃ የሚያባክን ነው፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ያለው የካፒታል ክምችት በጣም ውሱን በሆነበት ሁኔታ ቀላል ግምት የማይሰጠው ገንዘብ፣ የምርት መሳሪያ፣ ጉልበት ወዘተ. በመቅጠር ሳይሆን የመሬት ባለቤትነትን ከአንድ ሰው ወደሌላ ሰው ለማዘዋወርና በመሬት ሽያጭ ላይ እንዲውል ለማድረግ ይውላል፡፡ የመሬት ባለቤትነትን ማዘዋወር በራሱ የልማት ተግባር ባለመሆኑ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ካፒታል ከልማት ተግባር ውጪ ይሆናል፣ ይባክናል፡፡ በተለይም በረጅም ጊዜ ሊዝ ሰፊ መሬት ማግኘት በሚቻልበት አገር ይህ ከፍተኛ የካፒታል ብክነት ልማትን ከማፋጠን አኳያ የሚቀርብ አንዳችም አሳማኝ መከራከሪያ ሊገኝለት የማይችል ብክነት ነው፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ባለበት አገር በሰው ጉልበት ሊሰራ የሚገባውንና የሚችለውን ስራ ለመስራት ሰውን አፈናቅሎ በማሽነሪ መተካት በጣም ከፍተኛ የካፒታል ብክነትን የሚያስከትል ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ሁለተኛው አማራጭ መሬቱን በግዥ አስፋፍተው ከያዙ በኋላ ዘመናዊ ማሽነሪ በመጠቀም ሳይሆን በቦታው ላይ የነበረውን አርሶ አደር በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ቀጥሮ የማሰራት አማራጭ ነው፡፡ ይህ አማራጭ አንዳች አይነት የግብርና ዘይቤ ለውጥ ለማያመጣ ነገር የመሬት ባለቤትነትን ከአንድ ሰው ወደሌላ ሰው ለማዛወር ብቻ ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ገንዘብ በቀጥታ በልማት ተግባር ላይ ሊውል ይችል የነበረ ከመሆኑ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ባለባት አገራችን በምንም መልኩ ሊደገፍ የማይችል የካፒታል ብክነት የሚፈጥር አሰራር ነው፡፡

ይህ አማራጭ አርሶ አደሩን ከምርት ተግባር የማያፈናቅለው ሆኖ ቢገኝም እንኳ ጉልበትን ማባከኑ አይቀርም፡፡ በራሱ መሬት ሰርቶ የሚኖረው አርሶ አደር የስራ ፍሬው በሙሉ ለራሱ ስለሆነ፣ ባመረተው መጠን በቀጥታ የሚጠቀም ስለሆነ በትጋት ለመስራት የተሻለ እድል ይኖረዋል፡፡ መሬቱን ሸጦ ተቀጥሮ የሚሰራው ሰራተኛ ግን በዚህ ደረጃ በትጋት እንዲሰራ የሚያደርገው ነገር ስለማይኖር ይብዛም ይነስም ያለምጣል፡፡ በትጋት እንዲሰራ የሚቆጣጠር ተቆጣጣሪ መመደብም የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ ያለተቆጣጣሪ በትጋት ሲሰራ የነበረውን ሰው ተቆጣጣሪ ከተጨመረበት በኋላም የመሬቱ ባለቤት በነበረበት ወቅት ከነበረው ባነሰ ትጋት እንዲሰራ ማድረግ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አምራች የሰው ጉልበትን ማባከን ይሆናል፡፡

በመሆኑም አርሶ አደሩ መሬቱን እንዲሸጥ ቢፈቀድ



በሽያጩ አማካኝነት መሬቱ በጥቂት ሰዎች ቢሰባሰብ በየትኛውም የግብርና ዘይቤ ጥቅም ላይ ቢውል (አርሶ አደሩን በማፈናቀልም ሆነ ቀጥሮ በማሰራት) ካፒታልንና ጉልበትን በከፍተኛ ደረጃ ማባከኑ አይቀርም፡፡ በሌለን ካፒታል ላይ በከፍተኛ ደረጃ እያባከንን፣ ሰራተኛ የሰው ሃይላችንን በልማቱ ስራ በትጋትና በሰፊው እንዳይሳተፍ እያደረግን ልማታችንን ክፉኛ ከማቀጨጭ በስተቀር የሚመጣ ልማት አይኖርም፡፡ መሬት እንዲሸጥ እንዲለወጥ ማድረግ የሚኖረው ተጨባጭ ውጤት ልማታችንን ክፉኛ ማዳከም ነው፡፡ በመሆኑም ያለጥርጥር ፀረ-ልማት አማራጭ ነው፡፡

አሁን ባለው የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲ ይህን ችግር በአስተማማኝ ሁኔታ መቅረፍ ይቻላል፡፡ ሰፋፊ እርሻዎች ለማቋቋም የሚፈልጉት ያልታረሰ መሬት ባለበት አካባቢ በሊዝ መሬት እንዲያገኙ በማድረግ ለመሬት ግዥ የሚወጣ ወጪ እንዳይኖር ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚህ አሰራር መሰረት መጠነኛ የሊዝ ክፍያ ብቻ ነው የሚኖረው፡፡ ስለሆነም ለመሬት ባለቤትነት ለውጥ የሚውል ከልማት ስራ ውጪ የሚሆን ፋይዳ ያለው ገንዘብ አይኖርም፡፡ ያልታረሰ መሬት በመሆኑም የሚፈናቀል ሰራተኛ አይኖርም፡፡ ይልቁንም ማሽነሪም ቢጠቀም የተወሰነ ሰራተኛ መቀጠሩ ስለማይቀር ተጨማሪ የስራ ዕድል ይከፍታል፡፡ በደጋማው አካባቢም በውሱን መሬት የሚካሄድ ዘመናዊ እርሻ ማቋቋም ይቻላል፡፡ አርሶ አደሩ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ሊጠቀምበት ያልቻለውን መሬትን በመከራየት አርሶ አደሩን በማያፈናቅል መንገድ ዘመናዊ እርሻ ማቋቋም ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ የሚቋቋም ዘመናዊ እርሻ ተጨማሪ የስራ ዕድል ሊፈጥር የሚችልና አርሶ አደሩም ከዚህ ተምሮ የራሱን እርሻ እንዲያሻሽል የሚረዳ ይሆናል፡፡ የካፒታልም ሆነ የሰው ጉልበት በማያባክን

www.abyssinialaw.com

አኳኋን በደጋውም ሆነ በቆላው ከአካባቢው ሁኔታ ጋር የሚሄዱ ዘመናዊ የግል እርሻዎችን ማስፋፋት ይቻላል፡፡

ይህ ሲባል ግን ይህ አቅጣጫ ምንም አይነት ችግር አይገጥመውም ማለት አይደለም፡፡ በአፈፃፀም ደረጃ የሚታዩ በርካታ ችግሮች አሉ፡፡ ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች ሊቋቋሙ በሚችሉባቸው ቆላማ አካባቢዎች ከፍተኛ የመሰረተ ልማት እጥረት አለ፡፡ የሰራተኛ ጉልበት እጥረትም አለ፡፡ ቦታው ለተለያዩ በሽታዎች በተለይም ለወባ የተጋለጠ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቂ የጤና ጥበቃ አገልግሎት በሌለበት ቦታውን ለማልማት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ የእርሻ መሬትን በሊዝ የመስጠት ፖሊሲ አፈፃፀም ላይ የነበሩት ችግሮች በአብዛኛው እየተቀረፉ ያሉ ቢሆንም አልፎ አልፎ መፍትሄ የሚሹ ችግሮች መኖራቸውም አልቀረም፡፡

እነዚህ አካባቢዎች ከፍተኛ የልማት አካባቢዎችና ማዕከላት መሆን የሚችሉ በመሆናቸው እነዚህን ቦታዎች ለማልማት ልዩ ግምት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ የአካባቢውን የተቀናጀ የልማት እቅድ በማዘጋጀት በዚህ ላይ ተመስርቶ የመሰረተ-ልማት አገልግሎትን መዘርጋት፣ የጤና ጥበቃ በተለይም የወባ መከላከል ስራ በአጥጋቢ ደረጃ መስራት፣ ሰራተኛ ጉልበት ወደነዚህ አካባቢዎች እንዲሰማራ ማበረታታትና የመሬት ሊዝ አፈፃፀሙን በቀጣይነት ማሻሻል ይጠይቃል፡፡ ችግሮቹ ከመሬት ባለቤትነት ፖሊሲ ጋር የተያያዙ ባለመሆናቸው፣ ይልቁንም የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲው እነዚህን አካባቢዎች በላቀ ደረጃ ለማልማት በጣም የተመቸ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ በፖሊሲው ላይ በመመስረት ለልማት ማነቆ የሆኑትን ሌሎች ችግሮች ለማስወገድ መረባረብ ያስፈልጋል፡፡



አርሶ አደሩ መሬቱን ዘመናዊ እርሻ ለማቋቋም ለሚፈልጉ ባለሃብቶች ማከራየትን በተመለከተም በርካታ የአፈፃፀም ችግሮች አሉ፡፡ ምንም እንኳ አርሶ አደሩ በየአመቱ መሬቱን የሚያከራይ ቢሆንም የግል ባለሃብቶች በመሬቱ ላይ የልማት ስራ ለመስራት ረዘም ላለ ጊዜ መሬቱን መከራየት ይፈልጋሉ፡፡ ቢያንስ ከ10-20 አመታት ለሚደርስ ጊዜ መከራየት ይፈልጋሉ፡፡ ይህም በህግ በተመዘገበና ዋስትና ባለው አኳኋን እንዲፈፅምላቸው ይፈልጋሉ፡፡ የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲው ይህን ለማድረግ የሚያስችል ቢሆንም ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣትና ማስፈፀም ላይ ግን በርካታ ችግሮች ይታያሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የግል ባለሃብቶች ኩታ ገጠም በሆነ መልኩ በተነፃፃሪ ሰፋ ያለ መሬት መከራየት ይፈልጋሉ፡፡ ይህን ለማድረግ አርሶ አደሮቹን አስተባብሮ መከራየትን ይጠይቃል፡፡ የአካባቢው አስተዳደር ከፍተኛ እገዛ ባልተጨመረበት አኳኋን ይህንኑ ማስፈፀምም አስቸጋሪ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ አርሶ አደሩን የማስተባበር ችግር ያጋጥማል፡፡

በውሱን መሬት የላቀ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች በዘመናዊ አኳኋን በነዚህ አካባቢዎች ማስፋፋት (ለምሳሌ የአትክልት፣ አበባ፣ ፍራፍሬ እርሻዎች) ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነገር ነው፡፡ የግል ባለሃብቶች የተወሰነውን መሬት ራሳቸው ተከራይተው እያመረቱበት በቀረው ደግሞ በአካባቢው ያለው አርሶ አደር በተመሳሳይ መንገድ አምርቶ ምርቱን ለግል ባለሃብቶቹ የሚሸጥበት ስርአት (out grower system) በመጠቀም በግል ባለሃብቶቹ ዘመናዊ እርሻ ዙሪያ የአርሶ አደሩን የራሱን እርሻ ዘመናዊ ማድረግ ይቻላል፡፡ እንደነዚህ አይነቶቹ እርሻዎች ከአርሶ አደሩ የሰብል ማሳም በላይ የሰለጠነ የሰው ሃይል በሰፊው

www.abyssinialaw.com

የሚጠቀሙ በመሆናቸው የሰው ጉልበትን በሰፊው ከመጠቀም ስትራተጅያችን ጋር አብረው የሚሄዱ ናቸው::

ይህን ስራ አርሶ አደሩን በማያፈናቅል መልኩ መፈፀም ይቻላል:: ዘመናዊ እርሻዎቹ ከአርሶ አደሩ እርሻም በላይ ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙ ስለሆነ (ለምሳሌ የአበባ፣ የአትክልት እርሻዎች) አርሶ አደሩ የተወሰነውን መሬት ቆርሶ በማከራየት የቀረውን በዘመናዊ መንገድ ማረስ ይቻላል:: ይህ በተለይ ሰፋ ሰፋ ያለ መሬት ባለበት አካባቢ በሰፊው ተግባራዊ መሆን የሚችል ነው:: በሌሎች አካባቢዎች አርሶ አደሩ መሬቱንም አከራይቶ በዘመናዊ እርሻውም ተቀጥሮ በመስራት በፊት ሲያገኝ ከነበረው ገቢ በከፍተኛ ደረጃ የሚበልጥ ገቢ ሊያገኝ ይችላል:: በአጠቃላይ ጉልበትና ካፒታልን በማያባክንና አርሶ አደሩን በማያፈናቅል መልኩ መስራት ይቻላል::

ይህንን ስልት በተሟላ አኳኋን ተግባራዊ ለማድረግ በመጀመሪያ ደረጃ በየአካባቢው ያሉ አስተዳዳሪዎችና ህዝቡ በጉዳዩ ላይ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ ይህንኑ ለማስፋፋት ቆርጠው እንዲነሱ ማድረግ ያስፈልጋል:: በስልቱ ላይ የተሟላ ግልፅነት በሌለበትና የህዝቡና የአካባቢው አስተዳዳሪዎች እምነት ባልታከለበት ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አይደለም:: ከዚህ ጋር ተያይዞ አርሶ አደሩ ረዘም ላለ ጊዜ መሬቱን ለማከራየት የሚችልበት፣ ይህ ስራ የሁሉንም ወገኖች መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያስችል አኳኋንና ዋስትና ባለው መንገድ የሚፈፀምበት ዝርዝር ደንብና መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ የሚሆንበት ስርአት መፍጠር ይጠይቃል:: የአካባቢ አስተዳዳሪዎች በዚህ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሃብቶችን የሚያስተናግዱበት ኪራዩን ህጋዊ ዋስትና ባለው



አኳኋን የሚፈፅሙበት፣ አርሶ አደሮችን አስተባብሮ ኩታ ገጠም የሆነ መሬት ለባለሃብቶች ማከራየት የሚቻልበት ስርአትና አሰራር መፈጠር አለበት:: በግል ባለሃብቶቹ ዘመናዊ እርሻ ዙሪያ አርሶ አደሩም ወደተመሳሳይ የግብርና ስራ እንዲሸጋገር ከባለሃብቶቹ ጋር በመተባበር የተቀናጀ ስራ ለመስራት የሚያስችል አመለካከትና ስርአት መፈጠር አለበት::

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲ የፈጠራቸው አይደሉም:: ይልቁንም የመንግስት የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲ ዘመናዊ እርሻዎችን ለማስፋፋት እጅግ የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል:: ስለሆነም የችግሮቹን መነሻ ተገንዝቦ ለማስወገድ መረባረብ እንጂ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ ችግር የሌለበትንና የመፍትሄው መሰረታዊ አካል የሆነውን መተቸት ትክክለኛ መፍትሄን የሚያስገኝ አይሆንም::

የመሬት ባለቤትነት የመንግሰት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚቀርበው ሌላው ትችት መሬት የሚሸጥ የሚለወጥ ባለመሆኑ ለባንክ ብድር በመያዣነት አያገለግልም:: በመሆኑም በገጠር አካባቢ መያዣ የሚሆን መሬት በመጥፋቱ የባንክና የፋይናንስ አገልግሎት በገጠር ሊስፋፋ ብሎም የገጠር ልማት ሊቀላጠፍ አይችልም በሚል መልኩ የሚቀርበው ነው::

የባንክና የፋይናንስ አገልግሎት ማስፋፋት የግብርና ልማትን ለማፋጠን በጣም ተፈላጊ መሆኑ አያከራክርም:: ባንኮች የብድር አገልግሎት ለመስጠት ዋስትና ሆኖ የሚያገለግል ነገር ማግኘት እንዳለባቸውም የታወቀ ጉዳይ ነው:: ብቸኛው ዋስትና የገጠር መሬት ነው ባይባልም መሬት በዋስትና መያዣነት

ሊያገለግል የሚችል እንደሆነ እሙን ነው፡፡ ይሁንና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰው በተበጣጠሰ አነስተኛ ማሳ ላይ በተሰማራበት እንደኛ ባለው አገር መሬት በግል ቢያዝም ባይያዝም በገጠር ለባንክ አገልግሎት መስፋፋት ሲያገለግል አይታየም፡፡ ባንኮች ይህን የተበጣጠሰ መሬት በመያዣነት ቢይዙትና ብድሩ ባይመለስ መሬቱን ወርሰው ሊያስተዳድሩት አይችሉም፡፡ የገንዘብ ተቋሞች እንጂ የእርሻ ኩባንያዎች ስላልሆኑ የተበጣጠሰ መሬት አርሰው ወይ አከራይተው ሊካሱ አይችሉም፡፡ የሽያጭ ጉዳይም እንደዚሁ ከፍተኛ የጊዜና የሰው ሃይል ብክነትና አስተዳደራዊ ወጪን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

ስለሆነም ዘመናዊ ባንኮች መሬት በግል ቢያዝም ባይያዝም ለአነስተኛ አርሶ አደር የብድር አገልግሎት በመስጠት በሰፊው የሚያገለግሉበት ሁኔታ የለም፡፡ ጥቃቅን ብድሮች ለብዙ አርሶ አደሮች ሰጥተው ይህንኑ ማስተዳደር በጣም ከፍተኛ ወጪ ስለሚጠይቃቸውና አድካሚ ሆኖ ስለሚያገኙት ትላልቅ ባንኮች የሚገቡበት ስራ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ነው መሬት በግል በተያዘባቸው በአነስተኛ የአርሶ አደር ማሳ ላይ የተመሰረተ ግብርና ባላቸው ሌሎች አገሮች የገጠር የባንክና የፋይናንስ አገልግሎት ከኛም አገር እጅግ በባሰ ሁኔታ የተዳከመ ሆኖ የሚገኘው፡፡

ይህን በመሰሉ አገሮች የገጠር የፋይናንስ አገልግሎትን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሆኖ የተገኘው የቡድን ብድር አገልግሎት ነው፡፡ በገጠር የፋይናንስ አገልግሎት ለማስፋፋት የሚችሉ የገጠር ባንኮች ወይም የፋይናንስ ድርጅቶች በማቋቋም ብድሩን ተመራርጠው የሚሰባሰቡ አባላት ላሉዋቸው ቡድኖች በመስጠት፣ ብድሩን ለቡድኑ አባላት



በየተራና አስቀድሞ የተበደረው ብድሩን ከፍሎ ሲጨርስ በመስጠትና የቡድኑ አባላት ብድሩን የማስተዳደርና የመመለስ ሃላፊነት እንዲሸከሙ በማድረግ የሚፈፀም ነው፡፡ የብድሩ ዋስትና በንብረት መያዣ ላይ ሳይሆን በሚቋቋመው ቡድን አስፈፃሚነትና ብድር የማግኘት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ ስርአት የተጀመረው መሬት በግል በተያዘበት በባንግላዴሽ ሲሆን እያደር በብዙ አገሮች እየተስፋፋ ይገኛል፡፡ በአገራችንም እንደነዚህ አይነት የገጠር ባንኮች ተቋቁመው በአንዳንድ ክልሎች የመላውን አርሶ አደር የፋይናንስ አገልግሎት መሸፈን የሚችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ የብድር አገልግሎት ከመስጠትም አልፈው የተሟላ የባንክ አገልግሎት ለመስጠት በሚችሉበት ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይልቁንም ይህ ስርአት በተሳካ ሁኔታ እየተፈፀመባቸው ካሉት በቅድሚያ ከሚጠቀሱት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ሆናለች፡፡ መሬትን በመያዣነት ለመያዝ አለመቻል የባንክ አገልግሎት በገጠር እንዳይስፋፋ እንቅፋት እንደማይሆንና መሬት በግል መያዙ በገጠር የባንክ አገልግሎት እንዲስፋፋ የማያደርግ እንደሆነ ከዚሁ ተጨባጭ ተግባር በላይ ማረጋገጫ ሊገኝ አይችልም፡፡

ይሁንና የቡድን ብድር አገልግሎት ብቻውን በገጠር የፋይናንስ ስርአት ማስፋፊያ መንገድ ተደርጎ መወሰድ ያለበት አይደለም፡፡ የአርሶ አደሩ ምርት በመያዣነት ሊያዝ የሚችል ነው፡፡ የአርሶ አደሩ ተንቀሳቃሽ ንብረትም በመያዣነት ሊያዝ የሚችል ነው፡፡ የህብረት ስራ ማህበራትም የብድር ቡድኖች የሚሰጡትን ጥቅም ለመስጠትም ይችላሉ፡፡ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ለትላልቅና ዘመናዊ የግብርና ስራ ከተመቻቹት ሰፋፊ እርሻዎች በመለስ የአርሶአደሩን አነስተኛ መሬት በመያዣነት መያዝ ሳያስፈልግ የገጠር የፋይናንስ ስርአትን በተለያዩ

www.abyssinialaw.com

ስልቶችና በተለያዩ አደረጃጀቶች በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋት ይቻላል፣ ይገባልም፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ በተግባር ጥሩ ውጤት ያስገኘውን የገጠር ባንኮች ስርአታችንን ልንቀጥልበትና በየጊዜው እየገመገምን ልናሻሽለው የሚገባን ቢሆንም ሌሎች ተጨማሪ ስልቶችና አደረጃጀቶችን በመጠቀም የገጠር የፋይናንስ ስርአቱ የላቀ ስፋትና ጥልቀት እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል፡፡

በመሬት ባለቤትነት ዙሪያ የሚቀርበው ሌላው ትችት የአርሶ አደሩን መሬት መንግስት ስለሚወስድበት ወይም መልሶ ስለሚያከፋፍልበት ሁኔታ የሚቀርበው ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የሚቀርበው ትችት መንግስት ለተለያዩ የልማት ስራዎች ሲፈልገው መሬቱን ስለሚወስድበት ከዚያም አልፎ መሬቱን በየጊዜው ሊያከፋፍለው ስለሚችል አርሶ አደሩ በመሬቱ የመጠቀም መብቱ ላይ ተማምኖ ማሳውን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት አያደርግም፣ ኢንቬስት አያደርግም የሚለው ነው፡፡ ከዛሬ ነገ መሬቱ ተወስዶ ይከፋፈላል በሚል ስጋት መሬቱ ላይ ኢንቬስት ሳያደርግ ቀርቶ መሬቱ ይጎዳል፣ የግብርና ልማትም ይዳከማል የሚል ነው፡፡

መንግስት ለልማት ስራ ያስፈልጋል ብሎ (ለመንገድ፣ ትምህርት ቤት፣ የከተሞች መስፋፋት ወዘተ.) መሬት መውሰዱ መሬት በግል በተያዘበትም አገር ቢሆን ያለ ነው፡፡ መሬት በግል በተያዘበትም አገር ቢሆን መንግስት ካሳ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል እንጂ ለልማት ተፈላጊ የሆነ መሬት የመውሰድ መብት በህግ ይረጋገጥለታል፡፡ በኛም ሁኔታ መንግስት አርሶ አደሩ የሚጠቀምበትን መሬት ለልማት ስራ ተፈላጊ በመሆኑ ሲወስደው በቂ ካሳ መክፈል እንዳለበት ፖሊሲው ያዛል፡፡ የመሬት ባለቤትነት የመንግስት በመሆኑ ከዚህ አኳያ የሚመጣ



ለውጥ የለም፡፡ ዞሮ ዞሮ በሁሉም አማራጮች ካሳ ከፍሎ መውሰድ ያለ ነው፡፡ ይህ አሰራር ካሳ የሚከፈልበትና በዚህ መልኩ የሚወሰድ መሬት በጣም ውሱን በመሆኑ በየትኛውም አማራጭ ቢሆን አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ ኢንቨስት እንዳያደርግ ትርጉም ያለው ተፅእኖ የሚያሳርፍ አይደለም፡፡

ከዚህ ለየት የሚለው መሬት መላልሶ የማከፋፈሉ ጉዳይ ነው፡፡ መሬቱ በተጨባጭ ተደጋግሞ ባይከፋፈልም ይከፋፈላል የሚል ስጋት ካለ አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ የሚያደርገውን ኢንቨስትመንት ሊቀንሰው ይችላል፡፡ ከዚህ አኳያ መሬት በየጊዜው እንዳይከፋፈል ማድረግ የራሱ ጠንካራ ጎን ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ይህ የጉዳዩ አንድ ገፅታ ብቻ ነው፡፡ መሬት በየጊዜው በማይከፋፈልበት ወቅት መሬቱ መጀመሪያ ሲከፋፈል መሬት ያልተሰጠው ሰው በተለይም ወጣቱ ትውልድ የሚታረስ መሬት አጥቶ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው አምራች ጉልበቱ ባክኖ ሊቀር ይችላል፡፡ ስለሆነም ይህ ችግር መፈታት ካለበት ሁሉንም ገፅታዎች ባገናዘበና ሁሉንም ችግሮች ሊያስወግድ በሚችል አኳኋን መፈፀም ያለበት ነው፡፡

እንደአጠቃላይ አቅጣጫ ልንከተለው የሚገባን ነገር መሬትን ደጋግሞ አለማከፋፈል ነው፡፡ መሬት የመንግስት ስለሆነ ብቻ በየጊዜው መከፋፈል አለበት ማለት አይደለም፡፡ የመሬት ባለቤትነት ጉዳይና መሬትን በተደጋጋሚ የማከፋፈል ጉዳይ ሁለት በጣም የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በተጨባጭ ተግባርም ባለፉት አስር አመታት ተግባራዊ የሆነው አጠቃላይ አቅጣጫ መሬትን በየጊዜው ያለማከፋፈል አቅጣጫ ነው፡፡ ይህ ብቻም በቂ አይደለም፡፡ አርሶ አደሩ በመሬቱ የመጠቀም ዋስትናው በይበልጥ እንዲረጋገጥለት መሬቱ ተመዝግቦ የተጠቃሚነት

www.abyssinialaw.com

ዋስትና ማረጋገጫ ሊሰጠው ይገባል። ከዚሁ ጋር በማያያዝ መሬቱ ረዘም ላለ ጊዜ (20-30 አመታት) እንደማይከፋፈል ዋስትና መስጠት ይቻላል፣ ይገባልም። አንዳንድ ክልሎች ይህንኑ ተግባራዊ ማድረግ መጀመራቸው በበጎ ገፅታው መታየት የሚገባው ነው። ይልቁንም ይህ አሰራር በተጀመረበት አካባቢ በይበልጥ ሊጠናከርና ሊሻሻል፣ ባልተጀመረበትም አካባቢ በተቻለ ፍጥነት ሊስፋፋ የሚገባው አሰራር ነው። የመሬት ባለቤትነት የመንግስት ከመሆኑ ጋር ምንም ግጭት የሌለውና በተግባርም በአንዳንድ ክልሎች በመፈፀም ላይ ያለ ነው።

ይህ በመሬት የመጠቀም ዋስትና አሁን ካለውም ሁኔታ እጅግ የተሻለ ሁኔታ ፈጥሮ የችግሩን አንድ ገፅታ በአስተማማኝ መንገድ የሚያስወግድ ቢሆንም፣ በተለይም ወጣቱ መሬት በማግኘት ረገድ እያገጠመው ያለውን ችግር የሚፈታ አይደለም። ይህም ችግር ከረጅምም ሆነ ከአጭር ጊዜ አኳያ አስተማማኝ መፍትሄ ሊገኝለት የሚገባ ጉዳይ ነው።

ከረጅም ጊዜ አኳያ ችግሩን በአስተማማኝ መንገድ የሚያስወግደው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ ነው። ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በሚረጋገጥበት ወቅት ኢንዱስትሪና ከግብርና ውጭ ያሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች በከፍተኛ ፍጥነት ማደጋቸውና ለወጣቱ ትውልድ ከግብርና ውጪ ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠራቸው አይቀርም። ይልቁንም ምንም እንኳ በአሁኑ ወቅት የልማቱ መሪ ግብርና ቢሆንም ይህ ልማት በተሳካ ሁኔታ ከተፈፀመ ኢንዱስትሪ በፍጥነት አድጎ በሂደት የመሪነቱን ሚና መጨበጡ አይቀርም። ኢንዱስትሪና ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች በዚህ መልኩ በፍጥነት እያደጉ ሲሄዱ በግብርና ዘርፍ የሚሰማራው ወጣት ቁጥሩ እየቀነሰ ይሄዳል። በገጠር የሚኖረው



የመሬት ጥበትም በዚያው መጠን እየተወገደ ይሄዳል። በዚሁ ምክንያት ከወላጅ በውርስ የሚገኘው መሬት በግብርና ዘርፍ ለሚሰማሩት ቁጥራቸው እየቀነሰ ለሚሄድ ወጣቶች በቂ የሚሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ይህ መፍትሄ ግን የረጅም ጊዜ መፍትሄ ከመሆን አልፎ አሁን በተጨባጭ እያጋጠመን ያለውን የመሬት ችግር ሊፈታ የሚችል አይደለም። ይህንን ችግር የተለያዩ ስልቶችን አቀናጅቶ በመጠቀም ብቻ ነው መፍታት የሚቻለው። በመጀመሪያ ደረጃ አነሰም በዛም የተሻለ የመሬት አጠቃቀም ዘይቤ በመጠቀም የግብርና ምርት ሊያስገኝ የሚችል መሬት በየአካባቢው ያለ በመሆኑ ይህንኑ በብቃት ለመጠቀም የሚያስችል አቅጣጫ በመከተል መሬት ለሌላቸው ወጣቶች ማከፋፈል ይቻላል፣ ይገባልም። ከዚሁ ጎን ለጎን በፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚካሄድ የሰፈራ ፕሮግራምን ተግባራዊ በማድረግ የመሬት ችግርን ከማቃለል ባሻገር ያልለሙ አካባቢዎችን በማልማት የአገራችንን አጠቃላይ እድገት ማፋጠን ይቻላል።

በሶስተኛ ደረጃና በአግባቡ በተግባር ላይ ከዋለ ከፍተኛ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት ነው። ይህ በሚሆንበት ወቅት በማሳው ላይ ተፈላጊ የሚሆነው ጉልበት ዛሬ አርሶ አደሩ በእርሻ ማሳው ላይ ከሚያሰማራው ጉልበት የላቀ ይሆናል። አልፎ ተርፎም አርሶ አደሩ ተጨማሪ ጉልበት ካላገኘ በስተቀር በቴክኖሎጂው በሚገባ ለመጠቀም የማይችል ይሆናል። ለምሳሌ በአትክልት እርሻዎች፣ በመስኖ እርሻዎች ወዘተ. እንደዚህ አይነት የቴክኖሎጂ እድገትና የግብርና ዘይቤ ለውጥ በሚመጣበት ወቅት ወላጆች በቅድሚያ የልጆቻቸውን ጉልበት

www.abyssinialaw.com

መጠቀምን የሚመርጡበት ሁኔታ ስለሚፈጠር የወጣቶቹ ጉልበት በመሬት እጦት ምክንያት ባክኖ እንዳይቀር ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህን የመሰለ ሁኔታ በሚፈጠርበት ወቅት በወላጅና ልጅ መካከል ያለው ቤተሰባዊ ትስስር የሁሉንም ወገኖች ጥቅም በሚያስጠብቅ አኳኋን በአካባቢው የሚገኘውን አምራች ጉልበት አሟጦ መጠቀም የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጥራል ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ እንደየአካባቢውና እንደየነገሩ ሁኔታም ይህንኑ በህግና በመመሪያ መደገፍ ይቻላል፡፡

በአጭሩ መሬት የመንግስት መሆኑ ብቻ መሬትን በየጊዜው ማከፋፈል የሚጠይቅ አይሆንም፡፡ ይልቁንም በህገ-መንግስታችን የሰፈረው የመሬት ፖሊሲ ራሱ አርሶ አደሩ አርሶ እንዲጠቀምበት የተሰጠውን መሬት ለልጆቹ ማውረስ ይችላል ብሎ በግልፅ መደንገጉ መሬቱን በየጊዜው ማከፋፈል ከመሬት ፖሊሲው መሰረታዊ ባህሪ የማይመነጭ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ መሬትን በየጊዜው ማከፋፈል የሚያስከትለው የፖሊሲው አላማ ሳይሆን በገጠሩ አካባቢ መሬት የሌላቸው ወጣቶች የመኖራቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይህንኑ ችግር ከረጅም ጊዜ አኳያ በፈጣን ልማት፣ ከአጭር ጊዜ አኳያ ደግሞ ከላይ የተገለፁትን ስልቶች በቅንጅት በመጠቀም መፍታት ይቻላል፡፡ ይህን በማድረግ በመሬት የመጠቀም ዋስትናን በአስተማማኝ ሁኔታ አረጋግጦ ልማትን ማፋጠን ይቻላል፡፡ መሬት የመንግስት መሆኑ ይህን ከማድረግ አኳያ የሚፈጥረው አንዳችም እንቅፋት የለም፡፡ ስለሆነም ከዚህ በመነሳት የሚቀርበውም ትችት ምንም መሰረት የለውም፡፡

በመሬት ይዞታ ፖሊሲው ላይ የሚቀርበው ሌላው ትችት የመሬት ባለቤትነት በመንግስት ተይዞ እንዳይሸጥ በመከልከሉ



ከዚህም ባሻገር አርሶ አደሩ መሬቱን ማውረስ የሚችል በመሆኑ በውርስ ሲተላለፍ በይበልጥ እየተበጣጠሰ ፋይዳ ያለው የግብርና ልማት ሊካሄድ በማይችልበት ደረጃ ላይ ይደረሳል፡፡ መሬት የሚሸጥ ቢሆን ግን በግል ባለሀብቶች እጅ እየተሰባሰበ ከመበጣጠቅ ሊድን ይችላል በሚል የሚቀርበው ነው፡፡

በግብርና ስራ ላይ የተሰማራውን የሰው ሃይል በልማት ስራ ላይ ለማሰማራት የሚያስችል ከግብርና ውጪ የሆነ የስራ ዕድል ባልተፈጠረበትና ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ባለበት ሁኔታ መሬት በሽያጭ በጥቂቶች እጅ እንዲሰባሰብ ማድረግ የአገሪቱን አጠቃላይ እድገት ክፉኛ የሚጎዳ እንደሆነ ቀደም ሲል ተዘርዝሮ የተቀመጠ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ አማራጭ ልማታችንን አስተጓጉሎ ለባሰ አደጋ ያጋልጠን እንደሆን እንጂ መፍትሄ ሊሆን የሚችል አይደለም፡፡ ይህ አማራጭ ከሚያስከትለው የኢኮኖሚ ጉዳት በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት ተግባራዊ ይሁን ቢባል በጣም ብዙ አርሶ አደር አማራጭ የስራ ዕድል ሳይኖረው ተፈናቅሎ ለከፍተኛ ችግር የሚጋለጥበት፣ ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ ፈጥሮ ሰላማችንን ብሎም ልማታችንና ህልውናችን ለአደጋ የሚያጋልጥ ይሆናል፡፡

ኋላቀር ግብርና ባለበትና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በሌለበት ሁኔታ መሬት በግል ቢያዝም ከትውልድ ወደ ትውልድ በውርስ ሲተላለፍ እየተበጣጠሰ መሄዱ የማይቀር ነው፡፡ ከመሬት ይዞታ ለውጡ በፊት በአገራችን በተለይም የርስት አካባቢ ተብሎ በሚታወቀው መሬቱ ለዘመናት በይበልጥ እየተበጣጠሰ ሲመጣ የነበረ መሆኑን መገንዘብ የመሬት ባለቤትነት የመሬት መበጣጠስን በማስቀረት ረገድ የሚኖረው ሚና አነስተኛ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህ ይልቅ መፍትሄ የሚሆነው ፈጣን እድገትን ማረጋገጥ ነው። ፈጣን እድገት እውን በሚሆንበት ወቅት ኢንዱስትሪና ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች በፍጥነት ያድጋሉ፣ በሂደትም የኢኮኖሚው ዋነኛ ክፍል ወደመሆን ይሸጋገራሉ። በዚህ ሂደት በግብርና ለተሰማራው የሰው ሃይል ሰፊ የስራ እድል ይከፍታሉ። ከገጠሩ ወጣት ውስጥ በግብርና ስራ የሚሰማራው ቁጥሩ ደረጃ በደረጃ እየቀነሰ ይሄዳል። በግብርና ስራ ላይ የሚሰማራው የሰው ሃይል እየቀነሰ በሄደ ቁጥር የእርሻ ማሳ መበጣጠሱ ቀርቶ መሰባሰብ ይጀምራል። መሬት በግል የተያዘ በሆነበት አገር መሬቱ በእርሻ ስራ ለመቀጠል ለሚፈልገው እየተሸጠ ይሰባሰባል። መሬት የመንግስት በሆነበት አካባቢ መሬት የሚሰጠው በግብርና ስራ ለሚሰማራው ብቻ ስለሆነ ከግብርና ውጪ በቂ መተዳደሪያ ካለው እየተወሰደ በግብርና ስራ ለቀረው እየተሰጠ ይሰባሰባል። የበለፀጉ አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው ይህ ሂደት በመጨረሻው በገጠር ከፍተኛ የሰው ሃይል እጥረት እየፈጠረ ጉልበት በማሽነሪ እየተተካ ይሄዳል። ከዚህም አልፎ በአንዳንድ አካባቢዎች ገጠሮች ወጣት አልባ እየሆኑ የህፃናትና የሽማግሌዎች መናኸሪያ እስከመሆን ይደርሳሉ።

የብዙ አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው የመሬት መበጣጠስን በአስተማማኝ መልክ የሚያስቀረው የመሬት ባለቤትነት ፖሊሲ ሳይሆን ፈጣን እድገት ነው። በፈጣን እድገት ሂደት ህዝቡ ከግብርና ስራ እየወጣ ከግብርና ውጪ ወዳሉት ዘርፎች ይሸጋገራል። ለምሳሌ በአሜሪካን አገር እጅግ በጣም ዘመናዊና ምርታማ የሆነ የግብርና ዘርፍ ያለ ቢሆንም በአገሪቱ አጠቃላይ እድገት ምክንያት በዚሁ ስራ ላይ የተሰማራው



ከአገሪቱ አጠቃላይ ህዝብ ውስጥ ከሶስት በመቶ የሚያንስ ነው። እንደዚህ አይነት ሂደት በሚኖርበት ወቅት መሬት ከመሰባሰብ ውጪ ሊበጣጠስ አይችልም። የተከተልነው የልማት አቅጣጫ ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን እድገት ለማረጋገጥ የሚያስችል ዋነኛውና ብቸኛው አማራጭ ነው። በመሆኑም በሂደት መሬት ከመበጣጠስ ይልቅ እንዲሰባሰብ ለማድረግ የሚያስችል አስተማማኝ አማራጭ ነው። የገጠሩ ህዝብ በሂደት ከግብርና ስራ ውጪ የሚሰማራ እየሆነ በሄደ ቁጥር መሬት በመንግስት መያዙ ሌላ መተዳደሪያ ካለው መሬቱ እየተወሰደ በግብርና ለሚተዳደረው እየተሰጠ፣ መሬት በግል ቢያዝ ሊኖር ከሚችለው የመሬት መሰባሰብ በቀለለና በፈጠነ አኳኋን እንዲሰባሰብ ማድረግ ያስችላል። በመሆኑም መሬት እንዳይበጣጠስ ለማድረግ ያለውን አማራጭ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ መሬት በመንግስት መያዙ፣ በግል ከሚያዝ ይልቅ የቀለለ ያደርገዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ሌላም ትችት አለ። አርሶ አደሩ ቁራጭ መሬት በማግኘቱ ከቀየው ተሰዶ የተሻለ ኑሮ ከማፈላለግ ይልቅ በመንደሩ ታስሮ እንዲኖር ያደርጋል፣ የሰው ጉልበት በይበልጥ ውጤታማ ወደሚሆንበት አካባቢ እንዳይፈልስና በዚህም የኢኮኖሚ እድገት እንዳይቀላጠፍ ይደርጋል የሚል ትችትም ይቀርባል።

አርሶ አደሩ በግብርና ከሚያገኘው ገቢ የተሻለ ገቢ ካገኘ የተሻለ ገቢ ወደሚያገኝበት አካባቢ እንደሚፈልስና በገጠር መሬት ያለው መሆኑ ይህንን እንደማያስቀር በአሁኑ ወቅት ከገጠር ወደ ከተማ እያደረገ ያለውን ፍልሰት በማየት ብቻ

www.abyssinialaw.com

ማረጋገጥ ይችላል፡፡ ፍልሰቱ ከገጠር ወደከተማ ብቻም አይደለም፡፡ በቂ ዝናብና መሬት ከሌላቸው ገጠሮች በቂ መሬትና ዝናብ ወዳላቸው ገጠሮችም ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም የመሬት ባለቤትነት ስርአቱ በአገራችን ውስጥ የሰራተኛ ጉልበት ዝውውር እንዳይኖር በምንም አይነት መልኩ እንቅፋት አልሆነም፡፡

አርሶ አደሩ በመንደሩ ቁራሽም ትሁን መሬት ያለው መሆኑ በሰራተኛ ጉልበት ዝውውር ላይ ያስከተለው ተፅእኖ ቢኖር ሌላ የተሻለ አማራጭ የስራ እድል ወይም ቦታ ካላገኘ መንደሩን ለቆ እንዳይሄድ በማድረግ መልኩ ነው፡፡ የተሻለ አማራጭ አገኛለሁ ብሎ ሄዶ፣ ይህንኑ አማራጭ ሳያገኝ ቢቀር ተመልሶ ወደመንደሩ ገብቶ ያለችውን መሬት እንዲያርስ በማስቻል መልኩ ነው፡፡

አርሶ አደሩ የተሻለ ገቢ ሊያገኝ በሚችልበት ወቅት መንደሩን ለቆ መሄዱ ለራሱ ኑሮ መሻሻል ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱ አጠቃላይ እድገትም ጠቃሚና አስፈላጊ ነው፡፡ አሁን ያለው የመሬት ይዞታ ፖሊሲ እንደዚህ አይነቱን የሰራተኛ ጉልበት ዝውውር የሚያስቀር አለመሆኑ ፖሊሲው ከዚህም አኳያ ልማትን የማያስተጓጉል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የተሻለ የስራ አማራጭ በማይኖርበት ወቅት የሰራተኛው ጉልበት በመንደሩ ያለችውን ማሳ በማረስ ላይ እንዲወሰን ማድረጉ አነሰም በዛም በዚህ ስራ ገቢ ማግኘት የሚችለው ሰው ከመንደሩ ተነቅሎ በስራ አጥነት ባክኖ እንዳይቀር በማድረግ ምንም አይነት ልማታዊ አስተዋፅኦ የሌለው የጉልበት ዝውውር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ይህም የሰውን ኑሮ ከመጠበቅና የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ከማቀላጠፍ አኳያ እጅግ ጠቃሚና ተፈላጊ ነው፡፡



መሬት የግል ቢሆን ግን መሬቱን ከሸጠ በኋላ የስራ ዕድል ቢኖረውም ባይኖረውም መመለሻ ስለማይኖረው ከምርት ተግባር ተፈናቅሎ ኑሮው የሚጎሳቆልበት የአገሪቱም ልማት የሚስተጓጉልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በሌላ አነጋገር መሬት የመንግስት በመሆኑ የሰራተኛውን ኑሮ የሚያሻሽልና የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት የሚያቀላጥፍ የሰራተኛ ጉልበት ዝውውርን ሳያስቀር፣ የሰራተኛውን ኑሮ የሚያበላሽ፣ አምራቹን ሃይል በማምከንም የአገሪቱን እድገት የሚጎዳ የሰራተኛ ጉልበት ዝውውርን በማስቀረት በሰራተኛ ጉልበት ዝውውር አኳያ የላቀ ውጤት የሚያስገኝ ይሆናል፡፡

በማጠቃለል ሲታይ መሬት የመንግስት ሆኖ በግብርና ስራ ለመተዳደር የሚፈልግ ዜጋ መሬት የማግኘት መብቱ መከበሩ፣ ህዝቡ የስራ ችሎታው ጎልብቶ፣ ይህንኑ በምርት ተግባር ላይ ለማሰማራት የሚያስችለው መሬት አግኝቶ በልማት ስራ ላይ በሰፊው እንዲሰማራ በማስቻል የአገራችንን ኢኮኖሚያዊ እድገት በማቀላጠፍ ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበት ይህንኑ በሰፊው የመጠቀም ስትራተጅን፣ ይህን በአገራችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ከማረጋገጥም ሆነ ህዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ አማራጭ የማይገኝለትን ስትራተጅ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ፖሊሲው በአገራችን ልማት ላይ ልዩና ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ፖሊሲ ይሆናል፡፡ የመሬት ይዞታ ፖሊሲን በሚመለከት የሚቀርቡ ትችቶችም አንድ በአንድ ሲመረመሩ የተሳሳቱና መሰረተ-ቢስ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ፖሊሲውን በማስፈፀም ረገድ የሚታዩ ችግሮችን በማስወገድ ተግባራዊ ከተደረገ በማንኛውም መልኩ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ፖሊሲ ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## 3.2. የተስተካከለ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ መከተል፣

መሬቱ በግል ተያዘም በመንግስት ተያዘም አጠቃቀሙ የተስተካከለ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እያንዳንዷ ሜትር መሬት ለልማታችን የላቀ አስተዋፀኦ ማበርከት በምትችልበት ሁኔታ ጥቅም ላይ እየዋለች መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለቤትና ለከተማ ልማት መዋል የሚገባው መሬት የግጦሽ መሬት ከሆነ፣ የደንና የግጦሽ መሬት መሆን የሚገባው ከታረሰ፣ መታረስ የሚገባው መሬት ከተማ ከተስፋፋበት ወይም የግጦሽ መሬት እንዲሆን ከተደረገ ከመሬታችን ማግኘት የምንችለውንና ማግኘት የሚገባንን ልማት ስለማናገኝ አጠቃላይ ልማታችን መሰናከሉና መጓተቱ የማይቀር ይሆናል፡፡

እያንዳንዱ ሜትር መሬት የበለጠ ጥቅም ሊሰጥ በሚችልበት ስራ ላይ መዋሉ አንድ ጉዳይ ነው፡፡ የበለጠ ጥቅም ሊሰጥ በሚችልበት ስራ ላይ ከዋለም በኋላ አጠቃቀሙ እንክብካቤ የጎደለው ከሆነ ታጥቦ ጭቃ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ለምሳሌ የእርሻ መሬት ከአጠቃቀም ጉድለት አፈሩ ከተከላ ወይም በሂደት ጨዋማ ከሆነ ያ መሬት ከጥቅም ውጪ ሆኖ ልማታችን የኋሊት መጓዙ፣ አገራችን ለሰው ኑሮ የማትመች እየሆነች መሄዷ የማይቀር ይሆናል፡፡ እያንዳንዷ መሬት የላቀ ልማታዊ አስተዋፅኦ በምታበረክትበት አኳኋንና ዘላቂ ጥቅም ለመስጠት በሚያስችል አኳኋን በእንክብካቤ ጥቅም ላይ መዋልዋን ማረጋገጥ የሚቻለው ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላና የተስተካከለ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ሲኖር ነው፡፡ በአገራችን እንደዚህ አይነቱ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ በተሟላ መልኩ አለመውጣቱና ተግባራዊ አለመሆኑ በተለይም ከረጅምና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ ሲታይ በልማታችን ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊደቅን የሚችል ነው፡፡



ይህ ችግር በአንድ መልኩ ሲታይ እያንዳንዱ ሄክታር መሬት ለምን ስራ መዋል እንዳለበትና ምን አይነት እንክብካቤ ማግኘት እንዳለበት ዘርዝሮ በማስቀመጥና እነዚህን በደንብና በመመሪያ አስደግፎ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆኑበት የአፈፃፀም አቅም ለመፍጠር አለመቻልን ያመለክታል፡፡ እንደዚህ አይነቱን የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ለማውጣት በፌዴራል መንግስት ደረጃ አንዳንድ ሙከራዎች የተደረጉና አንዳንድ ክልሎችም በዚህ ረገድ ቀላል ግምት የማይሰጠው ስራ የሰሩ ቢሆንም ስራው አጥጋቢ በሆነ መልኩ ገና አልተሰራም፡፡ ስራው የሚጠይቀው ጊዜና ሙያተኛ ከፍተኛ መሆኑ አንድ ጉዳይ ሆኖ ለስራው የተሰጠው ትኩረትና አፈፃፀሙ እንዴት እንደሚሆን በውል ተለይቶ አለመቀመጡም ሌላው ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ይህን ጉዳይ በተመለከተ ያሉትን ችግሮች አስወግዶ ፖሊሲው የሚወጣበትንና ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ በተቻለ ፍጥነት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

ነገር ግን የመሬት አጠቃቀምን በሚመለከት ዋናው ችግር ፖሊሲ ያለማውጣትና የአፈፃፀም ስርአቱን አለመገንባት አይደለም፡፡ ይህ ችግር የራሱ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሚና ቢኖረውም ዋናው ችግር ድህነትና ኋላ ቀርነት ነው፡፡ በብዙ አካባቢዎች መታረስ የማይገባው ተዳፋት መሬት ይታረሳል፣ ደን ይጨፈጨፋል፡፡ ለእርሻ በሚሆነው ማሳ ላይ የሚካሄደው የግብርና እንቅስቃሴ ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲሻሻል ቢደረግ ህዝቡ ተዳፋት መሬት ወደማረስም ሆነ ደን ወደ መጨፍጨፍ ባልገባ ነበር፡፡ ድህነቱና ኋላ ቀርነቱ ነው ህዝቡን

www.abyssinialaw.com

በመሬት ያለአግባብ ወደ መጠቀም እየመራው ያለው፡፡ ተዳፋት መሬቶች ሳይታረሱ ለህዝቡ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኙበት ስልት ቢቀየስና ቢተገበር፣ ደኖች ለህዝቡ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ የሚሆኑበት አሰራር ቢኖር ህዝቡ እነዚህን ከመጨፍጨፍ ይልቅ በእንክብካቤ ይዞ ገቢውን ማሳደግ በመረጠ ነበር፡፡

በመሆኑም የመሬት አጠቃቀምን በከፍተኛ ደረጃና በርግጥም ተግባራዊ በሚሆን መልኩ ለማሻሻል ድህነትንና ኋላ ቀርነትን የማጥፋት እንቅስቃሴው ተጠናክሮ መካሄድ ይኖርበታል፡፡ ለእርሻ የተመቹ መሬቶችን ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል በዚህ አካባቢ የሚካሄደው የግብርና ስራ በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች እንዲደገፍ፣ የውሃ ማቆርና አጠቃቀም ስርአታችንን በማሻሻል ከውሱን የእርሻ ማሳ የላቀ ገቢ ማስገኘት የምንችልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ ይህ ሲሆን ህዝቡ የእርሻ ማሳውንም በላቀ ደረጃ ተንከባክቦ ይጠቀምበታል፣ ተዳፋት መሬት ወደማረስና ደን ወደ መጨፍጨፍም አይገባም፡፡

ጥሩ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ማለት የተወሰነውን መሬት የህዝቡን ኑሮ ለሚያሻሽል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ተጠቅሞ የተቀረውን ለኢኮኖሚ ልማት በማይውል አኳኋን መጠበቅ ማለት አይደለም፡፡ ተዳፋት መሬት መታረስ የለበትም፣ ደን መጨፍጨፍ የለበትም ሲባልም እነዚህን መሬቶች ለህዝቡ ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማይሰጥ አኳኋን እንዲጠበቁ ከመፈለግ አይደለም፡፡ ይልቁንም እነዚህ መሬቶች የላቀ እንክብካቤ ሊደረግላቸውና ሊጠበቁ የሚችሉት ለህዝቡ ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ መስጠት ሲችሉ ነው፡፡ ስለሆነም ተዳፋት መሬቶችን ሳይታረሱ ለግጦሽ፣ የተለያዩ ተክሎችን ለማልማት ወዘተ. በመጠቀም ህዝቡ በቀጥታና በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም



እንዲያገኝባቸው መደረግ ይገባቸዋል፡፡ ደኖችም በተመሳሳይ መልኩ ለህዝቡ የገቢ ምንጭ መሆን አለባቸው፡፡ ይህን ለማድረግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፖኬጅ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ካልሆነ በስተቀር፣ ድህነትንና ኋላቀርነትን ከማስወገድ ትግል ውጪ እነዚህ አካባቢዎች ሊጠበቁና በአግባቡ ልንጠቀምባቸው አንችልም፡፡

የተስተካከለ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ በማውጣትና በመተግበር፣ ካለችን ከእያንዳንዷ ሄክታር መሬት የላቀ የኢኮኖሚ ጥቅምና ልማት እንድናገኝ ሁለቱን ነገሮች በቅንጅትና በተቻለ ፍጥነት መስራት ይኖርብናል፡፡ በአንድ በኩል መሬታችንን እንደየባህሪው ለህዝቡ የላቀና ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ አኳኋን ልንጠቀምበት የሚያስችለን የቴክኖሎጂ ፖኬጅ ማዘጋጀትና አርሶ አደሩን ይህን ተግባራዊ ሊያደርግ በሚችልበት ደረጃ ላይ ማድረስ አለብን፡፡ ከመሬት አጠቃቀማችን አኳያ በተግባር የላቀ ደረጃ ላይ ሊያደርሰን የሚችለው ዋናው ስራም ይህ መሆን አለበት፡፡ ይህ ስራ በየጊዜው እየተሻሻለ፣ ስፋትና ጥልቀት እያገኘ የሚሄድ እንጂ አንድ ጊዜ ተሰርቶ የሚያልቅ እንዳልሆነ መገንዘብም ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ስራ ጎን ለጎንና በዚህ ስራ ላይ ተመስርተን የተሟላ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ማውጣት፣ ይህንኑ በአፈፃፀም ደንቦችና መመሪያዎች መደገፍ፣ ፖሊሲውን የሚያስፈፅም አካል መሰየምና ማብቃት አለብን፡፡ ይህም ስራ አንዴ ተሰርቶ የሚያበቃ ሳይሆን አንድ ደረጃ ላይ ተጀምሮ በሂደት እየተሻሻለ፣ ስፋትና ጥልቀት እያገኘ የሚሄድ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 3.3. የውሃ አጠቃቀማችንን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል፣

የግብርና ስራ ያለውሃ ሊታሰብ የሚችል ጉዳይ አይደለም:: የግብርና ስራ እጅግ ውጤታማ የሚሆነው የግብርናው ምርት የሚፈልገውን ውሃ በሚፈልገው መጠንና ጊዜ ሲያገኝ ብቻ ነው:: የውሃ አቅርቦቱ ከሚፈለገው በላይ ወይ በታች ከሆነ ወይም በሚፈለግበት ጊዜ ካልተገኘ የግብርና ምርቱ በከፍተኛ ደረጃ ሊቀንስ ወይም ጭራሹን ሊጠፋ ይችላል:: በመሆኑም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት ለማረጋገጥ ከተፈለገ አስተማማኝ የውሃ አቅርቦትና አስተዳደር (ሜኔጅመንት) ስርአት መኖር አለበት:: በግብርና ስራ ላይ የተሰማራው ህዝብ አመቱን ሙሉ ለግብርና ስራ የሚያገልግል በቂ ውሃ ካገኘ በአነስተኛ ማሳ እጅግ በጣም ከፍተኛ ምርት ለማግኘት፣ የሰውን ጉልበት አመቱን ሙሉ በምርት ስራ ላይ ለማሰማራት ይችላል:: እንደግብ መቀመጥ ያለበትም ይህንኑ ማሟላት ነው::

አገራችን ከፍተኛ የገፀ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃ ሃብት እንዳላት ይታወቃል:: ይህንኑ ሃብት በአግባቡ ለመጠቀም የሚቻለው የዚህ ሃብት አጠቃቀም ፖሊሲ ይህንኑ ለማስፈፀም የሚያስችል ህግና ደንብ ሲኖርና ተግባራዊ ሲሆን ነው:: ውሃም እንደመሬት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለውና ውሱን ሃብት ነው:: በቁጠባና የላቀ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በሚያስገኝ አኳኋን ጥቅም ላይ ካልዋለ በስተቀር ሊባክን ይችላል፣ የኢኮኖሚ እድገታችንም በዚያው መጠን ሊዳከም ይችላል:: ይህን ሃብት በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል በቅድሚያ መሰራት ካለባቸው ስራዎች አንዱ ይህንኑ የሚመለከት ፖሊሲ፣ ህግና ደንብ



ማውጣት ነው:: የፌዴራል መንግስት ፖሊሲውንና አስፈላጊ ህጎችን አውጥቶ ተግባራዊ ሊሆኑ በሚችሉባቸው አካባቢዎች ሁሉ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል:: በመሆኑም በዚህ ረገድ የሚሻሻል ስራ የለም ባይባልም ዋናው ነገር ተከናውኗል ማለት ይቻላል::

የውሃ አጠቃቀማችንን ለማሻሻል አጠቃቀሙ የሚመራበት ፖሊሲና ህግ የመኖሩ ጉዳይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቢሆንም የውሃ ማቆርና ማስተዳደር አቅም መገንባት ካልተቻለ ሌላው ሁሉ ፋይዳ አይኖረውም:: የአገራችንን የከርሰ-ምድርና የገፀ-ምድር ውሃ በአግባቡ ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር የሚያስችል አቅም ባለመገንባታችን ከፍተኛ የገፀ-ምድርና የከርሰ--ምድር ውሃ ባለበት የአገራችን አካባቢ ህዝባችን በውሃ እጥረት የከብት ጭራ ተከትሎ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ በኋላ ቀር የከብት ርቢ ስርአት ውስጥ በከፍተኛ ድህነት ይኖራል:: የማይቆራረጥ በቂ ዝናብ ባላቸው የአገራችን አካባቢዎች አመቱን ሙሉ የግብርና ምርት ስራ መስራት ሳይቻል እየቀረ ማግኘት የሚገባንን ያህል እድገትና የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ሳናገኝ እንቀራለን:: ይልቁንም በአመት አንዴ የሚገኘውን ምርት ለማግኘትም አንዳንዴ ዝናቡ እየበዛና ወቅቱን ያልጠበቀ እየሆነ፣ ሌላ ጊዜ ዝናቡ እያጠረ የምናገኘው ምርት ከአመት አመት በከፍተኛ ደረጃ ሲዋዥቅ ይታያል:: እጅግ በሚያሰጋ አኳኋን እየሰፋ በመምጣት ላይ ባለ የአገራችን አካባቢ ዝናቡ እየተቆራረጠና እያጠረ ህዝባችን ለቀጣይና አስከፊ ረሃብ እየተጋለጠ ይገኛል::

የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው እንዲሉ ከፍተኛ የገፀ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃ ባላት አገራችን ይህንኑ የውሃ

ሃብት በሚገባ ተቆጣጥረን ለልማታችን ማዋል የሚያስችል አቅም ስለሌለን በውሃ እጥረት ለረሃብና ለድህነት ተጋልጠን ቆይተናል፡፡ የውሃ ሃብታችንን ለማልማትና በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችለን የገንዘብና የሙያተኛ አቅም ባለመገኘቱ የአበው ተረት እንደሚገልፀው ትልቅ ወንዝ ዳር ላይ ተቀምጠን እንጠማለን፡፡ ይህ የሆነው በርካታ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ስለነበሩ ነው፡፡

ብዙዎቹ ወንዞቻችን በተለይም ወደምዕራብ የሚፈሱት የናይል ወንዝ ተፋሰሶች ድንበር ተሻጋሪ ናቸው፡፡ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ከመሆናቸውም አልፎ ሱዳንና ግብፅ በተለይም ግብፅ በዚህ ወንዝ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥገኛ የሆኑና ይህንኑ ወንዝ በላቀ ደረጃ እየተጠቀሙበት የሚገኙ ናቸው፡፡ ለወደፊቱም እስካሁን ካለው በላይ ለመጠቀም ቅድመ ዝግጅታቸውን እየጠናቀቁ ያሉ ናቸው፡፡ በዚህ በኩል የላቀና ወሳኝ ሚና እየተጫወተች ያለችው ግብፅ ነች፡፡ ኢትዮጵያ በውሃ ሃብቷ በሰፊው መጠቀም ብትችል የግብፅ ጥቅም ይነካል የሚል አስተሳሰብ በግብፅ መሪዎች ዘንድና በተወሰነ ደረጃም በህዝቡ ዘንድ በጥብቅ ሲታመንበት የቆየ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ግብፅ ያላትን ተሰሚነትና ወዳጆችዋን በመጠቀም ኢትዮጵያ የውሃ ሃብቷን ለማልማት የሚያስፈልጋትን የውጭ ብድርና ርዳታ እንዳታገኝ ለማድረግ ከሞላ ጎደል የተሳካ ስራ ሰርተዋል፡፡ የውሃ ሃብትን በሰፊው ለማልማት ከፍተኛ የገንዘብ አቅም የሚጠይቅ በመሆኑና በአገራችን ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ያለ በመሆኑ ይህ ችግር የውሃ ሃብታችንን በላቀ ደረጃ እንዳንጠቀምበት እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ችግር በመገንዘብ በአንድ



በኩል የውሃ ሃብታችንን አቅማችን እስከፈቀደ ድረስ በራሳችን ገንዘብ ለማልማት ጥረት እያደረገ (ለምሳሌ የጢስ አባይ አዲሱ ግድብ፣ ወደፊት ሊሰራ የታቀደው የተከዜ ግድብ) በሌላ በኩል የናይል ተፋሰስ ውሃን ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን ለመጠቀም የሚያስችል ስርአት እንዲዘረጋ፣ የአለም ህብረተሰብ ይህንኑ አላማ እንዲደግፍ፣ በወንዙ ተጠቃሚ የሆኑ አገሮችም ከዚህ ውጪ ዘላቂና አስተማማኝ መፍትሄ እንደሌለ እንዲገነዘቡ ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በራሳችን አቅም የማልማቱን ጉዳይ በተመለከተ ዋናው ገደብ የገንዘብ አቅም ስለሆነ የገንዘብ አቅማችን በፈቀደው መጠን ለማልማት ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን፣ በዚህም ረገድ ቀላል ያልሆነ ውጤት አግኝተናል፡፡ የናይል ተፋሰስን የውሃ አጠቃቀም ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ የተደረገው ጥረትም በአሁኑ ወቅት አንዳንድ ተስፋ ሰጪ ውጤቶችና ፍንጮች ማሳየት ጀምሯል፡፡ በአለም ባንክ አስተባባሪነት የናይል ተፋሰስ ውሃ አጠቃቀምን በተመለከተ በሚመለከታቸው አገሮች መካከል የጋራ አመለካከት ለመፍጠር ሲካሄድ የነበረው ጥረት የሚያበረታታ ውጤት አስገኝቷል፡፡

የተፋሰሱን ውሃ አጠቃቀም በሚመለከት የጋራ የልማት ሃሳብ ለማመንጨት በተደረገው ጥረት የጋራ የ20 አመት ጠቋሚ የውሃ ሃብት ልማት እቅድ ተዘጋጅቶ ኢትዮጵያ ሱዳንና ግብፅ ሊስማሙበት ችለዋል፡፡ ኢትዮጵያን በተመለከተ እቅዱ ሰፊ የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ስራን፣ በአባይና በሌሎቹ የናይል ተፋሰስ ወንዞች ላይ ከፍተኛ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ተሰርተው የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ሃይል ከኢትዮጵያ ፍጆታ በላይ ስለሚሆን ወደጎረቤት አገሮች እንዲሸጥ፣ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የመስኖ ልማት ስራ እንዲሰራ የሚጠቁም ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

ይህ አጠቃላይ ስምምነት ወደተግባር ምን ያህል ይተረጎማል የሚለው ጉዳይ በሂደት የሚታይ ነው። ፕሮግራሙን ለመፈፀም በተለይም የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤን በተመለከተ ርዳታ ይገኛል ተብሎ የሚታሰብ ቢሆንም ሌላው ስራ በተለይም የግድቦቹ ስራ በዋነኛነት የግል ባለሃብቶችን በማሳተፍ ይሰራል ተብሎ የሚገመት ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ሱዳንና ግብፅ በተለይም ግብፅ ኢትዮጵያ በናይል ተፋሰስ ወንዞች ላይ በርካታና ከፍተኛ ግድቦች መስራቷንና ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የመስኖ ስራ መስራቷን እንደግፋለን ማለታቸው አንድ መሰረታዊና ትልቅ ርምጃ ነው። በዚህ ላይ ተመስርቶ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ብድርና ርዳታ ለማሰባሰብ የግል ባለሀብቶችን ለማንቀሳቀስ የተሻለ እድል ሊፈጥር ይችላል ተብሎ ይገመታል።

ከገንዘብ እጥረቱ ባልተናነሰ ሁኔታ የውሃ ሃብታችንን በአግባቡ እንዳንጠቀም ገድቦን የሚገኘው ሌላው ትልቅ ችግር የውሃ ሃብት አጠቃቀም ሞያተኞች ከፍተኛ እጥረት ያለ መሆኑ ነው። እጥረቱ በዩኒቨርስቲዎች የሰለጠኑ ከፍተኛ ሙያተኞች ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በየደረጃው መኖር የሚገባቸው ቴክኒሻኖችንና ሌሎች ሙያተኞችንም የሚመለከት ነው። ይህ ችግር የተስተካከለ የውሃ ሃብት እቅድ በየደረጃው ለማውጣትና ለማስፈፀም ሳይቻል እንዲቀር አድርጓል። ይህ ችግር በአስተማማኝ መልኩ ካልተወገደ በስተቀር በራሳችን አቅም ለመስራት የሚቻለውም ሆነ፣ የውጭ ብድርና ርዳታ በማሰባሰብና የግል ባለሃብቶችን በማስተባበር ሊሰራ የሚችለው የውሃ ሃብት ልማት ስራ በሚፈለገው ደረጃ ሊካሄድ አይችልም። በመሆኑም በዚህ መስክ በተለያዩ ደረጃዎች የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት የውሃ ሃብታችንን ለማልማት ሲባል ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ ተሰጥቶት መፈፀም ያለበት ነው።



መንግስት ይህንኑ አቅም ለመፍጠር የተለያዩ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። የዋና ዋና ወንዞቻችንን የውሃ ሃብት ልማት ማስተር ፕላን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ የብዙዎቹ ተዘጋጅቷል፣ በመዘጋጀት ላይ ያለም አለ። ይህን ማስተር ፕላን በውጭ ሞያተኞች ማዘጋጀት አማራጭ ያልነበረው በመሆኑ የአገር ውስጥ ሙያተኞች ከውጪ ሞያተኞች ጋር ተባብረው እንዲሰሩ በማድረግ በአንድ በኩል ስራው በተሻለ ጥራት እንዲሰራ በሌላ በኩል ደግሞ የአገር ውስጥ ሞያተኞች በስራው ላይ ልምድ እንዲያገኙ ለማድረግ ተችሏል። የአርባ ምንጭ የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን በማጠናከርና በማስፋፋት በከፍተኛና በመካከለኛ ደረጃ ሞያተኞችን ለማሰልጠን ጥረት ተደርጓል። ይህ ስራ ወደፊትም በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክሮ የሚቀጥልና መቀጠልም የሚገባው ነው። በቅርቡ በተጀመረው የላቀ ሞያ ያላቸው በየቀበሌው የሚመደቡ ሙያተኞችን በመለስተኛ ኮሌጆችና በሌሎች የሞያ ማሰልጠኛ ተቋሞች የማሰልጠን ስራ ለውሃ ሃብት ልማት ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶታል። በየቀበሌው ከሚመደቡት ሙያተኞች አንዱ በተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና በውሃ ሃብት ልማት፣ በመለስተኛ የመስኖ ስራ የሰለጠነ እንዲሆን ይደረጋል። ይህም በየቀበሌው በየአርሶ አደሩ ማሳ የሚሰራው የውሃ አጠቃቀምን የማሻሻል ስራ ብቃት ያለው የሞያ ድጋፍ እንዲያገኝ ያደርጋል። እነዚህ ስራዎች ለወደፊቱም ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚሰሩ ይሆናሉ።

የሰው ሃይላችንን ለማሰልጠን የምናደርገው ጥረት በውሃ ሃብታችን የመጠቀም አቅማችንን በከፍተኛ ደረጃ የሚያሻሽል ቢሆንም ያለብንን ከፍተኛ የካፒታል እጥረት የሚያስወግድ ግን አይሆንም። የሰው ሃይላችንን ለማሰልጠኑ ስራ ቅድሚያ ሰጥተን ከዚሁ ጎን ለጎን የገንዘብ እጥረት በውሃ ሃብታችን በአግባቡ

እንዳንጠቀም የሚፈጥርብንን እንቅፋት ለማስወገድ የሚያስችሉ ስልቶችን ነድፈን መንቀሳቀስ አለብን። ይህንኑ ከማድረግ አኳያ ያሉን አማራጮች ሶስት ሲሆኑ ሶስቱንም በቅንጅት መጠቀምና ተግባራዊ ማድረግ መቻል አለብን።

የካፒታል ችግር ሲያጋጥም የሰው ጉልበት ካፒታልን ሊተካ በሚችልበት ደረጃ በሰፊው መጠቀም በሁሉም የልማት ስራዎቻችን የምንጠቀምበት መንገድ ነው። የውሃ ሃብታችንን በማልማትም ረገድ ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ስለሚኖር ጉልበትን በሰፊው በሚጠቀም አኳኋን የውሃ ሃብታችንን የማልማት ስልትን ዋነኛው መፍትሄ አድርገን መውሰድ አለብን። አስተማማኝና ሰፊ የልማት ሃይላችን የሰው ሃይላችን ስለሆነ የውሃ ሃብታችንን በማልማት ስራም ላይ ያለብዙ የገንዘብ ወጪ በሰው ጉልበት ሊሰሩ በሚችሉ ስራዎች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ባለባት አገራችን ከፍተኛ ካፒታል በመጠቀም ላይ ያተኮረ የውሃ ሃብት ልማት አቅጣጫ መከተል አንችልም፣ ይህንን አቅጣጫ ብንከተልም የውሃ ሃብት ልማት እንቅስቃሴያችንን በከፍተኛ ደረጃ ከማዳከም አልፎ የሚገኝ ጥቅም አይኖርም።

የውሃ ሃብት አጠቃቀማችንን ለማሻሻል የአርሶ አደሩን የአስተራረስ ዘይቤ (አግሮኖሚክ ፕራክቲስ) ከማሻሻል ነው መጀመር ያለበት። በማሳው ላይ በሚዘንበውን ውሃ ለማስቀረትና በአግባቡ ለመጠቀም፣ ወደማሳው የሚገባውንም ሆነ ከማሳው የሚወጣውን ውሃ ለመቆጣጠርና አጠቃቀሙን ለማሻሻል የሚያስችሉ ስልቶችን መጠቀምንም መጨመር አለበት። ከዚህ አልፎም የአካባቢን ዝናብና ጎርፍ በማቆር ለመስኖ ልማት ለማዋል የሚያስችሉ በዝቅተኛ ዋጋና በአርሶ አደሩ በራሱ



ሊሰሩ የሚችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም መቻል አለብን። አነስተኛ የወንዝ ጠለፋና የግድብ ስራዎችም በዚሁ ክልል ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው።

ይህን አሰራር በተመለከተ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን በመነሻነት መጠቀም ያስጋልጋል። በመጀመሪያ ደረጃ በአርሶ አደሩ ማሳና በዙሪያው የሚዘንበውን ዝናብ የማቆር፣ የመቆጣጠርና አጠቃቀሙን የማሻሻል፣ ሌሎች የአካባቢ የውሃ ምንጮችንም በተመሳሳይ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችንና አማራጮችን በሙሉ በመዳሰስ፣ በርካታ አማራጮችን የያዘ ሁለገብ -ኬጅ የማዘጋጀት አማራጭ መከተል አለብን። አንድ የውሃ ሃብት አጠቃቀም ቴክኖሎጅ ምንም ያህል ውጤታማ ቢሆን ብቻውን የምንፈልገውን ውጤት ሊያስገኝልን አይችልም። በርካታ የውሃ ሃብት አጠቃቀም ቴክኖሎጂዎችን በማጣመር በጣም ቀላል ከሆነው ጀምሮ ሌሎችንም የሚያካትት -ኬጅ በማዘጋጀት ሁሉንም በጣምራና በቅንጅት በመስራት ነው የላቀ ውጤት ልናገኝ የምንችለው። ስለሆነም እስካሁን በዚህ ደረጃ የሚታወቁትን ገምግመንና ቀምረን እንደ -ኬጅ ተግባራዊ ማድረግ መጀመር አለብን። በየጊዜው -ኬጁን እያሻሻልን መሄድም አለብን።

ጉልበትን በላቀ ደረጃ የሚጠቀም የውሃ ሃብት አጠቃቀም ቴክኖሎጂን ከማስፋፋት አኳያ ሁለተኛው መሰረታዊ መነሻችን ዋናው ስራ በአርሶ አደሩ ማሳ ዙሪያና በአርሶ አደሩ በራሱ የሚሰራ መሆን እንዳለበት ነው። በርግጥ እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በተሟላ መንገድ እንዲጠቀም ለማድረግ አርሶ አደሩን በምክርና ስልጠና፣ እንዲሁም በብድር አገልግሎት መደገፍ አማራጭ አይኖረውም። ይሁንና እነዚህ ድጋፎች

www.abyssinialaw.com

ተሟልተው ስራው በዋነኛነት በአርሶ አደሩ በራሱ በማሳውና በማሳው ዙሪያ የውሃ ማቆርና አጠቃቀሙን የማሻሻል አቅጣጫን መከተል ይኖርብናል፡፡ ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ባለባት አገራችን ጉልበትን በሰፊው በመጠቀም የውሃ ሃብታችንን በአፋጣኝ ለማልማት የሚያስችለን አቅጣጫ ይኸው ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የቀበሌውን ህዝብ በማስተባበር ሊካሄዱ የሚችሉ የወንዝ ጠለፋ፣ የመለስተኛ ግድብ ስራዎችም መስራት ይኖርብናል፡፡ እነዚህን ስራዎች ህዝባችንን አነሳስተን የምክርና የብድር አገልግሎት ሰጥተን መስራት ከቻልን አሁን ለመገመት ከሚቻለው በላይ የውሃ ሃብታችንን መቆጣጠርና በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል እንችላለን፡፡

ዋናው የውሃ ሃብት አጠቃቀም አቅጣጫችን ጉልበትን በሰፊው በሚጠቀም ቴክኖሎጂ በመታገዝ በአርሶ አደሩ በራሱ በማሳውና በቀበሌው የሚሰሩ የውሃ ሃብት ልማት ስራዎችን መስራት ቢሆንም ይህ ብቻ በቂ አይሆንም፡፡ የግል ባለሃብቶች፣ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብቶች በውሃ ሃብት ልማት በሰፊው እንዲሳተፉ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡ ያለን ፖሊሲ የግል ባለሃብቶች የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድቦችን ሰርተው እንዲጠቀሙ የሚፈቅድና የሚያበረታታ ነው፡፡ በመስኖ ልማት ስራም ላይ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶች በሰፊው እንዲሳተፉ የሚፈቅድና የተለያዩ ማትጊያዎችን የሚሰጥ ፖሊሲ አለን፡፡ ፖሊሲዎቹንና ማትጊያዎቹን በሚመለከት ያሉንን መመሪያዎች በየጊዜው እየፈተሹ ማሻሻል ተገቢ ቢሆንም ዋናው ጉዳይ ግን ይህ አይደለም፡፡ ያሉት ፖሊሲዎችና ማትጊያዎች አሁን ባሉበት ደረጃም ሰፊ የግል ኢንቨስትመንትን ለመጋበዝ የሚችሉ ናቸው፡፡



በመስኖ ልማት ረገድ ትልቅ ማነቆ ሆኖ የሚገኘው ሌላው ጉዳይ ሰፋፊ የመስኖ እርሻዎች ሊቋቋሙ በሚችሉባቸው አካባቢዎች በቂ የመሰረተ-ልማት አገልግሎትና ሰራተኛ ጉልበት የሌለ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ችግር ቀደም ሲል እንደተገለፀው የነዚህን አካባቢዎች የተቀናጀ የአካባቢ ልማት እቅድ በማዘጋጀት መፈታት ያለበት ነው፡፡ በተለይም የውጭ ባለሃብቶችን ከመሳብ አኳያ በናይል ተፋሰስ ወንዞች ላይ ኢንቨስት እንዳያደርጉ ሲደረግባቸው የነበረው ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ተፅእኖ ከባድ ነው፡፡ ይህንን ችግር በተጀመረው የናይል ተፋሰስ ልማት የጋራ ራዕይ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመቅረፍ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ያሉት የኢንቨስትመንት ዕድሎች በኢንቨስተሮች አካባቢ በተፈላጊው ደረጃ አለመታወቃቸው ሌላው ችግር ስለሆነ ይህንኑ ለማስወገድ ሰፊ የማስተዋወቅና ኢንቨስተሮችን የመሳብ ስራ መስራት አለብን፡፡ በአጠቃላይ የግል ባለሃብቶችን በላቀ ደረጃ በማሳተፍ በካፒታል እጥረት ምክንያት የተፈጠረውን የውሃ ሃብታችንን በአግባቡ ለመጠቀም ያለመቻልን ችግር ለማቃለል ጥረት ማድረግ፣ የውሃ ሃብታችንን ለማልማት የምንጠቀምበት ሁለተኛው መሰረታዊ ስልት ነው፡፡

መንግስትም የውሃ ሃብታችንን ለማልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል፣ ይገባዋልም፡፡ በርግጥ ይህንን በተመለከተ የመንግስት ዋነኛ ትኩረት የሰው ሃይል በማሰልጠንና አርሶ አደሩ ጉልበትን በሰፊው በሚጠቀም አኳኋን የውሃ ሃብታችንን ለማልማት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ መደገፍ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁንና ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎችንም ስራዎች መስራት ይችላል፡፡ የግል ባለሃብቶች በውሃ ሃብት ልማት ስራ ላይ በሰፊው እንዲሰማሩ ለማበረታታትና ለማስተባበር የሚያስችል የተጠናከረ ስራ መስራት ይችላል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከዚህም ባሻገር የኤሌክትሪክ ሃይል ከማመንጨት ስራ ጋር በተያያዘ በተመረጡ አካባቢዎች ግድቦችን መስራት፣ እነዚህ ግድቦች የመስኖ ስራን ለማስፋፋት እንዲረዱ ማድረግ ይችላል::

በማጠቃለል የውሃ ሃብታችንን ማልማትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት የማረጋገጥ ስራችን የተመሰረተበት ሶስተኛው ምሰሶ ነው:: የውሃ አጠቃቀም ፖሊሲያችንንና ህጎችን በየጊዜው በማሻሻልና አፈፃፀሙን በማጠናከር፣ ለዚህ ስራ የሚፈለጉ ሙያተኞችን ለማፍራቱ ስራ የላቀ ግምት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ፣ ጉልበትን በሰፊው በመጠቀም የውሃ ሃብት የማልማትን አቅጣጫ በመከተልና የግል ባለሃብቶች በውሃ ሃብት ልማት ስራ እንዲሰማሩ በማበረታታት የውሃ ሃብታችንን ማልማትና አጠቃቀሙንም ማሻሻል አለብን::

## 4. ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የልማት ፖኬጅ ማዘጋጀት፣

በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በአገራችን በጣም የተለያዩ የአግሮ ኢኮሎጂ ዞኖች አሉ:: በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የምናካሂደው የግብርና ልማት እንቅስቃሴ ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት:: በተወሰኑ ምርቶች ላይ የማተኮር (የስፔሻላይዜሽን) የተለያዩ የግብርና ምርቶችን አጣምሮ የማምረት ስራን በተቀናጀ አኳኋን ለማስፈፀም የሚችል መሆን አለበት::



### 4.1. ዳይቨርሲፊኬሽንና ስፔሻላይዜሽንን ማጣመር፣

በአገራችን ልዩ ልዩ የአግሮ ኢኮሎጂ ዞኖች መኖራቸው በነዚህ የተለያዩ ዞኖች በላቀ ደረጃ ሊመረት የሚችለው የግብርና ምርት የተለያየ እንዲሆን ያደርጋል:: በአንድ የአግሮ-ኢኮሎጂ ዞን በላቀ ደረጃ ሊመረት የሚችለው ምርት በሌላው አካባቢ በፍፁም ሊመረት የማይችል ወይም ቢመረትም የላቀ ውጤት ሊያስገኝ የማይችል ይሆናል:: በዚህ ሁኔታ የተለያዩት የአግሮ-ኢኮሎጂ ዞኖች በአካባቢያቸው ሁኔታ የላቀ ውጤት በሚያስገኙላቸው የግብርና ምርት ላይ እንዲያተኩሩ ቢደረግና ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችላቸው የቴክኖሎጂ ፖኬጅ ቢዘጋጅ የየአካባቢው ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ ሊጠቀም ይችላል:: የአገሪቱ አጠቃላይ እድገትም ይፋጠናል:: በነዚህ ዞኖች መካከል በዚህ መልኩ የስራ ክፍፍልና ክባቢያዊ ስፔሻላይዜሽን ይዳብራል::

ይህንን ጉዳይ አንድ ምሳሌ በመውሰድ በይበልጥ መረዳት ይቻላል:: በአርሲና ባሌ ሰፋፊ ደጋማ ሜዳዎች የሰብል ምርትን በከፍተኛ ደረጃ ማምረት ይቻላል:: ይህ አካባቢ ለረጅም ጊዜ ዋነኛ የስንዴ አምራች አካባቢ ሆኖ ቆይቷል:: በሌላ በኩል ደግሞ በጌዴኦ ደጋማ አካባቢዎች በጥራቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት የቡና ምርት ሊመረት ይችላል፣ በመመረት ላይም ይገኛል:: በባሌና አርሲ ደጋማ አካባቢዎች ስንዴውንም ቡናውንም ሌላውንም እናምርት ቢባል፣ በጌዶኦ ከፍተኛ ቦታዎችም በተመሳሳይ መልኩ እንሂድ ቢባል የአካባቢውም የአገሪቱም ልማት ሊፋጠን አይችልም:: ከዚህ ይልቅ በአርሲና ባሌ ሜዳዎች የሰብል ምርቱን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻልን ማዕከል ያደረገ ልማት ቢካሄድ፣ በጌዴኦ ደጋማ አካባቢዎች የቡና ጥራትና

ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻልን ማዕከል ያደረገ ልማት ቢካሄድ የሁለቱም አካባቢዎች ህዝቦች በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፣ የአገሪቱም ልማት ይፋጠናል።

አንዳንድ አካባቢዎች ለዋና ዋና ከተሞች፣ ለዋና ዋና መንገዶችና ለአውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች ቅርብ ናቸው። በቅርብ ሰፊ ገበያ አላቸው። ምርታቸውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለተጠቃሚው ማድረስ ስለሚችሉ ቶሎ ሊበላሽ የሚችል የግብርና ምርት በሰፊው እያመረቱ ሊሸጡ ይችላሉ። ሌሎቹ አካባቢዎች ከዋና ዋና መንገዶች ከተሞችና የአውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች በጣም የራቁ ናቸው። ምርታቸውን ወደ ገበያ ለማጓጓዝ ረጅም ጊዜ ይጠይቃቸዋል። ቶሎ ሊበላሹ የሚችሉ ምርቶችን አምርተን እንሽጥ ቢሉ ከፍተኛ ብልሽት ይገጥማቸዋል። ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ አካባቢዎች በሁሉም ነገር አንድ አይነት ቢሆኑም ካላቸው የተለያየ ጆኦግራፊ አኳያ አንድ አይነት ምርት ቢያመርቱ እኩል ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም።

ለዋና ዋና ከተሞችና መንገዶች ቅርብ የሆኑት ቶሎ ሊበላሹ የሚችሉ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ምርቶችን ለምሳሌ አትክልቶችን፣ አበባዎችን ወዘተ. ቢያመርቱ፣ በቅርብ ያለውን ገበያ የሚመገብ የወተት ሃብት ቢያስፋፉ ወዘተ. በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፣ የአገሪቱ እድገትም ይቀላጠፋል። ከዋና ዋና መንገዶችና ከዋና ዋና ከተሞች የራቁት ደግሞ በቀላሉ የማይበላሹ ምርቶችን በማምረት ላይ ቢያተኩሩ በይበልጥ ይጠቀማሉ። ለሁለቱም አካባቢዎች አንድ አይነት የግብርና ልማት የቴክኖሎጂ ፖኬጅ ከማቅረብ ይልቅ ከሁኔታው ጋር የሚሄድ የተለያዩ ፖኬጆችን ማቅረብና ከባቢያዊ የስራ ክፍፍልን (ስፔሻላይዜሽን) ማጠናከር የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል።





ስፔሻላይዜሽን በተለይም በመጀመሪያዎቹ አመታት በዋነኛነት ከባቢያዊ ባህሪ የሚኖረው ቢሆንም በአንድ አካባቢ በሚኖሩ አርሶ አደሮችም ውስጥ የስራ ክፍፍል እየዳበረ መሄዱ የማይቀርና ጠቃሚም ይሆናል። ቀደም ሲል ያነሳናቸውን ምሳሌዎች እንደገና በማየት ይህንኑ በይልበጥ መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ በአርሲና ባሌ ሜዳዎች የሰብል ምርትን ማዕከል ያደረገ ልማት የሚካሄድ ከሆነ አንዳንድ አርሶአደሮች የላቀ ችሎታ ያላቸው በመሆናቸው ምርጥ የሰብል ዘር በማባዛት ስራ ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ። ይህን ቢያደርጉ እነሱም የበለጠ ገቢ ያገኛሉ፣ የአካባቢውም አርሶ አደር የላቀ ችሎታ ባላቸው አርሶ አደሮች የተመረተ ምርጥ ዘር አግኝተው ምርታቸውን ማሳደግ ይችላሉ። ይህ በአንድ አካባቢ ባሉ አርሶ አደሮች መካከልም የስራ ክፍፍል ሊኖር እንደሚችል ያሳያል። ይህ በተራዘመ ሂደት እየተስፋፉ ሊሄድና የስራ ክፍፍል (ስፔሻላይዜሽን) አድማስ በግብርና ዘርፍም በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ለቀጣይ የግብርና እድገት መሻሻል መሰረት ሊሆን ይችላል።

ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ስልት በመከተል፣ የአካባቢውን ሁኔታ በላቀ ደረጃ መጠቀም የግብርና ልማትና የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማሻሻል ይቻል ዘንድ የስራ ክፍፍልን የማጎልበት ስራ በግዳጅና በመመሪያ መፈፀም ያለበት ወይም የሚችል ነገር አይደለም። አርሶ አደሩ ይጠቅመኛል ብሎ አምኖ የሚፈፅመውና በሂደት የሚተገበር ነው ሊሆን የሚችለው። መንግስት የተለያዩ አካባቢዎችን ሁኔታ አጥንቶ በነዚህ አካባቢዎች የላቀ ጥቅም ሊያስገኙ የሚችሉ ፖኬጆችን አዘጋጅቶ አርሶ አደሩ ከነዚህ ውስጥ ይጠቅሙኛል የሚላቸውን መርጦ ተግባራዊ እንዲያደርግ በመርዳት መፈፀም ያለበት

www.abyssinialaw.com

ነው። ለኤክስቴንሽን ሰራተኞችም ሆነ ለተማረው አርሶ አደር በየአካባቢው የሚሰጠው የግብርና ሙያ ስልጠና በአካባቢው የላቀ ጥቅም ሊያስገኙ በሚችሉት በነዚህ ስራዎች ላይ ያተኮረ እንዲሆን በማድረግ መሰራትና መጠናከር ያለበት ስራ ነው። የአካባቢ የስራ ክፍፍልን (ስፔሻላይዜሽን) በማጠናከር ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ፣ እያንዳንዱ አካባቢ ሊያስገኝ የሚችለውን የላቀ ልማት ሊያስገኝ የሚችልበትን ሁኔታ የመፍጠር አቅጣጫ የግብርና ልማታችንን ለማፋጠን ከምንከተላቸው ቁልፍ ፖሊሲዎች አንዱ መሆን ይኖርበታል።

በግብርና ስራ ስር የሚካተቱ በርካታ ስራዎች ይኖራሉ። የእንስሳት ሃብት ልማት ስራ አንድ ራሱን የቻለ በውስጡ የተለያዩ ምርቶችና ስራዎችን ያቀፈ ስራ ነው። የአዝርእት ልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የቅመማ ቅመም ማምረት ስራዎች እንደዚሁ የተለያዩ ምርቶችንና ስራዎችን ያካተቱ ዘርፎች ናቸው። የአፈርና የውሃ ጥበቃና አጠቃቀም፣ የአግሮ-ፎረስተሪ ስራዎችም እንደዚሁ። በአጭሩ የግብርና ዘርፍ በውስጡ የተለያዩ የስራ ዘርፎች በነዚህ ዘርፎችም ውስጥ በጣም በርካታና የተለያዩ ምርቶች ያሉበት በጣም ሰፊ የስራ መስክ ነው። የግብርና ልማት ስራችን የግብርና ስራን ሰፊ አድማስ የዳሰሰ ነው። ከሁሉም ስራዎች በላቀ ደረጃ ለመጠቀም የሚያስችለን መሆን አለበት። ሰፊ አድማስ ያለውን የግብርና ልማት ስራ ለመስራት በአሁኑ ወቅት ያለን ዋነኛ አማራጭ አርሶአደሩ በርካታ የግብርና ምርቶችን አጣምሮ የሚያመርትበት ስርአት (የዳይቨርሲፊኬሽን ስርአት) ማስፋፋት ነው።

አርሶ አደሩ ባለችው ውሱን ማሳ የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ደራርቦና አጣምሮ እንዲያመርት ማድረግ በአሁኑ



ወቅት የአርሶ አደሩን የገቢ ዋስትና በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ትርጉም ያለው ነው። አንዱ የግብርና ምርት የተፈለገውን ምርት ሳያስገኝ ቢቀር በሌላው ምርት እየተደጎመ፣ የአንድ ምርት ዋጋ ቢያሽቆለቁል በሌላው ምርት ዋጋ እየተካሰ ገቢው የተረጋጋ እንዲሆን ለማድረግ ያስችላል። ባለን በጣም ዝቅተኛ የሆነ የግብርና ልማት ደረጃ በዚህ አኳኋን የአርሶ አደሩን የገቢ ዋስትና ማረጋገጥ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

በርካታ የግብርና ምርቶችን አጣምሮ የማምረት የስራ ሰው ጉልበትንና መሬትን በላቀ ደረጃ ለመጠቀምም የሚረዳ ነው። የአንደኛው ምርት ስራ ሲያልቅ አርሶ አደሩ ወደሌላ የግብርና ምርት ስራ እየተሸጋገረ አንዳንዶቹንም በጣምራ እየሰራ አመቱን ሙሉ የግብርና ምርት በማምረት ቀጣይ ስራ ላይ ለማሳለፍና መሬቱን ያለማቋረጥ ጥቅም ላይ ለማዋል ያስችለዋል። ይህ ስራ በተለይም ከውሃ አጠቃቀም መሻሻል ጋር ተደርቦ ከተሰራ ጉልበትንና መሬትን አመቱን በሙሉና በላቀ ደረጃ ለምርት ተግባር መጠቀም ያስችላል። ስለሆነም የሰው ጉልበትን በሰፊው በመጠቀም፣ መሬታችንን በላቀ ደረጃ በመጠቀም የግብርና ምርታችንን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግና የአርሶ አደሩንም ገቢ በቀጣይነት ለማሻሻል ይረዳል።

ይህን አካሄድ ተግባራዊ ለማድረግ በጣምራና በተደራራቢነት ሊሰሩ የሚችሉትንና የሚገባቸውን ስራዎች በመለየት እነዚህን የሚመለከቱ የተሟሉና የተለያዩ -ኬጆች አዘጋጅተን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ መቻል አለብን። ከዚህ በፊት ሲያደርግ እንደነበረው በአንድ አይነት ምርት ወይም በአንድ የግብርና ዘርፍ ብቻ የታጠረ ሳይሆን በአካባቢው የላቀ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ ምርቶችንና የግብርና ዘርፎችን በሙሉ

www.abyssinialaw.com

የሚዳስስና የሚያጣምር -ኬጅ ማዘጋጀት አለብን፡፡ አርሶ አደሩ እንደዚህ አይነቱ የተሟላ -ኬጅ ቀርቦለት ይሻሉኛል የሚላቸውን ምርቶችና የስራ ዘርፎች እንዲመርጥ ማገዝና ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ በየቀበሌው ቢያንስ በተለያዩ የግብርና ዘርፎች የሰለጠኑ ሶስት ሰዎችን መመደብ ለዚህ ተግባር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በእያንዳንዱ ዘርፍ በርካታ የግብርና ስራዎችን ለመስራት የሚያስችላቸውና በተለይም በሚመደቡባቸው አካባቢዎች ቢሰሩ የላቀ ጥቅም በሚያስገኙ ስራዎች ላይ የጠለቀ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግም ተገቢ ይሆናል፡፡ ለተማሩ አርሶ አደሮች የሚሰጠው የሞያ ስልጠናም በጣምራ ሊሰሩ የሚችሉ የግብርና ስራዎችን እንዲሰሩ ለማድረግ የሚያስችል ይሆናል፡፡

የግብርና ቴክኖሎጂያችን እየተሻሻለና እድገታችን እየተፋጠነ ሲሄድ እያንዳንዱ አርሶ አደር በተሻለ ደረጃ የሚሰራውንና የላቀ ገቢ የሚያስገኝለትን ምርት እየመረጠ በዋነኛነት በዚህ ላይ እያተኮረ መሄዱ በመሆኑም በአንድ አካባቢም በራሱ በግብርና ስራ ውስጥ የስራ ክፍፍል እየተፈጠረ መሄዱ የማይቀር ነው፡፡ ይህንኑ ሂደት በርካታ ምርቶች አጣምሮ በማምረት ስራ መጀመር ከላይ የተጠቀሰውና ከአጭርና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ የሚያስገኘው ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ በሂደት በአርሶ አደሮች መካከል ለሚኖረው የስራ ክፍፍልም የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ለማጠቃለል ያህል የግብርና ልማትን ለማፋጠን የምናቀርባቸው ፖኬጆችና የምናካሂዳቸው ስልጠናዎች የስራ ክፍፍልንና፣ በርካታ ምርቶችን ጎን ለጎን ማምረትን አጣምረው ያየዙ መሆን አለባቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት የስራ ክፍፍሉ በአብዛኛው



የአግሮ-ኢኮሎጂና ሌሎች ልዩነቶችን መሰረት አድርጎ እያንዳንዱ አካባቢ የላቀ ምርትና እድገት በሚያስገኝለት ስራ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ የሚፈጠር ከባቢያዊ የስራ ክፍፍል ነው፡፡ በርካታ ምርቶች አጣምሮ ማምረትን በተመለከተ ከላይ በተጠቀሰው ከባቢያዊ የስራ ክፍፍል ማዕቀፍ ስር በርካታ ምርቶችን አጣምሮ በማምረት የሚካሄድ ነው፡፡ በከባቢያዊ ስፔሻላይዘሽን ላይ የተመሰረተ የግብርና ምርት ዳይቬርሲፊኬሽን አቅጣጫን ነው የምንከተለው፡፡ ለየአካባቢው የሚሆኑ የተለያዩ ፖኬጆችን፣ በዚሁ ማዕቀፍ ስር በአንድ አካባቢ በጣምራ ሊሰሩ የሚችሉትን ያካተቱ ሰፊ አድማስ ያላቸው -ኬጆችን በማዘጋጀትና በማሻሻል፣ የኤክስቴንሽንና የግብርና ሙያ ስልጠና ፕሮግራማችን ይህንኑ መሰረት ያደረገ እንዲሆን በማድረግ የሚፈፀም ነው፡፡ እያንዳንዱ አካባቢ ማምጣት የሚችለውን የላቀ ልማት እንዲያመጣ በማድረግና የሰው ሃይላችንንና መሬታችንን አመቱን ሙሉ በማያቋርጥ የምርት ተግባር በማሰማራት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማምጣት የሚያስችለን መሰረታዊ አቅጣጫም ነው፡፡

## 4.2. በድርቅ አካባቢዎች የሚሰራ ስራ፣

ቀደም ሲል ያስቀመጥናቸው የስፔሻላይዜሽንና ዳይቨርሲፊኬሽን መርሆዎች በአገራችን በአጠቃላይ የሚሰሩ መርሆዎች ናቸው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ትኩረት በሚጠይቁ አካባቢዎች መሰራት የሚገባው ስራ ምን መሆን እንዳለበት ዘርዘር አድርጎ ማስቀመጥም ያስፈልጋል፡፡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ለረሃብ እንዲጋለጡ ምክንያት በሆነውና በየአመቱ ስፋቱ እየጨመረ በመሄድ ላይ ባለው የድርቅ አካባቢ ምን እንደሚሰራ መለየት ተፈላጊ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በርካታና ስፋታቸው እየጨመረ በመሄድ ላይ የሚገኙ አካባቢዎች ከፍተኛ የዝናብ እጥረትና የዝናብ መቆራረጥ የሚያጋጥማቸው በተለምዶ የድርቅ አካባቢዎች ተብለው የሚጠሩ ናቸው፡፡ እነዚህ አካባቢዎች ለረጅም ጊዜ የተፈጥሮ እንክብካቤ በጎደለው አኳኋን ጥቅም ላይ የዋለ መሬት ያላቸው በመሆኑ በአፈር መከላት የመሬቱ ለምነት ክፉኛ የተጎዳባቸው አካባቢዎችም ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ የእርሻ መሬት ጥበት ያላቸውም ናቸው፡፡ የድርቅ አካባቢ ተብለው የሚታወቁት ከላይ የተጠቀሱትን ባህሪያት ሁሉንም ወይም የተወሰኑትን የያዙ ናቸው፡፡ የምግብ ዋስትና ችግር በሁሉም የአገራችን አካባቢዎች ያለ ቢሆንም ዋናው የምግብ ዋስትና ችግር የድርቅ አካባቢዎች እያልን በምንጠራቸው በነዚህ አካባቢዎች የሚከሰት ነው፡፡ ይህ አካባቢ ስፋቱ እጅግ አሳሳቢ በሆነ መንገድ እየጨመረ በመሄድ ላይ የሚገኝም ነው፡፡

በነዚህ አካባቢዎች የምናካሂደው የግብርና ልማት ስራ በዋነኛነት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥን ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ በርግጥ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ስራ በሌላ አካባቢም መካሄድ ይኖርበታል፡፡ ዋናው ችግር ያለው በነዚህ አካባቢዎች በመሆኑ ዋነኛው የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ስራም በነዚህ አካባቢዎች የሚካሄድ መሆን አለበት፡፡ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚቻለው በግብርና ስራ ብቻ አይደለም፡፡ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ማለት ዞሮ ዞሮ ዜጎች ከረሃብ ተላቀው በቂ ምግብ አግኝተው የሚኖሩበት ገቢ እንዲያገኙ ማድረግ ማለት እንጂ የግድ እያንዳንዱ ሰው የሚመገበውን ምርት ራሱ ማምረት አለበት ማለት አይደለም፡፡ በመሆኑም ከግብርና ውጪ በቂ ገቢ የሚያስገኝ ስራ በመስራትም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህንን አማራጭ በላቀ ደረጃ መጠቀምም የምግብ



ዋስትና ፕሮግራማችን አንድ አካል መሆን አለበት፡፡ ይሁንና እንደዚህ አይነቱ ከግብርና ውጪ የሆነ የስራ እድል በምግብ ዋስትና ለሚሰቃዩት ወገኖች ሁሉ መፍትሄ ሊሆን አይችልም፡፡ በአሁኑ ሰአት ያለን ዋነኛ የስራ እድል ግብርና ነው፡፡ በመሆኑም ዋነኛው የምግብ ዋስትና ስራችን በግብርና ዙሪያ የሚሽከረከር መሆን አለበት፡፡

የአገራችን የግብርና ምርት በዝናብ ውሀ ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ ያለአግባብ ጥቅም ላይ የዋለው መሬታችን አፈሩ በመከላቱና የግብርና ቴክኖሎጂያችን ዝቅተኛ በመሆኑ ከአመት አመት ከፍተኛ የምርት መዋዠቅ የሚታይበትና ለተለያዩ አደጋዎች በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጠ ነው፡፡ የግብርና ምርታችን ለአደጋ ተጋላጭነት በገጠር ልማት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳድር ጉዳይ ነው፡፡

ከረጅምና ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ ትኩረታችን ለአደጋ ተጋላጭነትን በመቀነስ ላይ መሆን ይኖርበታል፡፡ የውሀ አጠቃቀም ስርአታችንን በቀጣይነት ለማሻሻል፣ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤን በማጠናከርና የግብርና ቴክኖሎጅያችንን በአፋጣኝና በቀጣይነት ለማሻሻል ተጋላጭነቱን ለመቀነስ በሂደትም በወሳኝነቱ ለማስወገድ ይቻላል፡፡ እስከዚያው ድረስ በዚህ አደጋ ምክንያት በህዝባችን ኑሮ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ስርአት ሊኖረን ይገባል፡፡ ይህ ስርአት የገጠር ልማት ስራችንን የሚደግፍ እንዲሆን ለማድረግም መጣር ይኖርብናል፡፡ መንግስት ቀደም ሲል ያወጣው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፖሊሲ ከዚህ አኳያ ሲታይ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚሁ መሰረት ለአደጋ የሚጋለጡ ዜጎችና አካባቢዎች ከግብርና ስራቸው ሳይፈናቀሉ ርዳታ የሚያገኙበትን ስርአት ማጠናከርና ማሻሻል ይኖርብናል፡፡ የሚሰጠው ኖርዳታ ሰርተው ለመኖር የሚችሉ ዜጎች በነፃ ከሚያገኙት ይልቅ የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን ወይም የራሳቸውን ምርታማነት ለማሻሻል በሚያስችሉ ስራዎች እንዲሳተፉ በማድረግ በክፍያ መልክ እንዲሰጣቸው፣ መስራት የማይችሉት ብቻ በነፃ እንዲሰጣቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ አካሄድ ለአደጋ መቋቋሚያ የሚሰጠውን ርዳታ ለአደጋ ተጋላጭነትን ለዘለቄታው ለማስወገድ በሚያስችል አኳኋን ለማከፋፈልና የገጠር ልማታችንን ለማፋጠን በሚያስችል መልክ ለመጠቀም የሚያስችለን ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ እስከዛሬ የተሰራውን ስራ በየጊዜው እየፈተሹ ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል የሚሰጠው ርዳታ ከውጭ በሚገኝ የምግብ ርዳታ መልክ መሆኑ የህዝብን ህይወት ለማዳን የሚጫወተው ከፍተኛ ሚና ቢኖርም የራሱ ጉዳት ያለው መሆኑ በተግባር እየታየ ነው፡፡ ለአደጋ በተጋለጡት አካባቢዎች የምግብ እጥረት በሚያጋጥምበት ወቅት በሌሎች አካባቢዎች ትርፍ ምርት ይኖራል፡፡ ይህንን ገዝተን ከመጠቀማችን በፊት ከውጭ የእህል ርዳታ ሲመጣ ትርፍ ምርት ያመረቱት አርሶ አደሮች በገበያ እጦት በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር ለአደጋ የተጋለጠው ህዝብ እህል በግብይት መልክ ከሚገዛ ይልቅ በአይነቱ ሲሰጠው የገጠር ግብይት ስርአቱን ሊያቀጭጨው ይችላል፡፡ በመሆኑም ሁኔታው በፈቀደው መጠን የሚሰጠው ርዳታ ለስራ በሚከፈል ገንዘብ (ካሽ ፎርወርክ) መልክ እንዲሆን፣ የምግብ አቅርቦቱም በተቻለ መጠን ከአገር ውስጥ ምንጮች የሚገኝ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አደጋ



መከላከልንና ልማት ማፋጠንን አቀናጅቶ ለመስራት የሚቻለው እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ስልቶችን በመከተል በመሆኑ ለአደጋ ተጋላጭነት የተጠቀሱትን ስልቶች በተግባር ላይ በማዋል ለመከላከል እንሰራለን፡፡

## (ሀ) ሰፈራን እንደመፍትሄው አካል መውሰድ፣

በአገራችን ታሪክ ውስጥ ህዝቡ የመሬት ጥበት ካለበት ወደሌለበት፣ ከደጋ ወደ ቆላ እየፈለሰ ኑሮውን ሲያሻሻል ቆይቷል፡፡ ይህ በተናጠል የሚደረግ ሰፈራ በአንድ አካባቢዎች የሚፈፀም ቢሆንም ክልል እያቆራረጡ የሚከናወኑ ሰፈራዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህ በግል የሚደረጉ የሰፈራ እንቅስቃሴዎች ለረጅም ጊዜ የቆዩና አሁንም በመካሄድ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት እየታየ ያለው በተናጠል የሚካሄድ ሰፈራና ይህ እንቅስቃሴ የወለደው ችግር በተናጠል መፍትሄ ሊገኝለት የሚችል አይደለም፡፡ በተናጠል የሚካሄደው ሰፈራ በከፍተኛ ቁጥር በሚፈፀምበት ወቅት ለከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት መባከንና በህዝቦች መካከል ለሚፈጠር መቃቃር ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨባጭም ይኸው እየታየ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የሰፈራ ስራ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንዳያይል ከተፈለገ በእቅድና በመንግስት እገዛ የሚፈፀም መሆን ይኖርበታል፡፡ የተናጠልና የግል የሰፈራ ሙከራ ባለንበት ወቅት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀውስ የሚፈጥር ጉዳይ ሆኗል፡፡ ጠቃሚነቱ እያበቃለት ያለ አማራጭ ነው ሊባል ይችላል፡፡

ይሁንና በእቅድና በመንግስት ዋነኛ ተዋናይነት የሚፈፀም የሰፈራ ስራም ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን የሚችልበት ዕድል እንዳለ በደርግ ዘመን የተደረጉ ሰፈራዎች ተጨባጭ

www.abyssinialaw.com

ማረጋገጫዎች ናቸው። የደርግ የሰፈራ ፕሮግራም ዋነኛው ጉድለት የሰፈራው ፕሮግራም በሰፋሪው ፈቃድና ፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ የነበረ መሆኑ ነው። በግዴታ የተፈፀመ ነገር ቀጣይነት ያለውና የተሳካ ሊሆን ስለማይችል ይኸው የሰፈራ ፕሮግራምም በሰፋሪዎቹ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ በመሰረቱ ወድቋል። የደርግ የሰፈራ ፕሮግራም ችግር በተሳሳተ የፖለቲካ አመለካከት የተመራ መሆኑ ነው። ጻር አገር በሚባሉ አካባቢዎች ከሌሎች ክልሎች ሰዎችን በማስፈር የአካባቢውን ደህንነትና ፀጥታ የማረጋገጥ አላማም የነበረው ነው። ይህ በህዝቦች መካከል አላስፈላጊ መጠራጠርንና መቃቃርን ሊፈጥር የሚችልና በተጨባጭም የፈጠረ እንዲሆን አድርጎታል። በመሆኑም ፕሮግራሙ የተሳካ ሊሆን አልቻለም። ሌላው የደርግ የሰፈራ ፕሮግራም ጉድለት በችኮላ የታቀደና የተፈፀመ፣ ከሰፈራው አካባቢ አጠቃላይ ልማት ጋር ያልተሳሰረ መሆኑ ነው።

በመንግስት ድጋፍና በእቅድ የሚፈፀም የሰፈራ ፕሮግራም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጫ አንድ መፍትሄ እንደሆነ ተቀብለን መስራት አለብን ስንል ለደርግ የሰፈራ ፕሮግራም መውደቅ ምክንያት የሆኑትንና በወቅቱ የተወገዙና አሁንም መወገዝ ያለባቸውን የተሳሳቱ አቅጣጫዎች በማስወገድ በተስተካከሉ አቅጣጫዎች ላይ ተመስርተን የምናካሄደው መሆን አለበት ማለታችን ነው።

የድርቅ አካባቢ ብለን የምንጠራቸው አካባቢዎች በአሁኑ ወቅት ባለው የግብርና ቴክኖሎጂና የአካባቢዎቹ የልማት ደረጃ በላያቸው ላይ የሰፈረውን ህዝብ መቀለብና ማኖር የሚችሉ አይደሉም። ይህም በመሆኑ ነው በየአመቱ በሚልዮኖች ለሚቆጠሩ ዜጎች የምግብ ርዳታ ማቅረብ አማራጭ የሌላው



ጉዳይ ሆኖ የሚገኘው። የአካባቢውን የልማት ደረጃ በመሰረቱ በመቀየርና የግብርና ቴክኖሎጅያችንን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ እነዚህ አካባቢዎች በላያቸው ላይ የሰፈረውን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ እንዲሸከሙ ማድረግ ይቻላል። ይሁንና ይህ አማራጭ ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ አይቀርም። ይህ እስኪፈፀም ድረስ ህዝቡ በሚሊዮኖች በረሃብ እየተገረፈ ይጠብቅ ማለት አይቻልም፣ አይገባምም። ስለሆነም በነዚህ አካባቢዎች ከሚኖረው ህዝብ ውስጥ የተወሰነውን ክፍል በቂ መሬትና ዝናብ ወደአለበት አካባቢ ወስዶ ማስፈር የምግብ ዋስትናን በተቻለ ፍጥነት ለማረጋገጥ የሚያስችል አንድ መሰረታዊ አቅጣጫ ነው።

በእርግጥ በነዚህ አካባቢዎች ያለው ህዝብ በቂ ዝናብና መሬት ባለበት አካባቢ ሄዶ መስፈር የማይፈልግ ከሆነ ሰፈራን እንደ አንድ የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ስልት መጠቀም አይቻልም። ይሁንና ህዝቡ በእቅድ የሚመራና የመንግስት ድጋፍ ያለው የሰፈራ ፕሮግራም በሌለበትም ወቅት ቢሆን በራስ ተነሳሽነት የተሻለ ዝናብ ያለበት ለምና ሰፊ መሬት ፍለጋ በሺዎች እየፈለሰ ነው። በዚህም ምክንያት የተለያዩ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች የተፈጠሩበት ሁኔታ አለ። የተሟላ እቅድና የመንግስት ድጋፍ ያለው የሰፈራ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት በጣም ብዙ ህዝብ በፍላጎቱ ለመስፈር እንደሚወስን ብዙም አያጠራጥርም። ሰፈራን እንደ አንድ የምግብ ዋስትና መሰረታዊ መፍትሄ መውሰድ እንችላለን የምንለው የህዝቡ ፍላጎት በተጨባጭ ስላለና በመንግስት የታቀደና ድጋፍ የሚያገኝ ፕሮግራም ከቀረበለት ይኸው ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨምር በእርግጠኝነት መናገር ስለሚቻል ነው። ከሰፋሪው የተሟላና ነፃ ፍላጎት ውጪ አንድንም ሰው ማስፈር ምንም

አይነት ጠቃሚ ውጤት የማያስገኝ፣ በወንጀልነት የሚፈረጅ ስራ በመሆኑ ነው የህዝቡ ፍላጎት እንዳለ ማረጋገጥና ፕሮግራሙም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በህዝብ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ መሰራት ያለበት::

የሰፈራ ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ ለመስፈር የሚፈልግ ሰው ብቻ ሳይሆን ሊሰፍርበት የሚችል ቦታም መኖር አለበት:: የቦታው አመራረጥ በደርግ የሰፈራ ፕሮግራም የተፈፀመውን ፖለቲካዊ ወንጀል በማይደግም መልኩ ለመፈፀም የሚያስችልም መሆን አለበት:: ይህን ለማድረግ ሰፈራው በመሰረቱና በቅድሚያ ህዝቦችን ከክልል ክልል በማሸጋገር ሳይሆን በየክልሉ ውስጥ የሚፈፀም መሆን አለበት:: ደግነቱ ሁሉም ክልሎች ለሰፈራ ስራ ሊያገለግል የሚችል ሰፊ ያልታረሰ መሬት አላቸው:: ስለሆነም ፕሮግራሙን በዋነኛነት በየክልሉ ውስጥ እንዲፈፀም የማድረግ አቅጣጫ መከተል ይገባል፣ ይቻላልም::

ይሁንና ህዝብ ሊሰፍርባቸው ይችላል ተብለው የሚገመቱት አብዛኞቹ መሬቶች ያሉት በቆላማ አካባቢዎች ነው:: ይህ ነው የሚባል የመሰረተ-ልማት አገልግሎት የሌላቸው፣ ከፍተኛ የጤና ችግር ያለባቸው አካባቢዎች ናቸው:: እነዚህን ችግሮች የሚፈታ የመንገድ፣ የጤና አገልግሎቶች የመጠጥ ውሃ፣ የትምህርት መሰረተ-ልማት ዝግጅት ሳይጠናቀቅ የሰፈራ ስራን ማስጀመርም የሚታሰብ መሆን የለበትም:: ይሁንና በነዚህ አካባቢዎች እንደዚህ አይነቱ የመሰረተ-ልማት ስራ የሚሰራ ከሆነ የሰፈራ ፕሮግራሙን በተናጠል በማየት ብቻ የሚፈፀም መሆን የለበትም:: የአካባቢውን አጠቃላይ ልማት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በነዚህ አካባቢዎች የሰፈራ ስራ ቢሰራና የመሰረተ-



ልማት ስራ ቢካሄድ በአካባቢው የግል ባለሃብቶች እንዲሰማሩ ለማድረግ የሚያስችል የመሰረተ-ልማት አቅርቦትና የሰራተኛ ጉልበት መገኘት ጉዳይም እንደሚሟላ ታሳቢ ያደረገ፣ ሰፈራንና የግል ኢንቨስትመንትን ባካተተ መልኩ አካባቢውን በአፋጣኝና በከፍተኛ ደረጃ ለማልማት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል::

መንግስት የሰፈራ ፕሮግራምን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የሚጠበቅበት ዋናው ስራም የአካባቢ ሁለገብ የልማት ዕቅድን መሰረት በማድረግ ሰፈራ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የመሰረተ-ልማት ስራዎችን አስቀድሞ ማካሄድ ነው:: ከዚህ ውጪ ያለው ስራ በአብዛኛው በሰፋሪዎቹ መሰራት ያለበት ነው:: ሰፋሪዎቹ የየራሳቸውን ቤት መስራት መቻል አለባቸው:: መንግስት በመጀመሪያው አመት የማቋቋሚያ ርዳታ ሊሰጣቸው የሚገባ ቢሆንም ሰፋሪዎቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሳቸውን መቻል ይኖርባቸዋል::

ይህንኑ ስራ ለማገዝና ሰፈራውን ደረጃ በደረጃ በህዝቡ ፈቃድ ለማስፈፀም የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀምም ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ያህል ሰፋሪውን ቤተሰብ በሙሉ ከመጀመሪያው አመት ጀምሮ ከማስፈር ይልቅ በመጀመሪያው አመት አባወራዎችን ብቻ ወስዶ በምርት ተግባር ላይ እንዲሰማሩ፣ ሰፈራቸውን እንዲያመቻቹና ይህን ካደረጉ በኋላ ቤተሰቦቻቸውን እንዲወስዱ ማድረግ ይቻላል:: በተጨማሪም ሰፋሪዎቹ ራሳቸውን የሚችሉበት ደረጃ ላይ እስኪደርሱ ድረስ ሞፈር ዘመት ተብሎ ከሚታወቀው ልማዳዊ አሰራር በመማር ለተወሰነ ጊዜ በሰፈራ ቦታውም ቀድሞ በነበሩበት ቀየም መሬት እንዲኖራቸው ማድረግ ይቻላል:: በተመሳሳይ መልኩ በመጀመሪያ የተወሰኑ ሰዎችን አስፍሮ፣ እነሱ በሚገባ ከተቋቋሙ

www.abyssinialaw.com

በኋላ ተጨማሪ ሰፋሪዎችን በማምጣት ሰፈራውን ማስፋፋት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ በችኮላ ሳይሆን ቀስ በቀስና በተጨባጭ ከሚያጋጥሙ ስህተቶች እየተማሩ ለማስተካከል ዕድልና ጊዜ በሚሰጥ አኳኋን፣ ሰፋሪው በጉልበቱ የላቀ አስተዋፅኦ ማድረግ በሚችልበትና በአፋጣኝ ራሱን በሚችልበት አኳኋን እንዲፈፀም ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሰፈራው በተፈፀመበት አካባቢ ስራው በጥንቃቄ ታቅዶ ካልተፈፀመ በስተቀር ከፍተኛ የአካባቢ ውድመት ሊያስከትል ይችላል፡፡ የተፈጥሮ እንክብካቤን በጥብቅ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን በእቅድ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ ሰፈራው በዘፈቀደ የሚካሄድ እንዳይሆን ከአካባቢው የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ጋር በጥብቅ በተጣጣመ አኳኋን የሚፈፀም መሆን አለበት፡፡ እያንዳንዱ የመስፈሪያ አካባቢ ለላቀ ጥቅም በሚያገለግል፣ ነባር የተፈጥሮ ሃብቶችን በማያባክንና ለተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያውል መልክ የሚፈፀም እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ የደንና የዱር አራዊት ሃብታችንን ለመጠበቅና ለማልማት የመሬትና የውሃ አጠቃቀም ችሎታችንን ለማዳበር በሚያስችል መልኩ የሚፈፀምም መሆን ይገባዋል፡፡ በነዚህም አካባቢዎች የተሟላ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት መቻል አለበት፡፡ ይህም በውሱን መሬት የላቀ ምርት ማግኘትን እንጂ ሰፊ አካባቢ በመያዝ አካባቢውን በሚያወድም አኳኋን መጠቀምን የሚያስወግድ መሆን አለበት፡፡

ሰፈራው ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን ከተፈፀመ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ሃይል በቂ ዝናብና መሬት አግኝቶ ምርቱ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምርና የምግብ ዋስትናውን እንዲያረጋግጥ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከጥቂት አመታት በኋላ



የሰፈራው ተጠቃሚ የሆኑ ወገኖች ራሳቸውን ከመቻል አልፈው በድሮው መንደራቸው ያሉ ዘመዶቻቸውን መርዳትም ይችላሉ፡፡ የምግብ ዋስትናንና የአገሪቱን ልማት በማፋጠን ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላሉ፡፡ ሰፈራው ከአካባቢ የተቀናጀ ልማት ጋር ተያይዞ ከተፈፀመ፣ ሰፈራው ዘመናዊ እርሻዎች በተስፋፉበትና በሚስፋፉበት አካባቢ እንዲሆን ከተደረገ ሰፈራው በሚከናወንባቸው አካባቢዎች የመሰረተ-ልማትና የሰራተኛ ጉልበት አቅርቦት ተሟልቶ፣ የግል ባላሃብቶች እነዚህን አካባቢዎች በማልማት ስራ ላይ በሰፊው እንዲሳተፉ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታም መፍጠር ይቻላል፡፡ እስካሁን በአግባቡ ሳይለሙ የቀሩ አካባቢዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ልማት የሚካሄድባቸው የልማት ማዕከላት (ግሮውዝ ሴንተርስ) እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ ለአገሪቱ አጠቃላይ እድገት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡

የሰፈራው ፕሮግራም በጎ ውጤት ሰፈራው በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ብቻ የታጠረም አይሆንም፡፡ የድርቅ አካባቢ በሚባሉት አካባቢዎችም ላይ በጎ ተፅዕኖ የሚያሳርፍ ይሆናል፡፡ ሰፈራው በነዚህ አካባቢዎች የሚታየውን የመሬት ጥበት በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ የመሬት አጠቃቀምን ለማሻሻልና የቀረውን ህዝብ የምግብ ዋስትና ለማጎልበት በር የሚከፍት ይሆናል፡፡ በቂ ዝናብና መሬት ባለበት አካባቢ የሰፈሩት ሰዎች ከጥቂት አመታት በኋላ በድሮው ቀያቸው የሚኖሩ ወገኖቻቸውን ሊረዱ የሚችሉበት ሁኔታ ስለሚፈጠር የነዚህን አካባቢዎች የምግብ ዋስትና በማሻሻል ረገድ ተጨማሪ አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በመሆኑም የሰፈራ ፕሮግራም የምግብ ዋስትና ችግርን ለማስወገድና ይህንኑ በተቻለ ፍጥነት

www.abyssinialaw.com

ለመቅረፍ የሚያስችለን ቁልፍ የመፍትሄው አካል ነው፡፡ ስራው ከሰፈራ አካባቢዎች የተቀናጀ ልማት ጋር ተቀናጅቶ ከተፈፀመ ለአጠቃላይ እድገታችን ከፍተኛ ትርጉም የሚኖራቸው የእድገት ማዕከላትን ለመፍጠር የሚያስችለን አማራጭም ነው፡፡ በመሆኑም የሚገባውን ትኩረት አግኝቶ መፈፀም የሚገባው መሰረታዊ የልማት ስራ ነው፡፡

### (ለ) የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና የእንስሳት ሃብት ልማት፣

የድርቅ አካባቢ የሚባሉት በዋነኛት የዝናብ እጥረትና መቆራረጥ ያለባቸው አካባቢዎች ቢሆኑም ከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት መመናመን፣ የደኖች መጨፍጨፍና የአፈር መከላት፣ እንዲሁም የተጻፋት ቦታዎች አለአግባብ መታረስ የሚታይባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡ የሰፈራ ፕሮግራም በነዚህ አካባቢዎች ያለውን የመሬት ጥበት በመቀነስ የተፈጥሮ ሃብትን ለመንከባከብ የተጻፋት ቦታዎችን መታረስ ለማስወገድና የደኖች መጨፍጨፍን ለማስቀረት ሰፊ ዕድል ይሰጣል፡፡ በዚህ ዕድል በመጠቀም የተመናመነውን የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት መንከባከብና ማሻሻል ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ስራ ነው፡፡ አካባቢው በጠቅላላው የግብርና ስራ ሊሰራበት የማይችል ከጥቅም ውጪ የሆነ አካባቢ ከመሆኑ በፊት ይህንን ስራ በአፋጣኝ መስራት በአካባቢው ቀጣይነት ያለው ፈጣን የግብርና ልማት ለማምጣት መተኪያ የሌለው መሰረት ሆኖ ያገለግላል፡፡

የሚካሄደው የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ስራ ለህዝቡ ተጨባጭና ከፍተኛ ጠቀሜታ በሚያስገኝ አኳኋን መፈፀም ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ ተጻፋት ቦታዎችን ከእርሻ ስራ ነፃ



በማድረግ በነዚህ አካባቢዎች የግጦሽ ሳር፣ ለእንስሳት መኖ መሆን የሚችሉ ልዩ ልዩ ዛፎችን መትከል፣ በቦታዎቹ ላይ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች መስራት ይቻላል፡፡ ይህ ስራ በአንድ መልኩ የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት ለመጠበቅ የሚያስችል ሲሆን በሌላ በኩል ግን አርሶ አደሩ በነዚህ ቦታዎች የሚመረተውን ሳርና የመኖ ተክሎች በአግባቡ በመጠቀም በቦታው ላይ የተሳካ የእንስሳት ሃብት ልማት ስራ እንዲያካሂድ ማድረግ ይቻላል፡፡

የደን ልማትም በተመሳሳይ መልኩ ሊታይ የሚገባውና የሚችል ነው፡፡ ስራው በደፈናው ደን ማልማት በሚል የሚካሄድ መሆን የለበትም፡፡ በቦታው የሚተከሉ ዛፎች ለአካባቢው ህዝብ አንድ አይነት ተጨባጭ የኢኮኖሚ ጥቅም የሚሰጡ መሆን አለባቸው፡፡ የአግሮ-ፎሬስተሪ ስራ መሆን አለበት፡፡ አርሶ አደሩ ደኑን ሳያወድም የደን ምርቶችን በመሰብሰብ ሸጦ መጠቀም መቻል አለበት፡፡ እንጨት አምርቶ በመሸጥ፣ የዛፍ ተክሎች ምርት የሆኑ የተለያዩ ፍሬዎችና ምርቶችን ሸጦ በመጠቀም ገቢ ማግኘት መቻል አለበት፡፡

የተፈጥሮ ሃብትን የመንከባከብና በዚህ ሂደት ህዝቡ ቀጥተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያገኝ ማድረግ ከፍተኛ ትዕግስት፣ ጊዜና ጥረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህን አካባቢዎች ተንከባክቦ ተጨባጭ የኢኮኖሚ ጥቅም ማስገኘት የሚችሉበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ረዘም ያለ ጊዜና ከፍተኛ ስራ ይጠይቃል፡፡ አርሶ አደሩ ጥቅሙን ማግኘት እስከሚጀምር ድረስ ከአጭር ጊዜ አኳያ ተጨባጭ የኢኮኖሚ ጥቅም ሳያገኝ እንዲሰራ የሚጠየቅበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በመሆኑም ህዝቡን ማሳመንና በነዚህ አካባቢዎች ለሚሰራው ስራ የመንግስት እገዛ ማድረግ

ያስፈልጋል፡፡ የነዚህ አካባቢዎች የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ስራ ለአካባቢው ህዝብ ተጨባጭና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ እንዲሆን ለማድረግ ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የሚሄዱ ቴክኖሎጂዎች መምረጥና በፖኬጅ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ይህን በተመለከተ የቆየ የተሟላ ልምድ የሌለን መሆኑም ጉዳዮን ውስብስብና አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ይሁንና ከሌሎች አገሮች ልምድ በሰፊው መማርና መውሰድ ከቻልን የራሳችንንም ልምድ በአግባቡ መቀመር ከቻልን በመነሻነት ሊያገለግል የሚችል አጥጋቢ -ኬጅ ማዘጋጀትና በሂደት በይበልጥ እያሻሻሉ መሄድ ይቻላል፡፡

የዝናብ እጥረትና የአፈር መከላት ለሰብል ልማት ያልተመቹ እንዲሆኑ ባደረጋቸው በነዚህ አካባቢዎች በእንስሳት ሃብት ልማት ላይ ማተኮር ከፍተኛ ትርጉም ያለው ነገር ነው፡፡ የእንስሳት ሃብት ልማት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ምርቶችን ውሱን ዝናብና መለስተኛ ለምነት ባለው አካባቢ ሊካሄድ የሚችል ዘርፍ ነው፡፡ እንደ ዶሮ ርቢና የንብ ርባታ ያሉትም በጠባብ መሬት ሊከናወኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ አምራቾቹ ምርቱን በመመገብ ከሚያገኙት የላቅ ጥቅም በተጨማሪ እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦን በመሸጥ በምግብ ራሳቸውን በመቻል በአካባቢው ሊመጣ የሚችለውን የላቀ ልማት ማምጣት ይችላሉ፡፡ ይህ ስራ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተያይዞ ሲሰራ የእንስሳት መኖንም በአካባቢው ጥበቃ ፕሮግራም አማካኝነት በሰፊው ማምረት ስለሚቻል በይበልጥ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም በድርቅ አካባቢዎች የላቀ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የእንስሳት ሃብት ልማት ስራ ይሆናል፡፡

የእንስሳት ሃብት ልማትን በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል



የእንስሳት ሃብታችንን ዝርያ ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ ምርታማነታቸው ከፍ ያሉ ዝርያዎችን በየጊዜው በማባዛት ካልተንቀሳቀስን በስተቀር በዚህ አካባቢ የሚኖረውን ህዝብ የኑሮ ደረጃ ያለማቋረጥ ከፍ ማድረግ አንችልም፡፡ የእንስሳት ዝርያዎችን ማሻሻል አለብን ሲባል ምርጥ ዝርያዎች ሁሉ ከውጭ መምጣት አላባቸው ማለት አይደለም፡፡ በአካባቢያችን አገሮችና በአገራችን ውስጥ የሚገኙትን ምርጥ ዝርያዎች በመላ አገራችን በማስፋፋትና እነዚህን ዝርያዎች ደረጃ በደረጃ በማሻሻል የእንስሳት ሃብታችንን ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል እንችላለን፡፡ እነዚህ ዝርያዎች ያን ያህል ከፍተኛ እንክብካቤ የማይጠይቁና ከአገራችን ሁኔታ ጋር የተላመዱ በመሆናቸው መላው አርሶ አደር በተለይም በድርቅ አካባቢ ያለው አርሶ አደር በሰፊው ሊጠቀምባቸው ይችላል፡፡ በከተሞች ዙሪያና በዘመናዊ አርሶ አደሮች በሚካሄዱ የእንስሳት ሃብት ልማት ስራዎች ምርታማነታቸው በጣም ከፍተኛ የሆነና በጣም ከፍተኛ እንክብካቤ የሚጠይቁትን መጠቀም ይቻላል፣ ይገባልም፡፡ በመሆኑም እንደሁኔታው የአገራችንንና የአካባቢያችንን ምርጥ ዝርያዎች ከውጭ ዝርያዎችን ጎን ለጎን በመጠቀም የእንስሳት ሃብታችንን ምርታማነት ከፍ ማድረግ የምንከተለው የልማት አቅጣጫ ይሆናል፡፡

እንስሳት በቂ ምግብና መኖ ካላገኙ በስተቀር ሊበራከቱና ምርታማነታቸው ሊሻሻል አይችልም፡፡ በመሆኑም የእንስሳትን መኖና ምግብ ማምረትና በየጊዜው ማሻሻል በድርቁ አካባቢ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በአካባቢው የሚካሄደው የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና የአግሮ ፎሬስተሪ ስራ ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ ምርቶች (ለንቦች የሚሆኑ አበቦችም ጭምር) ለማምረት እንደሚያስችል ይገመታል፡፡ ይህ እንደአንድና ዋነኛ ምንጭ

www.abyssinialaw.com

ተወስዶ አርሶ አደሩ ይህን በሚገባ በማዘጋጀት የእንስሳት መኖ ፍላጎቱን ማርካት የሚችልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። የማሳ ቃርሚያ በመጠቀም ብቻ ሳይሆን ማሳውን ለእንስሳት መኖና ምግብ የሚሆን ምርት እንዲያመርትበት በማበረታታት ይህንኑ በመጠንና በአይነት ማሻሻል ይቻላል፣ ይገባልም። የእንስሳት መኖ ልማት የማካሄድ ስራ በተለይ በደጋማው የአገራችን ክፍል ደረጃ በደረጃ ልቅ ግጦሽን በሚያስወግድና አርሶ አደሩ ለከብት መኖነት የሚያገለግሉ የሳር አይነቶችን እያለማ አጭዶ ጥቅም ላይ የሚያውልበት አሰራር እንዲስፋፋ ጥረት ማካሄድ ይገባል። በተለይም የጓሮ እርሻና የውሃ ማቆርና በአግባቡ የመጠቀም ስራ ተሰርቶ የመስኖ ልማት በተካሄደበት አካባቢ ይኸው ስራ በሰፊው ሊካሄድ ይችላል። የእንስሳት መኖና ምግብ የሚያመርቱ ተቋሞችና ፋብሪካዎችም ይህን ችግር ከመፍታት አኳያ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። በመሆኑም የክልል መንግስታት ለነዚህ ተቋሞች ቅድሚያ ሰጥተው በተቻለ መጠን በግል ባለሀብቶች አማካይነት እንዲስፋፉ ለማድረግ፣ የግል ባለሃብቶች ሊሳተፉበት ባለመቻላቸው አማራጭ የሌለው ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በመንግስት እንዲቋቋሙ ጥረት መደረግ አለበት።

የእንስሳት ሃብታችን ልማት ሊጠናከር የሚችለው የእንስሳት ሃብት ልማት ስራችንና ቴክኖሎጅያችን እየተሻሻለ ሲሄድ ብቻ ነው። በመሆኑም በእንስሳት ሃብት ልማት ስራ ላይ ላልተማረው አርሶ አደርም፣ ተምሮ የግብርና ስልጠና ለወሰደው አርሶ አደርም የሚሆኑ ከደረጃቸው ጋር የሚመጥኑ -ኬጆች መዘጋጀትና በየጊዜው መሻሻል አለባቸው። በየቀበሌው ከሚመደቡት ሞያተኞች አንዱ በእንስሳት ሃብት ልማት የላቀ ስልጠና ያገኘ መሆኑ ለዚህ ስራ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይገመታል። ከዚህ በተጨማሪ የእንስሳትን ጤንነት



ለመጠበቅ በአርሶ አደሩ የሚደረገው እንክብቤ፣ በአካባቢ ደረጃ የሚሰራው የክትባትና የእንስሳት ጥበቃ ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ የእንስሳት ህክምና ሞያተኞችን በተለያየ ደረጃ በስፋት በማሰልጠን ማሰማራት ያስፈልጋል።

የእንስሳት እና የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቱን ያሳደገው አርሶ አደር ከምርቱ የተወሰነውን ለራሱ ፍጆታ በማዋል የምግብ ፍላጎቱን ማርካት እንደሚችል ይገመታል። ይህ ብቻ ግን በቂ አይሆንም። ምርቱን ሸጦ የሚያስፈልጉትን የምግብና ሌሎች የፍጆታ ሸቀጦችን መግዛትና ኑሮውን ማሻሻል መቻል አለበት። በአካባቢው የሚኖረው ገበያ በዚህ ረገድ የሚኖረው አስተዋፅኦ ቀላል ግምት የማይሰጠው ቢሆንም ምርቱ በተቻለ መጠን የአለም ገበያን ሰብሮ መግባት አለበት። የእንስሳት ሃብት ግብይትን ስርአት ለማስያዝና አስተማማኝ የውጭ ገበያን ለማግኘት በፌዴራል ደረጃ ራሱን የቻለ መስሪያ ቤት ተቋቁሞ አበረታች እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይኸው ስራ ለወደፊቱም ተጠናክሮ ተጨባጭ ውጤት የሚያስገኝበት ሁኔታ መፈጠር አለበት።

በድርቅ አካባቢዎች የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና የእንስሳት ሃብት ልማት በጣምራ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከምንጠቀምባቸው ቁልፍ ስልቶች ውስጥ በመሆናቸው ስራዎቹን በጣምራ መፈፀምና ያለማቋረጥ ማሻሻል ያስፈልጋል።

### (ሐ) የውሃ ሃብት አጠቃቀምን ማሻሻል፣

በድርቅ አካባቢም ሆነ በሌላ በማንኛውም አካባቢ የሚካሄድ ስራ፣ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና የእንስሳት ሃብት ልማት ስራን ጨምሮ ያለበቂ ውሃ ሊካሄድ አይችልም። በድርቅ

www.abyssinialaw.com

አካባቢዎች የዝናብ እጥረትና መቆራረጥ አለ ቢባልም በድምር በአንድ አመት ውስጥ በነዚህ አካባቢዎች የሚዘንበው ዝናብ የተሳካ የግብርና ስራ ለመስራት በቂ ነው፡፡ በዚህ ላይ የድርቅ አካባቢ ተብለው በሚታወቁት በብዙዎቹ ቦታዎች በቂ የከርሰ-ምድርና የገፀ-ምድር ውሃ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በዚህ አካባቢ ያለው ዋናው ችግር የውሃ እጥረት ችግር ሳይሆን የውሃ አጠቃቀም ችግር ነው፡፡ ይህ የውሃ አጠቃቀም ችግር ካልተወገደ በስተቀር በነዚህ አካባቢዎች ፋይዳ ያለው የግብርና ልማት ስራ መስራት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በነዚህ አካባቢዎች የውሃ አጠቃቀምን ማሻሻል የሁሉም የግብርና ልማት ስራዎቻችን ማዕከል መሆን ይገባዋል፡፡

የውሃ ሃብት ልማትን ለማፋጠን በዋነኛነት በአርሶ አደሩ ማሳ ዙሪያና በራሱ በአርሶ አደሩ የሚከናወኑ፣ በቀበሌ ደረጃ የሚሰሩ የመለስተኛ ግድብና ወንዝ ጠለፋ ስራዎችን ጨምሮ የተሟላና የተለያዩ የውሃ አጠቃቀም ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችን አጣምረው የያዙ ፖኬጆች ማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግና በየጊዜው ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ቀደም ብለው በቀረቡት ትንተናዎች በሰፊው ተገልፃል፡፡ ይህ ስራ በሁሉም ቦታዎች ሊሰራ የሚችልና የሚገባውም ነው፡፡ ነገር ግን ከሁሉም ሌሎች አካባቢዎች በላይ ተፈላጊ የሚሆነውና የላቀ ውጤትም የሚያስገኘው የድርቅ አካባቢ ተብለው የሚታወቁት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ የውሃ ሃብት ልማት ስራ በነዚህ አካባቢዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶትና የግብርና እንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ እምብርት መሆኑ ታውቆ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

እነዚህን ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ መላውን አርሶ አደር ማነሳሳት ማስተባበርና ከአቅሙ ጋር በሚመጥን



አኳኋን ማሰልጠን ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በነዚህ አካባቢዎች የሚካሄድ የአርሶ አደሮች ስልጠና ዋናው ትኩረትና መሰረት ይኸው መሆን ይኖርበታል፡፡ የተፈጥሮ ሃብትና የእንሰሳት ልማትም ሆነ የአዝርእት ልማት የሚካሄደው በውሃ ሃብት ልማት ስራ ላይ በመመስረት ስለሆነ የሚሰጠውም ስልጠና ይህንኑ መሰረት ያደረገና በዚሁ ላይ ተመስርቶ ሌሎችንም ያካተተ መሆን አለበት፡፡

የተዘጋጁትን ቴክኖሎጅዎች ለማስፈፀም በተጨማሪ ከፍተኛ የቴክኒክ ድጋፍና የብድር አገልግሎት ያስፈልጋል፡፡ የኤክስቴንሽን ሰራተኞች እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በማስፈፀም ረገድ በቂ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ የውሃ ማቆርና አጠቃቀሙን የማሻሻል ስራ ለመስራት አነሰም በዛም የግንባታ ስራ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ አርሶ አደሩ ይህንን ለመፈፀም የብድር አገልግሎት ያስፈልገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በውሃው በአግባቡ ለመጠቀም የተለያዩ ቁሳቁሶች ማስፈለጋቸው አይቀርም፡፡ እነዚህ ቁሳቁሶች በሚፈለገው መጠንና ጥራት ተባዝተው በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩ እንዲደርሱ መደረግ አለበት፡፡ እነዚህን ለመግዛትም የብድር አገልግሎት ያስፈልገዋል፡፡ በመሆኑም በነዚህ አካባቢዎች የውሃ አጠቃቀምን ለማሻሻል ከቴክኒክ ድጋፍ በተጨማሪ የብድር አገልግሎትና የተፈላጊ ቁሳቁሶች መሟላት ወሳኝ ይሆናል፡፡ የምግብ ዋስትና ፕሮግራማችን እነዚህን በተሳካ ሁኔታ ማቅረብ መቻል አለበት፡፡

በነዚህ አካባቢዎች ያለው አፈር ለረጅም ጊዜ ያለአግባብ ጥቅም ላይ በመዋሉና በመሸርሸሩ ለምነቱ በከፍተኛ ደረጃ የተጻከመ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በነዚህ አካባቢዎች ከፍተኛ

www.abyssinialaw.com

የመሬት ጥበት ችግር አለ። መታረስ የማይገባቸው መሬቶች ከእርሻ ውጪ እንዲሆኑ ሲደረግ የሚታረሰው መሬት በባሰ መጥበቡ የማይቀር ነው። ስለሆነም የአፈሩን ለምነት ለመጠበቅና ያለውን ውሱን መሬት አጠቃቀም ለማሻሻል ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል።

በዚህ ረገድ ወሳኙ ጉዳይ የአፈር መሸርሸርን ለመቋቋም የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች መርጦ በፖኬጅ አዘጋጅቶ ተግባራዊ የማድረግ ስራ ነው። ይህ ስራ አጥጋቢ በሆነ አኳኋን ካልተፈፀመ በስተቀር የአፈሩን ለምነት ለመጠበቅና ለማሻሻል የሚደረግ ማንኛውም ስራ ቀጣይነት ያለው ውጤት ሊያስገኝ አይችልም። በዚህ ስራ ላይ ተመስርቶ የአፈሩን ለምነት ለመጠበቅ ሰፊ ርብርብ መደረግ አለበት። ከዚህም አኳያ የአፈርን ለምነት በአፋጣኝ በማሻሻል ረገድ ፈጣን ውጤት ያስገኛሉ ተብለው ለሚገመቱ ተፈጥሮአዊ ለሆኑ አማራጮች (ባዮሎጂካል ሜተድስ) ቅድሚያ በመስጠት መረባረብ ያስፈልጋል።

የአፈሩን ለምነት ለመጠበቅና ለማሻሻል የሚደረጉ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው በማሳው ላይ ምን ይመረት የሚለው ጉዳይ እንደ የአካባቢው ሁኔታ መመለስ ይኖርበታል። የመስኖ ልማት ከተስፋፋ መሬቱ ጠባብ ቢሆንም ተደጋግሞ ስለሚታረስ ውጤቱ የላቀ እንደሚሆን መገመት ይቻላል። ይሁንና በነዚህ አካባቢዎች የሰብል እህል ልማት ሊካሄድ የሚችል ቢሆንም ዋናው ስራ ይህ መሆን አይኖርበትም። በጠባብ መሬት ከሰብል ልማት ይልቅ የተለያዩ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች፣ አትክልቶች፣ ቅመማ ቅመሞች፣ ፍራፍሬዎች ማምረት የሚመረጥ ይሆናል። ከዚህም ሌላ በአካባቢው ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ከሚስፋፋው የእንስሳት ሃብት ልማት ስራ ጋር



በተያያዘ ለእንስሳት መኖ ልማትም ትኩረት መስጠት ያሻል። ምን? የት? ሊመረት እንደሚችል መወሰን ያለበት የገበያ ዕድሎችንን የአካባቢውን ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባል። እዚህ ላይ ሊቀመጥ የሚገባው አቅጣጫ ከመሬቱ ጥበት ጋር ተያይዞ እርሻው ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው የግብርና ምርቶች ላይ ቢያተኩር የሚመረጥ መሆኑ ነው።

ቀደም ሲል እንደተለገፀው ምንም እንኳ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ፕሮግራማችን ከግብርና ውጪ የስራ ዕድሎች መፍጠርን የሚያካትት ቢሆንም ዋናው መንገድ ሰፈራን ጨምሮ በግብርና ዙሪያ በሚካሄዱ የልማት ስራዎች የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው። ይሁንና ከላይ እንደተዘረዘረው ይህ በግብርና ልማት ዙሪያ የሚካሄደው የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ስራ አርሶ አደሩ ምግቡን ራሱ አምርቶ እንዲመገበው በማድረግ የሚፈፀም አይደለም። የግብርና ምርት አምርቶ የተወሰነውን ራሱ ተጠቅሞበት የተቀረውን ሽጦ ምግቡንና ሌሎች ፍላጎቶቹ ከገበያ በመግዛት የምግብ ዋስትና የሚያረጋግጥበት ነው። ገበያን ማዕከል ያደረገ የምግብ ዋስትና ስትራተጂ ስለሆነ ለግብይት ስርአቱ መሻሻል ልዩ ትኩረት መስጠትን የሚጠይቅ ይሆናል።

## 4.3. በቂ ዝናብ ባላቸው የአርሶ አደር አካባቢዎች የሚሰራ ስራ፣

በቂ ዝናብ ባላቸው የአርሶ አደር አካባቢዎች የምግብ ዋስትናው ችግር በድርቅ አካባቢዎች እንደሚታየው ባይሆንም አካባቢዎቹ ከአስከፊ ድህነት የተላቀቁ ናቸው ማለት አይደለም። ስለሆነም በነዚህ አካባቢዎችም ማግኘት የሚቻለውን የላቀ

የግብርና ልማት ለማምጣት ከፍተኛ ርብርብ መደረግ አለበት፡፡ ይልቁንም እነዚህ አካባቢዎች በአሁኑ ወቅት የምግብ ሰብሎችን በማምረት ረገድ ወሳኝ ሚና በመጫወት ላይ ያሉ በመሆናቸውና ለወደፊቱም የላቀ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው በነዚህ አካባቢ የሚካሄደው ልማት በአገር አቀፍ ደረጃ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው በድርቅ አካባቢዎች የሚካሄደው ልማት በነዚህ አካባቢዎች ለሚኖረው ህዝብ የምግብ ዋስትና የሚያረጋግጥለት ገቢ ያስገኝለታል ተብሎ የሚገመት ቢሆንም ተፈላጊው የሰብል እህል በነዚህ አካባቢዎች ይመረታል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በቂ ዝናብ ካላቸው የአርሶ አደር አካባቢዎች የሚሸመት ይሆናል ተብሎ ነው የሚገመተው፡፡ በመሆኑም በነዚህ አካባቢዎች ፈጣን የግብርና እድገትን ማረጋገጥ ከፍተኛ አገር አቀፋዊ እንድምታ ያለው ጉዳይ ነው፡፡

በቂ ዝናብ ባላቸው አካባቢዎች የሚሰራው የግብርና ልማት ስራ በድርቅ አካባቢዎች ከሚሰራው ስራ ጋር በብዙ መልኩ ተመሳሳይና አንድ ነው፡፡ በነዚህ አካባቢዎችም የውሃ አጠቃቀም ስርአታችንን ማሻሻልና በመሬታችን አመቱን በሙሉ ለመጠቀም መቻል ይኖርብናል፡፡ በነዚህ አካባቢዎችም የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ስራ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በነዚህ አካባቢዎችም የእንስሳት ሃብት ልማት ስራ አንድ ትልቅ የግብርና ዘርፍ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም፡፡ ይሁንና በነዚህ አካባቢዎች የሚሰራው ስራ ከትኩረት አቅጣጫው አኳያ በድርቅ አካባቢዎች ከሚሰራው የተለየ መሆኑ አይቀርም፡፡

በነዚህ አካባቢዎች በአመት ቢያንስ አንድ ጊዜ በቂ ምርት ለማምረት የሚያስችል ዝናብ ያለ መሆኑ የውሃ



አጠቃቀምና መስኖ ስራ ተፈላጊ ቢሆንም በድርቅ አካባቢ እንደሚታየው በጣም አጣዳፊ ስራ አይሆንም፡፡ የዝናብ ውሃን በላቀ ደረጃ በመጠቀም ብቻ በነዚህ አካባቢዎች አሁን ከምናገኘው እጅግ የላቀ ምርት ማግኘት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በነዚህ አካባቢዎች ከአጭርና መካከለኛ ጊዜ አኳያ የመስኖ ስራ የሚሰራ ቢሆንም የመንግስት ትኩረት የዝናብ ውሃውን በላቀ ደረጃ በመጠቀም ምርትን በማሳደግ ላይ መሆን ይኖርበታል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች የመስኖ ስራ ጭራሹን አይሰራም ባይባልም፣ በተጨማሪም የመስኖ ስራ አማራጮች ቀርበው ህዝቡ መሄድ እስከቻለበት ድረስ እንዳይሄድ የሚደቀንበት እንቅፋት ባይኖርም፣ በአካባቢው ያለውን በቂ የዝናብ ውሃ በመጠቀም ብቻ ከፍተኛ የግብርና እድገት ማረጋገጥ ስለሚቻል የመንግስት ትኩረት የዝናብ ውሃውን በላቀ ደረጃ በመጠቀምና ይህንኑ ተጠቅሞ የግብርና ምርትን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ ላይ ይሆናል፡፡

በቂ ዝናብ ባላቸው የአርሶ አደር አካባቢዎች የተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ የአግሮ ፎሬስትሪና የእንስሳት ሃብት በሰፊው ሊሰራ የሚችልና የሚገባው ነው፡፡ ይሁንና እነዚህ አካባቢዎች ዋናው ትኩረታቸውን በዚህ ላይ የሚያደርጉበት በቂ ምክንያት አይኖርም፡፡ በተለይም በተነፃፃሪ ሰፋ ሰፋ ያለ የእርሻ ማሳ ያላቸው አካባቢዎች የሰብል ምርትን በከፍተኛ ደረጃ ማምረትና ከዚሁ መጠቀም ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ አካባቢ የሚገኙ ህዝቦችን ኑሮ ከማሻሻልም ሆነ የአገሪቱን አጠቃላይ እድገት ከማቀላጠፍ አኳያ የላቀ አስተዋፅኦ የሚኖረው የአግሮ ፎሬትሪና የእንስሳት ሃብት ልማት ስራ ሳይዘነጋ የህዝቡና የመንግስት ዋነኛ ትኩረት በሰብል ምርት ላይ ቢሆን ነው፡፡ ምርጥ ዘሮችን በማቅረብና በየጊዜው በማሻሻል፣ ተፈጥሯዊና ተፈጥሯዊ ያልሆነ

www.abyssinialaw.com

ማዳበሪያን በሰፊው በመጠቀም፣ የዝናብ ውሃ አጠቃቀማችንን በማሻሻል፣ ምርታማነትን የሚጨምሩ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመጠቀም በነዚህ አካባቢዎች የሰብል ምርት ያለማቋረጥ ከፍተኛ እድገት እንዲያስመዘግብ ማድረግ ይቻላል። የመንግስት ዋነኛ ትኩረትም በዚህ ላይ መሆን ይገባዋል።

ይሁንና በቂ ዝናብ ያላቸው ነገር ግን ከፍተኛ የመሬት ጥበት ያላቸው አካባቢዎችም ይኖራሉ። በመሬት ጥበቱ ምክንያትም የሰብል እህል ማምረት የሚመረጥ ላይሆን ይችላል። በነዚህ አካባቢዎች የህዝቡን ኑሮ በተሻለ ደረጃ የሚያሻሽልና የአገሪቱን አጠቃላይ እድገት የሚያቀላጥፍ አማራጭ ባለው ውሱን መሬት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች ማምረት ሊሆን ይችላል። የህዝቡ የእስካሁኑ ልምድም ወደዚሁ የሚያደላ ነው። የዛፍ ተክሎችና (ቡና፣ እንሰት ወዘተ.) የተለያዩ ቅመማ ቅመሞች በአብዛኛው የሚመረቱት በነዚህ አካባቢዎች ነው። ለወደፊቱም ቢሆን ይህንኑ መሰረት በማድረግ በውሱን መሬት የላቀ ጉልበት በመጠቀም የተሻለ ገቢ በሚያስገኙ ምርቶች ላይ ማተኮር የሚመረጥ ይሆናል።

እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባ አንድ መሰረታዊ ጉዳይ አለ። መንግስት በምንም አይነት መንገድ በዚህ አካባቢ ቢመረት የተሻለ የሚሆነው ይህ ነውና አርሶ አደሮች ይህንኑ ማምረት አላባችሁ ከዚህ ውጪ መንቀሳቀስ የለባችሁም ብሎ የሚሰጠውና የሚያስፈፅመው ምንም አይነት ትእዛዝ አይኖርም። ይህ ቢደረግም በፍፁም የሚሰራ አይደለም፣ ፀረ-ህዝብ ወንጀል ከመሆን ሊያልፍም አይችልም። መንግስት ያለው አማራጭ የተሻለ ነው ብሎ የሚያምንበትን መጠቆም የተለያዩ የቴክኖሎጂ ፖኬጆችን ማቅረብና አርሶ አደሩ የመረጠውን ተግባራዊ



እንዲያደርግ መፍቀድ ነው። የግብርናው እድገት ሂደት ራሱ አርሶ አደሩ በበለጠ የሚጠቅመውን ምርት በትክክል እንዲለይ ያስችለዋል። ይህንኑ ለይቶ በምርት ተግባር ላይ በሚሰማራበት ወቅት መንግስት ድጋፉን ይሰጣል። ከዚህ መርህ ውጪና ይህንኑ መርህ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚፃረር ስራ መስራት ፈፅሞ የተከለከለ መሆን አለበት።

ቀደም ሲል እንደተቀመጠው በየትኛውም አካባቢ ያለው አርሶ አደር በርካታ የግብርና ምርቶችን አጣምሮ ማምረት መቻል ይኖርበታል። ባለንበት የእድገት ደረጃ ለአርሶ አደሩ ኑሮ መሻሻልም ሆነ ለአገሪቱ አጠቃላይ እድገት የሚበጀው ይኸው ነው። ስለሆነም በዚህ አካባቢ ዋናው ትኩረት በዚህ ላይ መሆን አለበት። በሌላው አካባቢ ደግሞ ዋናው ትኩረት በሌላ ላይ መሆን አለበት ወዘተ. ሲባል ትኩረት ይሰጠዋል ከተባለው ምርት ውጪ ሌላ የግብርና ምርት መመረት የለበትም ማለት አይደለም። የአካባቢው የግብርና ምርት እንቅስቃሴ እምብርት ትኩረት ይሰጠዋል የተባለው ምርት ሆኖ በዚሁ ዙሪያ ግን ከዚህ ምርት ጋር በጣምራ ሊሰሩ የሚችሉ ሌሎች የግብርና ስራዎች መስራት አለባቸው ማለት ነው። ይህንኑ ነጥብ በሚገባ ተገንዝቦ በዚሁ መሰረት መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ ሌላው ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ነው።

## 4.4. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚሰራ ስራ፣

በአርብቶ አደሩ አካባቢ በድርቅ አካባቢዎች ከሚታየው የማይለይ ከፍተኛ የምግብ ዋስትና ችግርና ድህነት ይታያል። ምንም እንኳ በነዚህ ቦታዎች ከፍተኛ የገፀ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሃ ሃብት ያላቸው በርካታ አካባቢዎች መኖራቸው

www.abyssinialaw.com

ቢታወቅም በየአመቱ የሚዘንበው ዝናብ ውሱንና የተቆራረጠ በመሆኑ በዚህ ላይ በመመስረት በቋሚነት የሚካሄድ የእርሻ ስራ መስራት የሚቻል አልሆነም፡፡ በመሆኑም የህዝቡ ኑሮ በከብት ርባታ ላይ የተመሰረተና ከቦታ ቦታ መዘዋወርን የሚያስከትል ሆኗል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማምጣት የህዝቡ ኑሮ ከተመሰረተበት የግብርና ዘይቤ መነሳት አለብን፡፡ የህዝቡ የኑሮ መሰረት ተንቀሳቃሽ የከብት ርቢ በመሆኑ የልማት ጥረታችንና እንቅስቃሴያችንም በዚሁ ላይ መመስረት ይኖርበታል፣ የእንስሳት ሃብት ልማትን ማዕከል አድርጎ መነሳት ይኖርበታል፡፡

የእንስሳት ሃብት ልማትን በተመለከተ ከድርቅ አካባቢዎች የልማት እንቅስቃሴ ጋር አያይዘን ያስቀመጥናቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች እዚህም ላይ ይሰራሉ፡፡ እነዚህን መድገም ተፈላጊ ባለመሆኑ ከአካባቢዎቹ ለየት ያለ ሁኔታ በመነሳት በእንስሳት ሃብት ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ በነዚህ አካባቢዎች ለየት ያለ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ተገቢ ይሆናል፡፡

በእነዚህ አካባቢዎች በተለይም የዝናብ ወቅት ካለፈ በኋላ ለሰውም ሆነ ለእንስሳት የሚሆን የመጠጥ ውሃ ከፍተኛ እጥረት ይታያል፡፡ የመጠጥ ውሃ ባለበት አካባቢ ደግሞ ከፍተኛ የእንስሳት ሃብት ክምችት ስለሚኖር በአካባቢው የግጦሽ እጥረት ያጋጥማል፣ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት መመናመንንም ያስከትላል፡፡ በመሆኑም የመጠጥ ውሃ ባለበት አካባቢ የግጦሽ ችግርና የተፈጥሮ ሃብት መመናመን እያጋጠመ፣ ሰፊ የግጦሽ አካባቢ ግን በአቅራቢያው የመጠጥ ውሃ ባለመኖሩ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሳይውል ይቀራል፡፡ ከብት አርቢው የመጠጥ ውሃንና ግጦሽን ፍለጋ ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሰ ለመኖር ይገደዳል፡፡



ከዚህ በመነሳት የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና የግጦሽ አቅርቦትን ማቀናጀት በአካባቢው የእንስሳት ሃብት ልማትን ለማሻሻል እጅግ መሰረታዊ ትርጉም ያለው ነገር ይሆናል፡፡ በብዙ አካባቢዎች ለሰውና ለእንስሳት የሚሆን በቂ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ በአግባቡ ጥቅም ላይ ያልዋሉ የግጦሽ መሬቶችን ጥቅም ላይ ማዋልና፣ በተወሰኑ የግጦሽ መሬቶች ላይ እየታየ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት መመናመን ማስቀረት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በነዚህ አካባቢዎች በመጀመሪያ ደረጃ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ በተመረጡ በርካታ አካባቢዎች የእንስሳትና የሰው የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጭ በነዚህ አካባቢዎች የእንስሳት ሃብት ልማትን ማሻሻል የሚታሰብ አይሆንም፡፡

የመጠጥ ውሃ አቅርቦቱ ሲሻሻል የግጦሽ ችግርም በከፍተኛ ደረጃ የሚቃለል ቢሆንም ይህ ብቻ የግጦሽን ጉዳይ በዘላቂነት ይፈታዋል ማለት አይቻልም፡፡ የግጦሽ መሬት አስተዳደርና እንክብካቤ መሻሻል አለበት፡፡ ከህብረተሰቡ የጎሳ አወቃቀር ጋር በተያያዘ የግጦሽ መሬት አጠቃቀም ባህሎች ያሉ ቢሆንም እነዚህን መሰረት አድርጎ ስርአቱን ለማጠናከርና ለማሻሻል ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ የግጦሽ አቅርቦት ተፈጥሮ የሰጠውን መቀበል ብቻ ሳይሆን የተመናመነውን ማሻሻል፣ የተቀረውን ደግሞ አጠቃቀሙን ማሳመር ይጠይቃል፡፡ ከጎሳ መሪዎች የህዝብ ተመራጮችና ተጠሪዎች ጋር በመሆን የግጦሽ መሬት አስተዳደርና እንክብካቤን ለማሻሻል ሰፊ ስራ መሰራት አለበት፡፡

የአካባቢው ከብት አርቢዎች በልምድ ያዳበሩት ቀላል ግምት የማይሰጠው የከብት ርቢ ሙያ አላቸው፡፡ ይህንኑ

ሳይገነዘቡና መሰረት ሳያደርጉ የአካባቢውን የከብት ርቢ ሞያ ለማሻሻል መሞከር የሚጠቅምም፣ ሊሳካ የሚችልም ነገር አይደለም:: በመሆኑም የአካባቢውን የከብት ርቢ ቴክኖሎጂ ለማሻሻል በመጀመሪያ ደረጃ በአካባቢው ያለውን ልምድ በዝርዝር መገምገም፣ ጠንካራና ደካማ ጎኑን ለይቶ ማስቀመጥ ያስፈልጋል:: ከዚህ በኋላ ጠንካራ ጎኖቹን ይበልጥ በማጎልበት ደካማ ጎኖቹን ለማስወገድ የሚያስችል ፖኬጅ መዘጋጀትና ለአርብቶ አደሩ መቅረብ ይገባዋል:: በዚህ አካባቢ የሚካሄደው የግብርና ልማት የእንስሳት ሃብት ልማት በመሆኑ የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ስልጠናም ሆነ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ በዚህ ላይ ያተኮሩ መሆን ይገባቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪ ከህዝቡ ተንቀሳቃሽነትና የጎሳ አወቃቀር ጋር በተያያዘ መልክ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችል ከአካባቢው ጋር የሚሄድ የኤክስቴንሽን ስርአት በተለየ ሁኔታ መቀየስና ተግባራዊ መሆን አለበት::

የእንስሳት ሃብት ልማት የኤክስቴንሽን አገልግሎት በተሳካ ሁኔታ ከተፈፀመ የእንስሳቱ እንክብካቤ በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽሎ ጤናቸውም በዚያው መጠን እንደሚሻሻል መገመት ይቻላል:: በዚህ ላይ የተሟላ የእንስሳት ክትባት አገልግሎት ስርአት በአካባቢው በመዘርጋት የክትባት አገልግሎት ከታከለበት በእንስሳቱ ጤንነት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል:: ይሁንና ከዚህ በተጨማሪ የእንስሳት ህክምና አገልግሎትም መጠናከር አለበት:: የእንስሳት ህክምና አገልግሎት ስርአቱ ከከብት አርቢው ተነቃናቂነት ጋር የሚጣጣም እንዲሆን ማድረግም አስፈላጊ ነው::

የእንስሳት ግብይት ስርአቱን ማሻሻል ለነዚህ አካባቢዎች



እጅግ በጣም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ጉዳይ ነው:: ቀደም ሲል እንደተዘረዘረው ይህንኑ ስርአት ለማሻሻል ጥረት በመደረግ ላይ ያለ ሲሆን ለወደፊቱም ጥረቱ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል:: ይህ በአገር አቀፍ ደረጃ እየተሰራ ያለ ስራ ነው:: ከከብት አርቢው አካባቢ ልዩ ሁኔታ ጋር በማያያዝ በነዚህ አካባቢዎች ለየት ያለ ስራ የሚጠይቁ ጉዳዮችም ይኖራሉ::

በመጀመሪያ ደረጃ የአካባቢው ህዝብ ከሌላውም በበለጠ ዋነኛው ትኩረቱ የከብቱን ብዛት በመጨመር ላይ እንጂ ከእያንዳንዱ ከብት የሚያገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማሳደግ ላይ ያተኮረ አይደለም:: በመሆኑም ከብቶቹን ቶሎ ቶሎ እየሸጠ የመጠቀም ልምድ የለውም:: ይህንኑ ባህል ደረጃ በደረጃ መቅረፍ ካልተቻለ የአካባቢው ህዝብም ሆነ አገሪቱ ከእንስሳት ሃብታችን በሚገባ መጠቀም አይችሉም:: የእንስሳት ሃብት ልማት እንቅስቃሴያችንም በሚፈለገው ደረጃ ሊቀላጠፍ አይችልም::

በአካባቢው ብቃት ያለው የእንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ ግብይት ስርአት ከተፈጠረ አካባቢውን በይበልጥ ለማልማትና የህዝቡንም ባህል ለማሻሻል ይቻላል:: ስለሆነም የእንስሳት ግብይት ስርአትና ይህንኑ ለማከናወን የሚችሉ ድርጅቶችን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል ያስፈልጋል:: ፌዴራል መንግስትና የአካባቢው አስተዳደሮች በጋራ በነዚህ አካባቢዎች የግል ባለሃብቶች የእንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ ኩባንያዎችን እንዲያቋቁሙ በሰፊው ማበረታታት ይገባቸዋል:: (የከብት ማድለቢያ፣ የከብት ገበያዎችና ማጓጓዣ፣ የስጋና ቆዳ ፋብሪካዎች ወዘተ.) ይህ ስራ በሚገባ ሲፈፀም ለአካባቢው ልማት የሚኖረውን ወሳኝነት በመገንዘብ የግል ባለሀብቶች በዚህ መስክ እንዳይሰማሩ እንቅፋት

www.abyssinialaw.com

የሚሆኑባቸውን ነገሮች ለይቶ በማጥናት በአፋጣኝ መፍታት ያስፈልጋል፡፡ በግል ባለሀብቶች ሊሰሩ ያልቻሉና አማራጭ ያልተገኘላቸውን ስራዎች መንግስት በተለይም የአካባቢዎች የመንግስት አካላት እንዲሰሯቸው ማድረግም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

ህዝቡ በተንቀሳቃሽ የከብት ርቢ ስራ ላይ የተሰማራ ነው ሲባል አመቱን በሙሉ እንቅስቃሴ ላይ ይሆናል፣ ወይም ቤተሰብ በሙሉ እኩል ይንቀሳቀሳል ማለት አይደለም፡፡ ምንም እንኳ የእንቅስቃሴው መጠንና አድማስ ከቦታ ቦታ የሚለያይ ቢሆንም በብዙዎቹ አካባቢዎች ህዝቡ ለበርካታ ወራት በአንድ አካባቢ የሚሰፍርበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ከዚህም በላይ የቤተሰብ እንቅስቃሴ አድማስና መጠን ከአባወራዎቹ እንቅስቃሴ ያነሰ ሆኖ ይገኛል፡፡ ህዝቡ በተለይም ቤተሰብ በአንድ አካባቢ ለበርካታ ወራት በሚሰፍርበት ወቅት ይህንኑ ምቹ ሁኔታ በመጠቀም በዚሁ አካባቢ በተጠቀሱት ወራት ሊከናወኑ የሚችሉ የግብርና ስራዎችን ለይቶ እነዚህን ስራዎች በስፋትና የተሻለ ምርታማነትን ሊያረጋግጥ በሚችል አኳኋን መፈፀም ይቻላል፡፡ የህዝቡን ኑሮ ከማሻሻል አኳያ ይህ ስራ ከፍተኛ ትርጉም ሊኖረው ስለሚችል የግብርና ልማት እንቅስቃሴያችን ለዚህ ተግባር ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

ከአጭርና በተወሰነ ደረጃም ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ በነዚህ አካባቢዎች የተንቀሳቃሽ የከብት ርቢ ስራን በማሻሻል ላይ ያተኮረ የግብርና ልማት እንቅስቃሴ ከማድረግ ውጪ አማራጭ የሌለን ቢሆንም ከረጅም ጊዜ አኳያ ይህ አካሄድ ዘላቂና ቀጣይነት ያለው የአካባቢ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል አይሆንም፡፡ ለተንቀሳቃሽ ህዝብ ብቃት ያለው



የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሰረተ-ልማት አገልግሎት መስጠት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች ቀጣይነት ያለው ፈጣን ልማት ማረጋገጥ የሚቻለው ህዝቡ እንዲሰፍር ከተደረገ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የሰፈራ ፕሮግራም በተለይም ከረጅም ጊዜ አኳያ በነዚህ አካባቢዎች ከሌሎች አካባቢዎች ሁሉ የላቀ ትርጉምና አስፈላጊነት ይኖረዋል፡፡

በነዚህ አካባቢዎች የሚደረገው የሰፈራ ስራ በሌሎች አካባቢዎች ከሚደረገው የሰፈራ ስራ ጋር የሚያመሳስሉት በርካታ ነገሮች እንደሚኖሩ እሙን ነው፡፡ በተለይም የሰፈራ ፕሮግራማችን የሚመራባቸው መሰረታዊ መርሆዎች በሁሉም አካባቢዎች የሚሰሩና በጥብቅ መከበር ያለባቸው ይሆናሉ፡፡ ይሁንና የሰፈራ ፕሮግራሙ በነዚህ አካባቢዎች ካለው ለየት ያለ ሁኔታ የሚመነጬ ለየት ያሉ ባህሪያትም ይኖሩታል፡፡ ቀደም ሲል የተዘረዘሩትን መሰረታዊ የሰፈራ መርሆዎች እዚህ ላይ መድገም አስፈላጊ ስለማይሆን ለየት ያለ ትኩረት የሚሹትን ነጥቦች ብቻ እንዘረዝራለን፡፡

በሌላው አካባቢም እንደሚደረገው ሰፈራው በመሰረቱ በክልሉ ውስጥ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ይልቁንም በነዚህ አካባቢዎች ካለው የጎሳ አወቃቀር በመነሳት የሰፈራው ስራ በተቻለ መጠን ጎሳው በሚኖርበት አካባቢ እንዲፈፀም ማድረግ አስፈላጊና ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በነዚህ አካባቢዎች በዝናብ ውሃ ላይ ብቻ የተመሰረተ ቋሚ የእርሻ ስራ መስራት አይቻልም፡፡ በሌሎች አካባቢዎች ህዝቡን በቂ ዝናብና የእርሻ መሬት ወዳለበት አካባቢ ወስዶ ማስፈር ሲቻል በከብት አርቢው ይህ አማራጭ በአብዛኛው ዝግ ነው፡፡ በነዚህ

www.abyssinialaw.com

አካባቢዎች የሚካሄደው የሰፈራ ስራ ከመስኖ ልማት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ካልሆነ በስተቀር ሊሳካ የሚችል አይደለም። ስለሆነም በነዚህ አካባቢዎች የሰፈራ ቦታ አመራረጥ በአካባቢው በቀላሉ ለመስኖ ልማት ሊውል የሚችል የገፀ-ምድር ወይም የከርሰ-ምድር ውሃ መኖሩን ከማረጋገጥ ጋር በቀጥታ የተያያዘ መሆን ይኖርበታል።

የመስኖ ስራ የሚጠይቀውን ከፍተኛ ወጪ ለመሸፈን የአካባቢውን ህዝብ ጉልበት በሰፊው መጠቀም የሚገባ ቢሆንም፣ ይህ ጉዳይ በነዚህ አካባቢዎች ለየት ያለ ባህሪ ምክንያት እንዲህ በቀላሉ የሚሳካ አይሆንም። ስለሆነም በሌላ አካባቢ ከሚደረገውም በላይ የገንዘብ ወጪ የሚጠይቅ ይሆናል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ የምንከተላቸው የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች በተቻለ መጠን በዝቅተኛ ወጪ ሊሰሩ የሚችሉ እንዲሆኑ ማድረግና አፈፃፀሙም በተራዘመ ጊዜ በትንሽ በትንሹ እንዲሆን ማድረግ ነው። በአጭሩ በነዚህ አካባቢዎች የሚከናወነው የሰፈራ ስራ የመስኖ ልማትን መሰረት ያደረገ ይሆናል።

በድርቅ አካባቢዎች የሚካሄደው የሰፈራ ስራ የቦታ ለውጥን ብቻ የሚመለከት የሰፈራ ስራ ነው። በአንድ አካባቢ በቋሚ የእርሻ ስራ ላይ ተሰማርቶ የነበረውን አርሶ አደር የተሻለ መሬትና ዝናብ ወደአለበት አካባቢ ወስዶ ይህን የለመደውን የቋሚ እርሻ ስራ እንዲቀጥልበት የማድረግ ስራ ነው። በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚካሄድ የሰፈራ ስራ ግን ከቦታ ለውጥ በላይ የሚሄድ መሰረታዊ የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ነው። በተንቀሳቃሽ የከብት ርቢ ስራ ላይ የነበረን ሰው በቋሚ እርሻ ወደሚተዳደር አርሶ አደር የመለወጥ ጉዳይ ነው። በቋሚ እርሻ ስራ ላይ ይህ ነው የሚባል እውቀትና ልምድ ስለማይኖረው



ይህንኑ ስራ ሀ ብሎ የማስተማርና የማስለመድ ከባድና ውስብስብ ስራን የሚጠይቅ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘም ከፍተኛ የባህል ለውጥ የሚጠይቅ ይሆናል። ስለሆነም የሰፈራውን ፕሮግራም ለማሳካት በአንድ በኩል ሰፊና መሰረታዊ የቋሚ እርሻ ስልጠና ማካሄድ የሚጠይቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሰፈራ ስራውን ደረጃ በደረጃ በመፈፀም አስቀድሞ የሰፈረው ተከትሎ የሚመጣውን የሚያስለምድበትንና የሚያሰለጥንበትን ስልት መከተል አስፈላጊ ይሆናል።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በነዚህ አካባቢዎች የቦታ አመራረጥ ከሌሎች አካባቢዎች በተለይም የጎሳ ግንኙነቶችን በዚህ ረገድ ያሉ ስሜቶችና ትስስሮችን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት። አፈፃፀሙም ተመሳሳይ ባህሪ ሊኖረው ይገባል። በመጀመሪያ ደረጃ ፕሮግራሙ ፍላጎቱ ያላቸውን የተወሰኑ ግለሰቦችን የማስፈር ጉዳይ ብቻ አይ ደለም። በሂደት በነዚህ አካባቢዎች ያለውን መላውን ህዝብ አሳምኖ የማስፈር ጉዳይ ነው። ስለሆነም ምንም እንኳ ሰፈራው በተወሰኑ ሰዎች ጀምሮ በሂደት እየተስፋፋ መላውን ህዝብ በሚያቅፍ መልኩ መፈፀም ያለበት ቢሆንም ስራው ከመጀመሪያ ጀምሮ ህዝቡን በአጠቃላይ በማሳመን መጀመር አለበት። ህዝቡ ቢያንስ ሰፈራን በተወሰኑ ሰዎች ለመጀመርና ለመሞከር ዝግጁ የሚሆንበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። የመጀመሪያው ሙከራ የተሳካ እንዲሆን ህዝቡ በአጠቃላይ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ዝግጁ መሆንና ሲሳካም ተጨማሪ ሰዎችን እያሰፈረ ፕሮግራሙን ለማስቀጠል ፈቃደኛ የሚሆንበት ደረጃ ላይ ማድረስ ያስፈልጋል። የጎሳ አወቃቀሩ ህዝቡን ለማሳመን የሚኖረውን ተፅእኖ ግምት ውስጥ ያስገባ ህዝቡን የማሳመን ስራ መሰራት ይኖርበታል። ይህንና ሌሎችንም የህዝብ ተሳትፎ ማረጋገጫ መንገዶች በመጠቀም

www.abyssinialaw.com

ህብረተሰቡ የአካባቢውን ችግሮች በመለየት፣ የመፍትሄ ሃሳቦችን በማፍለቅና መወሰድ ያለባቸውን ርምጃዎች በማመላከት እንዲሁም በህብረተሰብ ደረጃ ለፕሮግራሙ ተፈፃሚነት ሊያበረክተው የሚችለውንና የሚገባውን ነገር እንዲወስን በማድረግ ተሳትፎውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

መላውን አርብቶ አደር ህዝብ በሂደት ማስፈር መቻል እንዳለብን ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና ይህንን ለመፈፀም የሚጠይቀው ወጪ፣ የሚያስከትለው የባህል ለውጥና የሚጠይቀው ህዝቡን የማሳመን የፖለቲካ ስራ ግምት ውስጥ ሲገባ ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ ስራ የአስርት አመታት ስራ እንደሚሆን ሊታወቅ ይገባል፡፡ ረጅም ጊዜ ይውሰድም አይውሰድም የግድ መሰራት ያለበት ስራ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በአካባቢዎቹ ዘላቂ ቀጣይነት ያለውና ፈጣን ልማት ማምጣትና የህዝቡን ኑሮ ማሻሻል አይቻልም፡፡ ስለሆነም ከወዲሁ የላቀ ትኩረት ሰጥተን መረባረብ ይኖርብናል፡፡ የረጅም ጊዜ ስራ ከአሁኑ ካልተጀመረ መቼም አይፈፀምም፡፡ በመሆኑም ከአጭርና መካከለኛ ጊዜ አኳያም ቢሆን በተንቀሳቃሽ የከብት ርቢ ስራ ላይ አተኩረን የሰፈራ ስራውን ጎን ለጎን ማስኬድ አለብን፡፡

ከወዲሁ በቀላል ዋጋ የመስኖ ስራ ሊሰራባቸው የሚችሉ ቦታዎችን መለየት፣ በነዚህ አካባቢዎች ሊሰራ የሚገባውን የግብርና -ኬጅ ማዘጋጀትና ለሰፈራው ስልጠና ሊሰጥ የሚችልበትን ስርአት መፍጠር አለብን፡፡ የትና በየትኛው ሰፋሪ ጀምረን ወዴት ማስፋት እንደምንችል ለይቶ የሚያስቀምጥ ፕሮግራም መንደፍ አለብን፡፡ በዚሁ መልኩ ሊለሙ የሚችሉ አካባቢዎችን በሚጠይቁት ወጪ መሰረት በቅደም ተከተል ማስቀመጥ አለብን፡፡ የህዝቡን ፍላጎት መሰረት በማድረግ



ፕሮግራሙን ለማፋጠንም ሆነ ለማዘግየት የሚያስችለን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አለብን፡፡

የአርብቶ አደሩን አካባቢ ህዝብ ማስፈርና በዚሁ ላይ ተመስርቶ ኑሮውን በቀጣይነትና በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል ከማንም በላይ የሚጠቅመው የአካባቢውን ህዝብ ነው፡፡ ይሁንና የአገራችንን አጠቃላይ ልማት በማፋጠን ረገድም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ፕሮግራም ነው፡፡ መላው ህዝባችን የከብት ጭራ ተከትሎ ከመንከራተት ሲድን፣ ያ ቀን በአገራችን እድገት ላይ አንድ አይነተኛ ለውጥ የተመዘገበበት የተከበረ ዕለት ይሆናል፡፡ ስራው በዋነኛነት በአካባቢው ህዝብና በአካባቢው የመንግስት አካላት መፈፀም ያለበት ነው፡፡ ይሁንና አገራዊ እንድምታ ያለው ስራ በመሆኑ ፌዴራል መንግስትና በሌሎች አካባቢዎች የሚኖረውም ህዝብ ማድረግ የሚችለውን አስተዋፅኦ ሁሉ ከማበርከት ወደኋላ ሊል አይችልም፣ አይገባምም፡፡

## 4.5. ያልታረሰ ሰፊ መሬት ባላቸው አካባቢዎች የሚሰራ ስራ፣

በአገራችን በተለይም ከሰሜን እስከ ደቡብ ጫፍ በተዘረጋው የምዕራባዊ ቆላ ክፍልና በሌሎችም ቦታዎች ሰፊ ያልታረሰ ለግብርና ስራ በአጠቃላይም ሆነ ለመስኖ ስራ የተመቸ አካባቢ እንዳለና ይህንን አካባቢ በአፋጣኝ ማልማት በአጠቃላይ እድገታችንን ከፍተኛ ትርጉም ያለው ነገር እንደሆነ ተገልፇል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች ምን መሰራት እንዳለበትና እንዴት ሊሰራ እንደሚችል በተለያዩ አርእስቶች ተገልፇል፡፡ ይህንኑ መድገም አስፈላጊ ባለመሆኑ ሊሰመርባቸው በሚገባ በጥቂት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነገር ማስቀመጥ ብቻ በቂ ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com

በመጀመሪያ ደረጃ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ እነዚህ አካባቢዎች ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው የኢኮኖሚያዊ እድገት ማእከሎች መሆን እንደሚችሉና እንደሚገባቸው ነው:: በመሆኑም በነዚህ አካባቢዎች የሚሰራው የልማት ስራ የአካባቢዎቹን የተቀናጀ ልማት እቅድ መሰረት ያደረገና በነዚህ አካባቢዎች አማካይነት ያሉበትን ክልልና አገሪቱን በአጠቃላይ በማልማት ረገድ ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው የልማት ማዕከላትን ለመፍጠር የሚያስችል ቅኝት ያለው መሆን ይኖርበታል:: ይህን የመሰለውን የተሟላ የአካባቢ ልማት ራዕይ መሰረት ያላደረገና በተበጣጠሰ አኳኋን የሚፈፀም የልማት ስራ ከአካባቢዎቹ ማግኘት የምንችለውንና የሚገባንን ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችለን አይሆንም::

ከዚሁ ቀጥሎ የሚሰመርበት ጉዳይ በነዚህ አካባቢዎች ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት ከፍተኛ ችግር እየሆነ ያለው ዋነኛ ጉዳይ የመሰረተ-ልማት አገልግሎትና የበቂ ሰራተኛ ጉልበት አቅርቦት ጉዳይ ነው:: በቂ የመንገድ የቴሌኮምዮኒኬሽንና የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት የለም:: አካባቢው በበሽታ በተለይም በወባ የሚጠቃ ሆኖ ሳለ ይህንኑ ለመቋቋም የሚያስችል የመሰረተ ጤና አገልግሎት የለም:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ በብዙዎቹ ቦታዎች ከፍተኛ የሰራተኛ ሰው ሃይል እጥረት አለ:: እነዚህ ችግሮች በፌዴራል መንግስትና በክልሎች የተቀናጀ ጥረት በተቻለ ፍጥነት መፈታት ያለባቸው ናቸው::

ፌዴራል መንግስት እነዚህን ክልሎች ለልማት ክፍት እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ቅድሚያ የሚሰጠውን የዋና መንገዶች ስራ መስራት አለበት:: በእቅድ ሆን ተብሎ እነዚህን አካባቢዎች



ለልማት ክፍት የማድረግ አላማ ያላቸው መንገዶች ተቀይሰው መገንባት አለባቸው:: የክልል መስተዳድሮች ይህን መሰረት በማድረግ በነሱ መሰራት ያለባቸውን መጋቢ መንገዶች መስራት አለባቸው:: የቴሌኮምዮኒኬሽን አገልግሎት ሁኔታው በፈቀደው መጠን መስፋፋት አለበት:: አዋጭ ሆኖ በተገኘበት አካባቢ ሁሉ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲኖር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት መደረግ አለበት:: እነዚህን የመሰረተ-ልማት ስራዎች በመስራት ስራ ላይ የተሰማሩት የፌዴራል መንግስት ተቋሞች ይህን ስራ የአጠቃላይ የመሰረተ ልማት ማስፋፋት ተልእኳቸው የማይነጠል አካል ማድረግና ከክልሎች ጋር በቅንጅት እንዲፈፀም ማድረግ መቻል አለባቸው:: የክልል መስተዳድሮች ይህንኑ መሰረት በማድረግ በነሱ መፈፀም ያለባቸውን የመሰረተ-ልማት ስራዎች (የመጋቢ መንገድ፣ ጤናና ትምህርት አገልግሎት የመጠጥ ውሃ ወዘተ.) በተቻለ ፍጥነት ማሟላት አለባቸው::

በሶስተኛ ደረጃ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ይህን አካባቢ በላቀ ደረጃ ማልማት የሚቻለው አርሶ አደሮችን በአካባቢዎቹ በስፋት በማስፈርና፣ የግል ባለሃብቶች ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎችና አግሮ-ኢንዱስትሪዎችን በቦታው በማስፋፋት እንዲሳተፉ በማድረግ፣ በሁለቱ ጣምራ ጥረት መሆኑን ነው:: አርሶ አደሮችን በስፋት በዚህ አካባቢ በምናሰፍርበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ተጨባጭ ተገልጋይ በሌለበት አካባቢ የመሰረተ-ልማት አገልግሎትን ለማስፋፋት ሲሞከር የሚያጋጥመውን ችግር ለመፍታት የሚያስችል እድል ይፈጠራል:: በተጨባጭ የሰፈሩትን ሰዎች መነሻ በማድረግ በጥቅም ላይ የሚውል የመሰረተ-ልማት አገልግሎት ለማስፋፋት ይቻላል:: በዚሁ መልክ የሚስፋፋው የመሰረተ-ልማት አገልግሎት ለግል ባለሃብቶች

ኢንቨስትመንትም የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል። በነዚህ አካባቢዎች አርሶ አደሮች በሰፊው በሚሰፍሩበት ወቅት አርሶ አደሮቹ በትርፍ ጊዜያቸው በጉልበት ስራ ላይ በመሰማራት በአካባቢው የሚያጋጥመውን ከፍተኛ የሰራተኛ ጉልበት እጥረት ለመቅረፍ ሊያግዙ ይችላሉ። ከዚህም በላይ ቦታው በሰፋሪዎች ሲሟሽ እነሱን ተከትሎ ወደአካባቢው ለመሰማራት የሚፈልግ ሰራተኛ የሰው ሃይል በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨምር መገመት ይቻላል። ስለሆነም ሰፈራንና የግል ባለሀብቶችን ኢንቨስትመንት በጣምራ ማስኬድ የመሰረተ-ልማትም ሆነ የሰራተኛ ጉልበት አገልግሎት እጥረቶችን በአስተማማኝ መንገድ ለማስወገድ ያስችላል። በመሆኑም ይህ አካሄድ የአካባቢው ልማት ስራ አንድ መሰረታዊ አቅጣጫ መሆን ይኖርበታል።

በመጨረሻም ምንም እንኳ በአሁኑ ወቅት ያሉት የኢንቨስትመንት ፖሊሲና የማትጊያ መመሪያዎች በአካባቢው ኢንቨስትመንትን ለማደፋፈር የሚያስችሉ ቢሆኑም ከዚህ አኳያ ሊሻሻሉ የሚችሉ ነገሮች ካሉ በየጊዜው እየፈተሹ ማስተካከል እንደሚያስፈልግ ሊሰመርበት ይገባል። በዚህ ደረጃ ሊመደቡ ከሚችሉት አካባቢዎች አንዳንዶቹ በክልሉ ትልቅ ግምት ያለው ሰፋሪ ህዝብ የሌላቸው ሊሆኑ እንደሚችሉና ይህም አካባቢዎቹን በተፈለገው ፍጥነት ለማልማት ችግር ሊፈጥር እንደሚችል መገመት ይቻላል። ስለሆነም በመጀመሪያ ደረጃ እንደዚህ አይነት ችግር የሌለባቸው አካባቢዎች ላይ በመወሰን ስራውን በአፋጣኝ መጀመርና ማስፈፀም፣ ከዚሁ የሚገኘውንም ልምድ መቀመር ያስፈልጋል። ከዚሁ ቀጥሎ ይህ ችግር ያለባቸው ክልሎች ከሌሎች ክልሎች ሰራተኛ ጉልበት ሊገኝ የሚችልበትን ሁኔታ በተሟላ መልኩ እንዲያጤኑትና በላኪውም በተቀባዩም ክልልና ህዝብ የተሟላና የተስተካከለ የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝ ማድረግ



ያስፈልጋል። እንደዚህ አይነት የጋራ ግንዛቤ ሳይያዝ ይህን ስራ በሰፊው ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትልና የአካባቢውን ልማት ሊያሰናክል የሚችል ስለሚሆን ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

## 5. በገበያ የሚመራ የግብርና ልማት እንዲኖር ማድረግ፣

### 5.1. በገበያ ያልተመራ የግብርና ልማት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ሊሆን አይችልም፣

የግብርና ምርት ብዙውን ጊዜ አምራቹ ራሱ ለራሱ ፍጆታ በሰፊው ሊጠቀምበት የሚችል ነው። አምራቹ የሚሸጠው ከዚህ የሚተርፈውን ነው። ይልቁንም በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከግብርና ምርታችን ውስጥ እጅግ የሚበዛው ክፍል በራሱ በአምራቹ ለግሉ ፍጆታ የሚውል ነው። ይህም ሆኖ አብዛኛው አርሶ አደር ለፍጆታ የሚያስፈልገውን ምርት በበቂ መጠን አያመርትም። በመሆኑም በመጀመሪያ ከሚመጣው የግብርና ምርት እድገት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሌላ ገበያ ሳያስፈልገው የአምራቹን የፍጆታ ፍላጎት በሚፈለገው መጠን ለማሟላት ሊውል የሚችል ነው። በዚህ መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ተጨማሪ የግብርና ምርት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይሆንም። ነገር ግን የአምራቹን ፍጆታ ማርካት ብቻውን ለፈጣንና ቀጣይ የግብርና እድገት መሰረት ሊሆን አይችልም።

የአርሶ አደሩ ኑሮ መሻሻል ካለበት ራሱ ሊያመርት የሚችለውን የምግብ ምርት በበቂ መጠን ማግኘቱ በቂ

www.abyssinialaw.com

አይሆንም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመጠንና በአይነት እየጨመረ የሚሄድ ራሱ ሊያመርታቸው የማይችል የፍጆታ ዕቃዎችና የተለያዩ አገልግሎቶችን ማግኘት አለበት፡፡ ከዚህም ባሻገር የምርት እንቅስቃሴውን የሚያሻሽሉ በመጠንና በአይነት እየጨመሩ የሚሄዱ የማምረቻ መሳሪያዎችና የተለያዩ ግብአቶች ያስፈልጉታል፡፡ ለራሱ ፍጆታ ከሚያስፈልገው በላይ የግብርና ምርት አምርቶ ይህንኑ ሸጦ ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን መግዛት ካልቻለ ኑሮው በቀጣይነት ሊሻሻል አይችልም፡፡ አርሶ አደሩ የግብርና ምርቱን በቀጣይነት እንዲያሻሽል ሊገፋፋው የሚችል ዋነኛው ነገርም እነዚህን ሸቀጦችና አገልግሎቶች የማግኘት ፍላጎትና ዕድል ነው፡፡ እነዚህን ሸቀጦችና አገልግሎቶች የማግኘት ፍላጎት ከሌለው አርሶ አደሩ ለራሱ ፍጆታ የሚያስፈልገውን ብቻ አምርቶ ይቆማል፡፡ ከዚያ በላይ የሚያመርበት ምንም አይነት ምክንያት አይኖርም፡፡ እነዚህን ሸቀጦችና አገልግሎቶች የማግኘት ፍላጎት ኖሮት እነሱን የማግኘቱ ዕድል በጣም ዝቅተኛ ከሆነም ምርቱን የማሳደግ ፍላጎቱ በተወሰነ ደረጃ ላይ ተገድቦ ይቀራል፡፡

በመሆኑም የግብርና ምርታችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ሊኖረው የሚችለው ከአምራቹ የፍጆታ ፍላጎት በላይ የሆነ ለገበያ የሚቀርብ ምርት በማምረት ላይ ሲመሰረት ነው፡፡ የአርሶአደሩ ኑሮ በቀጣይነት መሻሻል የሚችለው በዚህ ደረጃ አምርቶ ምርቱን በገበያ ሸጦ በመጠንና በአይነት እየጨመሩ የሚሄዱ ሸቀጦችና አገልግሎቶችን መግዛት ሲችል ነው፡፡ የግብርና ልማት መሰረታዊ አላማም አርሶ አደሩን እነዚህን ሸቀጦችና አገልግሎቶች በብዛት መግዛትና መጠቀም የሚችልበት ደረጃ ላይ ማድረስ ነው፡፡ አርሶ አደሩ እነዚህን የማግኘት ከፍተኛ ፍላጎትና ዕድል ከሌለው በስተቀር በቀጣይነት



ምርቱን ለማሳደግ አይንቀሳቀስም፡፡ የግብርና ልማታችን በገበያ የሚመራ የግብርና ልማት ካልሆነ በስተቀር ፈጣንና ቀጣይነት አይኖረውም የምንለውም ለዚሁ ነው፡፡

አርሶ አደሩ ከራሱ የፍጆታ ፍላጎት በላይ የሆነውን የግብርና ምርት መሸጥ ካለበት በመጀመሪያ ደረጃ መዳሰስ ያለበት የአካባቢው፣ የአገር ውስጥ ገበያው ነው፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የስራ ክፍፍል እየተስፋፋ ሲሄድ አርሶ አደሩም በአካባቢው የማይመረት የግብርና ምርት መሸመት ስለሚጀምር የአገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ገበያ በከፍተኛ ደረጃ ሊጨምር ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ እስኪሆን ድረስ ረጅም ጊዜ እንደሚጠይቅ መታወቅ ይገባዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትና ከአጭርና መካከለኛ ጊዜም አኳያ በአርሶ አደሮች መካከል የሚኖረው የግብርና ምርቶች ግብይት በጣም ውሱን መሆኑ አይቀርም፡፡ ከአጭርና መካከለኛ ጊዜ አኳያ ዋናዎቹ ገበያዎች የአገራችን ከተሞች መሆናቸው አይቀርም፡፡

የከተማው ህዝብ ለምግብ የሚያስፈልገውን የግብርና ምርት ከሞላ ጎደል በሙሉ የሚያገኘው ከገጠር ነው፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በከተማ የሚኖረው ህዝብ ከአገሪቱ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት ከ15% የማይበልጥ ነው፡፡ የከተማው ህዝብ ቁጥርና የኑሮ ደረጃ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የግብርና ምርት ፍላጎቱ በተነፃፃሪ እየጨመረ እንደሚሄድ መገመት ይቻላል፡፡ የግብርና ምርቶችን በጥሬ እቃነት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች እየተስፋፉ እንደሚሄዱም ግልፅ ነው፡፡ ይሁንና የከተሞቻችን ገበያ በፈለገው ፍጥነት ቢያድግም መነሻው በጣም ጠባብ በመሆኑ ለፈጣንና ቀጣይ የግብርና ልማት በቂ መሰረት ሊሆን አይችልም፡፡ ይህንኑ ገበያ በተቻለ ፍጥነት ማስፋትና ለግብርና ልማታችን መጠቀም

www.abyssinialaw.com

የሚገባን ቢሆንም ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ገበያዎችን ማፈላለግና መጠቀም አለብን::

እንደዚህ አይነቱ ሰፊ የገበያ ዕድል የሚገኘው የውጭ ገበያዎችን በመዳሰስ ነው:: ይህ ገበያ በአገራችን ሊመረት ከሚችለው የግብርና ምርት አኳያ ሲታይ በጣም ሰፊና ምርታችንን ሊውጥ የሚችል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: ይህንን ገበያ በብቃት ሰብረን መግባት ከቻልን ለግብርና ምርታችን ሰፊና አስተማማኝ ገበያ በማግኘት የማያቋርጥና ፈጣን እድገት ለማረጋገጥ ያስችለናል:: የግብርና ምርቶችን በመሸጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ያስችለናል:: የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ለግብርና ልማት ለራሱም ተፈላጊ ሲሆን ከዚያም አልፎ የኢንዱስትሪና ሌሎች ዘርፎችን እድገት ለማፋጠን በፍፁም መተኪያ የማይገኝለት ይሆናል:: የግብርና ልማት ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ልማትም በቂ አስተዋፅኦ ለማበርከትና አመራር ለመስጠት ያስችለዋል:: በመሆኑም የግብርና ምርታችን የአለም ገበያን ሰብሮ መግባትን በመሰረታዊ መመሪያነት ይዞ የሚንቀሳቀስ መሆን ይኖርበታል:: የግብርና ልማታችን በገበያ የሚመራ መሆን አለበት፣ በገበያ በአጠቃላይ ብቻ ሳይሆን በተለይም የአለም ገበያን ሰብሮ መግባትን እንደአላማ የወሰደ መሆን አለበት የምንለውም ለዚሁ ነው:: ከዚህ ውጭ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት ማረጋገጥ በፍፁም የማይታሰብ ስለሆነ ነው::



## 5.2. በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን የሚያመርት የግብርና ዘርፍ መገንባት አለብን፣

በአጠቃላይ በገበያ በተለይ ደግሞ በአለም ገበያ የሚመራ የግብርና ልማት ይኖረናል፣ ከዚህ ውጭ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት ማበብም አይቻልም ስንል እንዲሁ አጠቃላይ ንድፈ-ሃሳባዊ ነገር ማስቀመጣችን አይደለም:: በተጨባጭ የዕለት ተዕለት የግብርና ምርት እንቅስቃሴያችንን የሚመራና መምራትም ያለበት ነገር ማስቀመጣችን ነው:: እያንዳንዷ የግብርና ምርትን የማሳደግ እንቅስቃሴያችን በገበያ ተፈላጊነት ያለውና በጥራትም ሆነ በዋጋ በገበያ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ለማምረት የምታስችለን መሆኗ እየተመዘነ መፈፀም አለባት ማለት ነው::

በገበያ ተፈላጊነት ያለው ምርት ማምረት አለብን ስንል በአካሄዳችን ላይ መሰረታዊ ትርጉም ያለው ለውጥ መምጣት አለብን ማለታችን ነው:: ማምረት የምንችለውን ምርት ሁሉ ካመረትን በኋላ ትርፍ ሲገኝ ገበያ የማፈላለግ አቅጣጫ መከተል አለብን ማለት አይደለም:: ይህ አሁንም ካለው አካሄድ ያልተለየና በገበያ የሚመራ ልማት ሊከተለው የማይችልና የማይገባ አቅጣጫ ነው:: ገበያ መፈለግ ያለበት ካመረትን በኋላ ሳይሆን ከማምረታችን በፊትና ምን እንደምናመርት በምንወስንበት ወቅት ነው:: ምን እንደምናመርት ስንወስን በመጀመሪያ ደረጃ ልናመርት ከምንችላቸው ምርቶች ውስጥ ሰፊ ገበያና ተፈላጊነት ያለው ምርት ምን እንደሆነ በጥንቃቄ አጥንተን መወሰን አለብን:: በዚህ መልኩ ካጠናን በኋላ ልናመርት ከምንችላቸው ምርቶች ውስጥ ሰፊ ገበያና ተፈላጊነት ያላቸውን መርጠን ማምረት መጀመር አለብን::

www.abyssinialaw.com

በገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች ብቻ በሚገባ እየለዩና እያጠኑ የማምረት አካሄድ አንድ ጊዜ ከተሰራ በኋላ ያለ ለውጥ የሚቀጥል ነገር አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ የአለም ገበያ በየጊዜው ተለዋዋጭ ነው። በአንድ ወቅት ተፈላጊነት የነበረው ምርት ሌላ ጊዜ ተፈላጊነቱ ሊቀንስ ወይም ሊጠፋ ይችላል። ጥሩ ዋጋ ያስገኝ የነበረው ዋጋው ተከስክሶ፣ ደካማ የነበረው ዋጋው ሊጨምር ይችላል። በገበያ የሚመራ የግብርና ልማት ማለት እነዚህን ለውጦች በቅርብ እየተከታተሉ በገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች ከገበያው ሁኔታ ጋር እየቀያየሩ ማምረት ማለት ነው። ከዚህም ባሻገር የአርሶ አደሩ ገቢ በቀጣይነት ማደግ ካለበት ምርታማነቱን መጨመር ብቻ ሳይሆን የሚያመርታቸውን ምርቶች ራሳቸውን ዝቅተኛ ዋጋ ካላቸው ከፍተኛ ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች በቀጣይነት ማሸጋገር ያስፈልጋል። ይህም የገበያውን ሁኔታ በቅርብ እየተከታተሉ ይህን አላማ የሚያሟሉ ምርቶችን እየመረጡ ማምረትን ይጠይቃል።

ለፈጣንና ቀጣይነት ላለው የግብርና እድገታችን አማራጭ የማይገኝለትን በገበያ የሚመራ ልማት ከመከተል ይልቅ አምርተን ሲተርፈን ገበያ የማፈላለጉ አካሄድ መፍትሄ ወደሌለው ቀውስ ብቻ ያመራናል። ስለሆነም ወደ ልማት የማያመራውን አቅጣጫ ትተን ከማምረታችን በፊት በየጊዜው በገበያ ተፈላጊነት ያለውን ምርት ለይተን ይህን ወደማምረት ተግባር የመግባትን አሰራር መከተል እንዳለብን ግልፅ ነው። ነገር ግን ይህ ብቻም በቂ አይደለም። የምናመርተው ምርት በገበያ በዋጋ ተወዳድሮ ማሸነፍ ካልቻለ ተመርቶ ከጥቅም ውጭ መሆኑና አምራቹም ሆነ የአገሪቱ ኢኮኖሚ መክሰራቸው



አይቀርም። ስለሆነም በዋጋ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችለንን ምርት መምረጥና ይህንኑ በዋጋ ተወዳዳሪ ለመሆን በሚያስችለን አኳኋን ማምረት መቻል አለብን። ከዚህ ውጭ በገበያ የሚመራ የግብርና ልማት ሊኖረን አይችልም።

በገበያ በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት የማምረቱ ስራ መጀመር ያለበት የምርቱን አይነት በመምረጥ ነው። ምን ማምረት እንዳለብን ስንመርጥ በገበያ ተፈላጊነት ያለውን ምርት ብቻ ሳይሆን በገበያ ተፈላጊነት ካላቸው ምርቶች ውስጥ እኛ በዋጋ ተወዳዳሪ በሆነ አኳኋን ልናመርት የምንችለውን ነው መምረጥ ያለብን። በገበያ ተፈላጊነት አለው ስለተባለ ብቻ በዋጋ ተወዳደሪ በምንሆንበት አኳኋን ልናመርት የምንችለውንና የማንችለውን አግበስብሰን እናምርት ብንል ከኪሳራ በስተቀር የምናገኘው ቀጣይነት ያለው ፈጣን ልማት አይኖርም። በዋጋ ተወዳዳሪ በሆነ አኳኋን ልናመርት የምንችለውን ምርት ከመረጥንም በኋላ ይህንኑ ምርት በከፍተኛ ምርታማነት በዝቅተኛ ዋጋ ለማምረት ያለማቋረጥ መጣር አለብን።

አንድ አርሶ አደር አንድን ተጨባጭ ምርት ለማምረት ከራሱ ጉልበት በተጨማሪ የተለያዩ ግብአቶችንና የእርሻ መሳሪያዎችን መጠቀሙ አይቀርም። እነዚህን ግብአቶች በላቀ ደረጃ ተጠቅሞ፣ ምንም አይነት ብክነት በማያስከትል አኳኋን የላቀ መጠን ያለው ምርት ካመረተ የሚያገኘው ትርፍ ከፍተኛ ይሆናል። በዝቅተኛ ወጪ ብዙ ምርት አምርቶ በመጠነኛ ዋጋ ቢሸጠውም ወጪው ዝቅተኛ ጠቅላላ ገቢው ከፍተኛ ስለሚሆን ትርፉ ከፍተኛ ይሆናል። በመሆኑም ኑሮውና የአገሪቱ እድገት ይሻሻላል። በቀጣይነት ወጪውን ለመቀነስና ምርታማነቱን ለመጨመር የማያቋርጥ ጥረት ካላደረገ ወጪው ከፍተኛ ገቢው

www.abyssinialaw.com

ደግሞ ዝቅተኛ እየሆነ ገቢው በዚያው መጠን መቀነሱ በሂደትም ምርቱን በዋጋ ተወዳዳሪ ሆኖ መሸጥ የማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱ አይቀርም። ስለሆነም ወጪን መቀነስና ምርታማነትን መጨመር ያለማቋረጥ በእያንዳንዱ አርሶ አደር ደረጃም ይሁን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚፈፀም የማያቋርጥ የቀን ተቀን ስራ መሆን አለበት። ከዚህ ውጪ በገበያ የሚመራ የግብርና ልማትም ሆነ ቀጣይነት ያለው ፈጣን የግብርና እድገት ሊታሰብ የሚችል አይሆንም።

እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባ ሌላም ጉዳይ አለ። ይህም የድጎማ አማራጭ በዚህም መስክ እንደመፍትሄ ሊቀርብ የሚችል ያለመሆኑ ጉዳይ ነው። ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ በኛ አገር ሁኔታ የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበት፣ ይህንኑ በሰፊው የሚጠቀም የልማት ስትራተጅ በመከተል ካልሆነ በስተቀር በድጎማ ኑሮውን ማሻሻል እንደአማራጭ ሊታሰብም የሚችል ነገር እንዳልሆነና ቢፈለግም እንኳንስና ለድጎማ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሰረተ-ልማት አውታሮችን ለማዳረስም ገንዘብ የሌለን በመሆኑ የድጎማ አሰራር የሚያዋጣ እንዳልሆነ ገልፀን ነበር። የግብርና ልማታችን ሊፋጠን የሚችለው ያለድጎማ በገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ በመገኘት ብቻ ነው። መንግስት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ በሚያደርገው ጥረት ወጪዎችን በከፊል ራሱ የሚሸፍንበት በተወሰነ ደረጃ እንደ ድጎማ ሊወሰድ የሚችል ነገር ያለ ቢሆንም ሌላው ራሱ ያለ ድጎማ በገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ በመገኘት ብቻ ሊፈፀም የሚችል ነው። ለዚህም ነው በገበያ በዋጋም ሆነ በጥራት ተወዳዳሪ በመሆን መሸጥን እንደብቸኛ የልማት አማራጭ መውሰድና ድጎማን ከሂሳብ ውጭ ማድረግ አስፈላጊ የሚሆነው።



ይሁንና በተለይም የአለም ገበያን ሰብሮ መግባትን በተመለከተ በገበያ ተፈላጊነት ያለው ምርት ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ ማምረት ብቻውን በቂ አይሆንም። የጥራት ጉዳይ በተለይም የግብርና ምርትን በሚመለከት ወሳኝነት ያለው ጉዳይ ነው። በርግጥ አርሶ አደሩ ለራሱ ፍጆታ የሚያመርተውን ምርት በተመለከተ የጥራትና የዋጋ ጉዳይ ይህን ያህል ቁልፍ ላይሆን ይችላል። በአገር ውስጥ ገበያ ላይ በሚሸጠው ምርት ረገድ ዋጋ ቁልፍ ቢሆንም ጥራት የአለም ገበያን ያህል ተፈላጊ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን ምርታችን ለአርሶ አደሩ ፍጆታ ወይም ለአገር ውስጥ ገበያ ብቻ የሚቀርብ አይደለም። መጠኑ እየጨመረ የሚሄድ ምርት ለአለም ገበያ ማቅረብ ካልቻልን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት አይኖረንም። ይህን ለማድረግ ጥራትን ማረጋገጥ አለብን።

ጥራት የማረጋገጡ ጉዳይ ከምናመርተው ምርት ምርጫ ነው መጀመር ያለበት። ምን ማምረት እንዳለብን ስንወስን በአለም ገበያ ተፈላጊነት ያለውንና በተወዳዳሪ ዋጋ ልናመርተው የምንችለውን ብቻ ሳይሆን በተፈላጊው ጥራት ልናመርተው የምንችለውንም ነው መምረጥ ያለብን። በዚህ መልኩ ምርቱን በጥንቃቄ ከመረጥን በኋላ አርሶ አደሩ በጥራት እንዲያመርተው ማድረግ መቻል አለብን። የግብርና ምርት ጥራት አደጋ ለይ የሚወድቀው ብዙውን ጊዜ ምርቱ በሚመረትበት ወቅት ሳይሆን ከተመረተ በኋላ በመሰብሰብ፣ ደረጃውን በመለየትና አሽጎ በማጓጓዝ ላይ ነው። ስለሆነም የምርታችን የጥራት አጠባበቅ ስራ ምን ማምረት እንዳለብን በመምረጥና ይህንኑ በማምረት ጉዳይ

www.abyssinialaw.com

ላይ ሳይወሰን የድህረ-ምርት እንቅስቃሴያችንንና ቴክኖሎጂዎችን የሚጨምር መሆን አለበት፡፡

በገበያ በተለይም በአለም ገበያ የሚመራን የግብርና ልማት ለማስፈፀም በገበያ ተፈላጊነት ያለው፣ በተወዳዳሪ ዋጋና ጥራት ልናመርት የምንችለውን ምርት መርጠን ማምረት፣ የማምረቻ ወጪያችንን በመቀነስና ምርታማነታችንን በማሻሻል፣ በምርት ተግባር ላይም ሆነ በድህረ-ምርት እንቅስቃሴያችን የምርታችንን ጥራት ለመጠበቅ መንቀሳቀስ ይኖርብናል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለን የግብርና እንቅስቃሴ በመሰረቱ በገበያ ላይ ሳይሆን የአርሶ አደሩን ፍጆታ በመሟላት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የአርሶ አደሩን የፍጆታ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል በቂ ምርት ማምረት ሳንችል በገበያ ወደሚመራ የግብርና ልማት መሸጋገር የሚቻል ነገርም አይደለም፡፡ ይሁንና በአሁኑ ወቅት በገበያ በተለይም በአለም ገበያ የሚመሩ የግብርና ምርቶች እንዳሉን ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ ያህል የቡና ምርታችን በዚሁ ክልል የሚታይ ነው፡፡ ስለሆነም በዋናነት በአምራቹ ፍጆታ ላይ የተመሰረተ ነገር ግን በገበያ የሚመራ ገፅታ ያለውን ግብርና መሰረት አድርገን በገበያ ወደሚመራ የግብርና ዘርፍ እንዴት መሸጋገር እንደሚቻል በውል ለይተን ማስቀመጥ አለብን፡፡

ይህን በተመለከተ በመጀመሪያ ሊሰመርበት የሚገባው ነገር ይህ ጉዳይ በመሰረቱ የሽግግር ጉዳይ እንደሆነና በአጭር ጊዜ የሚፈፀም እንዳልሆነ፣ ተሟልቶ እስኪፈፀም ድረስ በገበያ የሚመራውንና በዚሁ የማይመራውን ክፍል አጣምረን መቆየታችን እንደማይቀር ነው፡፡ ጉዳዩ ጊዜ መጠየቁ የማይቀር የሽግግር ሂደት ቢሆንም በተቻለ ፍጥነት በገበያ ወደሚመራ የግብርና እንቅስቃሴ መሸጋገር መቻላችን የልማታችንን



ቀጣይነትና ፈጣንነት ለማረጋገጥ መሰረታዊ ተፈላጊነት ያለው ጉዳይ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ የሽግግር ጉዳይ ነው ብለን እግራችንን ከጎተትን በጣም አደገኛ ይሆናል፡፡ ሽግግሩን ለማፋጠን በአሁኑ ወቅት በገበያ እየተመረቱ ያሉትን ምርቶች በማጠናከር መጀመርና ከዚህ በኋላ ደረጃ በደረጃ ሌሎችንም ምርቶች እንዲሸፍን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ተምረው የግብርና ስልጠና ያገኙት አርሶ አደሮች ገና ከመጀመሪያው በገበያ የሚመራ የልማት ስራ እንዲሰሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ግብርናችንን በገበያ ወደሚመራ ለፈጣንና ቀጣይ እድገት ሰፊ ዕድል ወዳለው ግብርና ለማሸጋገር የአርሶ አደሩ ጥረት ተፈላጊ ቢሆንም መንግስትና የኤክስቴንሽን ስርአታችን ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በአርሶ አደሩ የሚመረተውን ምርት ከመምረጥ ጀምሮ እስከ ድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ ድረስ ያለውን ሁሉ በፖኬጅ አዘጋጅቶ የሚያሰራጨው የምርምርና የኤክስቴንሽን ስርአታችን ነው፡፡ አርሶ አደሩን የሚያሰለጥነውና የምክር አገልግሎት የሚሰጠው ይኸው ስርአት ነው፡፡ ተዘጋጅቶ ለአርሶ አደሩ የሚቀርበው ፖኬጅ ከላይ በዘረዘርናቸው መርሆዎች ጭምር ተመዝኖ በጥንቃቄ የተመረጠ ከሆነ፣ ለአርሶ አደሩ ባለማቋረጥ የሚቀርበው የተሻሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ ይህንኑ በተፈለገው ጥራትና ዋጋ ለማምረት የሚያስችል ከሆነና በዚሁ ላይ በቂ የምክርና የስልጠና አገልግሎት ከተሰጠ አርሶ አደሩ ወደዚህ ስርአት ለመሸጋገር የሚከብደው አይሆንም፡፡ ወደዚህ ስርአት መሸጋገር ማለት በቀጥታ ገቢውን ማሳደግ ማለት ስለሚሆን ከራሱ ተግባራዊ ተሞክሮ ተነስቶ ሊቀበለውና ሊፈፅመው የሚችል ነው፡፡ ስለሆነም ዋናው ጉዳይ የምርምርና ኤክስቴንሽን ስርአቱ በገበያ በተለይም በአለም ገበያ የሚመራ

www.abyssinialaw.com

የግብርና ልማት ለማምጣት የሚያስችል አመለካከትና ብቃት እንዲኖረው ማድረግ ነው::

## 5.3. የግብርና የግብይት ስርአትን በቀጣይነት ማሻሻል፣

በገበያ ተፈላጊነት ያለውን ምርት መርጠን በገበያ ተወዳዳሪ ሊሆን በሚችል ዋጋና ጥራት አምርተን ስናበቃ በወቅቱ ወደገበያ ለማድረስ የሚያስችለን የግብይት ስርአት ከሌለ የተሰራው ስራ ሁሉ መና ሆኖ መቅረቱ የግድ ነው:: ምርታችን ለገበያ የሚቀርብበት ዋጋ የትራንስፖርትና የግብይት ወጪውን በመጨመር ነው:: ይህ ስርአት ቀልጣፋና በዋጋም ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችለን ካልሆነ ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ አምርተን እያለ ቀልጣፋና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ የግብይት ስርአት ስለሌለን ያመረትነው ምርት ዋጋ ከመጠን በላይ ጨምሮ ሳንሸጥ ልንቀር ወይም አርሶ አደሩ ከሽያጩ የሚያገኘው ገቢ በጣም አነስተኛ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል:: ምርታችንን በተፈላጊው ጥራት አምርተንና አዘጋጅተን ስናበቃ የግብይት ስርአታችን ይህንኑ ጥራት ጠብቀን ወደሚፈለገው ቦታ ለማድረስ ካላስቻለን ታጥቦ ጭቃ መሆንና መክሰር መምጣቱ አይቀርም:: ስለሆነም ቀልጣፋ፣ የምርታችንን ጥራትና ተወዳዳሪነት ለመጠበቅ የሚያስችለን የግብይት ስርአት መፍጠርና ይህንኑ በቀጣይነት ማሻሻል ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት ከማረጋገጥ አኳያ በፍፁም አማራጭ የሌለው ስራ ይሆናል::

### (ሀ) የደረጃ ምደባ ስርአት መፍጠር፣

ምርታችን ጥራቱ ተጠብቆ በቀልጣፋ የግብይት ስርአት ወደተጠቃሚው እንዲደርስ ለማድረግ የደረጃ ምደባና ጥራቱ



የተጠበቀ የአለካክ ስርአት መኖርና መጠናከር ቁልፍ ተፈላጊነት አለው:: አንድ ምርት ተፈላጊውን ጥራትና ደረጃ የጠበቀ እንደሆነ ለማረጋገጥ የሚቻለው በውል ተለይቶ የሚታወቅ ደረጃ ሲቀመጥለት ነው:: አምራቹም ደረጃውን የጠበቀ ምርት ሊያመርት የሚችለው የጥራት ደረጃዎች በውል ተለይተውና ተዘርዝረው ሲቀርቡለት ነው:: ሸማቹም ተፈላጊው ጥራት ያለው ምርት እየገዛ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚችለው የጥራት ደረጃዎች ተለይተው ሲታወቁ ነው:: ደረጃዎችን ማውጣትና አምራቹም ሸማቹም እንዲያውቃቸው ማድረግ ከዚህ ጋር በተያያዘም ትክክለኛ የአለካክ ስርአትና በዚህ ላይ የተመሰረቱ መለኪያ መሳሪያዎች እንዲስፋፉ ጥረት ማድረግ ከዚህ አኳያ ሲታይ በጣም ተፈላጊ ይሆናል::

የግብርና ምርቶች ደረጃዎችን ለመለየት ሁለት አማራጮች አሉን:: አንደኛው አማራጭ እኛው ራሳችን ደረጃዎችን መድበን ለአምራቹም ለተጠቃሚውም ማሳወቅ ነው:: በተለይም በአገራችን ብቻ የሚመረቱ ምርቶች ሲሆኑ (ለምሳሌ ጤፍ) ይህ አማራጭ ብቸኛ አማራጭ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: ሌላው አማራጭ በአለም አቀፍ ደረጃ እውቀት ያላቸው ተቋሞች የሚያወጧቸውን ደረጃዎች ተቀብለን ይህንኑ ለሸማቹም ለአምራቹም ማሳወቅ ነው:: ምርቶቻችን የአለም ገበያን ሰብረው እንዲገቡ ከተፈለገ የጥራት መመዘኛቸው አለም አቀፋዊ እውቅና ያገኘው መመዘኛ እንጂ እኛ የምናወጣው መመዘኛ ሊሆን አይችልም:: ስለሆነም የተሻለው አማራጭ እነዚህን የደረጃ ምደባዎች መውረስና በአገራችን ተግባራዊ ማድረግ ነው:: ደረጃዎች ማውጣትና መመደብ ከፍተኛ ጊዜና የሞያተኛ አቅም የሚጠይቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሲታይ አለም አቀፋዊ የደረጃ ምደባ ከሌላቸው ምርቶች ውጪ ሌሎቹን በአለም አቀፋዊ

ደረጃዎች መሰረት መመደብ ስራውን በፍጥነት ለመፈፀም የሚያስችል አማራጭ ነው፡፡

የግብርና ምርቶቻችንን ደረጃ መለየት የሚያስፈልገን ምርቶቻችንን በተፈለገው ጥራት አምርተን ለሸማቾች ለማቅረብ ሲባል ብቻ አይደለም፡፡ የግብይት ስራውን ራሱን ለማቀላጠፍም እጅግ በጣም ተፈላጊ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ደረጃቸው ተለይተው ያልታወቁ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የግብርና ምርቶች ይመረታሉ፡፡ ጤፍን እንኳ ብንወስድ የጤፍ አይነትና ደረጃ እንደየአካባቢው ብቻ ሳይሆን እንደ እያንዳንዱ አርሶ አደር ሁኔታ ይለያያል፡፡ ሸማቾች ከእያንዳንዱ አርሶ አደር የሚሰባሰበውን ምርት መፈተሽ ይኖርባቸዋል፡፡ በየግብይት ምዕራፉ ይህ ሲደረግ የግብይት ስርአቱን በጣም ቀርፋፋና ውድ እንደሚያደርገው አያጠራጥርም፡፡ በተጨማሪም በውል ተለይተው የሚታወቁ የጤፍ አይነቶችና ደረጃዎች ስለሌሉ ደረጃቸውን ለመወሰን በጣም አስቸጋሪና ለውጣ ውረድ የተጋለጠ ይሆናል፡፡ ደረጃቸው በውል ተለይቶ የማይታወቅና እጅግ በጣም ብዙ አይነት ያላቸውን ምርቶች እያመረቱ ቀልጣፋ የገጠር የግብይት ስርአት መፍጠር አይቻልም፡፡

ደረጃቸው በውል ተለይቶ የሚታወቅ ውሱን አይነቶች ቢኖሩ ግን ስራውን በከፍተኛ ደረጃ ያቃልለዋል፡፡ ለምሳሌ ሶስት ወይም አራት የጤፍ አይነቶችና ደረጃዎች ቢመደቡና ጤፍ የሚያመርተው አርሶ አደር እነዚህን ብቻ ቢያመርት፣ እያንዳንዱ አርሶ አደርም ሆነ ሸማች የምርቱን ጥራትና ደረጃ ለመቆጣጠርና ለመመደብ በጣም ይቀልለታል፡፡ የእያንዳንዱ ደረጃ የገበያ ዋጋ የሚታወቅ ስለሚሆንም የገበያ ንትርክና ውጣ ውረድ ቀርቶ በገበያ በሚታወቀው ዋጋ ቶሎ ገዝቶና ሸጦ



መለያየት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የምርቶቹን ደረጃ በገበያው ተአማኒነት ያለው ወይም ያላቸው ተቋሞች አረጋግጠው የሚያሽጉበትና ለገበያ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ቢፈጠር ስራው እጅግ በጣም ቀልጣፋ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ አምራች ሻጭም ደረጃ መዳቢም፣ እያንዳንዱ ሸማች ገዥም ደረጃ መዳቢም እየሆነ የሚፈጠረው የጊዜ መጓተትና የዋጋ መናር ሊወገድ ይችላል፡፡ ለምሳሌ የህብረት ስራ ማህበራት ዮኒየኖች የአርሶ አደሩን ምርት አሰባስበው ደረጃውን አረጋግጠውና መድበው ለገበያ ቢያቀርቡት ሻጩም ገዥውም ይህን ምደባ ተቀብሎ በመግዛትና በመሸጥ ስራ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ሊደረግ ይችላል፡፡ መንግስትም የደረጃ ምደባ ስራ የሚሰሩ ተቋሞች በገበያው ተአማኒነት እንዲያገኙ ለማድረግና ሲያጭበረብሩ ከተገኙ በአፋጣኝና በአጥጋቢ ደረጃ ለማስተካከል የሚያስችለው ስርአት መዘርጋት አለበት፡፡

የደረጃ ምደባና ማረጋገጫ ስርአት መፍጠርና ማሻሻል ቀልጣፋ የግብርና ግብይት ስርአት ለመፍጠር እጅግ ተፈላጊ የመሆኑን ያህል ተግባራዊ ማድረጉ ግን ይህን ያህል ቀላል ስራ አይሆንም፡፡ ረጅም ጊዜና ከፍተኛ ርብርብ የሚጠይቅ ነው፡፡ የደረጃዎች ምደባ ስራ ተሰርቶ ቢያንስ ዋና ዋና ምርቶቻችን በውል ተለይቶ የሚታወቅ ደረጃ ሊቀመጥላቸውና አምራቹና ሸማቹ እንዲያውቃቸው ሊደረግ ይገባል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚሰራው ስራ በአብዛኛው አለም አቀፋዊ ደረጃዎችን መቅዳት ነው ቢባል እንኳ ይህ ስራ ራሱ ከፍተኛ ጊዜና የሰለጠነ የሰው ሃይል የሚጠይቅ ነው፡፡

የምርቶቻችን በተለይም የዋና ዋና ምርቶቻችን ደረጃ ተለይቶ ከታወቀ በኋላም እነዚህን የምርት አይነቶችና ደረጃዎች

አባዝቶ ወደአርሶ አደሩ ለማድረስ፣ አርሶ አደሩ ደረጃቸው የተለየላቸውን ምርቶች በማምረት ስራ ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ፣ የምርታችን ጥራት በምርት ሂደትም ሆነ በድህረ-ምርት እንቅስቃሴ የተጠበቀ እንዲሆን በቂ ስልጠና መስጠት ከፍተኛ ጊዜና ጥረት የሚጠይቅ ነው። የምርምርና ስርፀት ተቋሞቻችን የዚህን ጉዳይ አስፈላጊነት ተገንዝበው ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አቅም ገንብተው በአጭር ታጥቀው መረባረብ ይኖርባቸዋል።

የምርቶችን ጥራት ፈትሾ ደረጃቸውን የመመደብ ጉዳይ ቀላል ስራ አይደለም። ለዚህ ስራ ተብሎ በቂ ስልጠና ያገኘ የሰው ሃይል ያስፈልጋል። የህብረት ስራ ማህበራት ዩኒየኖችና ሌሎችም ተቋሞች ተደራጅተውና ተጠናክረው ደረጃ ለመመደብ የሚያስችላቸው አቅም ገንብተው ስራውን መስራት የሚችሉበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ጥረትና ጊዜ መጠየቃቸው አይቀርም። እነዚህ በደረጃ ምደባ ላይ ተሳታፊ የሆኑ ተቋሞች በገበያው ተአማኒነት እንዲያገኙ ለማድረግና መንግስት በዚህ በኩል መጫወት የሚገባውን ሚና ለመጫወት የሚያስችለው አቅምና ስርአት መፍጠርም የሚጠይቀው ጥረት ቀላል አይደለም። ይሁንና ይህ ስራ ምንም ያህል ከባድና አድካሚ ቢሆንም በአግባቡ ካልተሰራ በስተቀር ቀልጣፋ የግብርና ግብይት ስርአት ሊኖረን ስለማይችል በቂ ትኩረት ሰጥቶ ከመረባረብና ለማቀላጠፍ ከመጣጣር በስተቀር ሌላ አማራጭ የለም።

በሌላ በኩል የምርቶችን ጥራት ፈትሾ ደረጃቸውን ለመመደብ ተገቢ ርምጃዎችን የመውሰዱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ስራ ያለንን ሰፊ ስነ-ህይወታዊ ሃብት ለመጠበቅና ለማልማት ከሚያስችል እንቅስቃሴ ጋር ተቀናጅቶ መፈፀም



ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የምንከተለው አቅጣጫ አገራችን ያላትን ስነ-ህይወታዊ ሃብት ሁሉ በአግባቡ ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለማልማት የሚያስችል አቅም እየፈጠርን ካለን ስነ-ህይወታዊ ሃብት ውስጥ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡትን ለይተን የማልማትና ሌሎችን ደግሞ በጥንቃቄ የማስቀመጥ ሊሆን ይገባዋል። በመሆኑም ባለን ስነ-ህይወታዊ ሃብት ላይ የማያቋርጥ ምርምር እያካሄድን የምናገኘውን ውጤት በአግባቡ በመጠበቅና በማልማት ለአገራችን እድገትና ለህዝባችን ተጠቃሚነት እናውለዋለን። የሚካሄደው ምርምር በአንድ የዝርያ አይነት ላይ ብቻ የማይታጠር፣ በብዙ የሰብል አይነቶች ላይ የሚያተኩርና በእያንዳንዱ የሰብል አይነትም የተለያዩ ከፍተኛ ምርት የሚያስገኙ ዝርያዎች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የደረጃ ምደባ የሚካሄድላቸው ምርቶችም የአገራችን ስነ-ህይወታዊ ሃብት መጠበቅና መዳበሩን በሚያረጋግጥ አኳኋን የሚፈፀም ይሆናል።

## (ለ) የገበያ መረጃ አቅርቦትን ማሻሻል፣

በማንኛውም የግብይት ስርአት የተሟላ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ የማግኘት ጉዳይ እጅግ መሰረታዊ የሆነ ጉዳይ ነው። ቀልጣፋና የዳበረ የግብርና ግብይት ስርአት ባላቸው አገሮች ምን አይነት ምርት በየትኛው ቦታ በምን ያህል ዋጋ እንደሚሸጥ የሚገልፅ የተሟላ ደረጃ ይቀርባል። የዋጋ ውጣ ውረዱን እየተከታተለ በየደቂቃው የዋጋ ለውጡን መረጃ የሚያቀብል ስርአትም ይኖራል። ከዚያም ባሻገር የዋና ዋና ምርቶች የወደፊት የዋጋ ትንበያም ይቀርባል። በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ የሚተነበየው ዋጋና በተግባር የሚታየው ዋጋ መለያየታቸው ባይቀርም አጠቃላይ አዝማሚያው የመጨመር ወይ የመቀነስ መሆኑን በትክክል ለማመላከት ይችላል። ከዚህም

www.abyssinialaw.com

ባሻገር ዋና ዋና የግብርና ምርቶች በአገር አቀፍ ደረጃ በሚታወቁ ውሱን ገበያዎች ወይም የሸቀጥ ልውውጥ ማዕከላት (ኮሞዲቲ ኤክስቼንጅ ማርኬትስ) ስለሚፈፀም መረጃውን በተሟላ ሁኔታ ለማግኘት ከማገዙም በላይ ሸቀጡ ከተመረተበት ቦታ ሳይነቃነቅ የጥራት ደረጃውን፣ ያለበትን ቦታና ዋጋውን በመግለፅ ብቻ ለመሸጥና ከተሸጠ በኋላ ወደሚፈለገው ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚቻልበት ሁኔታም ይፈጠራል፡፡ በነዚህ ገበያዎች የተመረቱ በእጅ ያሉ ምርቶችን ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ ተመርተው የሚቀርቡ ምርቶችንም አስቀድሞ መሸጥ የሚቻልበት ዕድል ይገኛል፡፡

እንደዚህ አይነቱ የተሟላ የገበያ መረጃ የሚገኝበት የግብይት ስርአት ለአምራቹና ለሸማቹ እጅግ በጣም ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡ አርሶ አደሩ የምርቱ ዋጋ ምን እንደሚሆን ስለሚያውቅ በትክክለኛ ዋጋ መሸጥ ይችላል፡፡ የዋጋዎችን አዝማሚያ በመመልከትም ምን እንደሚያመርት፣ ያመረተውን መቼ እንደሚሸጥ ለመወሰን ይችላል፡፡ ምርቱ ለአላስፈላጊ የትራንስፖርት ወጪ ሳይዳረግ ባለበት ቦታ ተሸጦ ከተሸጠ በኋላ ጥቅም ላይ ወደሚውልበት ቦታ በቀጥታ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ይችላል፡፡ ይህም ምርቱ በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማድረግ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ምርቱ ገና ሳይመረት መሸጥ የሚቻልበት ሁኔታ ሲፈጠር ገና ከመመረቱ በፊት ገበያ የማግኘት ዋስትና ስለሚኖረው የገቢ መዋዥቅ ሳያጋጥመው ምርቱን በትክክል አቅዶ ለማምረት ዕድል ይሰጠዋል፡፡ ሸማቹም ያለ ብዙ ውጣ ውረድና ወጪ የሚፈልገውን የምርት አይነት በሚፈለገው መጠን በገበያ በትክክል በሚታወቅ ዋጋ ገዝቶ ምርቱ በተፈለገው ጊዜ ወደተፈለገው ቦታ በቀጥታ እንዲደርስ ማድረግ ይችላል፡፡ እንዲህ አይነቱ የግብይት ስርአት በጣም



ቀልጣፋ፣ የግብይት ወጪው በጣም ዝቅተኛ የሆነ በመሆኑ በገበያ ተወዳድሮ ለማሸነፍ በጣም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ካለንበት የግብይት ስርአት ተነስተን እላይ የተጠቀሰውን ወደሚመስል የግብርና ግብይት ስርአት ለመድረስ ረጅም ጊዜና ከፍተኛ ጥረት እንደሚጠይቅ ግልፅ ነው፡፡ የግብርና እድገታችን ፈጣንና የማያቋርጥ እድገት እንዲያረጋግጥ ከተፈለገም በሂደት እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ እንዳለብን ግልፅ ነው፡፡ ስለሆነም ተመሳሳይ ደረጃ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ጥረትና ጊዜ እንደሚያስፈልገን አውቀን እዚያ ላይ መድረስ እንዳለብንም ተገንዝበን ይህንኑ በተቻለ ፍጥነት ለመፈፀም ከወዲሁ ለቀልጣፋ የግብይት ስርአት መሰረት የሆነውን የገበያ መረጃ ስርአት ማሻሻል መጀመር አለብን፡፡

ይህን የመሰለውን ስርአት በመገንባት ረገድ የሸቀጥ ልውውጥ ማዕከላት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው በመሆኑ፣ እንደዚህ አይነቶቹን የልውውጥ ማዕከላት በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጠንካራ የህብረት ስራ ማህበራትና የህብረት ስራ ማህበራት ዮንየኖች በሌሉበት ማስፈፀም አስቸጋሪ በመሆኑ የሸቀጥ ልውውጥ ማዕከላትን ለማቋቋም በነዚህ ማዕከላት አማካኝነት የሚሸጡት የግብርና ሸቀጦች ደረጃ በደረጃ እየጨመረ እንዲሄድ ማድረግና የነዚህ ተቋሞች መፈጠርና መጠናከር ከህብረት ስራ ማህበራትና ከዮንየኖቻቸው መጠናከር ጋር ተቀናጅቶ እንዲፈፀም ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እንደዚህ አይነቶቹ ተቋሞች እስኪደራጁና እስኪጠናከሩ ድረስ ጊዜ መውሰዱ ስለማይቀር የገበያ መረጃ በተወሰነ ቦታ ላይ ሆኖ በተሟላ መልኩ የሚገኝ አይሆንም፡፡ እንደዚህ አይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ወቅት ኋላ ቀርም ቢሆን ለየት ያለ መረጃ የማሰባሰብና የማሰራጨት ስርአት መኖር ይኖርበታል፡፡

www.abyssinialaw.com

የሸቀጦች ዋጋ በብዙ ገበያዎች ብዙ ሻጮችንና ገዥዎችን በማነጋገርና ይህንኑ በማጠናቀር ነው ሊገኝ የሚችለው፡፡ በዚህ መልክ የሚሰባሰብ መረጃ የጥራት ውሱንነት የሚኖረው ከመሆኑም በላይ በየደቂቃው ቀርቶ በየቀኑም ለተጠቃሚው ለማድረስ የሚከብድ ይሆናል፡፡ ይህን መረጃ መሰብሰብና ማሰራጨት የሚቀለው ለመንግስት በመሆኑ መንግስት እነዚህን መረጃዎች በተቻለ መጠን በጥራት የሚሰባሰቡበትና መረጃዎቹ በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት በተቻለ ፍጥነት ለተጠቃሚዎች የሚያደርሱበት ስርአት መፍጠርና በየጊዜው እየተሻሻለ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአለም ገበያ ዋጋዎችንና የዋጋ እድገቶች አዝማሚያ ይህን አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋሞች የተወሰነ ዋጋ ከፍሎ ማግኘት የሚቻል ስለሆነ መንግሰት ይህንኑ በየወቅቱ ለተጠቃሚዎች በመገናኛ ብዙሃን ማሰራጨት አለበት፡፡ ይህን መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም (ኢንተርኔት ወዘተ) ማግኘት ለሚችሉ ሁሉ አገልግሎቱ እንዲቀርብ ማደፋፈር፣ በግል ባለሃብቶች መስራት ካልተቻለም አገልግሎቱን ራሱው መስጠት መቻል አለበት፡፡

በአንድ በኩል እንደዚህ አይነቱን የመረጃ ማሰባሰብና ማሰራጨት ስርአት እየገነባንና በቀጣይነት እያሻሻልን፣ በሌላ በኩል ድግሞ የሸቀጥ ልውውጥ ማዕከላትን በመፍጠርና በማጠናከር አስተማማኝ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ ለማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለብን፡፡ ሁለቱንም ስራዎች ከወዲሁ መጀመር፣ በቀጣይነት ማሻሻልና ማጠናከር አለብን፡፡ የመረጃ አቅርቦት ስርአቱን የመገንባት ስራ ቢያንስ በመጀመሪያው ምዕራፍ በዋነኛነት በመንግስት የሚከናወን መሆኑ አይቀርም፡፡ በሂደት ግን በሌላውም አገር እንደታየው መረጃ በጥራት እየሰበሰቡ ዋጋ እያስከፈሉ የሚሸጡ የግል ኩባንያዎች



ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ መንግስት የግል ባለሃብቶች የመረጃ አቅርቦት ስርአቱን በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ በመገንዘብ በዚሁ መስክ የግል ባለሃብቶችን ተሳትፎ ማበረታታት አለበት፡፡

## (ሐ) የህብረት ስራ ማህበራትን ማስፋፋት፣ ማጠናከር፣

እንደኛ ባለ በሚሊዮኖች የሚቆጠር አርሶ አደር በተበጣጠሰ ማሳ ላይ የሚያመርተው የግብርና ምርት ዋናው የግብርና ዘይቤ በሆነበት አገር የህብረት ስራ ማህበራት የግብርና ግብይት ስርአትን በማሻሻልም ሆነ በሌሎች የግብርና ልማት ስራዎች ምንም መተኪያ የማይገኝለት ቁልፍ ስራ ይሰራሉ፡፡ በመሆኑም እንደኛ በመሰለ አገር በአጠቃላይ የግብርና ልማት በተለይ ደግሞ የግብርና ግብይት ስርአት በቀጥታ ከህብረት ስራ ማህበራት መኖርና መጠናከር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት በነዚህ አገሮች ጠንካራ የህብረት ስራ ማህበራት ካሉ ከፍተኛ የግብርና ልማትና የግብርና ግብይት ስርአት እድገትና መሻሻል ሊኖር ይችላል፣ እንደዚህ አይነት የህብረት ስራ ማህበራት ከሌሉ ከፍተኛ የግብርና ልማትና የግብርና ግብይት ስርአት እድገትና መሻሻል አይኖርም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

የህብረት ስራ ማህበራት በአጠቃላይ በግብርና ልማት ላይ በተለይ ደግሞ በግብርና ግብይት ስርአት ላይ ይህን ያህል ወሳኝ ሚና የሚኖራቸው ያለምክንያት አይደለም፡፡ አርሶ አደሩ ያመረተውን ምርት ራሱ ልሸጥ ቢል አርሶ አደርም ነጋዴም ሆኖ ከፍተኛ ጊዜና ወጪ የሚጠይቀው ይሆናል፡፡ በተለይም ሸማቹ ከእልፍ አእላፍ አርሶ አደሮች የሚፈልገውን ምርት በትንሽ በትንሹ ገዝቶ ለማጠራቀም ቢሞክር በጣም ውድ

ይሆንበታል፡፡ ይህን የሚሰሩ ነጋዴዎች በየደረጃው ይኑሩ ቢባል ከአንዱ ደረጃ ወደሌለው ሲቀባበል የሚወስደው ጊዜና የሚጠይቀው ወጪ እጅግ በጣም ከፍተኛ ይሆናል፡፡ እያንዳንዳቸው ሸማቾችና ሻጮች ራሳቸው የደረጃ መዳቢና ተቆጣጣሪ እንሁን ቢሉም የግብይት ስርአቱ በዚያው መጠን ቀርፋፋና ውድ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አርሶ አደሩ ምርቱን በተናጠል የሚሸጥበት ስርአት እንደኛ ባሉ አገሮች በፍፁም ቀልጣፋና በርካሽ ዋጋ የሚፈፀም ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም እንዲህ አይነቱ ስርአት የፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት እንቅስቃሴ መሰረት ሊሆን አይችልም፡፡

የህብረት ስራ ማህበራትና ዮኒየኖቻቸው ይህን ችግር በመሰረቱ በአስተማማኝ ሁኔታ ሊቀርፉ ይችላሉ፡፡ የብዙ አርሶ አደሮችን ምርት በማሰባሰብ በአግባቡ የማከማቸትና የመጋዘን አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ሸማቾች የሚፈልጉትን ምርት በሚፈልጉት መጠን ከአንድ ወይም ውሱን ማህበራት ሊገዙ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ የደረጃ ምደባ ስርአት ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት ደረጃ መዳቢዎችን አሰልጥነውና ቀጥረው የሚያሰባስቡትን ምርት ደረጃ ለይተውና አሽገው ለገበያ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በደረጃ ምደባቸው ላይ የተጭበረበረ ነገር ሲገኝ በቀጣዩ ምርታቸውን መሸጥ እንደማይችሉ ስለሚታወቅና መንግስትም ይህን ስርአት ለማጠናከር ርምጃ ሊወስድ ስለሚችል የምርታቸውን ደረጃ በመመደብ ረገድ በገበያው ተአማኒነት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ለአርሶ አደሩም የደረጃ ምደባ ስልጠና ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ለአርሶ አደሩ የሚከፍሉት ዋጋ በምርቱ መጠን ብቻ ሳይሆን በምርቱ ጥራትም ላይ ስለሚመሰረት ጥራቱ የተጠበቀ ምርት የማምረትን ባህል በአርሶ አደሩ ውስጥ ማስረፅ ይችላሉ፡፡



አርሶ አደሩ የሚያስፈልጉትን ሸቀጦች በተለይም ዋና ዋና የምርት ግብአቶችን በተናጠል ልግዛ ቢል፣ ሻጮችም ለአርሶ አደሩ በተናጠል እንሽጥ ቢሉ ከአንዱ ነጋዴ ወደሌላው እየተሸጋገረ አርሶ አደሩ ዘንድ እስኪደርስ ድረስ የሚወስደው ጊዜና የሚያስከትለው የዋጋ ጭማሪ በጣም ከፍተኛ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ የህብረት ስራ ማህበራት በአርሶ አደሩ የሚፈለጉ ዋና ዋና ሸቀጦችን በተለይም ግብአቶችንና የማምረቻ መሳሪያዎችን ለአርሶ አደሩ በቀጥታ ማከፋፈል ቢችሉ ግብይቱ የሚጠይቀው ጊዜና ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ ሊቀንስ ይችላል፡፡ የግብአትና የማምረቻ መሳሪያዎች አምራቾችና አስመጪዎች ምርታቸውን በቀጥታና በሰፊው የማስራጨት አገልግሎት የሚሰጣቸው በዚህ ረገድ ተወዳዳሪ ሊገኝለት የማይችል ድርጅት ያገኛሉ፡፡ አርሶ አደሩም ፍላጎቱን አውቆ ወሳኝ የሆኑ ግብአቶችና የማምረቻ መሳሪያዎችን በተፈላጊው ጊዜና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያቀርብለት ድርጅት ያገኛል፡፡

በአጭሩ የህብረት ስራ ማህበራት የግብይት ጊዜን በማሳጠር፣ የግብይት ወጪን በከፍተኛ ደረጃ በመቁረጥ እንደኛ ባለ በተበጣጠሰ ማሳ ላይ የሚያርስ አርሶ አደር ወሳኝ ሚና በሚጫወትበት አገር ቀልጣፋ የግብርና ግብይት ስርአት በመፍጠር ረገድ ምንም አይነት አማራጭ የሌለው ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የህብረት ስራ ማህበራት ዋነኛው ተግባርም ይህ ነው፡፡ ማህበራቱ ከዚህ ውጭ ሌላ ምንም አይነት አገልግሎት የማይሰጡም ቢሆኑ እንኳ በግብርና ልማት ውስጥ ወሳኝ ሚና ካላቸው አደረጃጀቶች መካከል በቅድሚያ መጠቀሳቸው ባልቀረ ነበር፡፡ ነገር ግን የህብረት ስራ ማህበራት ከግብይት አገልግሎት በተጨማሪ በርካታ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡

www.abyssinialaw.com

የህብረት ስራ ማህበራት በገጠር የፋይናንስ አገልግሎትን በማስፋፋት ረገድም ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ:: ገቢያቸውን በባንክ በማስቀመጥ ከግብርና የሚገኘው ካፒታል በባንክ ስርአቱ ውስጥ ገብቶ የላቀ ጥቅም በሚያስገኝበት አኳኋን ጥቅም ላይ እንዲውል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ:: ገንዘብ ከባንኮች ተበድረው ለአርሶ አደሩ መልሰው በማበደር አርሶ አደሩ ምርቱን ሲሸጥ የተበደረውን ያህል እያስቀሩ በመሰብሰብ ከፍተኛ አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ:: በሂደት አርሶ አደሩ ምርቱን ለሽያጭ ወደነሱ በሚያስረክብበት ወቅት ደረሰኝ እየሰጡ ደረሰኙ አስተማማኝ የዋስትና መያዣ ስለሚሆን ይህንኑ አስይዞ ከገጠር ባንኮችም ሆነ ከሌላ በቂ ብድር እንዲያገኝ በር ሊከፍቱለት ይችላሉ:: የተጠናከሩ የህብረት ስራ ማህበራት የራሳቸው ባንክ እስከመፍጠር ሄደው ከአርሶ አደሩ ተቀማጭ ገንዘብ እያሰባሰቡ ተመልሰው ለአርሶ አደሩ በማበደርም ሆነ ለሌላ በማበደር፣ ሌሎችንም የባንክ አገልግሎቶች በመስጠት የገጠር የፋይናንስ ስርአትን ለማጠናከር ይችላሉ:: በአጭሩ የህብረት ስራ ማህበራት የገጠር የፋይናንስ ስርአትን በተለያዩ መንገዶች በማጠናከር ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ::

የህብረት ስራ ማህበራት አርሶ አደሩ በተናጠል ሊገዛቸውና ሊጠቀምባቸው የማይችሉ መሳሪያዎችን ገዝተው በማከራየት የግብርና ቴክኖሎጂንና ምርትን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል ይችላሉ:: የአርሶ አደሩን ምርቶች ሰብስበው በአግባቡና በጥንቃቄ በማከማቸት የመጋዘንና የትራንስፖርት አገልግሎት ከመስጠት ጀምሮ እነዚህ ምርቶች የተሻለ ዋጋ እንዲያስገኙ ትናንሽ ተቋሞችን በመመስረት የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት ስራ ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ:: ለአርሶ



አደሩ የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋሞችን በማደራጀትና በማቋቋም ስራ ላይም ሊሳተፉ ይችላሉ::

ከላይ የተጠቀሱት ስራዎች ያለ ህብረት ስራ ማህበራት ሊታሰቡ የማይችሉ በመሆናቸው የህብረት ስራ ማህበራትን በየደረጃው ማቋቋምና ማጠናከር የገጠርና የግብርና ልማት አላማችን አንድ መሰረታዊ ምሰሶ ይሆናል:: ይሁንና እነዚህን ማህበራት ለማስፋፋትና ለማጠናከር አሁን ያለባቸውን ችግር በዝርዝር ለይቶ በማወቅ መፍታትና፣ በዚህ ረገድ አገራችን ያላት መጥፎ ልምድ እንዳይደገም ማድረግ ያስፈልጋል::

በደርግ ጊዜ የተቋቋሙት የህብረት ስራ ማህበራት በግዴታ የተቋቋሙ የየአካባቢው መሪዎችና ካድሬዎች በከፍተኛ ደረጃ ጣልቃ የሚገቡባቸው ብቻ ሳይሆኑ እንደፈለጉ የሚያሽከረክሩዋቸው የነበሩ በመሆናቸውና ለአርሶ አደሩም ተጨባጭ ጥቅም ስላልሰጡ ሊጠናከሩና አርሶ አደሩም እንደራሱ ድርጅቶች ቀጥሮ ሊንከባከባቸው አልቻለም:: የህብረት ስራ ማህበራት የአርሶ አደሩ የኢኮኖሚ ማህበራት ናቸው:: በአንድ በኩል አርሶ አደሩ የሚያቋቁማቸው የሼር ኩባንያዎች እንደሆኑ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: ፖለቲካዊ ድርጅቶች አይደሉም፣ መሆንም አይገባቸውም:: ስለሆነም በህዝቡ፣ በአባላቱ ነፃ ፍላጎትና በአባላቱ ነፃ ፍላጎት ብቻ የሚመሰረቱ፣ ማንኛውም አባል አባልነቱን ባልፈለገበት ወቅት ለቆ መውጣት የሚችልባቸው ድርጅቶች መሆን አለባቸው:: የማስገደድ ጉዳይ ሽታውም በሌለበት አኳኋን ካልተፈጠሩ በስተቀር ሊጠናከሩና ፋይዳ ያለው አገልግሎት ሊሰጡ አይችሉም::

www.abyssinialaw.com

ከደርግ ውድቀት በኋላ እንደገና በመቋቋም ላይ ያሉት የህብረት ስራ ማህበራት በግዳጅ ሳይሆን በአባላት ነፃ ፍላጎት እየተቋቋሙ ያሉ በመሆናቸው በዚህ ረገድ የነበረው ችግር ተወግዷል ሊባል ይችላል፡፡ ይህንኑ ጠብቆና አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ በአባላት ፍላጎት በነፃ አኳኋን ከተደራጀ በኋላ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ካለ ለአባላት ጥቅም በአባላት የቆሙ የኢኮኖሚ ድርጅቶች መሆናቸው ይቀርና ለተለያዩ አደጋዎች ይጋለጣሉ፡፡ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነትን በተመለከተ በደርግ ጊዜ ከነበረው ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰና መልኩንም የቀየረ ቢሆንም ጨርሶ ጠፍቷል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ለሙስናና ለምዝበራ ተብሎ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት አሁንም መታየቱ አልቀረም፡፡ ይህ ችግር በአንዳንድ የአገራችን ክፍሎች በተለይም የህብረት ስራ ማህበራት የተሻለ የኢኮኖሚ ልማት ተቋም ለመሆን በሚያስችላቸው የምርትና የአገልግሎት ስራ ላይ በተሰማሩባቸው አካባቢዎች ጉልቶ ይታያል፡፡ የህብረት ስራ ማህበራቱ በስንት ድካም ያፈሩትን ሃብት ለመቀራመት ከመሻት የሚፈልቅ ጥገኛ አስተሳሰብ ቀላል የማይባል ጣልቃ ገብነትን ሲያስከትል ቆይቷል፡፡ ይህን የመሰለው አፍራሽ ጣልቃገብነት በየትኛውም ደረጃና መልክ እንዳይከሰት ቀጣይ ትግል ሊካሄድበት ይገባል፡፡ ይህ ትግል በቅድሚያ የአስፈፃሚ አካላትን ለጣልቃ ገብነት የሚገፋፋውን አመለካከት በማስተካከል መካሄድ ያለበት ቢሆንም የህብረት ስራ ማህበራትን የሚመለከቱ የአገሪቱ ህጎች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ በማረጋገጥ የሚፈፀምም እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የማህበራቱን ነፃነት ለመጠበቅ የሚያስፈልገውን አመለካከትና ፈቃደኛነት ለማዳበር ከሚካሄደው ጥረት ጎን ለጎንና ይህንኑ በሚያጠናክር አኳኋን የህጉን ተፈፃሚነት በማረጋገጥም የሚከናወን እንዲሆን ይደረጋል፡፡



ለአላስፈላጊ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ምክንያት የሚሆነው አንዱ ጉዳይ የየአካባቢው አስተዳዳሪዎች እነዚህ ተቋሞች በገጠር ልማት ላይ ያላቸውን ወሳኝ አስተዋፅኦ በመገንዘብ እንዲጠናከሩ ለመርዳት በሚል ጀምሮ ወደ ጣልቃ ገብነት የሚሸጋገሩ መሆናቸው ነው፡፡ በርግጥ የየአካባቢው አስተዳዳሪዎች እነዚህን ተቋሞች ለመርዳትና ለማጠናከር የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ የህብረት ስራ ማህበራት እንዲቋቋሙ አርሶ አደሩን ማስረዳትና ማሳመን ይገባቸዋል፡፡ ከምስረታው በኋላ ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ልዩ ልዩ የቴክኒክና ሞያ እገዛ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ የተቋሞቹ መሪዎች በህብረት ስራ አመራር ላይ ስልጠና እንዲያገኙና አባላቱም የማህበራቱ አሰራርና የራሳቸው ሚና ምን መሆን እንዳለበት እንዲያውቁ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ተቋማቱ የመጋዘን የትራንስፖርትና የፋይናንስ አቅማቸውን እንዲያዳብሩ ሊተባበሩዋቸው ይገባል፡፡ የኦዲት አገልግሎትም ሊሰጡዋቸው ይገባል፡፡

እነዚህ እገዛዎች እንጂ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነቶች አይደሉም፡፡ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የሚጀመረው የማህበራቱ መሪዎች እነማን መሆን እንዳለባቸው በምርጫ ለመወሰን በሚደረገው እንቅስቃሴ የአካባቢው አስተዳዳሪዎች የሚፈልጉዋቸውን ሰዎች ለማስመረጥ ሲንቀሳቀሱ ነው፡፡ ይህ ተገቢ አይደለም፡፡ በደል ፈፅመዋል የሚባሉ መሪዎችን አጣሪ ከሳሽና ዳኛ በመሆን ማስወገድ ሲጀምሩ ነው፡፡ ተከሶ የቀረበ ሰው በአፋጣኝ ብሩን እንዲያገኝ ለማድረግ አጣሪ ከሳሽና ዳኛ መሆን አይገባቸውም፡፡ ጣልቃ ገብነቱ የተለያዩ የሞያ እገዛዎች ከመስጠት አልፎ መሪዎቹ ምንና እንዴት መስራት እንዳለባቸው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በመንገር በማዘዝ መልኩ ሲገለፅ ነው፡፡ ለወደፊቱም ጣልቃ ገብነትና ቴክኒካዊ እገዛ

www.abyssinialaw.com

መስጠትን ለይተን የተሟላ ቴክኒካዊ እገዛ የሚሰጥበት፣ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት በፍፁም የሚቀርበት የሚወገዝበትና ተፈፅሞ ሲገኝም የማያወላውል ቅጣት የሚሰጥበት ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

በመለስተኛ ደረጃ የሚፈፅምን ጣልቃ ገብነትም ጭምር በጥብቅ መዋጋት በጣም አስፈላጊ ቢሆንም የህብረት ስራ ማህበራት በአሁኑ ወቅት ያላቸው ዋነኛ ችግር የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ሳይሆን የአስተዳደርና የአመራር ብቃት ማነስ ነው፡፡ የሚመረጡት መሪዎች የህዝቡ አጠቃላይ የትምህርትና ስልጠና ደረጃ ዝቅተኛ በመሆኑ ከፍተኛ የአመራር ብቃት ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ በህብረት ስራ ማህበራት የሰለጠኑ ሞያተኞችን ቀጥረው የአመራር ብቃታቸውን እንዳያሳድጉ በዚህ ሞያ የሰለጠኑ በቂ ሰዎችም የሉም፣ ማህበራቱም ሞያተኛ ቀጥሮ የማሰራት አቅም የላቸውም፡፡ አባላቱ መሪዎቹን የመቆጣጠር ብቃትም ሆነ ዝግጁነት ስለሚጎድላቸውና የኦዲትና ቁጥጥር ስርአቱም ደካማ ስለሚሆን ማህበራቱ ብዙውን ጊዜ ለብክነትና ለምዝበራ የተጋለጡ ይሆናሉ፡፡

እነዚህ መሰረታዊ የአመራር ችግሮች ካልተፈቱ በስተቀር የህብረት ስራ ማህበራት በሚፈለገው ደረጃ ሊጠናከሩና መጫወት የሚገባቸውን ሚና ሊጫወቱ አይችሉም፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትና በዚህ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ የሞያ ስልጠና እየተጠናከረ ሲሄድ አባላቱም መሪዎቹም የተማሩና የሰለጠኑ ይሆናሉ፡፡ አባላቱም መሪዎቻቸውን የመቆጣጠር የተሻለ አቅም ይኖራቸዋል፡፡ መሪዎቹም በቀጣይ ስልጠና በይበልጥ ሊጠናከር የሚችል የተሻለ የአመራር አቅም ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሆኖ ማህበራት በህብረት ስራ ማህበራት ስራ የሰለጠኑ ሞያተኞች



ቀጥረው ማሰራት ካልቻሉ በሚፈለገው ደረጃ ብቃት ያለው አመራር ሊያገኙ አይችሉም፡፡ ይህንኑ ለማድረግ መንግስት እንደዚህ አይነቶቹን ሞያተኞች በሚፈለገው መጠን ማሰልጠን አለበት፣ ማህበራቱም እንደነዚህ አይነቶቹን ሞያተኞች ቀጥረው ማሰራት የሚችሉበት አቅም መገንባት አለባቸው፡፡ የማህበራት የፋይናንስ ስርአት፣ የኦዲትና ቁጥጥር ስርአት የተስተካከለ እንዲሆን መንግስት ህግና፣ ሞዴል መመሪያ እያዘጋጀ ማጠናከርና በየጊዜው ማሻሻል አለበት፡፡ በየደረጃው ለማህበራቱ የቴክኒክ እገዛና የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ በሚገባ የሰለጠኑ ሞያተኞች ያሉት የህብረት ስራ ማህበራት ድጋፍ ሰጪ መዋቅር መስፋፋትና መጠናከር አለበት፡፡

ማህበራቱ በአሁኑ ሰአት በብዙ አካባቢዎች በጣም ደካማ የፋይናንስ አቅም ያላቸውና ለአባላቱ በሚፈለገው ደረጃ አገልግሎት የማይሰጡ ሆነው ይታያሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ መጋዘንና የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የማይችሉ፣ የአርሶ አደሩን ምርት በተገቢው መጠን አሰባስበው ለመሸጥም ሆነ መሰረታዊ ግብአቶችን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ የማይችሉ ሆነው ይገኛሉ፡፡ መንግስት እነዚህ ተቋሞች በአግባቡ እስኪደራጁና የፋይናንስ አቅማቸውን እስኪያጠናክሩ ድረስ በተለያየ መንገድ መርዳት አለበት፡፡

ማህበራቱ የአካባቢውን ህዝብ አስተባብረው በቂ መጋዘኖች እንዲሰሩና ከሁኔታቸው ጋር የሚሄድ የትራንስፖርት አቅም እንዲገነቡ ህዝቡን በማስተባበርም ሆነ ልዩ ልዩ የቴክኒክ አገልግሎቶችን በመስጠት ሊተባበሯቸው ይገባል፡፡ ለአርሶ አደሩ የሚቀርቡ ግብአቶችን በማሰራጨት ረገድ የህብረት ስራ ማህበራት ወኪሎች ሆነው የሚሰሩበትና በዚህ አኳኋን የፋይናንስ

www.abyssinialaw.com

አቅማቸውን የሚያጎለብቱበት ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ ማህበራቱ በደንብ ተቋቁመው በአግባቡ መንቀሳቀስ ከጀመሩ በኋላ የፋይናንስና የአመራር አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ በዮኒዮኖች እንዲሰባሰቡ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ የፋይናንስ ስርአታቸውና ገበያቸው እየተሻሻለ ሲሄድ ከባንኮች የብድር አገልግሎት ሊያገኙ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸትም ይገባል፡፡ እነዚህንና መሰል ስልቶችን በመጠቀም የህብረት ስራ ማህበራትን በማስፋፋትና በማጠናከር የግብርና ግብይት ስርአታችንን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻልና ሌሎች ለግብርና ልማት አጋዥ የሆኑ አገልግሎቶችንም ማስፋፋት ይቻላል፡፡

## (መ) የግል ባለሃብቶች በግብርና ግብይት ስርአት ያላቸውን ተሳትፎ ማሻሻልና ማጠናከር፣

የህብረት ስራ ማህበራት በግብርና ግብይት ስርአታችን ውስጥ ወሳኝ ሚና መጫወት ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም ማለት ስራው በማህበራቱ ብቻ ይከናወናል ወይም የግል ባለሃብቶች ከዚህ አኳያ ቁልፍ አስተዋፅኦ የላቸውም ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም የግል ባለሃብቶች ቁልፍ አስተዋፅኦ ካልታከለበት በስተቀር የህብረት ስራ ማህበራት የማይሸፍኗቸው ቀዳዳዎች ስለሚኖሩ ስርአቱ በአጠቃላይ ሊሰራ የማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡ ይህ ስራ በችርቻሮም ሆነ በጅምላ ሽያጭ እንደዚሁም የግብርና ምርቶችን ተቀብሎ በፋብሪካዎች በማዘጋጀት መልኩ ሊገለፅ የሚችል ነው፡፡

የግብርና ምርቶች ከአርሶ አደሩ ወደ ነጋዴ ከዚያም ከፍ ወዳለ ነጋዴ በቅብብሎሽ መሄዳቸው ጊዜን ከማባከን አልፎ በዋጋዎች ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ እንደሚያሳርፍና፣ አርሶ አደሩ



የሚፈልጋቸው ወሳኝ ግብአቶችም በተመሳሳይ ሰንሰለት ይለፉ ቢባል በዋጋና ጊዜ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ እንደሚያሳድር ግልፅ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ግብይት በሂደት በህብረት ስራ ማህበራትና በዋና ተጠቃሚዎች፣ ጅምላ ሻጮች አስመጪዎችና ኤክስፖርተሮች መካከል በሚፈጠር የግብይት ሰንሰለት መተካት ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት ግን የችርቻሮ ነጋዴዎችና ሌሎች አነስተኛ ባለሃብቶች በዚህ ስራ ላይ ሚና አይኖራቸውም ማለት አይደለም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በአርሶ አደሩና በአቅራቢያው በሚገኙ መለስተኛ ገበያዎች መካከል የሚኖር የንግድ ልውውጥ በነዚህ አማካኝነት እንደሚፈፀም ግልፅ ነው፡፡ ከዋና ዋና የግብርና ምርቶች፣ ግብአቶችና ማምረቻ መሳሪያዎች ውጭ ያለው የንግድ ልውውጥም በአብዛኛው በእነዚህ አማካኝነት እንደሚፈፀም እሙን ነው፡፡ አርሶ አደሩ ገቢው እየጨመረ ሲሄድ ከሸቀጦች በተጨማሪ በአይነትና በመጠን እየጨመሩ የሚሄዱ የተለያዩ አገልግሎቶችን መፈለጉ አይቀርም፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች በአቅራቢያው በማደራጀትና በማቅረብ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉት አነስተኛ አርሶ አደሮች ናቸው፡፡ እነዚህ በህብረት ስራ ማህበራት ሊሸፈኑ የማይችሉ ስራዎች በግል ባለሃብቶች ካልተሰሩ ስርአቱ የተሟላና ቀልጣፋ ሊሆን አይችልም፡፡

የህብረት ስራ ማህበራት የአርሶ አደሩን ምርት ካሰባሰቡ በኋላ ምርቱ ለዋነኛ ተጠቃሚዎች (ጅምላ ሻጮች፣ የግብርና ምርትን በጥሬ ዕቃነት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች ኤክስፖርተሮች ወዘተ.) ባልተንዛዛ ሰንሰለት አማካኝነት መድረስ መቻል አለበት፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አርሶ አደሩ የሚፈልጋቸው መሰረታዊ ግብአቶች፣ የማምረቻ መሳሪያዎች ወዘተ. ይህንኑ ከሚያመርቱ አምራቾችና አስመጪዎች በቀጥታ ወደ ህብረት ስራ ማህበራት መተላለፍ አለባቸው፡፡ የህብረት ስራ ማህበራት መኖር

www.abyssinialaw.com

የቅብብሎሽ ሰንሰለቱን በከፍተኛ ደረጃ በማሳጠር ጊዜንና ወጪን ይቀንሳል እንጂ የቅብብሎሽ ሰንሰለቱን አያስቀረውም:: ዋና ዋና የግብርና ምርቶችን ከህብረት ስራ ማህበራት የሚቀበሉ፣ ዋና ዋና ግብአቶችንና የማምረቻ መሳሪያዎችን የህብረት ስራ ማህበራት የሚያቀብሉ የግል ባለሃብቶች ከሌሉና ካልተጠናከሩ የግብይት ስርአቱ ሊሰራ አይችልም:: ስለሆነም የግብይት ስርአቱን የተሟላና ቀልጣፋ ለማድረግ የህብረት ስራ ማህበራትን ከማጠናከር በተጨማሪ ከነዚህ ጋር በቅብብሎሽ የሚሰሩትን የግል ባለሃብቶች ማጠናከርና ቀልጣፋነታቸውን ማሻሻል ያስፈልጋል::

ከህብረት ስራ ማህበራት ጋር በቅብብሎሽ የሚሰሩ ባለሃብቶች በነፃ የገበያ ውድድር መርህ እንዲሰሩ ማድረግና ይህንኑ በጥብቅ መቆጣጠር እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑ እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባ ነው:: በአገራችን የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ የሞኖፖሊ አሰራር የቆየና ስር የሰደደ ችግር ነው:: ነፃ ውድድር በሞኖፖሊ በሚተካበት ወቅት በውድድር ጥራትንና ዋጋን የማሻሻል ዕድል ይጠባል:: ስለሆነም ነው የዳበረ የገበያ ኢኮኖሚ ያላቸው አገሮች ውድድርን የሚያስቀሩ የሞኖፖሊና ሌሎች ተመሳሳይ አሰራሮች እንዳይፈጠሩ በንቃት የሚጠብቁትና ሲፈጠሩም ፈጣን ርምጃ ወስደው የሚያፈራርሱት:: በኛም ሁኔታ በቅብብሎሽ ሰንሰለት ውስጥ ነፃ ውድድር መኖሩን ማረጋገጥና የሞኖፖሊና ሌሎች ፀረ ውድድር አሰራሮችን ማፈራረስ፣ እንደገና እንዳያቆጠቁጡም በንቃት መከላከል በጣም አስፈላጊ ይሆናል::



በተደጋጋሚ እንደተገለፀው የግብርና ልማታችን በአጠቃላይ በገበያ መመራት ብቻ ሳይሆን በተለይ የውጭ ገበያን ሰብሮ በመግባት ቅኝት መመራት ያለበት ነው:: ምርቶቻችንን በውጭ ገበያ በስፋት ለመሸጥ ከአመራረታቸው እስከአስተሻሸጋቸው ድረስ ጥራታቸው የተጠበቀ መሆን እንዳለበትና በዋጋም ተወዳዳሪ ሆነው መገኘት እንዳለባቸው የታወቀ ነው:: የእነዚህን ምርቶች እሴት ለመጨመር በተቻለ መጠን የአግሮ ፕሮሰሲንግ ፋብሪካዎችን ለማስፋፋት መንቀሳቀስ እንዳለብንም እሙን ነው:: ምርቶቻችን በአለም ገበያ ያላቸውን ታዋቂነት ለማጠናከር የንግድ ምልክት (ብራንዲንግ) ጉዳይ ከፍተኛ ፋይዳ ስላለው ይህንኑ ለማስፋፋትም ጥረት ማድረግ አለብን:: ለምሳሌ ቡናችን በጣዕሙ በአለም ደረጃ የታወቀ፣ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ የሚመረት (ኬሚካል ወዘተ. ያልተጨመረበት ኦርጋኒክ ምርት) መሆኑ የራሱ ታዋቂነትና (ብራንድ) እንዲኖረው ለማድረግ የተመቸ ነው:: ይህንን ብናደርግ ገበያችን በከፍተኛ ደረጃ ሊጨምር እንደሚችልም የታወቀ ነው::

እነዚህ ስራዎች በአለም ገበያ በሰፊው መግባት እንድንችልና ለምርቶቻችን የምናገኘው ዋጋ ከፍ እንዲል ከማድረግ አኳያ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ የመሆኑን ያህል አፈፃፀማቸው ግን በጣም አስቸጋሪ ነው:: የአለም ንግድ በተለይም የዋና ዋና የግብርና ምርቶችና በነዚህ ላይ የተመሰረቱ የፋብሪካ ምርቶች ንግድ በታላላቅ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ቁጥጥር ስር ያለ ነው:: የታወቁ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኩባንያዎችና ታላላቅ የንግድና ችርቻሮ ኩባንያዎች የሚቆጣጠሩት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ገበያውን ሰብሮ ለመግባትና ሰብረው ከገቡ በኋላም ጥሩ ዋጋ ለማግኘት

በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም በራሳችን የግል ኩባንያዎችና የህብረት ስራ ማህበራት የሚደረገው የኤክስፖርት ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ ታዋቂ የአለም ኩባንያዎች ምርታችንን ለአለም ገበያ በማቅረብ ረገድ በሰፊው እንዲሳተፉ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡

ታዋቂ የአግሮ-ፕሮሰሲንግ ኩባንያዎች ወደአገራችን ገብተው ቢሰሩ የምርታችን ጥራት እንዲጠበቅና ምርታማነታችን እንዲሻሻል በማድረግ በኩል በከፍተኛ ደረጃ ሊያግዙን ይችላሉ፡፡ ምርታችንን ብራንድ ለማድረግና ጥሩ ዋጋ እንድናገኝበት ለማድረግም ሊረዱን ይችላሉ፡፡ ሸቀጦችን በአለም ደረጃ የሚያከፋፍሉበት የራሳቸው የተጠናከረ ሰንሰለት ስለሚኖራቸው ለምርታችን የውጭ ገበያ በማፈላለግ ረገድ ከምንም በላይ የተሻሻለ ስራ መስራት ይችላሉ፡፡ ታላላቅ የግብርና ምርት አከፋፋይ ኩባንያዎችም ከህብረት ስራ ማህበሮቻችን ጋር በቀጥታ መተሳሰር ከቻሉ ተመሳሳይ አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በሂደት ከዚህ የምናገኘውን እውቀትና ልምድ ተጠቅመን በራሳችን አቅም የአለም ገበያ ድርሻችንን የማሻሻል አቅም ልንገነባ እንችላለን፡፡ ስለሆነም ታዋቂ ድንበር ዘለል የግብርና ምርት አከፋፋይ ኩባንያዎችንና የአግሮ-ፕሮሰሲንግ ኩባንያዎችን ወደአገራችን ለመሳብ ባለን አቅም ሁሉ መረባረብ፣ ከነዚህ የምናገኘውን እውቀትና ልምድ በላቀ ደረጃ በመጠቀም በየራሳችን የአለም ገበያ ድርሻችንን የማሻሻል አቅም ለመገንባት መንቀሳቀስ ልዩ ክብደት የሚሰጠው ስራ መሆን ይኖርበታል፡፡

የግል ባለሃብቶች በግብርና ምርት ዘርፍ በሂደት እየጨመረ የሚሄድ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ እነዚህ ባለሀብቶችም የህብረት ስራ ማህበራት አቋቁመው ምርታቸውን መሸጥ



ይችላሉ፡፡ በተለይም መለስተኛ አቅም ያላቸው የግል ባለሃብቶች የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ተመሳሳይ የሽያጭ አገልግሎት የሚሰጡ የጋራ ድርጅቶች አቋቁመው ቢሰሩ በበለጠ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ምርታቸውን በቀጥታ ለዋና ተጠቃሚው ለመሸጥ፣ ራሳቸውን ችለው ኤክስፖርት ለማድረግም ሆነ ለማከፋፈል የሚችሉ ይኖራሉ፡፡ ምርታቸውን ፋብሪካ አቋቁመው እሴት እንዲጨምር ማድረግም የሚችሉ ይኖራሉ፡፡ ይህንኑ ማድረግ የሚችሉ ባለሃብቶች በዚሁ መልክ እንዲቀጥሉ መደገፍና ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

## 6. የገጠር የፋይናንስ ስርአትን ማሻሻል፣

የግብርና ልማት ስትራተጅያችን የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበትና ይህንኑ በሰፊው በመጠቀም ላይ የተመሰረተ፣ የፋይናንስ አቅማችን ውሱን በመሆኑ ደግሞ ይህንኑ በቁጠባ በመጠቀም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይሁንና ያለ ፋይናንስ ግብርናን ማልማት እንችላለን ማለት አይደለም፡፡ ምንም ያህል በቁጠባ ብንጠቀምበት መጠኑ ይቀንስ እንደሆነ እንጂ በዜሮ ፋይናንስ መንቀሳቀስ አይቻልም፡፡ አርሶ አደሩ የተለያዩ ግብአቶችና የማምረቻ መሳሪያዎች መግዛቱ አይቀርም፡፡ ይህንኑ በመገንዘብ አጠራቅሞ ይግዛው ቢባል ልማትን በሚዘጋ አዙሪት ውስጥ መግባትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ አርሶ አደሩ ገንዘብ ስለሌለው እነዚህን ግብአቶችና መሳሪያዎች አይገዛም፡፡ እነዚህን ገዝቶ ባለመጠቀሙ ምርቱ አያድግም፣ ገንዘብም አይኖረውም፡፡ ገንዘብ ስለማይኖረውና ምርቱ ስለማያድግ በሚቀጥለው ዙርም አይገዛም፡፡ ወዘተ. መውጫ ወደሌለው አዙሪት መግባት ይመጣል፡፡ ይህንኑ አዙሪት መስበር የሚቻለው ለአርሶ አደሩ በቂ የብድር አገልግሎት በመስጠት ነው፡፡ ተበድሮ ገዝቶ ጥቅም ላይ በማዋል

www.abyssinialaw.com

ምርቱን አጎልብቶ  ገንዘብ ያገኛል። በተገኘው ገንዘብ ብድሩን ከፍሎ፣ ተጨማሪ ብድርንና የራሱን ገንዘብ ተጠቅሞ ግብአቶችንና መሳሪያዎችን በተሻለ መጠንና አይነት ይገዛል፣ ከዚህም የላቀ ምርትና ገንዘብ ያገኛል። እንዲህ በማድረግ ቀጣይ ልማት ሊረጋገጥ ይችላል። የግብርና ኢንቨስትመንትን ለማጠናከርና እድገታችንን ለማፋጠን ለአርሶ አደሩ በቂ የብድር አገልግሎት የሚሰጥ የፋይናንስ ስርአት በገጠር ማስፋፋት አለብን።

ጠንካራ የፋይናንስ ስርአት መኖሩ ለግብርና ኢንቨስትመንት ብቻ ሳይሆን ለግብርና ግብይት ስርአት መጠናከርም ያስፈልጋል። ምንም እንኳ የህብረት ስራ ማህበራት ግብአቶችንና መሳሪያዎችን ገንዘብ አውጥተው ሳይገዙ የዋና አስመጪዎችና ፋብሪካዎች አከፋፋይ በመሆን መስራት ቢችሉም፣ የአርሶ አደሩን ምርት ገንዘብ ሳይከፍሉ አሰባስበው ምርቱ ከተሸጠ በኋላ መክፈል ቢችሉም፣ ምንም እንኳ ይህ አሰራር የህብረት ስራ ማህበራት የፋይናንስ አቅም ባልተጠናከረበት ሁኔታ በሰፊው ስራ ላይ መዋል የሚችልና የሚገባው አሰራር ቢሆንም ይህ ብቻ የተሟላ የግብይት ስርአት እንዲኖር ሊያደርግ አይችልም። ግብአቶችንና የማምረቻ መሳሪያዎችን እንዲሁም የአርሶ አደሩን ምርት ገንዘብ እየከፈሉ የሚገዙበት አሰራርም መኖር አለበት። ጠንካራ የፋይናንስ አገልግሎት መኖሩ ይህን የግብይት እንቅስቃሴ ለማስፈፀምና ለማቀላጠፍ ይረዳል።

በገጠርና በግብርና ላይ ያተኮረ የልማት ስትራቴጅ እንድንከተል የሚያደርገን አንዱ መሰረታዊ ምክንያት ያለ ከፍተኛ የካፒታል ወጪ ሊመጣ የሚችለውን ከፍተኛ የግብርና እድገት በማረጋገጥ፣ በዚሁ የእድገት ሂደት የካፒታል አቅማችንን ለማጠናከርና በዚሁ በመጠቀም የኢንዱስትሪና የሌሎች የኢኮኖሚ



ዘርፎችን እድገት ለማሻሻል ነው። በገጠር ጠንካራ የፋይናንስ ስርአት ካልተፈጠረ በስተቀር ለኢንዱስትሪና ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚሆን ካፒታል ማከማቸትና ወደሚፈለገው ዘርፍ ማሸጋገር አይቻልም።

በርግጥ የግል ባለሃብቶች የግብርና ምርትን ገዝተው ሲሸጡ ወይም በፋብሪካ እሴት ጨምረው ሲሸጡ፣ ምርታቸውን ለአርሶ አደሩ ሲሸጡ ትርፍ ማግኘታቸው አይቀርም። የግብርና ፈጣን እድገት በሚረጋገጥበት ወቅት የግብርና ምርቶች ዋጋ ከሌሎች ምርቶች ጋር ሲነፃፀር መቀነሱ አይቀርም። በዚህ አማካኝነት ከግብርና ዘርፍ ወደሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚተላለፍ ካፒታልም ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። በተለይም በእድገት ሂደት የግብርና ምርት ዋጋ ከሌሎች ዘርፎች ምርት ዋጋ በላቀ ፍጥነት መቀነሱ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ገንዘብ ከአንዱ ዘርፍ (ከግብርና) ወደሌላው ዘርፍ (ኢንዱስትሪ) መተላለፉ አይቀርም። ነገር ግን ይህ ብቻ በቂ ሊሆን አይችልም።

በግብርናው ልማት ሂደት የአርሶ አደሩ ገቢ እየጨመረ መሄዱ አይቀርም። ከዚህ ውስጥ የተወሰነውን የግብርና ስራውን ለማሻሻል በግብርና ዘርፍ ኢንቨስት ያደርገዋል። የተወሰነውን ልዩ ልዩ ሸቀጦችና አገልግሎቶችን ይገዛበታል፣ ይህን በማድረግ ገንዘቡ ወደ ኢንዱስትሪና ንግድ ዘርፍ ይተላለፋል። እነዚህ ወጪዎች ዞረው ዞረው ለግብርናና ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኢንቨስትመንት መዋላቸው አይቀርም። ከዚህ ውጭ የሚያጠራቅመው ገንዘብም ይኖረዋል፣ ሊኖረውም ይገባል። ይህ ገንዘብ በተጠናከረ የፋይናንስ ስርአት ውስጥ ከገባ አርሶ አደሩም ወለድ ያገኝበታል። ሌሎች ዘርፎችም ብድሩን ተበድረው ለኢንቨስትመንት ስራ ይጠቀሙበታል። በሌላ አነጋገር ጠንካራ

www.abyssinialaw.com

የፋይናንስ ስርአት በገጠር መፈጠሩ ከግብርና የሚገኘው ልማትና የካፒታል ክምችት ለኢንዱስትሪ ልማትም እንዲያገለግል፣ የአገሪቱ አጠቃላይ እድገት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ አማራጭ የሌለው ይሆናል::

በዚህ ዘርፍ ላይ ለሚሰማሩ ተቋሞች ልዩ ግምት ሰጥተን ልናበረታታው የሚገባን የገጠር የፋይናንስ ስርአት መጠናከር ለግብርና ልማትም ሆነ፣ በግብርና ልማት የሚገኘውን ገቢ ለኢንዱስትሪ ልማት ለማዋል፣ በአጠቃላይም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገትን ለማምጣት መተኪያ የሌለው በመሆኑ ነው:: የህብረት ስራ ማህበራት በሌሉበት የምንፈልገው ልማት የማይኖረውን ያህል፣ የተጠናከረ የገጠር የፋይናንስ ስርአት በሌለበት የምንፈልገው ልማት ሊኖር አይችልም::

## 6.1. ባንኮችና የገጠር የፋይናንስ ስርአት፣

የገጠር ልማትን ስናስብ አርሶ አደሩ ከእጅ ወደአፍ ከሚያመርትበት የኢኮኖሚ ስርአት ተላቅቆ ለገበያ ወደሚያመርትበት የገበያ ኢኮኖሚ ስለመሸጋገር ነው የምንናገረው:: ይህን በመሰለው ኢኮኖሚ ውስጥ ደግሞ የገንዘብ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው:: ምርት ለማምረት የሚያስፈልጉ ግብአቶችንና መሳሪያዎችን ለመግዛት፣ ካመረቱም በኋላ ወደገበያ ለማጓጓዝና ለመሸጥ፣ ለኑሮ የሚያስፈልገውን የፍጆታ እቃ ለመግዛትም ሆነ ለመሳሰለው በገጠር ከፍተኛ የገንዘብ ዝውውር ሊኖር ይገባዋል:: ለአገራዊ ቁጠባችን መጠናከር የሚበጅ ቁጠባ የማሰባሰብ ስራም በገጠሩም ሊካሄድ ይገባዋል:: ከዚህ አኳያ የገንዘብ ድርጅቶች የተለየ ሚና ይጫወታሉ:: ለገጠርና ግብርና ልማት መፋጠን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከሚያደርጉት የገንዘብ



ድርጅቶች መካከል በገንዘባዊ አቅማቸው ደረጃ ሲመዘኑ በከተሞች ውስጥ የተመሰረቱ ዋና ዋና ባንኮች፣ የገጠር ባንኮችና የህብረት ስራ ማህበራት ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: በዚህ ቅደም ተከተል የሚጫወቱትን ሚና ቀጥለን እንዘረዝራለን::

በከተሞች ውስጥ የተመሰረቱ ዋና ዋና ባንኮች በተበጣጠሰ ማሳ ላይ የተመሰረተ የግብርና ስራ ላይ ለተሰማራው ሰፊ አርሶ አደር የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት አይችሉም:: ለአርሶ አደሩ በተናጠል ብድር በመስጠት፣ የአርሶ አደሩን ቁጠባ በማጠናከርና በማሰባሰብ፣ እንዲሁም ሌሎች የባንክ አገልግሎቶችን በመስጠት ስራ ላይ እንሰማራ ቢሉ አስተዳደራዊ ወጭው በጣም ስለሚከብዳቸው ለኪሳራ ሊዳረጉ ይችላሉ:: በመሆኑም በኛ አገር ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አገሮች ባንኮች ትርጉም ባለው ደረጃ ለአርሶ አደሮች በቀጥታ የባንክ አገልግሎት በመስጠት ስራ ላይ ሊሰማሩ አይችሉም:: አስተዳደራዊ ችግሮቹን በቀላሉ ሊወጣ የሚችል ሌላ ተቋም ሲኖር ነው ባንኮቹ በቀጥታ ሳይሆን በተቋሞቹ አማካኝነት የባንክ አገልግሎትን ለአርሶ አደሩ መስጠት የሚችሉት::

በባንኮችና በአርሶ አደሩ መካከል ሆነው በአገናኝነት ሊሰሩ ከሚችሉት ተቋሞች ውስጥ የህብረት ስራ ማህበራት በቅድሚያ ሊጠቀሙ የሚችሉ ናቸው:: ባንኮች የህብረት ስራ ማህበራት ለሚያከናውኗቸው የተለያዩ የግዥና የሽያጭ የኢንቨስትመንት ስራዎች ማበደር ይችላሉ:: የህብረት ስራ ማህበራቱ ተበድረው መልሰው ለአርሶ አደሩ ብድር እንዲሰጡ ማድረግም ይቻላል:: ከነዚህ አገልግሎቶች በተጨማሪ የህብረት ስራ ማህበረት የቁጠባ ገንዘብ በባንክ እንዲቀመጥና ሌሎችም የባንክ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል:: ይህን

www.abyssinialaw.com

ለማድረግ የሚያስፈልገው አስተዳደራዊ ወጭም የግል ባለሀብቶችን ለማገልገል ከሚያስፈልገው ወጭ ያንስ እንደሆነ እንጂ የሚበዛ አይሆንም፡፡

በደርግ ጊዜ የመንግስት ባንኮች በመመሪያ ለህብረት ስራ ማህበራት እንዲያበድሩ ይደረግ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ባንኮቹ የሚሰጡት ብድር አዋጪ መሆኑን በሚገባ ሳያጣሩ እያበደሩ የህብረት ስራ ማህበራቱ በጣም ደካማ የፋይናንስ አሰራርና አቅም እያላቸው ገንዘብ ተበድረው እያባከኑ ሁሉም ተያይዘው ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህ አሰራር ከቀረ በኋላ ደግሞ በአንድ በኩል አስተማማኝ የፋይናንስ አሰራርና አቅም ያላቸው የህብረት ስራ ማህበራት በሚፈለገው መጠን ባለመፈጠራቸው የባንክ አገልግሎት ጭራሹን ሲቋረጥ፣ ሻል ያሉ ናቸው ተብለው የሚታሰቡት በተለይም በቡና አምራች አካባቢዎች ያሉትም አሰራራቸው ያልተጠናከረና ለምዝበራ የተጋለጡ በመሆናቸው ችግሮች እየተፈጠሩ ይገኛሉ፡፡

በባንኮችና በህብረት ስራ ማህበራት መካከል ጠንካራ የባንክ አገልግሎት ግንኙነት መፈጠሩ በገጠር ጠንካራ የፋይናንስ ስርአት ለመፍጠርና የአገሪቱ የፋይናንስ ስርአት በአጠቃላይ በጥብቅ የተሳሰረና የተቆራኘ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ይሁንና ይህ ስራ አጥጋቢ በሆነ አኳኋን ሊፈፀም የሚችለው ግንኙነቱ በግልፅ የንግድ ግንኙነት ስርአቶችና መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ባንኮች ለህብረት ስራ ማህበራት ብድር መስጠት ያለባቸው ለማንኛውም ተገልጋይ እንደሚሰጡት ሁሉ፣ አዋጪነቱን፣ የብድሩን የመመለስ እድል የተበዳሪው የፋይናንስ አያያዝ ጠንካራና ስርአት የተከተለ መሆኑን በማረጋገጥ ብቻ መሆን አለበት፡፡ ለህብረት ስራ



ማህበራት ተብሎ የባንክ ብድር አሰጣጥ ስርአት ከሚፈቅደው ውጭ ማበደር ባንኮችና የህብረት ስራ ማህበራቱ ተያይዘው እንዲወድቁ ከማድረግ ባሻገር የሚያስገኘው ጥቅም የለም፡፡ በመሆኑም በጥብቅ መወገድ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የህብረት ስራ ማህበራትም የፋይናንስ አሰራራቸውን ሳያጠናክሩ፣ ከባንክ በሚያገኙት ብድር የተሻለ ገቢ አግኝተው ብድሩን እስከነወለዱ በወቅቱ ለመመለስ የሚችሉ መሆናቸውን ሳያረጋግጡ መበደር የለባቸውም፡፡ የባንክ ብድር የመንግስት ባንኮች ብድርም ቢሆን በግድ መመለስ ያለበት እዳ እንጂ ድጎማ ወይም ባለቤት የሌለው ገንዘብ አይደለም፡፡

የባንኮችና የህብረት ስራ ማህበራት በተሟላ የባንክ አገልግሎት መስጠት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ትስስር ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ በመሆኑ ይህንኑ ትስስር ለመፍጠርና ለማጠናከር መረባረብ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ይህ ስራ የመልካም ምኞት ጉዳይ ወይም በትእዛዝና በመመሪያ የሚፈፀም አለመሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ባንኮች የብድር አሰጣጥ ስርአታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ማጠናከርና ማሻሻል ይገባቸዋል፡፡ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጡት ብድርም በተለመደው የብድር አሰጣጥ ስርአት መሰረት ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በዚህ የባንክ አገልግሎት ለመጠቀም የሚችሉ የህብረት ስራ ማህበራትን መፍጠርና ማጠናከር ይገባል፡፡ የማህበራቱ የፋይናንስ አሰራር ስርአት የተከተለ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የባንክ ገንዘብ ተበድሮ አለመክፈል በፍፁም የሚታሰብ ነገር እንዳልሆነና መንግስት በህጉ መሰረት የህብረት ስራ ማህበራትን ንብረት በሃራጅ በመሸጥ ጭምር ማስከፈል እንደሚኖርበት በሚገባ የተገነዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

ባለፉት አመታት በባንኮችና በአርሶ አደሩ መካከል በመሆን የባንክ አገልግሎት በተለይም የብድር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አቅም ባለመፈጠሩ የክልል መንግስታት ፌዴራላዊ መንግስት የሚሰጣቸውን የባጀት ድጎማ በመያዣነት በመጠቀም ከባንክ ተበድረው አርሶ አደሮች ግብኣቶችን በብዛት ለመግዛት የሚያስችላቸው ብድር እንዲያገኙ አድርገዋል፡፡ ባንኮቹ ከፍተኛ ገንዘብ ለማበደርና ብድራቸውም በአስተማማኝ ሁኔታ በወቅቱ እንዲመለስ ለማድረግ ችለዋል፡፡ አርሶ አደሩ የግብአት በተለይም የማዳበሪያ መግዣ ብድር ለማግኘት ችሏል፡፡ የክልል መንግስታት በብዙዎቹ አካባቢዎች ብድሩን በተገቢው መንገድ ማስመለስ ቢችሉም አልፎ አልፎ ችግሮች ተፈጥረው ከባጀታቸው ለመክፈል ተገደዋል፡፡ ይህ አሰራር በወቅቱ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ጠቀሜታ ያስገኘ ቢሆንም የራሱ የተወሳሰቡ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የክልል መንግስታት የፋይናንስ ድርጅቶች ስላልሆኑ ሊሰጡ የሚችሉት አገልግሎት በጣም ውሱን መሆኑ አይቀርም፡፡ ለተወሰኑ ግብአቶች መግዣ የሚሆን ብድር ከማቅረብ አልፈው የተሟላ የብድር፣ ቁጠባን የማሰባሰብና የማጠናከር አገልግሎትና ሌሎችም የባንክ አገልግሎቶች መስጠት አይችሉም፡፡ አሰራሩ በአካባቢ አስተዳዳሪዎች፣ የግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ላይ ከፍተኛ አስተዳደራዊ ጫናን የሚፈጥር ከመሆኑም ባሻገር ሃላፊዎቹ አበዳሪም፣ ብድር አስመላሽም፣ የኤክስቴንሽን ሰራተኛም፣ እየሆኑ የስራ መዘበራረቅና መጋጨት ፈጥሯል፡፡ በአርሶ አደሩ በኩል ደግሞ ብድሩን እንደመንግስት ድጎማ ወይም  እንደመብት የማየትና በአግባቡ ያለመጠቀምና ያለመመለስ አዝማሚያዎችም አልፎ አልፎ ታይተዋል፡፡ በዚህ ምክንያትና በብድር አሰባሰብ ላይ



በታዩ ችግሮች ምክንያት ያጋጠሙ ከፍተኛ ችግሮችም አሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ሲታይ ይህ አሰራር ዘላቂነት የሌለውና በተቻለ ፍጥነት በሌሎች አሰራሮች መተካት ያለበት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

የባንኮችና የገጠር ባንኮች በቅንጅት መሰረት ለገጠር የፋይናንስ ስርአት መጠናከርና የፋይናንስ ስርአታችን በአገር አቀፍ ደረጃ በጥብቅ የተሳሰረ እንዲሆን ለማድረግ ይረዳል፡፡ የባንክ ለባንክ ብድር ስርአት (የገንዘብ ገበያ) መፈጠሩ በከተማና ገጠር ባንኮች መካከል ብቻ ሳይሆን በራሳቸው በዋና ባንኮች መካከልም ቅንጅት ፈጥሮ ጥቅም ላይ ያልዋለ ገንዘብ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ይረዳል፡፡ ይህንኑ ስርአት ለመፍጠር የሚያስችሉ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተው ተግባራዊ መሆን ጀምረዋል፡፡ ይሁንና ስርአቱ በሚፈለገው መጠን ተግባራዊ እየሆነ አይደለም፡፡ በተፈለገው ደረጃ እንዳይፈፀም እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን አጥንቶ በማስወገድ የአገራችን የባንክ ለባንክ ብድር ስርአት እንዲጠናከር ማድረግ የገጠር የፋይናንስ ስርአትን ለማጠናከርም ሆነ አጠቃላይ የፋይናንስ ስርአታችንን ለማሻሻል እጅግ ተፈላጊ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ የገጠር ባንኮች የገጠር ልማትን በማፋጠን፣ በግብርናና በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ጠንካራ ትስስርና መደጋገፍ እንዲኖር በማድረግ፣ የአገራችን የፋይናንስ ስርአት ቀልጣፋና አገሪቱን በመላ የሸፈነ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ያላቸው ሚና እጅግ በጣም ከፍተኛ ስለሆነ መንግስት ልዩ ድጋፍ ሊሰጣቸው የሚገባ ተቋማት ናቸው፡፡ በተለይም በሰው ሀይል ስልጠናና በመሳሰሉት የአቅም ግንባታ መስክ የሚሰጠው ይህ ድጋፍ ባንኮቹ በራሳቸው ውስጣዊ እንቅስቃሴ ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት ተወዳዳሪነታቸውን ለማጎልበት የሚያደርጉትን ጥረት የሚደግፍ

www.abyssinialaw.com

እንጂ በድኅማና በመሳሰሉ መንገዶች በመንግስትና በህብረተሰቡ ትከሻ ታዝለው እንዲኖሩ የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

## 6.2. የገጠር ባንኮች፣

ባለፉት አመታት የገጠር የፋይናንስ ስርአትን ከማጠናከር አኳያ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ስራ ተሰርቷል ሊባል የሚችለው የገጠር ባንኮችን በማቋቋምና በማጠናከር ረገድ የተደረገው ስራ ነው፡፡ በርካታ ድርጅቶች የገጠር ባንኮች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት አሟልተው በገጠር ባንክነት ተመዝግበው በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡ በአንዳንድ ክልሎች እነዚህ ባንኮች መላውን የክልሉን አርሶ አደር ለማገልገል የሚያስችል መዋቅር ዘርግተው በየአመቱ እያንዳንዳቸው በመቶ ሺ ለሚቆጠሩ አርሶ አደሮች የብድርና አጠቃላይ የባንክ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

የገጠር ባንኮች ለአንድ አመት ከአምስት ሺ ብር በታች የሆነ አነስተኛ ብድር በመስጠት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ የሚሰጡት ብድር የቡድን ብድር አሰጣጥ ስርአትን የተከተለ ነው፡፡ ብድሩ በአብዛኛው የግብርና ግብአቶችን ለመግዛት የሚውል ቢሆንም በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ በሌሎች መስኮችም የብድር አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ የአርሶ አደሩን የቁጠባ ባህል በማጠናከርና ቁጠባውን በማሰባሰብ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ነው፡፡ ሌሎች የባንክ አገልግሎቶችን መስጠት የጀመሩ ቢሆኑም በዚህ በኩል የሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሰዋል ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ባንኮቹ በተጠናከሩበት አካባቢ የገጠር የፋይናንስ ስርአት ዋነኛ ምሰሶ በመሆን ለግብርና ገጠር ልማት መተኪያ የሌለው ሚና በመጫወት ላይ ያሉ ቁልፍ ተቋማት ናቸው፡፡



ይሁንና እነዚህ ተቋማት በልዩ ልዩ ችግሮች ነፃ የሆኑ አይደሉም፡፡ የሚመሩበት ደንብና መመሪያ ከአንድ አመት በላይና ከአምስት ሺ ብር በላይ እንዲያበድሩ የማይፈቀድላቸው ስለሆነ የአገልግሎት አድማሳቸውን ገድቦታል፡፡ ብሄራዊ ባንክ ይህንኑ ገምግሞና አጥንቶ መመሪያዎቹን በማስተካከል የአገልግሎት አድማሳቸውን ለማስፋት የሚችሉበት ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ተቋሞቹ የተሟላና ሁለገብ የባንክ አገልግሎት በመስጠት ረገድ ከፍተኛ ጥረት አድርገው የአገልግሎት አድማሳቸውን ማስፋት መቻል ይኖርባቸዋል፡፡

የቡድን ብድር አሰጣጥ ስርአት የራሱ የሆኑ ከፍተኛ ጥቅሞች ያሉት በመሆኑ ለወደፊቱም ሊሻሻልና ሊጠናከር የሚገባው ነው፡፡ ይሁንና ይህን አሰራር እንደ ብቸኛ አማራጭ መውሰድ ተገቢ አይሆንም፡፡ የገጠር ባንኮች አስተማማኝ አቅም ላላቸው የህብረት ስራ ማህበራት ማበደርም ይገባቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የአርሶ አደሩን ምርት በመያዣነት በመያዝ ለአርሶ አደሮች በተናጠል የብድር አገልግሎት የመስጠት አማራጭ ክፍት መደረግ ያለበትና በሂደትም መስፋፋት ያለበት ነው፡፡ በተለይም የገጠር ባንኮችንና የህብረት ስራ ማህበራትን ትስስር ማጠናከር በገጠርና ግብርና ልማት ላይ ወሳኝ ተፅእኖ ያላቸውን እነዚህን ድርጅቶች በይበልጥ የሚያጠናክር ስለሚሆን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

የገጠር ባንኮች አርሶ አደሩ ምርቱን ለማሻሻል የሚያስፈልገውን ብድር በሚሰጡበት ወቅት አርሶ አደሩ በድርቅም ሆነ በሌላ ምክንያት ከተዳከመ እነሱም በዚያው መጠን የሚጎዱበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ በተግባር እንደታየው እንደዚህ አይነት ችግር በማያጋጥምበት ወቅት ባንኮቹ ብድር

www.abyssinialaw.com

በማስመለስ ላይ በጣም የተሳካ ስራ ነው የሚሰሩት። ይሁንና በድርቅ ወይም በሌላ ምክንያት ተበዳሪው ምርት ማምረት ሳይችል ቢቀር ብድር አመላለስ ላይ ችግር መፈጠሩ የማይቀር ነው። በተለይም እንደዚህ አይነቱ የምርት ማሽቆልቆል አርሶ አደሮችን በተናጠል የሚጎዳ ሳይሆን በአንድ አካባቢ የሚገኙትን በሙሉ ወይም በአብዛኛው የሚነካ ስለሚሆን የገጠር ባንኮች በነዚህ አካባቢዎች ያበደሯቸው ብድሮች ሁሉ ለአደጋ ተጋልጠው ችግሩን ያወሳስበዋል።

የግብርና ምርት ዋስትና ስርአት ሲፈጠር ይህ ችግር ሊቀንስ እንደሚችል እሙን ነው። ይህን የመሰለውን የዋስትና አገልግሎት በገጠር ማስፋፋት በጣም አስቸጋሪና ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ አይቀርም። ስለሆነም ቢያንስ ከአጭርና መካከለኛ ጊዜ አኳያ ሌላ መፍትሄ መፈለግ ይኖርበታል። ባንኮቹ የባንክ አገልግሎት ስርአታቸውን አድማስ ማስፋት መቻላቸው ለዚህ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል። ከግብርና ስራ በተጨማሪ ይህን ለመሰለ አደጋ በማይጋለጡ በሌሎች መስኮች የሚሰጡትን ብድር በመጨመር፣ አርሶ አደሩ በርካታ ምርቶችን አጣምሮ እንዲያመርት በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፍ፣ የገንዘብ ክፍያና የሃዋላ አገልግሎት በመሳሳሉት የባንክ አገልግሎቶች ላይ በመሳተፍ የገቢ ምንጫቸውን መሰረት ማስፋት አለባቸው። በአንድ አካባቢ በሚያጋጥም የምርት ማሽቆልቆል ሊደርስ ለሚችል አደጋ መጠባበቂያ የሚሆን በቂ ገንዘብ እንዲኖራቸው ለማድረግና ያልተከፈሉ ብድሮች በተራዘመ ሂደት የሚከፈሉበትን መንገድ በማፈላለግ መንቀሳቀስ ይገባቸዋል። ብሄራዊ ባንክ የገጠር ባንኮች ከላይ የተጠቀሱትንና መሰል ርምጃዎችን ለመውሰድ እንዲችሉ የተመቻቸ የህግ ማዕቀፍ መፍጠርና ባንኮቹን ማስተባበር መቻል ይኖርበታል።



የገጠር ባንኮች በገጠር ላይ ያተኮሩ ከመሆናቸው በስተቀር በባንክ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ የንግድ ድርጅቶች ናቸው። በገጠር ልማት ላይ ያላቸው ተፅእኖ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ እንዲጠናከሩ መንግስት ባለው አቅም ሁሉ መደገፍ ያለበት ቢሆንም ከፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን ይኖርባቸዋል። ብሄራዊ ባንክ እነዚህንም ባንኮች ለመቆጣጠር ባለው ሃላፊነትና ስልጣን በመጠቀም መቆጣጠር፣ ሊጠናከሩ የሚችሉበት የህግ ማዕቀፍ ለመፍጠር ደንቦቹንና መመሪያዎቹን በየጊዜ እየፈተሸ ማስተካከልና ባንኮቹ አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት ይገባዋል። የአካባቢ አስተዳዳሪዎች የባንኮቹ ብድር በህጉ መሰረት እንዲመለስ የተለመደውን ህጋዊ ድጋፍ በመስጠትና በሰው ሃይል ስልጠና ሊረዷቸው ይገባል። የአካባቢውን የልማት ዕቅድ እንዲያውቁና አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ ባንኮቹ የባንክ አገልግሎታቸውን ከዚህ አኳያ እንዲቃኙና እንዲያስተካክሉ ስለሚያስችላቸው ሊበረታታ የሚገባው አሰራር ነው። ድጋፍ በመስጠት ስም ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ነገሮች ውጭ ጣልቃ መግባት ግን በጥብቅ መወገድ ያለበት ጉዳይ ነው።

አልፎ አልፎ የአካባቢ አስተዳዳሪዎች ብድር ሊያገኙ ይገባል ለሚሏቸው አርሶ አደሮች ባንኮቹ ብድር እንዲሰጡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተፅእኖ የሚያሳርፉበት ሁኔታ ይታያል። የአካባቢ አርሶ አደሮችና አስተዳዳሪዎች በነዚህ ባንኮች የሚሰጥን ብድር እንደመብት፣ ከዚያም አልፎ እንደ ድጎማ የሚወስዱበት አጋጣሚም ይታያል። ከዚህ በመነሳት የባንኮቹ ብድር አሰጣጥ ላይ ተገቢ ያልሆነ ተፅእኖ የማሳረፍና ከዚህም ጋር ተያይዞ አርሶ አደሩ ብድር በመመለስ ላይ ያለው አመለካከት የመዳከም አዝማሚያዎች ይታያሉ። እነዚህ ችግሮች ካልተወገዱና ካልተስተካከሉ በስተቀር የገጠር ባንኮች ሊከስሩና

ከስራ ውጭ ሆነው በገጠር ልማት እንቅስቃሴያችን ላይ በጣም ከፍተኛ ችግር ሊፈጠር ይችላል።

## 6.3. የህብረት ስራ ማህበራት፣

የህብረት ስራ ማህበራት የግብርና ግብይት ስርአትን በማሻሻል ረገድ ያላቸው ወሳኝ አስተዋፅኦ እንደተጠበቀ ሆኖ በገጠር የፋይናንስ ስርአቱን በማጠናከርም ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው። በዋና ባንኮች፣ በገጠር ባንኮችና በአርሶ አደሩ መካከል አገናኝ ሰንሰለት በመሆን ያገለግላሉ። የራሳቸውን ባንክ በማቋቋም ሊሰሩም ይችላሉ። በአጭሩ የህብረት ስራ ማህበራት ሌሎች የፋይናንስ ተቋሞች አገልግሎታቸውን እንዲሰጡ በማስቻል ሳይወሰኑ እነሱ ሊሸፍኑዋቸው ያልቻሉ አገልግሎቶችን በመሸፈን በገጠር የፋይናንስ ስርአቱ ውስጥ በማንም የማይተካ ቦታ አላቸው።

የገጠር የፋይናንስ ስርአት እንዲስፋፋ የህብረት ስራ ማህበራት መጠናከር ከፍተኛ ትርጉም ያለው ስራ የሚሆነውም ያለነዚህ ማህበራት ሌሎቹ ተቋሞች ስራቸውን መሆን በሚገባው ደረጃ ለማከናወን ስለማይችሉና ሳይሸፈን የሚቀረውን የገጠር የፋይናንስ ስርአት በከፍተኛ ደረጃ ሊያዳክም የሚችል ክፍተት ስላለ ነው። ይሁንና የህብረት ስራ ማህበራት ይህንን ቁልፍ ተግባር ሊፈፅሙ የሚችሉት የራሳቸውን የፋይናንስ አሰራርና አቅም ማጎልበትና ማስተካከል ሲችሉ ነው። የተስተካከለ የፋይናንስ አሰራር ስለሌላቸው ለኪሳራና ለምዝበራ የሚጋለጡ የህብረት ስራ ማህበራት ሌሎችን ተቋሞች ይዞ ከመውደቅ በስተቀር ገንቢ ሚና ሊጫወቱ አይችሉም። የባንክ ብድር የግድ መመለስ ያለበት፣ በጥንቃቄ መያዝና የላቀ ገቢ በሚያስገኝ



አኳኋን ጥቅም ላይ መዋል ያለበት መሆኑን የማይገነዘቡ አባላትና መሪዎች ያሉዋቸው የህብረት ስራ ማህበራት ጥፋትን እንጂ ልማትን ማረጋገጥ አይችሉም።

አርሶ አደሩ የተበደረውን ብድር እየተራበም ቢሆን የመክፈል ልምድና ባህል ያለው የህብረተሰብ ክፍል ነው። ይህ ባህል በገጠር የፋይናንስ አገልግሎትን በማስፋፋት ረገድ መተኪያ የሌለው ሚና የሚጫወት ባህል ነው። ይሁንና ይህ እጅግ ጠቃሚና አኩሪ የሆነ ባህል አደገኛ በሆነ አኳኋን በመሸርሸር ላይ ይገኛል። የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድጎማ ነክ የሆኑ በአግባቡ የማይመለሱ ብድሮችን አልፎ አልፎ መስጠታቸው ለዚህ ባህል መሸርሸር አስተዋፅኦ አድርጓል። በመንግስት ወይም በመንግስት አስተባባሪነት በሌሎች ተቋሞች የሚሰጡ ብድሮችም በአግባቡ ስለማይመለሱና እንደመብትና ድጎማ እየተወሰዱ ስለሄዱ የብድር መመለስን ባህል በማዳከም ረገድ ከፍተኛ አሉታዊ ሚና ተጫውተዋል። የህዝቡን ብድር የመመለስ ባህል መልሰን ማጠናከር ካልቻልን በገጠር ፋይዳ ያለው የፋይናንስ ስርአት መገንባት አንችልም። ስለሆነም ብድሮችን ተከታትሎ ማስመለስ በጥብቅ የሚፈፀም እንዲሆን በማድረግ፣ ህዝቡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተሟላ ግልፅነት እንዲኖረው በማድረግና በመሳሰሉት መንገዶች የገጠር የፋይናንስ ስርአትን ለመገንባት የሚያስችለንን መሰረታዊ የአመለካከት ንጣፍ ማጠናከር አለብን።

በተደጋጋሚ እንደተገለፀው የገጠር ፋይናንስ ስርአት የምንፈልገውን ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችለን ቁልፍ መሳሪያ ነው። ጠንካራ የገጠር የፋይናንስ ድርጅቶችን መፍጠር ካልቻልን የልማት አላማችን ሁሉ መና ሆኖ መቅረቱ አያጠያይቅም።

በአሁኑ ወቅት ቁልፍ ሚና እየተጫወቱ ያሉት የገጠር ባንኮች ስለሆኑ እነሱን በይበልጥ ማጠናከር በጣም ተፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና የፋይናንስ ስርአታችን ስፋትና ጥልቀት ያለው ይሆን ዘንድ በአንድ አይነት ተቋምና አንድ አይነት አሰራር ላይ ብቻ መንጠልጠል የለበትም፡፡ የህብረት ስራ ማህበራትና ባንኮችም በዚህ ስርአት ውስጥ ትልቅ ሚና እንዲጫወቱ መደረግ አለበት፡፡ መገንባት የሚገባን የተለያዩ ተቋሞችና አሰራሮችን በማቀናጀት መጠቀምን መሰረት ያደረገ ስርአት ነው፡፡ እያንዳንዱ ተቋም ወይም አሰራር ያሉበትን ችግሮችና ውሱንነቶች እያጠናን በማስተካከል፣ ይህንኑ ስራ በቀጣይነት በመስራት ነው ጠንካራ የገጠር የፋይናንስ ስርአት መገንባት የምንችለው፡፡

## 7. የግል ባለሃብቶች በግብርና ልማት ዘርፍ በሰፊው እንዲሳተፉ ማበረታታት፣

የግል ባለሃብቶች በግብርና ልማት ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳላቸው እሙን ነው፡፡ በርግጥ በአሁኑ ወቅት በግብርና ልማት ዘርፍ ወሳኝ ሚና የሚጫወተው አርሶ አደሩ ነው፡፡ ይሁንና አርሶ አደሩ ወሳኝ ሚና በሚጫወትበትና መጫወትም በሚገባው በአሁኑ ወቅትም ቢሆን የግል ባለሃብቶች በግብርና ልማት ስራ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡ የግብርና ልማታችን እየተፋጠነ ሲሄድ የግል ባለሃብቶች ሚናም በዚያው መጠን እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ይልቁንም የሌሎች የበለፀጉ አገሮች ታሪክ የሚያረጋግጠው በሂደት ከአርሶ አደሩ አንዳንዶቹ በሌሎች የስራ መስኮች እየተቀጠሩ የቀሩት ደግሞ በግብርና ዘርፍ በሚያካሂዱት ስራ እየበለፀጉና የግል ባለሃብት ወደመሆን እየተሸጋገሩ የአርሶ አደሩ ሚና እየሚሸሸ፣ የግል ባለሃብቶች ሚና እየተጠናከረ እንደሚሄድ ነው፡፡ በአገራችንም የተሳካና



ፈጣን የግብርና ልማት ከተካሄደ በሂደት የአርሶ አደሩ ሚና በግል ባለሃብቶች እየተተካ እንደሚሄድ አያጠራጥርም፡፡ ይህ ሂደት የማይቀር የተሳካ የገጠር ልማት ውጤት ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥም አማራጭ የሌለው ሂደት ነው፡፡

በግብርና ዘርፍ የግል ባለሃብቶች በሰፊው መሳተፍ አለባቸው ስንል ከእንደዚህ አይነቱ የረጅም ጊዜ ራዕይ በመነሳት መሆን አለበት፡፡ በአሁኑ ወቅት ወሳኙ ሃይል አርሶ አደሩ መሆኑን ተገንዝበን ከአርሶ አደሩ ውስጥ በዚህ የልማት ሂደት ወደበለፀገ ገበሬነትና የግል ባለሃብት ወደመሆን እንደሚሸጋገርና ይህም ተጨባጭ የልማት ውጤታችን እንደሚሆን አውቀን በዚሁ የተቃኘ ስራ መስራት አለብን፡፡ አብዛኛው የገጠር ህዝብ በተራዘመ የተሳካ የልማት እንቅስቃሴ ሂደት ከግብርና ዘርፍ እየወጣ ወደሌሎች ዘርፎች እንደሚገባና በነዚህ ዘርፎች ተቀጥሮ የሚሰራ እንደሚሆን አውቀን ይህንኑ ሽግግር ለማሳካት በሚያስችል ቅኝት መስራት አለብን፡፡ ያስቀመጥነው የልማት አላማ እጅግ በተሳካ ሁኔታ ከተፈፀመ የመጨረሻው ውጤት ይኸው እንደሚሆን ተገንዝበን በአርሶ አደሩ ላይ የተመሰረተው አቅጣጫችን ይህንኑ በተቻለ ፍጥነት ለማስገኘት እንደሚችል አድርገን መፈፀም አለብን፡፡ የግል ባለሃብቱ በአሁኑም ወቅት ቢሆን በግብርና ልማት የላቀ አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት ስንል ለዘለቄታው ደጋፊ ሚና የሚጫወት ነው ከሚል ታሳቢ በመነሳት ብቻ ሳይሆን በሂደት ይኸው ሚና በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ እንደሚሄድ ታሳቢ በማድረግ ጭምር ነው፡፡

የግል ባለሃብቶች የግብርና ግብይት ስርአትን በማጠናከር ረገድ ተኪ የሌለው ሚና እንዳላቸውና ድርሻቸውን በአግባቡ

www.abyssinialaw.com

እንዲወጡ ለማድረግ ይህን ማድረግ እንደሚገባን ቀደም ሲል ተቀምጧል። የአግሮ-ፕሮሰሲንግ ተቋሞችን በማቋቋም የግብርና ልማታችንን በመደገፍና የኢንዱስትሪ ልማታችንን በማቀላጠፍም ረገድ ያላቸው ቁልፍ ሚናም የሚታወቅ ነው። በዚሁ ርእስ ስር ማተኮር የተፈለገው የግል ባለሃብቶች በግብርና ዙሪያ ሊኖራቸው በሚገባው አስተዋፅኦ ላይ ሳይሆን በራሱ የግብርና ምርት ከማስፋፋት አኳያ ሊጫወቱት በሚችሉትና በሚገባቸው ሚና ላይ ነው።

የግብርና ምርትን ለማስፋፋት የግል ባለሃብቶች የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ በሚመለከት በተለያዩ አርእስቶች ስር ተገልፇል። እነዚህን በዚህ አርእስት ውስጥ መድገም አስፈላጊ አይሆንም። እዚህ ላይ የምናተኮረው ልዩ ግምት ሊሰጣቸው በሚገባና ከዚህ በፊት ተገቢው ትኩረት ባልተሰጣቸው ነጥቦች ላይ ነው። የውጭ ባለሃብቶች ሚና፣ የግል ባለሃብቶችን በመፍጠር ረገድ የግብርና ስልጠና የሚኖረው ሚናና በግል ባለሃብቶችና በአርሶ አደሮች መካከል መኖር ስለሚገባው የምርት ትስስር ላይ ነው የምናተኩረው።

## 7.1. የውጭ ኢንቨስተሮችን ወደ ግብርና ዘርፍ መሳብ፣

የግል ባለሃብቶች በግብርና ልማት ዘርፍ በሁለት አጠቃላይ አቅጣጫዎች ሊሳተፉ እንደሚችሉ ይታወቃል። አንደኛው አቅጣጫ ሰፋፊ ያልታረሰ መሬት ባላቸው አካባቢዎች ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎችን በማቋቋም፣ ይህን እንደሁኔታው ከመስኖ ልማትም ሆነ ከአግሮ-ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ጋር ማያያዝን ይመለከታል። በዚህ መልኩ የሚካሄድ የግብርና ኢንቨስትመንት ከፍተኛ የገንዘብ ወጭ፣ ትልቅ



የካፒታል አቅም የሚጠይቅ ነው። ሌላው አማራጭ በውሱን መሬት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች (ምሳሌ ፍራፍሬዎች አበባዎች ወዘተ.) ማምረት ነው። እንደነዚህ አይነቶቹ ስራዎች ይህን ያህል ከፍተኛ የካፒታል አቅም የሚጠይቁ አይደሉም። ከዚህ ይልቅ የግብርና ሞያ ብቃትና ገበያዎችን ሰብሮ የመግባት ችሎታን የሚጠይቁ ናቸው። የግል ባለሃብቶች በሁለቱም አቅጣጫዎች በሰፊው የመሳተፋቸው አስፈላጊነት የማያከራክር ነው። በየደረጃው ያሉት የመንግስት አካላት ይህን በሚገባ ተገንዝበው በጥብቅ ማስፈፀም መቻል አለባቸው።

የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በነዚህ መስኮች እንዲሳተፉ መርዳትና ማበረታታት የግል ኢንቨስትመንትን ከማጠናከር አኳያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡ በተለይም በዝናብ በሚለሙ ሰፋፊ እርሻዎችና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ምርቶች በሚያመርቱ መለስተኛ እርሻዎችን በመሳሰሉ ከፍተኛ የካፒታል አቅም በማይጠይቁ መስኮች ላይ አሁን ካለው በላይ መሳተፍ ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም። ይሁንና የአገራችን ባለሃብቶች የካፒታል አቅማቸው በጣም ውሱን እንደሆነ ይታወቃል። እነሱ ባላቸው የካፒታል አቅም ብቻ እንንቀሳቀስ ከተባለ በግብርና ልማት ዘርፍ ማምጣት የምንችለውን ያህል ፈጣን እድገት ማረጋገጥ አይቻልም። በአንዳንድ የግብርና ሙያዎች ላይ ያላቸው እውቀትና ከአለም ገበያ ጋር ያላቸው ትውውቅም መለስተኛ ነው። በመሆኑም በአንድ በኩል የአገራችን ባለሃብቶች በዚሁ ዘርፍ ማድረግ የሚችሉትን የላቀ ተሳትፎ ለማረጋገጥ እየተንቀሳቀስን በሌላ በኩል ደግሞ የውጭ ባለሃብቶችን ወደግብርና ልማት ለመሳብ በሰፊው መስራት አለብን። በተለምዶ የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚሞከረው ከግብርና ውጭ ባሉ ዘርፎች ነው። ብዙውን ጊዜ ግብርና ግምት ውስጥ አይገባም።

www.abyssinialaw.com

በዚህ ላይ ያለው የተዛባ አመለካከት ተስተካክሎ የግብርና ዘርፍ የውጭ ኢንቨስትመንት ከሚፈለግባቸው ዋነኛ መስኮች አንዱ መሆኑ ታውቆ ካልተሰራበት እድገታችን እንደሚፈለገው ሊሆን አይችልም፡፡

የግል ኢንቨስትመንትን ወደግብርና ዘርፍ ለመሳብ የመሰረተ-ልማትና የሰራተኛ ጉልበት አቅርቦትን ከማሻሻል ጀምሮ፣ አርሶ አደሮችን በማስተባበር የመሬት ማከራየቱ ስርአት ለግል ኢንቨስትመንት መስፋፋት የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጥር እስከማድረግ ድረስ የሚሄዱ የተለያዩ ስራዎች መሰራት እንዳለባቸው ቀደም ሲል ተገልፃል፡፡ እነዚህ መሰራት ያለባቸው ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው የውጭ ባለሃብቶችን ለመሳብ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዘርፍ ታዋቂነት ካተፈሩት ኩባንያዎች ጋር በመገናኘት፣ በአገራችን ኢንቨስት እንዲያደርጉ መሰራት ስላለባቸው ጉዳዮች በመመካከር መስራት ይኖርብናል፡፡ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚያስችሉ አጠቃላይ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ተፈላጊና ቀዳሚው ተግባር ነው፡፡ ይህ ብቻውን ግን በቂ አይደለም፡፡ በዚህ ስራ ላይ ሊሰማሩ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ኩባንያዎችንና ባለሃብቶችን በበቂ ጥናት ላይ ተመስርተን በማፈላለግ፣ ከነሱ ጋር በመመካከርና በቅንጅት በመስራት ተጨባጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚያስችል ስራ መስራት አለብን፡፡ የፌዴራል መንግስትና የክልል መንግስታት ይህንን አሰራር በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ በመደጋገፍና በቅንጅት መንቀሳቀስ ይገባቸዋል፡፡



## 7.2. የግብርና ሞያ ስልጠናና የግል ባለሃብቶች ተሳትፎ፣

ዘመናዊ እርሻዎችን ለማስፋፋት በግብርና ስራ በተለያዩ ደረጃዎች የሰለጠኑ ሰራተኞች ያስፈልጋሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት እየተካሄዱ ያሉት የግብርና ስልጠና ፕሮግራሞች የአርሶ አደሩን የማምረት አቅም በማጎልበት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ዋናው የግብርና ልማት ሃይላችን ይኸው ስለሆነ በዚሁ ላይ ማትኮሩም ተገቢ ነው፡፡ የአርሶ አደሩን የቴክኖሎጂ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል የምርምር ሰራተኛ፣ ቴክኖሎጂ በማሸጋገርና አርሶ አደሩን በማሰልጠን የሚሰማራ የኤክስቴንሽን ባለሙያ፣ የእንስሳት ጤና ሃኪሞችና የህብረት ስራ ሞያተኞች በማሰልጠን መንግስት የግብርና ልማትን ለመደገፍ የሚያስችለው አቅም ለመፍጠር ነው ርብርብ እየተደረገ ያለው፡፡ ከዚህም ባሻገር የተማረውን አርሶ አደር የግብርና ሞያ ስልጠና በማሻሻል ዘመናዊ አርሶ አደሮችን ለመፍጠር ነው ዝግጅት እየተደረገ ያለው፡፡ ይህ ተገቢና ትክክለኛም ነው፡፡

ይሁንና የግብርና ስልጠናችን ከወዲሁም የግል ባለሃብቶችንም መደገፍና ማጠናከር መቻል አለበት፡፡ በሂደትም በግብርና ዘርፉችን የሚኖረው የግል ባለሃብቶች ተሳትፎ እየጨመረ ስለሚሄድ የግብርና የሞያ ስልጠና ስርአታችንም በሂደት ይህንኑ ማገልገል በሚያስችለው አኳኋን እየተስተካከለ መጓዝ አለበት፡፡ ተመራማሪዎችን፣ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰራተኞችን የእንስሳት ሃኪሞችን ለማሰልጠን የምናደርገው ስራ መንግስት በነዚህ ዘርፎች ለአርሶ አደሮች የሚሰጠውን አገልግሎት ከማጠናከር ባሻገር ተመሳሳይ አገልግሎት ለግል ባለሃብቶች ለመስጠትም ያስችለዋል፡፡ ስለሆነም ይህ ፕሮግራም እዚያው ሳለም የግል ባለሃብቶችን መደገፍ የሚችል ነው፡፡ ይሁንና ይህ ብቻ በቂ ነው ተብሎ ሊወሰድ አይችልም፡፡

በግል ባለሃብቶች በሚካሄዱ ዘመናዊ እርሻዎች የሚፈለጉና ትኩረት በተሰጠው ፕሮግራም ውስጥ በሚፈለገው ደረጃ ያልተሸፈኑ የስልጠና ስራዎች እንደሚኖሩ አያጠያይቅም፡፡ የግብርና ማሰልጠኛ ተቋሞቻችን በግብርና ዘርፍ ከተሰማሩት ባለሃብቶች ጋር በመመካከር የሚፈለጉት ስልጠናዎች ምን እንደሆኑ ለይተው ማወቅ፣ ይህንኑ ምክክር በቀጣይነት ማካሄድና በዚሁ ላይ ተመስርተው የስልጠና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት መቻል አለባቸው፡፡ ተቋሞቹ ለግል ባለሃብቶቹና ለሰራተኞቻቸው የአጫጭር ስልጠናም ሆነ የመደበኛ ስልጠና አገልግሎቶችን መስጠት መቻል አለባቸው፡፡ ከዚህም በላይ በዘርፉ የሚፈለገው ሞያተኛ ምን አይነት እንደሆነና በምን ያህል መጠን እንደሚፈለግ አጥንተው የተማሪ ቅበላና የስልጠና ፕሮግራማቸውን ከዚሁ አኳያ ማስተካከል መቻል አለባቸው፡፡ እነዚህ ተግባራት በአሁኑም ወቅት በተወሰነ ደረጃ መሰራት ይገባቸዋል፡፡ በሂደት ግን የዚህ አካሄድ ስፋትና አድማስ እየጨመረ እንዲሄድ መደረግ ይኖርበታል፡፡

በግብርና ሞያ ማሰልጠኛ ተቋም የሚሰለጥነው ሰው ስልጠናውን ከጨረሰ በኋላ አንድም በመንግስት አለያም በተለያዩ ድርጅቶች ተቀጥሮ ይሰራል ተብሎ ነው የሚገመተው፡፡ ሰልጣኙ ራሱም ከዚህ ውጭ የሚያስብ አይደለም፡፡ መንግስትም ከዚህ ውጭ የሚያስብ አይደለም፡፡ በርግጥ በአንድ ወቅት ከግብርና ኮሌጅ ተመርቀው ዘመናዊ እርሻ በማቋቋም እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡ ጥቂት ግለሰቦች እንደነበሩና አልፎ አልፎ አሁንም እንደሚታዩ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን እነኚህ በጣም ጥቂቶች በመሆናቸው የስልጠና ስርአቱ አጠቃላይ ቅኝት ተቀጣሪ ማሰልጠን እንጂ ስራ ፈጣሪን ማሰልጠን አይደለም የሚለውን



www.abyssinialaw.com

ድምዳሜ ለመቀየር ምክንያት የሚሆኑ አይደሉም፡፡ ይህ የአመለካከት ችግር በግብርና ሞያ ስልጠና ላይ ብቻ የታጠረ ሳይሆን የትምህርትና ስልጠና ስርአታችንን በአጠቃላይ የሚመለከት ነው፡፡

የግብርና ልማትን በማፋጠን ረገድ ተገቢ ድርሻውን የሚወጣ የግል ባለሃብት እንዲኖር ለማድረግ ከተፈለገ ይህ ቅኝት መስተካከል አለበት፡፡ የግብርና ሞያ ስልጠና ያገኙ ወጣቶች የራሳቸውን የግብርና ተቋም አቋቁመው በሞያቸው ሰርተው ለመኖርና ለሌሎችም የስራ ዕድል እንዲፈጥሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ስራ በመደገፍ በግብርና ስልጠና ተቋሞች ውስጥ ከሌሎች ስልጠናዎች በተጨማሪ የግል ተቋም የመፍጠርና የማስተዳደር ስልጠና፣ ማለትም ኢንተርፕረነርሺፕን የማጠናከር ስልጠና መሰጠት አለበት፡፡ ሰልጣኞቹ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ የግብርና ምርት ተቋም አቋቁመው በዚሁ ስራ ለመሰማራት የሚያስችል ፍላጎት፣ ዝግጁነትና ብቃት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ስልጠና ማግኘት አለባቸው፡፡

የግብርና ልማት ተቋሞችን መስርተው ለመኖር ፍላጎቱም ሙያውም ያላቸውን ሰዎች መፍጠር ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ተማሪዎቹ ሰልጥነው ከወጡ በኋላ ስራቸውን የሚሰሩበት መሬት ማግኘት መቻል አለባቸው፡፡ አንዳንዶቹ መነሻ የሚሆን ካፒታል ከራሳቸው ምንጭ ማግኘት የሚችሉ ቢሆኑም ሌሎቹ እንደዚህ አይነቱ አቅም የሌላቸው ናቸው፡፡ የክልል መንግስታት እንደነዚህ አይነቶቹ ሰዎች ለግብርና ስራ የሚሆን መሬት የሚያገኙበት የተፋጠነ ስርአት ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ ይህ ስራ የማይክሮና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማስፋፋት ፕሮግራም አንድ ቁልፍ አካል ተደርጎ ተወስዶ

www.abyssinialaw.com

ተማሪዎቹ ከዚሁ ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረግ አለበት:: የስልጠና ተቋሞች ራሳቸው በዚህ መልክ ለመሰማራት የሚፈልጉ ተማሪዎቻቸው ስልጠናቸውን ከመጨረሳቸው በፊት በተቻለ መጠን እንደነዚህ አይነት ተቋሞችን ለመፍጠር የሚያስችላቸውን ፕላንና ሌላም ቅድመ ዝግጅት አጠናቅቀው እንዲወጡ ሊያግዟቸው ይችላሉ:: ከዚያም አልፈው በዚህ ስራ ላይ ለመሰማራት ከሚፈልጉ ተማሪዎች ጋር በመመካከር ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላትና በዚሁ ረገድ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ ተብለው ከሚገመቱ ድርጅቶች ጋር እየተገናኙ ሁኔታዎችን ሊያመቻቹላቸው ይችላሉ:: ዋናው ነገር በግብርና ሞያ የሰለጠኑ ተማሪዎች በዚሁ ስራ የራሳቸውን ተቋሞች መስርተው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ የተሟላ እገዛ መስጠትና ስራው በቂ ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ ነው:: አፈፃፀሙ በሂደት እየተሻሻለ ሊሄድ የሚችልና የሚገባውም ነው::

ለማጠቃለል ያህል የግብርና ሞያ ስልጠና በግብርና ዘርፍ የተሰማሩ የግል ባለሃብቶችን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ሊታወቅ ይገባል:: በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች የሚፈልጉዋቸው ሞያተኞች በሚፈለገው መጠን መሰልጠናቸውን ማረጋገጥና ይህን ለማድረግ የሚያስችል ስርአት መፍጠር የመጀመሪያው ጉዳይ ነው:: በነዚህ ተቋሞች የሰለጠኑት ሰዎች ራሳቸውን ችለው የግብርና ስራ ተቋሞችን ፈጥረው እንዲሰማሩ፣ በሞያው የሰለጠኑ የግል ባለሃብቶች እንዲፈጠሩና እንዲበራከቱ ማድረግ ሁለተኛው ጉዳይ ነው:: የስልጠና ተቋሞቻችን አሁን ያላቸው ትኩረት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከላይ የተጠቀሰውን ስራ ደርበው መስራት መጀመር አለባቸው:: በሂደት ዋነኛ ስራቸው ይኸው እየሆነ እንደሚሄድም ሊታሰብ ይገባል::



## 7.3. የግል ባለሃብቶችና የአርሶ አደሩ የግብርና ምርት ትስስር፣

አርሶ አደሩ በግብርና ምርት ዘርፍ ምንና እንዴት መስራት እንዳለበት፣ የግል ባለሀብቱም በተመሳሳይ መልክ ምንና እንዴት መስራት እንዳለበት ተቀምጧል:: መንግስት ይጠቅማል ብሎ የሚያስበው አቅጣጫ ምን እንደሆነ ተዘርዝሯል:: አቅጣጫዎቹ በዚሁ መልኩ ሲቀመጡ አርሶ አደሩና የግል ባለሃብቶች በምርት ተግባር ላይ ሲሰማሩ በተናጠልና በየራሳቸው የሚፈፅሙት እንጂ በሁለቱም መካከል በራሱ በግብርና ስራ ላይ ትስስር እንደማይኖር የሚያመለክት መስሎ ሊታይ ይችላል:: በርግጥም በግብይትና በአግሮ ፕሮሰሲንግ መካከል የሚኖረው ጠንካራ ትስስር እንደተጠበቀ ሆኖ በግብርና ምርት ስራ ላይ ብዙውን ጊዜ በሁለቱ መካከል ጠንካራ ትስስር ላይኖር ይችላል:: ይሁንና በሁለቱ መካከል ትስስር ቢኖር ሁለቱም ተጠቃሚ አይሆኑም ማለት አይደለም:: የሁለቱንም ጥቅም በላቀ ደረጃ የሚያስጠብቅና የግብርና ልማት እንቅስቃሴያችንን የሚያቀላጥፍ ትስስር ሊኖር ይችላል::

ከነዚህ ትስስሮች ውስጥ በይበልጥ የሚታወቀውና በአገራችንም በሰፊው ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በአርሶ አደሩና በግል ባለሃብቶች መካከል የሚፈጠር የምርት ኮንትራታዊ ትስስር ነው:: ይህ አሰራር በተለምዶ የአውት ግሮወር አሰራር ተብሎ የሚታወቀው ነው:: የዚህ ኮንትራታዊ ግንኙነት መልኮች በጣም በርካታ ቢሆኑም መሰረታዊ መርሁ አርሶ አደሮች ከግል ባለሃብቶች ጋር በሚፈጥሩት የኮንትራት ግንኙነት መሰረት በባለ ሃብቱ እገዛ የሚያመርቱበትና አምርተው ለባለሃብቱ የሚሸጡበት ስርአት ነው:: በባለሃብቶችና በአርሶ አደሩ መካከል

www.abyssinialaw.com

የሚፈጠረው ይህ የምርት ኮንትራታዊ ትስስር በዋነኛነት አብዛኛው ህዝብ በሰፈረባቸው የአገራችን ደጋማ አካባቢዎች ላይ ሊሰራ የሚችልና የሚገባው ዋነኛው አቅጣጫ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ግንኙነት ባለሀብቱ በደጋማው የአገራችን ክፍሎች የሚመረቱና ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ሊቀርቡ የሚችሉ ምርቶችን ለማምረት የሚኖርበትን የመሬት እጦት አርሶ አደሩ ከቦታው ሳይፈናቀል ለመመለስ ከመቻላችንም በላይ የጋራ ተጠቃሚነትን በከፍተኛ ደረጃ እናጠናክራለን፡፡ ለዘመናዊ እርሻዎች በተመቹ የአገራችን ቆላማ አካባቢዎች ግን ባለሃብቱ ሰፊ መሬት ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ የአውት ግሮወር አሰራር ደጋፊ ሚና የሚጫወት ከመሆን አያልፍም፡፡

ለምሳሌ አንድ በአበባ ምርት ላይ የተሰማራ ባለሀብትን ብንወስድ በራሱ ማሳ ላይ ሰራተኞች ቀጥሮ አበባ ያመርታል፡፡ በዚህ ላይ ብቻ ሳይታጠር በአካባቢው ካሉ አርሶ አደሮችም ጋር የምርት ትስስርና ኮንትራት ይፈጥራል፡፡ የአበባ ዘሩን ወይም ችግኙን ይሰጣቸዋል፡፡ አበባውን እንዴት ማምረት እንዳለባቸው ያስተምራቸዋል፣ በየጊዜው የምክር አገልግሎት ይሰጣቸዋል፡፡ ምርቱን ካመረቱ በኋላ በምን ያህል ዋጋ እንደሚገዛቸው ይገልፅላቸዋል፣ ምርታቸውን ለሱው ይሸጣሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ባለሃብቶች የራሳቸው የአበባ ምርት ማሳ ሳይኖራቸው አርሶ አደሮችን በማስተባበርና በማሰራት ብቻ ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡

ሌላ ምሳሌ እንውሰድ፡፡ አንድ ባለሃብት አንድ የሻይ ቅጠል ፋብሪካና በዙሪያው ሰፋ ያለ የሻይ ቅጠል እርሻ ይመሰርታል፡፡ በዚህ ብቻ ግን አይወሰንም፡፡ በዙሪያው ያሉ አርሶ አደሮችን አሰባስቦ የሻይ ቅጠል ተክል እንዲተክሉ



ያደርጋል፡፡ ይህን ለማድረግ የሚያስችላቸው አቅርቦትና የቴክኒክ እገዛ ይሰጣቸዋል፡፡ ምርቱ ሲደርስ በምን ያህል ዋጋ እንደሚገዛቸውም ያስታውቃቸዋል፡፡ ምርቱ ሲደርስ ለባለሃብቱ ይሸጡለታል፡፡ የባለሃብቱ ፋብሪካ ከራሱ እርሻ ምርት በላይ መጠቀም የሚችል ስለሚሆን ለፋብሪካው በተጨማሪ ጥሬ ዕቃነት ይጠቀምበታል፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ይህ የኮንትራት ወይም የአውት ግሮወር አሰራር በርካታ መልኮችና አፈፃፀሞች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች መሰረታዊ መርሁን ለማስቀመጥ በቂ ናቸው፡፡ ይህ አሰራር የአርሶ አደሩንና የባለሃብቱን ጥቅም በላቀ ደረጃ ያስጠብቃል፣ የአገሪቱንም የግብርና እድገት በከፍተኛ ደረጃ ሊያፋጥን ይችላል፡፡

አርሶ አደሩ ይህን ወደመሰለው ኮንትራት በሚገባበት ወቅት የላቀ ገቢ የሚያስገኝ ምርት ለማምረት የሚያስችለው ዘር፣ የምክር አገልግሎትና የቴክኒክ እገዛ ይገኛል፡፡ ምርታማነቱ፣ የምርቱ ጥራት በከፍተኛ ደረጃ ስለሚሻሻል ጠቅላላ ገቢውም ይጨምራል፡፡ ላመረተው ምርት ገበያ የማፈላለግ ችግር የለበትም፡፡ ያመረተውን ምርት ሁሉ ደረጃውን እስከጠበቀ ድረስ በሚታወቅ ዋጋ የመሸጥ ዋስትና አለው፡፡ አርሶ አደሩ በዘመናዊ እርሻ ላይ ለመሰማራት እንቅፋት የሚሆኑበት ነገሮች ሁሉ ከባለሃብቱ ጋር በሚያደርገው ኮንትራት ይወገዱለታል፡፡ ይህ ኮንትራት፣ ኮንትራት በመሆኑ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ግዴታዎችንም ያስከትላል፡፡ ባለሃብቱ በዚህ ኮንትራት ላይ ተማምኖ ከፍተኛ ወጭ ስለሚያወጣ አርሶ አደሩ ምርቱን በሚፈለገው ጥራትና ዋጋ ለባለሃብቱ መሸጥ አለበት፡፡ እንደአጋጣሚ የተሻለ ዋጋ ካገኘ የተሻለ ዋጋ አግኝቼበታለሁ

ብሎ ለሌላ ሰው መሸጥ አይችልም፡፡ በቸልተኝነት የምርቱን መጠንና ጥራት ማጓደል የለበትም፡፡ ግዴታውን ካልተወጣ ካሳ መክፈል እንዳለበትም ማወቅ አለበት፡፡

ይህ ኮንትራታዊ ግንኙነት የግል ባለሃብቱንም በከፍተኛ ደረጃ ይጠቅመዋል፡፡ የተወሰነ ግብአትና የቴክኒክ ድጋፍ ብቻ በመስጠት ያለ ብዙ ወጭ ለገበያ የሚያቀርበውን ምርት በከፍተኛ ደረጃ መጨመር ይችላል፡፡ አርሶ አደሩ በራሱ ማሳ ለራሱ ጥቅም የሚሰራ በመሆኑ ያለተቆጣጣሪ ሌት ተቀን እንደሚሰራ በዚህም ምክንያት በባለ ሃብቱ ማሳ ላይ ካለው የምምረቻ መንገድ ውጭ ምርት አምርቶ ዝቅ ባለ ዋጋ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ይህም የባለሃብቱን ትርፍ ያሻሽልለታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የገበያውን ሁኔታ እያየ ለገበያ የሚያቀርበውን ምርት በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ አርሶ አደሮችን በማሳተፍ ማስፋት ይችላል፡፡ መቀነስ ካስለፈገም ኮንትራቱን ሳይነካ ወደሌላ ምርት በመሸጋገር ወይ የተሳታፊ አርሶ አደሮችን ቁጥር በመቀነስ ሊያስተካክል ይችላል፡፡ ነገር ግን ጥቅሙን ብቻ መውሰድ አያስኬድም፡፡ ባለሃብቱም በኮንትራቱ መሰረት ለአርሶ አደሩ የተሟላ ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡ በኮንትራቱ በሚስማሙበት ዋጋ መሰረት አርሶ አደሩ ያመረተውን ምርት በሙሉ መግዛት አለበት፡፡

ይህ አሰራር ለአርሶ አደሩም ሆነ ለባለሃብቱ ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ በምርት ስራ ላይ የተሰማሩት ሁለቱ ወገኖች የምርታቸው ጥራትና ምርታማነታቸው እንዲሁም፣ ገበያ ሰብሮ የመግባት አቅማቸው ተሻሽሎ ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚያደርጉት አስተዋፅኦ እንደሚሻሻልም ገሃድ ነው፡፡ በሰፊው ቢሰራበት አገሪቱንና የሚመለከታቸውን ወገኖች ሁሉ የሚጠቅም ነው፡፡ በየደረጃው የሚገኙ ሃላፊዎች



ይህንኑ ተገንዝበው የአርሶ አደሮችና የግል ባለሃብቶች የምርት ትስስር ስርአትን ለማጠናከርና ለማስፋፋት ቆርጠው መነሳት ይገባቸዋል፡፡

ይህ አሰራር በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ከተፈለገ ሁለቱ ወገኖች እንዲገናኙ፣ እንዲተዋወቁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው የኮንትራት ግንኙነት እንደመሆኑ መጠን በሁለቱም ወገኖች መተማመንና ኮንትራቱ ላይ የተቀመጡትን ነገሮች በሙሉ ለመፈፀም ዝግጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ኮንትራቱ ግልፅና የሁለቱንም ወገኖች ጥቅም በትክክል የሚያስከብር መሆን ይኖርበታል፡፡ ማንኛውም ወገን ኮንትራቱን ቢያፈርስ አፋጣኝ የማስተካከያ ርምጃ ለመውሰድ የሚችል አካል መኖር አለበት፡፡ እነዚህ ነገሮች ካልተሟሉ በስተቀር ይህ ትስስር ሊፈጠርና ሊስፋፋ አይችልም፡፡ መንግስት ልማታችንን ለማፋጠን ካለው ሃላፊነት በመነሳትና የአውት ግሮወር አሰራር ከዚሁ አኳያ ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ ለአሰራሩ መስፋፋት የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች ለማሟላት መንቀሳቀስ አለበት፡፡

በአርሶ አደሩና በባለሃብቱ መካከል ተገቢውን ግንኙነት ከመፍጠርና ከማጠናከር አኳያ የአገራችን የምርምር ተቋማት ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም፡፡ በንግድም ሆነ በምርት ተግባር ላይ የተሰማራው የአገራችን ባለሃብት በምርቱ ጥራት የውጭ ገበያን ሰብሮ ለመግባት እንዲችል ከአርሶአደሩ የሚያገኘው ግብአት ጥራቱ የተጠበቀና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብለት ሊሆን ይገባዋል፡፡ አርሶ አደሩ ይህን የመሰለ ጥራት ያለውና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ ምርት ሊያመርት የሚችለው ደግሞ የምርምር ተቋማት ከፍተኛና ጥራት ያለው

www.abyssinialaw.com

ምርት የሚሰጡ ዝርያዎችን በቀጣይነት ሲያቀርቡለት፣ የአስተራረስ አግባቡን በማሻሻል ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ሲያግዙት ነው፡፡ ስለዚህም በአርሶአደሩና በባለሃብቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ስንሰራ የምርምር ተቋሞች ይህን ግንኙነት ከማጎልበት አኳያ ሊጫወቱ የሚችሉትንና የሚገባቸውን ሚና በአግባቡ እንዲጫወቱ እያደረግን መሆን ይገባዋል፡፡

ምንም እንኳ ትስስሩ በሁለቱ ነፃ ወገኖች ማለትም በአርሶ አደሩና በባለሃብቱ መካከል የሚካሄድ ኮንትራታዊ ትስስር ቢሆንም መንግስት ይህንኑ መሰረታዊ መርህ በማይጥስ አኳኋን ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ በዚህ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶችን በማፈላለግና አርሶ አደሮችን በማስተባበር ሁለቱንም ወገኖች የማገናኘት ስራ መስራት ይችላል፣ ይገባዋልም፡፡ ኮንትራቱ የሁለቱንም ወገኖች ጥቅም የሚያስከብር እንዲሆን የምክር አገልግሎት መስጠት ይችላል፣ ይህን ለማድረግ የሚረዱ ሞዴል ኮንትራቶችን ማዘጋጀትም ይችላል፡፡ ሁለቱም ወገኖች በኮንትራቱ መሰረት ያለባቸውን ሃላፊነት በሚገባ እንዲያውቁ የማስረዳትና ኮንትራቱን ለማስፈፀም ያላቸውን ዝግጁነት የማጠናከር ስራ መስራት አለበት፡፡ ማንኛውም ወገን ኮንትራቱን የሚያፈርስ ስራ ቢሰራ በህጉ መሰረት ፈጣን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አለበት፣ ሁለቱም ወገኖች ይህንኑ አስቀድመው ተገንዝበው እንዲገቡ ማድረግም ይገባዋል፡፡

## 8. የገጠር መሰረተ-ልማትን ማስፋፋት፣

የግብርና ልማትን ለማፋጠንም ሆነ አጠቃላይ የገጠር ልማትን ለማረጋገጥ የተሟላና ቀልጣፋ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ



መሰረተ-ልማት አገልግሎት መሟላት ወሳኝ ነው፡፡ የተሟላና ውጤታማ የትምህርት የስልጠናና የጤና አገልግሎት በሌለበት ሁኔታ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርናም ሆነ አጠቃላይ የገጠር ልማት ሊኖር አይችልም፡፡ የተሟላ የገጠር መንገድና ትራንስፖርት አገልግሎት በሌለበት ቀጣይነት ያለው ፈጣን የገጠር ልማት ሊታሰብ አይችልም፡፡ የገጠር ልማትና የመሰረተ-ልማት አገልግሎት መስፋፋት በፍፁም የማይነጣጠሉና ተያይዘው መሄድ ያለባቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ይልቁንም መንግስት የመሰረተ-ልማት አገልግሎቶችን ለማስፋፋት ካለው የላቀ ሚናና ሃላፊነት አኳያ ሲታይ የገጠር መሰረተ-ልማቶችን ማስፋፋትና እንዲስፋፉም ማስተባበር በገጠር ልማት ዘርፍ የሚሰራው ዋነኛ ስራ ነው ማለት ይችላል፡፡ መንግስት ዋነኛ ስራው የገጠር መሰረተ-ልማትን ማስፋፋትና እንዲስፋፉ ማድረግ፣ ሁለተኛ ስራው አርሶ አደሩን ለልማት ማነሳሳት፣ ማስተባበርና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታን መፍጠር ነው ማለት ይችላል፡፡

### 8.1. የትምህርትና የጤና ጥበቃ አገልግሎትን ማስፋፋት፣

የምንከተለው የልማት ስትራተጅ የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣ የህዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበት ረገድ የትምህርትና ስልጠና እንዲሁም የጤና ጥበቃ አገልግሎት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው መንግስት የገጠር ልማትን ለማፋጠን ከሚሰራቸው ዋነኛ ስራዎች እነዚህን አገልግሎቶች ማስፋፋት እንደሆነና እነዚህን እንዴት መፈፀም እንደሚገባ ቀደም ሲል በዝርዝር ቀርቧል፡፡ እነዚህ አገልግሎቶች በየቀበሌው በተመረጡ ማዕከላት መቋቋማቸውና

www.abyssinialaw.com

በነዚህ ማዕከላት እንዲሰባሰቡ የማድረጉ አስፈላጊነትም ተገልፃል። በዚህ ርእስ ስር እነዚህን ቀደም ሲል የተዘረዘሩትን ነጥቦች መድገም አስፈላጊ አይሆንም። አንድ ሊሰመርበት የሚገባ ነጥብን ብቻ አንስተን ወደሚቀጥለው ርዕስ መተላለፍ ተገቢ ነው።

እስካሁን የቀረበው ትንተና ላይ የጤና፣ የትምህርትና የስልጠና አገልግሎት የአርሶ አደሩን የማምረት አቅም ከማጎልበትና፣ ምርትን ከማሳደግ አኳያ ባላቸው ትርጉም ላይ ያተኮረ ነው። እነዚህ አገልግሎቶች ምርትን ለማሳደግ የላቀ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው፣ ምርትን ማሳደግ ደግሞ የህዝቡን ሁለንተናዊ ኑሮ የማሻሻል ስራ መስራት በመሆኑ አገልግሎቶችን በቅድሚያ ከዚህ አኳያ መተንተንና በዚህ አላማ የተቃኙ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊና ተገቢ ነው። ይሁንና የነዚህ አገልግሎቶች ፋይዳ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። እነዚህ አገልግሎቶች የልማት መሳሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ የልማት ውጤቶችና የተሻሻለ ኑሮ መገለጫዎችም ጭምር ናቸው።

የዜግነት መብቶች ለተማረውም ላልተማረውም ሰው በእኩልነት የሚከበሩና በእኩልነት መከበርም ያለባቸው መብቶች ናቸው። ይሁንና ያልተማረ ሰው በእነዚህ መብቶች በሰፊውና በብቃት የመጠቀም አቅሙ ውሱን ነው። ይህ በመሆኑም ነው ብዙዎች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መማር የዜግነት መብትና ግዴታ ነው የሚሉት። ከዚህ በመነሳት ነው መንግስት በተቻለ ፍጥነት ሁሉም ዜጎች ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ ያለበት። ይህ ትምህርት ከአገራችን ፈጣን እድገት ጋር መያያዙና በዚሁ መቃኘቱ ተገቢ ቢሆንም የትምህርት አገልግሎት ልማታዊ ፋይዳው ምንም ይሁን ምን የአንደኛ



ደረጃ ትምህርት የዜግነት መብት በዜግነት መብቶች በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል መሰረታዊ ትጥቅ በመሆኑ በአፋጣኝ መስፋፋት እንዳለበት ሊታመንበት ይገባል። የአንደኛ ደረጃም ሆነ ከዚያ በላይ ያለው ትምህርት መልካም አምራች ዜጋን የማፍራት ተልእኮ እንዳለው ታውቆ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል ይዘት እንዲኖረው መደረግ አለበት።

ትምህርት ከዚህም ባሻገር አንድ ሰው አእምሮውን ነፃ የሚያወጣበት፣ የእውቀትና የአስተሳሰብ አድማሱን የሚያስፋፋበት ትልቅ መሳሪያ ነው። በመሆኑም የትምህርት አገልግሎት መስፋፋት በቂ ምግብና ልብስ፣ ጥሩ የመኖርያ ቦታ ወዘተ. የማግኘት ያህል የኑሮ መሻሻል መገለጫና የልማት በጎ ውጤት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ትምህርት ከሌሎች ጥቅሞቹ በተጨማሪ በልማት እንደሚገኝ ማንኛውም የኑሮ መሻሻል ራሱን የቻለ አላማ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። መንግስት የትምህርት አገልግሎትን ለማስፋፋት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች በተቻለ ፍጥነት ለማዳረስ የሚረባረበው ከላይ የተጠቀሱትን አላማዎች በሙሉ በመያዝ ነው።

የጤና ጥበቃ አገልግሎትም በተመሳሳይ መልኩ የሚታይ ነው። ጤናማ አምራች ዜጋን መፍጠር ለልማት ያለው አስተዋፅኦ እንደተበጠቀ ሆኖ የተሟላ ጤንነትን ማግኘት ራሱን የቻለ አላማም ጭምር ነው። በተሻለ ቤት ውስጥ እንደመኖርና በቂ ምግብ እንደማግኘት ሁሉ የተሟላ ጤንነት በልማት ሂደት መሟላት ከሚገባቸው ዋነኛ አላማዎችና ግቦች አንዱ ነው። መንግስት ዜጎች በሙሉ የተሟላ ጤንነት እንዲያገኙ፣ አገልግሎቱ ለሁሉም ዜጎች ፍትሃዊ በሆነ አኳኋን እንዲዳረስ፣

አገሪቱ ባላት አቅም ይህን ማድረግ የሚቻለው በመሰረተ-ጤና አገልግሎትና በመከላከል ላይ በማተኮር መሆኑ እንዲሰመርበት የሚያደርገው ከላይ የተጠቀሱትን አላማዎች በሙሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

## 8.2. የገጠር መንገድና ትራንስፖርት አገልግሎትን ማጠናከር፣

በገበያ የሚመራ የግብርና ልማት ቀልጣፋ የመንገድና የትራንስፖርት አገልግሎት በሌለበት ሊታሰብ አይችልም። በገጠር የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት የሚቻለው ቀልጣፋ የመንገድና ትራንስፖርት አገልግሎት ሲኖር ነው። ስለሆነም የመንገድና የትራንስፖርት አገልግሎትን ማስፋፋት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የገጠር ልማት ለማረጋገጥ መወሰድ ካለባቸው ቁልፍ ርምጃዎች አንዱ ነው።

ስለገጠር መንገድና ትራንስፖርት መስፋፋት በሚነሳበት ወቅት መረሳት የሌለበት አንድ መሰረታዊ ጉዳይ አለ። የገጠር መንገድ ዞሮ ዞሮ ትርጉም የሚኖረው ገጠሮቻችንን ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማእከሎች እንዲሁም ከአለም ገበያ ጋር በማስተሳሰር በሚኖረው ፋይዳ ነው። የገጠር መንገዶች ጠቃሚ የሚሆኑት የአንድ አገር አቀፍ የመንገድ መረብ አካል ሲሆኑ ነው። ፈጣን አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ዋና መንገዶች በሌሉበት የገጠር መንገድ ቢስፋፋም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የገጠር ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል አይሆንም። ከዚህ በመነሳት ነው ፌዴራል መንግስት ዋና ዋና መንገዶችን በመስራት ስራ ላይ የሚያተኩረው። ፌዴራል መንግስት ዋና ዋና መንገዶችን ሲያስፋፋ በየክልሉ እኩል ርዝማኔ ያላቸው



መንገዶችን ለመስራት ሳይሆን አገሪቱን በሞላ በቀልጣፋ የትራንስፖርት መረብ ለማስተሳሰር በሚል አላማ መመራት ያለበት ከዚህ በመነሳት ነው። ይህም በመሆኑ ነው አገር አቀፍና ቀልጣፋ የመንገድ መረብን ለመፍጠር በየትኛውም አካባቢ የሚሰራው ስራ የሁሉንም አከባቢዎች ህዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ ስራ የሚሆነው።

ፌዴራል መንግስት ሁሉንም የአገራችንን አካባቢዎች ከዋና ዋና የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማዕከሎችና ከአለም ገበያ ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችሉ፣ ፍትሃዊ በመሆነ መንገድ የተመረጡ መንገዶችን የመገንባት ስራ ሲሰራ፣ ክልሎች በበኩላቸው የገጠር መንገዶችን በመስራት ገጠሮቻችንን ከዋና ዋና መንገዶች ጋር የሚያቀራኙ የመንገድ መረቦችን መስራት አለባቸው። ይህም ሆኖ ትላልቅ የልማት ማዕከል ሊሆኑ የማይችሉ ቦታዎች ለልማት ክፍት እንዲሆኑ የሚያደርጉ ዋና መንገዶችን የመስራት ስራ የፌዴራል መንግስት መሆን አለበት። ይህ ስራ በዘፈቀደ የሚሰራ ሳይሆን መረቡ ምን መምሰል እንዳለበት እቅድ ወጥቶለት መሰራት ያለበት ነው። የራሱ ቅደም ተከተል ሊኖረውም ይገባል። በመጀመሪያ ደረጃ የወረዳ ማዕከሎችን፣ ከዋና ዋና መንገዶች ጋር የማስተሳሰር ስራ መሰራት አለበት። ከወረዳዎች ቀጥሎ ቀበሌዎችን ከወረዳ ማዕከሎችና ከዋና ዋና መንገዶች ጋር የማስተሳሰር ስራ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ከዚህም ውስጥ ከፍተኛ የህዝብ ክምችት ያላቸው፣ መንገድ በተነፃፃሪ በቀላሉ ሊሰራላቸው ለሚችሉ ቀበሌዎች ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። ቀበሌዎችን ከወረዳ ማዕከሎችና ከዋና ዋና መንገዶች ጋር ለማስተሳሰር የሚሰሩ መንገዶች የቀበሌ ማዕከል ተብለው ወደ ተመረጡትና ትምህርት ቤት፣ ጤና ኬላ ወዘተ. የሚሰራባቸው ቦታዎች የሚያስገቡ መሆን አለባቸው።

www.abyssinialaw.com

የገጠር መንገዶች በቀን ሊሸከሙት ከሚችሉት የመኪና ብዛት አኳያ የተቀመጠ የደረጃ ምደባ አላቸው፡፡ በቀን አስር መኪና ማሳለፍ ከሚችሉት ጀምሮ በቀን ሃምሳ መኪና ማሳለፍ እስከሚችሉት መንገዶች ድረስ ያሉት በገጠር መንገድነት የሚመደቡ ናቸው፡፡ የሚጠይቁት ወጪም ከደረጃቸው ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡ በገጠር መንገድ አሰራራችን ላይ አልፎ አልፎ ከሚታዩት ችግሮች አንዱ በሳምንት አስር መኪና በማያልፍበት አካባቢ በቀን ሰላሳ ወይ ሃምሳ መኪና የሚያሳልፍ መንገድ የመስራት አካሄድ ነው፡፡ ይሄ አሰራር በሌለን ገንዘብ ላይ ከፍተኛ የገንዘብ ብክነት እንዲኖር የሚያደርግ፣ ገጠሮቻችን የሚያስፈልጋቸውን መንገድ ተፈላጊ በሆነው ደረጃ በአፋጣኝ እንዳያገኙ እንቅፋት የሚሆን አሰራር ነው፡፡ በጥብቅ መወገድ ያለበት አሰራር ነው፡፡

የገጠር መንገድ በምንሰራበት ወቅት ከፍተኛ ትራፊክ ያለበት መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር በዝቅተኛው ደረጃ ነው መጀመር ያለብን፡፡ ዝቅተኛ ደረጃ ያለው መንገድ በሚሰራበት ወቅት በሂደት የትራፊኩ መጠን እያደገ እንደሚሄድ ታሳቢ ያደረገና፣ እንደዚህ አይነቱ እድገት ሲመጣ የመንገዱን ደረጃ ከፍ የማድረግ ስራ እንደሚሰራ ታሳቢ ተደርጎ የሚቀየስ መሆን አለበት፡፡ በዚህ መልክ በፍጥነት በቂ የመንገድ አገልግሎት ለሁሉም ገጠሮቻችን ማዳረስ እንችላለን፡፡ በዝቅተኛ ደረጃ ከተሰሩት መንገዶች ውስጥ ከፍተኛ የትራፊክ እድገት የታየባቸውን መርጠን በትራፊኩ እድገት መጠን መንገዶቹን በቀጣይነት እናሻሽላለን፡፡ በዚህ መሰረት መንገዶቹ በዝቅተኛ ደረጃ መንገድነት ጀምረው ደረጃ በደረጃ የአስፋልት መንገድ እስከመሆን ድረስ ሊሄዱ እንደሚችሉ ታሳቢ መደረግ አለበት፡፡



የገጠር መንገዶችን በፍጥነት ማስፋፋት የሚቻለው በሰው ጉልበት የሚሰሩ፣ ለዚሁ በሚያመች አኳኋን የተሰራ ዲዛይን ያላቸውና በመለስተኛ ሞያተኛ ክትትል ሊሰሩ የሚችሉ ሲሆኑ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተም መንገድ በምንሰራበት አካባቢ ሁሉ የትራፊኩ መጠን ከሚጠይቀው በላይ ደረጃ ያላቸው መንገዶችን ከመስራት ዝንባሌያችን ጋር ተያይዞ የመንገዶቹ አቀያየስ ቀላል ያልሆነ ማሽነሪና የላቀ ሞያ ያላቸው ተቆጣጣሪዎችን የሚጠይቅ የመሆን ችግር ይታይበታል፡፡ በዚህ በኩል ያለብንን ችግር በመገምገም የሌሎች አገሮችንና የራሳችንን ልምድ በመቀመር፣ በተራ ጉልበት በቀላሉ ሊሰሩ የሚችሉ በመለስተኛ ሞያተኞች ክትትል ሊፈፀሙ የሚችሉ መንገዶችን የመቀየስና የመስራት ስርአት መገንባትና ልምዱንም ማካበት አለብን፡፡

በገጠር መንገድ ግንባታ ጉዳይ ላይ የሚታየው ሌላው ችግር የጥገና ችግር ነው፡፡ መንገዶች ከተሰሩ በኋላ በቂና ቀጣይ ጥገና ስለማያገኙ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከጥቅም ውጭ ይሆናሉ፡፡ የገጠር መንገዶች ክትትልና ጥገና ስርአት ከሌለ በስተቀር መንገዶች እየገነቡ ማፍረስ ስለሚሆን ልማትን የሚያረጋግጥልን አይሆንም፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የባለቤትነትን ጉዳይ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ የገጠር መንገዶች ባለቤት በየአካባቢው ያለው ህዝብ መሆን አለበት፡፡ ህዝቡ መንገዶቹን በመሰራት ተግባር ላይ በጉልበት በሰፊው ከመሳተፍ በተጨማሪ መንገዶቹን በባለቤትነት ተረክቦ በየአቅራቢያው ያሉትን መንገዶች የመጠገንና የመንከባከብ ሃላፊነት መውሰድ አለበት፡፡ ህዝቡ የዚህን አሰራር አስፈላጊነት እንዲገነዘብና በእምነት እንዲፈፅመው ጥረት መደረግ አለበት፡፡ የቀበሌ

www.abyssinialaw.com

አስተዳዳሪዎች ይህንኑ ስራ የመፈፀምና የማስተባበር ሃላፊነትን እንዲሸከሙ ማድረግና በውል የሚታወቅ የመንገድ ጥገናና እንክብካቤ ስርአት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ቀበሌዎቻችንን (የቀበሌ ማዕከላትን) ከወረዳ ማዕከሎችና ከዋና ዋና መንገዶች ጋር አስተሳስረን የገጠርና የግብርና ልማታችንን ለማፋጠን ከትራፊኩ መጠን ጋር የሚሄድ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው በጉልበት የሚሰሩ መንገዶችን መቀየስና መስራት አለብን ማለት ብቻ በቂ አይሆንም፡፡ እነዚህን መንገዶች ለመቀየስና አሰራራቸውን ለመከታተል የሚችል፣ ህዝቡ መንገዶችን የመጠገንና የመንከባከብ ሃላፊነቱን እንዲወጣ የቴክኒክ እገዛ፣ ስልጠናና ቁጥጥር አገልግሎት ለመስጠት የሚችል አቅም በየወረዳው መገንባት አለበት፡፡ ይህንኑ ስራ ለመስራት የሚያስፈልገው ስልጠና ታውቆ ስራውን ለመስራት የሚችሉ ሞያተኞች በተቻለ ፍጥነት ሰልጥነው በየወረዳው የሚፈለገው አቅም እንዲፈጠር መደረግ አለበት፡፡

በአገራችን የትራንስፖርት አገልግሎት ማለት አንድም መኪና ነው አለያም የሰው ወይም የጋማ ከብት ጀርባ ነው፡፡ በነዚህ በሁለቱ ጫፎች መካከል በርካታ አማራጮች ቢኖሩም በሚፈለገው ደረጃ የተስፋፉ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ በጋማ ከብቶች የሚጎተቱ ጋሪዎችን መጠቀም የትራንስፖርት አገልግሎቱን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሻሽለው ቢታወቅም በጥቂት አካባቢዎች ካልሆነ በስተቀር በገጠራቱ ኢትዮጵያ የተለመደ አይደለም፡፡ የብስክሌት፣ የሞተር ብስክሌት አጠቃቀምም ከከተሞች ውጭ የተዘወተረ አይደለም፡፡ እነዚህን አማራጮች ካላስፋፋን የትራንስፖርት አገልግሎታችን በሚፈለገው ፍጥነት ሊሻሻል አይችልም፡፡ ስለሆነም የግል ባለሃብቶችና የህብረት ስራ ማህበራት የጋራ ትራንስፖርትና ሌሎቹንም አማራጮች



በማስፋፋት ስራ ላይ እንዲሰማሩ፣ በቀበሌና ወረዳ ደረጃ ያሉ ሃላፊዎች ለእንደዚህ አይነቱ የትራስፖርት አገልግሎት መስፋፋት በቂ ትኩረት እንዲሰጡት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 8.3. የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻል፣

የገጠሩ ህዝብ በቂና ንፁህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ በመከላከል ላይ የተመሰረተ የጤና አገልግሎትን ለማስፋፋትና ጤናማ አምራች ዜጋን ለመፍጠር በቅድሚያ መሟላት ከሚገባቸው ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ይህንን አገልግሎት ማስፋፋት ማለት ጤንነትን በማረጋገጥ ከሚገኘው ደስተኛ ኑሮና የእድገት መሻሻል በተጨማሪ ለህክምና አገልግሎት የሚወጣውን ወጪ በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ማለት ጭምር ነው፡፡ በተጨማሪም የንፁህ ውሃ አቅርቦት የግልና የቤት ንፅህናን ለመጠበቅና በአካባቢው የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡ ተቋሞችን ለማስፋፋት፣ በአጠቃላይ ለአካባቢው እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በአገራችን የመጠጥ ውሃን ቀድቶ ተሸክሞ ወደቤት ማድረስ በዋነኛነት የሴቶች የስራ ድርሻ ተደርጎ የሚወሰድ ስለሆነ ለቤት ቅርብ በሆነ ቦታ ይህን አቅርቦት ማሟላት በሴቶች ላይ የሚጫነውን የስራ ጫና በመጠኑም ቢሆን መቀነስ ማለት ነው፡፡ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማረጋገጥ ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሞች ማግኘት ማለት ስለሆነና በዚህ በኩል በአገራችን ገጠሮች የከፋ ችግር ያለ በመሆኑ መላው የገጠር ህዝብ በተቻለ ፍጥነት የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖረው ማድረግ መንግስት ከገጠር ልማት አኳያ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ስራዎች አንዱ መሆን ይኖርበታል፡፡

የገጠር የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በአፋጣኝ ለማስፋፋት በአብዛኛው በጉልበት ሊሰሩ የሚችሉና የገንዘብ ወጪያቸው

www.abyssinialaw.com

ከፍተኛ ባልሆኑ አማራጮች ላይ ማተኮር አለብን፡፡ በዚህ ረገድ ምንጭ ማጎልበት፣ ጥልቅ ያልሆነ ጉድጓድ መቆፈር፣ የወንዝ ውሃ ማጣራትና የመሳሰሉት አማራጮች ሊታሰቡ ይችላሉ፡፡ በርካሽ ዋጋ በቂ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ማግኘት የሚችሉቱ በተቻለ ፍጥነት ይህንኑ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ውድ በሆነ ዋጋ ብቻ የመጠጥ አቅርቦት ማግኘት የሚችሉ ቀበሌዎች አገልግሎት እስኪደርሳቸው ድረስ የሚጠብቁበት አንድም ምክንያት አይኖርም፡፡ ከፍትሃዊነትም አንፃር ባለን ውሱን ገንዘብ የላቀ ቁጥር ላለው ህዝብ አገልግሎት መስጠት እንጂ ሶስት አራት ቀበሌዎችን ለማዳረስ በሚችል ወጪ አንድ ቀበሌን ማገልገል መሆን የለበትም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ማዕከላት ተብለው የሚመረጡት የአካባቢው የአገልግሎትና አስተዳደር ማዕከላት በመሆናቸው፣ ፈጣን እድገት ይኖራቸዋል ተብሎም ስለሚታሰብ እንደሌላው ነገር ሁሉ በመጠጥ ውሃ አቅርቦትም ቅድሚያ ማግኘት አለባቸው፡፡ የመጠጥ ውሃ አቅርቦቱም ከቀጣይ እድገታቸው ጋር የሚመጥን መሆን አለበት፡፡

በቅድሚያ በርካሽ ዋጋና በአብዛኛው በሰው ጉልበት በሚሰሩ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አማራጮች ላይ ያተኮረ ስራ መስራት የሚለው አማራጭ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚሁ መልክ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ማግኘት የማይችሉ ቀበሌዎች መኖራቸው አይቀርም፡፡ የነዚህን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ለማሻሻል ለየት ያለ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ተራቸውን ጠብቀው እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡ እዚህም ላይ ቅድሚያ ለቀበሌ ማዕከላት መሰጠት አለበት፡፡ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ተቋሞች ሁኔታው በፈቀደው መጠን ለቤቶች ቅርብና ውሃውን ለማጓጓዝ በሚያመች ቦታ ላይ የሚገነቡ መሆን አለባቸው፡፡



በመጠጥ ውሃ አቅርቦትም ላይ እንደገጠር መንገድ ስራ ሁሉ የጥገናና የእንክብካቤ ከፍተኛ ችግር ይታያል፡፡ የመጠጥ ውሃ -ምፖች ተበላሽተው በአጭር ጊዜ ውስጥ ከጥቅም ውጭ የሚሆኑበት የውሃው ንፅህና የሚበላሽበት አጋጣሚ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ የመጠጥ ውሃ አቅርቦቱ ተቋም የባለቤትነት ችግር፣ የጥገናና እንክብካቤ ስርአት አለመኖር በዋነኛነት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ይህን ችግር በአስተማማኝ መንገድ ካልፈታን በስተቀር አስተማማኝ የገጠር የመጠጥ ውሃ አገልግሎት በሚፈለገው ፍጥነት ማስፋፋት የሚቻል አይሆንም፡፡ ነገሩ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ መሆኑ የማይቀር ይሆናል፡፡

ይህንን ችግር ለማስወገድ በመጀመሪያ ደረጃ የባለቤትነት ጉዳይ መመለስ ይኖርበታል፡፡ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ተቋም ባለቤቶች የዚህ ተቋም ዋነኛ ተጠቃሚ የሆኑ የመንደር ጎጥ ደብር ወዘተ. ነዋሪዎች ናቸው፡፡ በቀበሌው ያሉ የመጠጥ ውሃ ነጥቦችን በሙሉ በበላይነት መቆጣጠርና ማስተባበር የቀበሌው አመራር ይሆናል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የቅርብ አመራርና ክትትል የሚሰጥ አካልም መኖር ይገባዋል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች እንደሚታየው የውሃ ኮሚቴ ከመንደርተኛው በምርጫ እንዲቋቋም ማድረግ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚህ አይነት ኮሚቴዎች በተቋቋሙበት አካባቢ ያለው ልምድ እንደሚያሳየው ከኮሚቴው አባላት ውስጥ አብዛኛዎቹ ሴቶች ሲሆኑ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል፡፡ የቤተሰብን የውሃ አቅርቦት ሃላፊነት በአብዛኛው የሚሸከሙት እነሱ ስለሆኑ የመንደሩን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በተሻለ ብቃት ሊሸከሙት የሚችሉት እነሱው ናቸውና፡፡ አቅም በተገኘበት አካባቢ የመጠጥ ውሃ ነጥቡን የሚጠብቅና የሚንከባከብ ተቀጣሪ ስራተኛ መመደብም ይገባል፡፡

ኮሚቴውና ተቀጣሪ ሰራተኛው በመጀመሪያ ደረጃ የመጠጥ ውሃ ነጥቡ ንፅህና በሚፈለገው መልኩ መጠበቁን፣ የውሃ ነጥቡ የሚያስፈልገውን እንክብካቤና ጥገና ማግኘቱን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው። የጥገና ወጪን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገቢም ከተጠቃሚው መገኘት ይኖርበታል። ስለሆነም ተጠቃሚው ለሚያገኘው የውሃ አገልግሎት ከህዝቡ የመክፈል አቅምና ከጥገናና እንክብካቤ ወጭው ጋር የሚሄድ ክፍያ መክፈል አለበት። ህዝቡ በይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆነው መለስተኛ ክፍያ እየከፈለ አስተማማኝ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሲያገኝ ነው። አከፋፈሉ ውሃ በሚቀዳበት ቦታ በሚቀዳው ውሃ መጠን ሊሆን ይችላል። ይህ በተለይም ቋሚ ተቀጣሪ ባለበት አካባቢ ሊሰራ ይችላል። እያንዳንዱ ቤተሰብ በወር የተወሰነ ገንዘብ እንዲከፍል በማድረግም ሊፈፀም ይችላል። ዋናው ነገር ባለቤቱ ተለይቶ፣ የእንክብካቤና ክትትል ስርአት ተፈጥሮ ህዝቡ የአገልግሎቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ መለስተኛ ክፍያ የሚከፍልበት አሰራር እንዲኖር የማድረግና ይህንኑ በቀጣይነት እየገመገሙ የማሻሻል ጉዳይ ነው።

የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ከማስፋፋት አኳያ ሌላው ችግር በመለስተኛ ዋጋ ሊሰሩ የሚችሉ የመጠጥ ውሃ ነጥቦችን የሚለይ፣ ግንባታቸውን የሚከታተልና የሚያስፈፅም፣ ከመንደርተኛው የቴክኒክ ችሎታ በላይ የሆኑትን የጥገና ስራዎች የሚሰራ፣ የገጠር መጠጥ ውሃ አገልግሎት ስርአቱን በቀጣይነት እየገመገመ እንዲሻሻል የሚያደርግ አቅም በቅርብ ቦታ አለመገኘቱ ነው። የገጠር የመጠጥ ውሃ አገልግሎትን በሚፈለገው መጠን ለማስፋፋት የሚቻለው ቢያንስ በየወረዳው እንደዚህ አይነቱ አቅም የተፈጠረ እንደሆነ ነው። በርካሽ ዋጋ በአብዛኛው



www.abyssinialaw.com

በጉልበት ሊሰሩ የሚችሉ የውሃ ነጥቦችን ሊያጠና፣ የግንባታ ቦታቸውን ሊወስንና ግንባታቸውን ሊከታተል የሚችለው ሞያተኛ የሚያስፈልገው ስልጠና ተለይቶ በቂ ስልጠና አግኝቶ እንዲሰማራ ማድረግ ያስፈልጋል። የገጠር መጠጥ ውሃ ነጥቦች ከመንደርተኛው አቅም በላይ የሆነ ጥገና ሲያስፈልጋቸው ለመጠገን የሚችል አቅምም በተመሳሳይ መልኩ መስልጠንና መመደብ ይኖርበታል። በወረዳ ደረጃ የሚፈጠረው ይህ አቅም የአካባቢውን የመጠጥ ውሃ አገልግሎት የማስፋፋት፣ የማሻሻልና የመከታተል ሃላፊነት መሸከም ይኖርበታል። ከራሱ የሞያ ደረጃ በላይ የሆኑ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ስራዎች በበላይ አካል እንዲሰሩ የመጠቆምና የመከታተል ሃላፊነትም ሊኖረው ይገባል።

## 8.4. ሌሎች የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን ደረጃ በደረጃ ማስፋፋት፣

በገጠሮች የቴሌኮምዮኒኬሽንና የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስፋፋት ጉዳይ አሁን በሰማይ ላይ ያለ ዳመና ቢመስልም በተቻለ ፍጥነት መሟላት ያለበት ነው። በርግጥ በአሁኑ ሰአት እየተደረገ እንዳለው ቀዳሚው ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ የወረዳ ማዕከሎችና ከተሞች የቴሌኮምዮኒኬሽንና የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ነው። ይህ ስራ በተቻለ መጠን መፋጠን ይኖርበታል። ከዚያ ቀጥሎ በተቻለ ፍጥነት የቀበሌ ማዕከላት ይህን አገልግሎት ማግኘት አለባቸው። ከረጅም ጊዜ አኳያ እነዚህ ማዕከሎች የቀበሌው የእድገት ማዕከል የሚሆኑና ወደ ትንሽ ከተማነት የሚለወጡ ስለሆኑ በአካባቢው እንዲስፋፋ ከሚፈለገው አገልግሎትና ከግብርና ውጭ ያሉት የኢኮኖሚ ዘርፎች እድገት አኳያ ሲታይ እነዚህን አገልግሎቶች በብቃት እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል። ከአጭርና መካከለኛ ጊዜ አኳያም እነዚህ ማዕከላት የትምህርት፣ የጤና የአስተዳደር፣

www.abyssinialaw.com

የግብርና ስልጠናና ኤክስቴንሽን፣ የህብረት ስራ ማህበራት ወዘተ. ተቋሞች የሚመሰረቱባቸው ናቸው። በነዚህ ተቋሞች የሚሰሩ ቀላል ቁጥር አላቸው የማይባሉ ሞያተኞች የሚሰፍሩባቸው ናቸው። ሞያተኞችን ለማትጋትና ስራቸውን በአግባቡ እንዲሰሩ ለማድረግ እነዚህ አገልግሎቶች መሟላት ይኖርባቸዋል። ስለሆነም ጉዳዩ ተጨባጭና አፋጣኝ መፍትሄ የሚሻ እንጂ በሰማይ ላይ እንዳለ ዳመና ተደርጎ መወሰድ ያለበት አይደለም።

በአለማችን እጅግ ፈጣን በሆነ አኳኋን እየተስፋፋ ያለው የቴሌኮምዮኒኬሽን ቴክኖሎጂ በገጠር የቴሌኮምዮኒኬሽን አገልግሎት የማስፋፋትን ጉዳይ በፊት እንደነበረው በጣም ከባድ ወጭና ረጅም ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ እንዲቀር አድርጎታል። ስለሆነም የተያዘውን የቴሌኮምዮኒኬሽን አገልግሎትን ለወረዳ ማዕከሎችና ለከተሞች የማዳረስ ስራ በአፋጣኝ አጠናቆ ወደሚቀጥለው ስራ መሸጋገር ያስፈልጋል። የሚቀጥለው ምዕራፍ አንድ ቁልፍ ስራም ለቀበሌ ማዕከላት ይህንኑ አገልግሎት የማዳረስ ጉዳይ ነው። የቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎትን የማስፋፋት ስራ ሲከናወን በሚፈጠረው ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የመረጃ አሰባሰብ ስርአታችንን ማሻሻልና ማጎልበትም ይገባል። በዚህ ረገድ መሰረታዊ የሆኑ መረጃዎች ተሰባስበው የሚያዙበትን ስርአት ለማሻሻል ከታች ወደላይና ከላይ ወደታች የሚተላለፉበት የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠርና ይህንኑ በየጊዜው ለምናዘጋጃቸው የልማት እቅዶች መነሻ ሆኖ እንዲያገለግል ለማድረግ ጥረት ይደረጋል። በአጠቃላይም ከቴሌኮምዩኒኬሽን አገልግሎት መስፋፋት ጎን ለጎን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅን ለገጠር ልማት እንቅስቃሴያችን መፋጠን የላቀ አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ጥረት መደረግ



ይኖርበታል። ይህንን በተቻለ ፍጥነትና በመለስተኛ ዋጋ ለማዳረስ የሚያስችሉ አማራጮች ተጠንተው፣ በዚህ ስራ ላይ ከቴሌኮምዮኒኬሽን ኮርፖሬሽን ጋር በቅንጅት ሊሰሩ የሚችሉ እንደ ህብረት ስራ ማህበራት የመሳሰሉ አካላት ተለይተው ተጨባጭና የጊዜ ገደብ ያለው እቅድ መዘጋጀት ይኖርበታል።

የኤሌክትሪክ ሃይል አገልግሎትን በተመለከተም በገጠር የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ለማስፋፋት ሊረዱ የሚችሉ አንዳንድ ቴክኖሎጂዎች በመፈጠር ላይ ያሉ ቢሆኑም (ለምሳሌ ሶላር ኤነርጂ፣ በንፋስ የሚሰሩ የኤሌክትሪክ ማመንጫዎች ወዘተ.) ይህንን አገልግሎት ማዳረስ የቴሌኮምዮኒኬሽን አገልግሎት ከማዳረስ የሚከብድ መሆኑ አያጠራጥርም። ይልቁንም ይህ አገልግሎት አለመዳረሱ የቴሌኮምዮኒኬሽን አገልግሎት በሚፈለገው መንገድ እንዳይዳረስ እንቅፋት መሆኑ አይቀርም።

የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽናችን ይህንን አገልግሎት በቅድሚያ በከተሞችና በወረዳ ማዕከሎች ለማስፋፋት የያዘውን እቅድ ማስፈፀም ይኖርበታል። ከዚህ ስራ ጋር በተደራቢነት አገልግሎት ማግኘት የሚችሉ ገጠሮች ሲኖሩም አገልግሎቱን እንዲያገኙ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። ይህ አገልግሎት ቢያንስ በተራዘመ ሂደት በብዙዎቹ የቀበሌ ማዕከላት ሊዳረስ የሚችልበትን እቅድ ማውጣትም ይጠይቃል። ከአጭርና መካከለኛ ጊዜ አኳያ ሲታይ ግን የኤሌክትሪክ ሃይል አገልግሎት ስርጭትን ለማስፋፋት ለየት ያሉ አማራጮች መዳሰስ ይኖርባቸዋል። የግል ባለሃብቶች ወይም የህብረት ስራ ማህበራት በናፍታ የሚሰሩ ትናንሽ ዲዝል ጀኔሬተሮችን ገዝተው ትርፍ በሚያስገኝ አኳኋን አገልግሎቱን እንዲሰጡ ማትጋትና ማበረታታት አንድ አማራጭ ነው። የፀሃይና የንፋስ ሃይልን

www.abyssinialaw.com

በመጠቀም ኤሌክትሪክ ማመንጨት የሚችሉ ተቋሞችን ለማቋቋም የአካባቢው አስተዳደርና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ. በሚሳተፉበት መንገድ መስራትም ሌላ አማራጭ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የባህላዊ የሀይል ምንጮች አጠቃቀም በማሻሻል የገጠር የሀይል አቅርቦት ስርአታችንን ማሻሻል ይኖርብናል፡፡ ባህላዊ የሀይል ምንጮች አጠቃቀምን ከማሻሻል ጎን ለጎን የነዚህ አጠቃቀም እስካሁን እንደነበረው ከፍተኛ የደን ውድመት እንዳያስከትል ከደን ልማት ስራችን ጋር በቅርብ የተቀናጀ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡ እነዚህንና ሌሎች አማራጮችን በመዳሰስ የተሻሉትን በመምረጥና እንደአስፈላጊነቱ አቀናጅቶ በመጠቀም አገልግሎቱን ለማስፋፋት መረባረብ ይጠይቃል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ የቀበሌ ማዕከላትን የማጠናከርና በነዚህ ማዕከላት የሚሰሩ ሞያተኞችን የማሰልጠን፣ የማሰማራትና የማትጋት ጉዳይ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት አርሶ አደሩ በአብዛኛው በተበታተነ ሁኔታ በመኖር ላይ ያለ ነው፡፡ በገጠር ልማት በሚፋጠንበት ሂደት መሰባሰብ ይኖርበታል፡፡ የዚህ መሰባሰብ አስኳል ሊሆኑ የሚችሉ ቦታዎችን በየቀበሌው መርጦ ከወዲሁ በማዕከልነት ማሳደግ ይህን ሂደት ሊያፋጥነው ይችላል፡፡ የገጠር ልማትን ለማፋጠን በየቀበሌው በርካታ ሞያተኞችን የሚጠይቁ ተቋሞች ማደራጀት ይጠይቃል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የጤና ኬላ፣ የኤክስቴንሽንና የግብርና ስልጠና ተቋማት ወዘተ. መቋቋም ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በየቀበሌው ከአስር የሚበልጡ ሞያተኞች መመደባቸውና በሂደትም ቁጥራቸው እየጨመረ መሄዱ አይቀርም፡፡ እነዚህን ሞያተኞችና ተቋሞች በየደብሩና



በየመንደሩ ከመበተን ይልቅ በተመረጡ የቀበሌ ማእከላት ማሰባሰብ ይጠቅማል፡፡ ስለሆነም እነዚህ አይነቶቹን የእድገት፣ የአስተዳደርና የአገልግሎት ማእከላት በየቀበሌው መርጦ ማሳደግና በሂደት ወደትንሽ ከተማነት የሚያድጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት የገጠር ልማት ስራችን አንድ መሰረታዊ አቅጣጫ ተደርጎ መታየት ይኖርበታል፡፡

ይህን ክቡር የገጠር ልማት አላማ ለማሳካት የሚቻለው የተጠቀሱት ሞያተኞች በየቀበሌው ተሰማርተው ህዝባቸውን ለማገልገልና አገራቸውን ለማልማት ቆርጠው የተነሱ እንደሆነ ነው፡፡ ይህን ህዝባዊ ግዴታ በእምነት ያልተቀበለ ወጣት በየቀበሌዎቹ ተመድቦ በቋሚነት እየሰራ የሚፈለገውን ልማት ማረጋገጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም እነዚህን ሰዎች የማስረዳት፣ የስራውን አስፈላጊነትና ክቡርነት ተገንዝበው እንዲሰማሩ ማድረግ ዋናው ስራ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ስራ አኳያ የገጠር ተማሪዎች ሆነው የሞያ ስልጠናውን ለማግኘት የሚያስችል የትምህርት ደረጃ ላላቸው ሰዎች ቅድሚያ መስጠት የራሱ ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም ስራው የገጠር ተወላጆች ስራ ብቻ ተደርጎ መውሰድ የለበትም፡፡ በከተማ ተወልዶ ያደገ ወጣትም በዚህ ስራ ላይ ለመሰማራት ዝግጁ ሊሆን እንደሚችል በደርግ ጊዜ በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች በተካሄዱት የትጥቅ ትግሎች የከተማው ወጣት የነበረውን ተሳትፎ በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ዋናውና ወሳኙ ነገር ሞያተኞቹ በስራው ላይ ጠንካራ እምነት እንዲኖራቸው ማድረግ ቢሆንም በዚህ ላይ የተመሰረቱ ተጨማሪ የማትጊያ መንገዶች መፈለግ አለባቸው፡፡ ሞያተኞቹ የሚኖሩበት ቤት የማግኘት ጉዳይ የመጀመሪያው መሰናክል መሆኑ አይቀርም፡፡ ህዝቡና የአካባቢው አስተዳደር በመተባበር

www.abyssinialaw.com

መኖሪያቸውን ለማሰራት ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው መረባረብ ይገባቸዋል፡፡ በየቀበሌው የተሰማሩ ሞያተኞች በመንግስት በሚሰጡ የትምህርት እድሎች የመጠቀም ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በገጠር ባገለገሉበት የጊዜ መጠን ሌሎች ማትጊያዎችንም ማግኘት አለባቸው፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ነገር ተጨማሪ ማትጊያዎች የመስጠቱ አስፈላጊነት፣ በስራው ላይ የሚሰማሩ ሰዎች የአጭር ጊዜ የቆይታ ቦታ አድርገው እንዳይወስዱትና ልምድ ያለው ሰው የማይቀመጥበት እንዳይሆን የመጠንቀቅ አስፈላጊነትን ለመጠቆም እንጂ የማትጊያ አይነቶቹን ለመዘርዘር አይደለም፡፡

## 9. ከግብርና ውጭ ያሉ የገጠር ልማት እንቅስቃሴዎችን ማጠናከር፣

በገጠር ልማት ውስጥ ባለንበት ጊዜ ዋናው ነገር የግብርና ልማት ነው፡፡ እጅግ የሚበዛው የገጠር ህዝብ በግብርና ላይ የተሰማራና በዚህ መሰማራቱ የማይቀር ነው፡፡ በገጠር ሌሎች ዘርፎች እንዲስፋፉ ለማድረግ በሩን የሚከፍተውም የግብርና ልማት ነው፡፡ የግብርና ልማት ሲፋጠን የህዝቡ ገቢ ይጨምራል፡፡ ባገኘው ገቢ ከግብርና ውጭና በራሱ ስራ የማያሟላቸውን ሸቀጦችና አገልግሎቶችን ለመግዛት ይፈልጋል፣ የመግዛት አቅሙም ይኖረዋል፡፡ አርሶ አደሩ ከእጅ ወደአፍ በሆነ ኑሮ በሚማቅቅበት ጊዜ ግን ከግብርና ውጭ የሆኑ ዘርፎችን በገጠር ፈጣንና ቀጣይነት ባለው አኳኋን ማስፋፋት አይቻልም፡፡ ለዚህ ነው የግብርና ልማት በገጠር ሌሎች የልማት ዘርፎችን ለማስፋፋት መሰረት ነው የምንለው፡፡

ቀደም ሲል የዘረዘርናቸው የመሰረተ-ልማት አገልግሎቶች በዋነኛነት የግብርና ልማትን ለመደገፍና



ለማገልገል ተብለው የሚስፋፉ ቢሆኑም እዚያው በዚያው ሌሎቹንም ዘርፎች ማገልገል የሚችሉ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ቁጥራቸው አነስተኛ ለሆኑ ሰራተኞችም የስራ እድል የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ከግብርና ውጪ ለሚደረገው ልማት መነሻዎቹ እነዚህ ሁለቱ ናቸው፡፡ እነዚህን መነሻ በማድረግና የሚፈጥሩትን ምቹ ዕድል አሟጦ በመጠቀም ነው ከግብርና ውጪ ያለውን የገጠር ልማት ማፋጠን የሚቻለው፡፡ የመሰረተ-ልማት አገልግሎቶቹ የልማት መሳሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ ከግብርና ውጪ የሚኖረው የገጠር ልማት አካላትና እርሾም ተደርገው መታየት አለባቸው፡፡

### 9.1. ከግብርና ወጪ የሚኖር ልማት አስፈላጊነት፣

በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት የገጠር ልማት ማዕከል ግብርና ነው በሚልበት ወቅት ከዚህ ውጪ የሆነ የገጠር ልማት የለም፣ አያስፈልግም ወይም በአሁኑ ወቅት በቂ ክብደት ተሰጥቶት መከናወን አይችልም ማለቱ አይደለም፡፡ ከግብርና ውጭ ያሉት የልማት ዘርፎች በልማት እንቅስቃሴያችን ሂደት የገጠር ልማት ዋነኛ አካል መሆናቸው አይቀርም፡፡ ይልቁንም የገጠር ልማት እንቅስቃሴያችን በማያዳግም አኳኋን ተሳክቷል ማለት የምንችለው በፈጣን የግብርና ልማት ሂደት በገጠርም በከተማም ዋናው የኢኮኖሚ ዘርፍ ግብርና መሆኑ ሲያቋርጥ ነው፡፡ ግብርናን በገጠር ልማት ማዕከልነት እንውሰድ ሲባል የግብርናን ልማት ማረጋገጥ ብቻውን የመጨረሻ ግብ በመሆኑ ሳይሆን ግብርና ወሳኝ ዘርፍ መሆኑ ወደሚያቋርጥበት የላቀ የገጠር ልማት ደረጃ በአስተማማኝ ሁኔታና በአፋጣኝ የሚወስደን ብቸኛው መንገድ እሱው ስለሆነ ነው፡፡ እነዚህን በአስተማማኝ መንገድ ለማልማት የሚችለውን ብቸኛ አማራጭ ማለት ግብርናን ማዕከል ያደረገ የገጠር ልማት

www.abyssinialaw.com

አቅጣጫ የሚከተለው ከግብርና ውጭ ስላሉት የልማት ዘርፎች ከማንም በላይ ትኩረት ስለሚሰጥ ነው፡፡

መንግስታችን በገጠር ልማት ስራ ውስጥ ከግብርና ልማት ውጪ ያሉ ዘርፎችም በቂ ክብደት ሊሰጣቸው ይገባል የሚለው ከረጅሙ ጉዞ አኳያ በማየት ብቻ አይደለም፡፡ በረጅም ጊዜ መከናወን አለበት የሚባል ስራ በተባለው ረጅም ጊዜም ቢሆን ሊሰራ የሚችለው ስራው ከወዲሁ መሰራት ሲጀምር ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ከረጅም ጊዜ አኳያ ከግብርና ውጭ ያሉት ዘርፎች ወሳኝ ሚና መጫወት አለባቸው ስንል አንድ ቀን እዚህ ደረጃ ላይ ይደርሳል በሚል ተስፋ ተማምነን ዛሬ እነሱን በሚመለከት ተጨባጭ ስራ አንሰራም ማለት ሳይሆን ይህንኑ ውጤት ለማስገኘት ከወዲሁ መረባረብ አለብን ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዛሬውኑ እነዚህ ስራዎች ተገቢው ክብደት ተሰጥቷቸው ካልተሰሩ በስተቀር የግብርና እድገት ሊፋጠን፣ የገጠሩ ህዝብ ኑሮ ሊሻሻል አይችልም፡፡

የትምህርትና የጤና አገልግሎት፣ የንግድና የግብይት አገልግሎት፣ የፋይናንስ አገልግሎት ወዘተ. ግብርናን የሚደግፉና የሚያገለግሉ ቢሆኑም ከግብርና ውጭ ያሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች ናቸው፡፡ በገጠር እነዚህን ማስፋፋት ማለት ከግብርና ውጭ ያለውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ማጠናከር በነዚህ ስራዎች ላይ ተሰማርቶ ኑሮውን የሚገፋና በተነፃፃሪ ሻል ያለ ገቢ ያለው የሰው ሃይል ቁጥር መጨመር ማለት ነው፡፡ ይሁንና እነዚህ ከግብርና ውጭ ያሉት አገልግሎቶች ካልተስፋፉ በስተቀር የግብርና ልማት ሊፋጠን አይችልም፡፡ ከግብርና ውጭ ላሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች በቂ ክብደት ሰጥቶ ዛሬውኑ ማደግ እንዲጀምሩ ካልተደረገ የግብርና እድገት አይፋጠንም ስንልም ይህንኑ ማለታችን ነው፡፡



አርሶ አደሩ በግብርናም ሆነ በሌላ ስራ ላይ የሚሰማራው አምርቶ ኑሮውን ለማሻሻል ነው፡፡ በዚህ ስራ ሂደት ገቢው ጨምሮ የተሻሉ የቤት ቁሳቁሶች፣ የተሻለና በርከት ያለ ልብስ ጫማ ወዘተ. እንዲኖረው ነው፡፡ ገቢውን አሳድጎ የተሻለ የትምህርት፣ የህክምና፣ የትራንስፖርት መዝናኛ ወዘተ. አገልግሎት እንዲያገኝ ነው፡፡ ያደገውን ገቢውን በመጠቀም የግብርና ስራውን የሚያሻሽሉለትና የሚያቃልሉለት ግብአቶችና የማምረቻ መሳሪያዎች እንዲያገኝ ነው፡፡ ገቢው አድጎ እንዚህን ማግኘት ካልቻለ ብር ስለከመረ ብቻ ኑሮው ተሻሻለ ማለት አይቻልም፡፡ እነዚህን ካላገኘ ብር ከመከመር ይልቅ የልማት እንቅስቃሴው ትጋት ወደመቀነስ መሄዱም አይቀርም፡፡ ለህዝቡ ኑሮ መሻሻል ተፈላጊ ናቸው ያልናቸው ነገሮች የሚገኙት በአብዛኛው ከግብርና ውጭ ባሉት ዘርፎች ነው፡፡ ስለሆነም ነው እነዚህ ከወዲሁ በቂ ክብደት ተሰጥቷቸው ካላደጉ በስተቀር የህዝቡ ኑሮ አይሻሻልም የምንለው፡፡

ብዙውን ጊዜ ከግብርና ዘርፍ ውጭ ባሉት ኢንዱስትሪዎችና አገልግሎቶች የሚሰማራ የሰው ሃይል በግብርና ዘርፍ ከሚሰማራው የሰው ሃይል የላቀ ምርታማነት ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ከላቀ ምርታማነቱ ጋር በተያያዘ መንገድም ገቢው ከአርሶ አደሩ ገቢ የተሻለ ይሆናል፡፡ በርግጥ ከግብርና ያነሰ ምርታማነትና ገቢ የሚያስገኙ ከግብርና ውጭ ያሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች እንዳሉ የታወቀ ነው፡፡ አጠቃላይ ሂደቱ ግን ከላይ እንደተገለፀው ነው፡፡ ስለሆነም የነዚህ ዘርፎች በይበልጥ መስፋፋት የገጠር ነዋሪው ገቢ በይበልጥ መጨመርና የኑሮው መሻሻል ማለት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ጭምርም ነው እነዚህ ዘርፎች ከወዲሁ በቂ ክብደት ተሰጥቷቸው ካልተስፋፉ በስተቀር የገጠሩ ህዝብ ኑሮ በሚፈለገው ደረጃ አይሻሻልም የምንለው፡፡

## 9.2. የግብርና ልማት የሚፈጥረውን እድል አሟጦ መጠቀም፣

የግብርና ልማትን ለማስፋፋት የግድ መቅረብ ያለባቸው የመሰረተ-ልማትና ሌሎች አገልግሎቶች አሉ። እነዚህ ቀደም ሲል የተዘረዘሩት አገልግሎቶች ራሳቸው የሚቀጥሩት ሻል ያለ ገቢ ያለው የሰው ሃይል ይኖራል። አገልግሎቶቹ በግብርናው ልማት ሂደት እየተስፋፉ በሄዱ ቁጥር በነዚህ ዘርፍ የሚቀጠረው የሰው ሃይልም እየጨመረ እንደሚሄድ እሙን ነው። ይህ ሂደት የሚፈጥረውን ዕድል አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ ከሚያስችሉት አማራጮች አንዱ የቀበሌ ማዕከላትን መምረጥ፣ እነዚህን እንደቀበሌው የእድገት ማዕከላት ወስዶ ማልማት ነው።

ለግብርና ልማት ተብለው የሚቀርቡት አገልግሎቶች ከአንድ ማዕከል እንዲሰጡና በአንድ ማዕከል እንዲሰባሰቡ ሲደረግ በነዚህ ማዕከላት የተሻለ ትምህርትና ሞያ፣ የተሻለ ገቢ ያለው የሰው ሃይል ይሰባሰባል ማለት ነው። ይህን ምሁራዊ አቅም በአንድ ላይ በማሰባሰብ ሊገኝ የሚችለው የምሁራዊ አቅሙ የተሻለ የአጠቃቀም ዕድል እንዳለ ሆኖ ይህን ሃይል ለማገልገል የሚችሉ ልዩ ልዩ የአገልግሎትና የንግድ ተቋሞች መፈጠራቸው አይቀርም። በነዚህ ተቋሞች የሚሰሩ ሰዎችም የተሻለ ገቢ ስለሚኖራቸው ተጨማሪ የስራ ዕድል መፍጠራቸው አይቀርም። በዚህ መልክ የመጀመሪያው ስብሰባ ተጨማሪ የስራ ዕድልና መሰባሰብ እየፈጠረ የቀበሌ ማዕከላቱ የእድገት ማዕከላት እየሆኑ፣ ከግብርና ውጭ ያሉት ዘርፎች በተሻለ ፍጥነት ሊያድጉ ይችላሉ።



በየገጠሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንደሚስፋፋ ተገልፃል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከጨረሱት የገጠር ወጣቶች በጣም የሚበዙት በግብርና ስራ ላይ የሚሰማሩ መሆን እንዳለባቸውም ግልፅ ነው። ነገር ግን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሸጋግረው በሌላ ስራ የሚሰማሩ ወጣቶችም ይኖራሉ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሁለተኛ ደረጃ ሳይሸጋገሩ ከግብርና ውጭ ያሉ የሞያ ስልጠናዎች አግኝተው የሚሰማሩም ይኖራሉ። ይልቁንም በሂደት ከግብርና ውጭ የሚሰማሩት ቁጥራቸው እየጨመረ እንደሚሄድ ግልፅ ነው። ይህንኑ ዕድል በገጠር ከግብርና ውጭ ያሉ ዘርፎች እንዲስፋፉ ለማድረግም መጠቀም ይቻላል። ግንበኞችን፣ አናጢዎችን፣ መለስተኛ ሜካኒኮችን፣ ዝቅተኛ የሂሳብ ሰራተኞችን ወዘተ. በማሰልጠን በተለያዩ የገጠር ድርጅቶችና ተቋሞች ተቀጥረው እንዲሰሩ ከማድረግ ባሻገር፣ የአርሶ አደሩን እየጨመረ የሚሄድ የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ፍላጎት በማሟላት ስራ ላይ የተሰማሩ የራሳቸው አነስተኛ ድርጅቶች እንዲያቋቁሙ ማድረግ ይችላል። ይህንኑ ለማገዝ ከስልጠናው በተጨማሪ የብድር አገልግሎት ማግኘት ይገባቸዋል።

የግብርና ልማት እንቅስቃሴው የሚፈጥረውን ምቹ ሁኔታ አሟጦ ከመጠቀም አኳያ ሌላው ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ የአርሶ አደሩን ምርቶች እሴት በመጨመር ስራ ላይ መሳተፍ ነው። ምርቶቹን ለሽያጭና ለትራንስፖርት በሚያመች አኳኋን የማሸግና የማዘጋጀት ስራ በዚሁ ክልል ሊጠቃለል የሚችል ነው። በትናንሽ ተቋሞች ሊሰሩ የሚችሉ የአግሮ-ፕሮሰሲንግ ስራዎችም ይኖራሉ። እነዚህን ስራዎች በማካሄድ ረገድ ዋነኛውን ሚና መጫወት የሚገባቸው የህብረት ስራ ማህበራት ናቸው። እነዚህ ተቋሞች በህብረት ስራ ማህበራትም

www.abyssinialaw.com

ሆነ በግል ባለሃብቶች ሲቋቋሙ ከግብርና ውጭ የሆነ ተጨማሪ የስራ ዕድል መፍጠራቸው የማይቀር ነው፡፡ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ስልቶች በመጠቀም ነው ከግብርና ውጭ ያሉት ዘርፎች ከወዲሁ መጠናከርና መስፋፋት ጀምረው በሂደት ወሳኝ ሚና መጫወት የሚችሉት፡፡

## 9.3. የገጠርና ከተሞች ትስስርን ማጠናከር፣

የግብርና ልማት ከግብርና ውጭ ለሆኑ ዘርፎች መስፋፋት አስተዋፅኦ የሚያደርገው በገጠሩ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ዋናው አስተዋፅኦ በከተሞች በሚደረገው የነዚህ ዘርፎች ልማት ነው፡፡ ዋናው የአግሮ ፕሮሰሲንግ ስራ የሚሰራው በገጠሮች ሳይሆን በከተሞች ነው፡፡ ዋናዎቹ የግብይት፣ የፋይናንስ አገልግሎት የትራንስፖርት አገልግሎት ማዕከላት ሊሆኑ የሚችሉት ከተሞች ናቸው፡፡ ከተሞች የገጠርንና የግብርናን ልማት በላቀ ደረጃ ማገልገልና መመገብ በሚችሉበት አኳኋን መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከተሞች ከገጠር ልማት የላቀ ጥቅም ለማግኘት፣ በገጠር ልማቱ እየተመገቡ በአፋጣኝ ለማደግ በሚያስችላቸው አኳኋን መደራጀት አለባቸው፡፡

የአከታተም ስርአታችን በእቅድ የሚመራና ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል መሆን ይገባዋል፡፡ ከተሞች የገጠር ልማትን ለማገልገልና በዚሁም ለመጠቀም መቻልን ማዕከል በማድረግ እንዲስፋፉ መደረግ አለበት፡፡ ለገጠር ልማት ሊሰጡት በሚችሉት አገልግሎትና ከዚሁ ለመጠቀም ባላቸው አቅም መሰረት ደረጃ ወጥቶላቸው የተባሉትን ነገሮች ለማሟላት የሚያስችላቸው የልማት እቅድ ወጥቶላቸው መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ ከተሞች ይህንኑ ስራ በብቃት ከሰሩ ቁጥሩ



እየጨመረ ለሚሄድ የገጠር ወጣት የስራ ዕድል እየፈጠሩ ይሄዳሉ፡፡ የገጠሩ ወጣት ከተማ ገብቶ ከግብርና ውጭ የሆነ ስራ መስራት ይችላል፡፡ ከገጠር ሳይወጣ  በአካባቢው ሰፋ ያለ ገበያ አግኝቶ ከግብርና ውጭ ያሉ ምርቶችን እያመረተ ሊሸጥ የሚችልበት ዕድልም ያገኛል፡፡ ስለሆነም በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በገጠር ከግብርና ውጭ የሆኑ ዘርፎች እንዲስፋፉ በር ሊከፍቱ ይችላሉ፡፡

ከግብርና ውጭ የሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች በገጠር ስለሚስፋፉበት ሁኔታ አጠቃላይ አቅጣጫዎችና አንዳንዴ ምሳሌዎችን ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ ዝርዝሮቹ በሂደት እየተፈጠሩና እየዳበሩ የሚሄዱ ናቸው፡፡ ዋናው ነገር እነዚህን ዘርፎች ማሳደግ የገጠር ልማት ስትራተጅያችን የማይነጠል አካል መሆኑን ተገንዝቦ ለዚሁ ስራ በቂ ትኩረት መስጠት ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

# ክፍል ሦስት

## የገጠር ልማት አመራር

የተስተካከለ የገጠር ልማት አላማ፣ የገጠር ልማት ራዕይ መያዝ፣ ይህንን ለመፈፀም የሚረዱ የተስተካከሉ ስትራተጅዎችና ፖሊሲዎች መንደፍ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የገጠር ልማትን ለማረጋገጥ ምን ያህል ቁልፍ እንደሆኑ የሚያከራክር አይደለም:: እነዚህ በሌሉበት የሚካሄድ የልማት ጉዞ አይንን ጨፍኖ በዳበሳ ለመንቀሳቀስ ከመሞከር የተለየ አይሆንም:: ውጤቱም ተከስክሶ ከመውደቅ ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም:: ይሁንና ዞሮ ዞሮ የፈለገው ጥራት ያለው አላማ፣ ስትራተጅ፣ ፖሊሲ ወዘተ. ቢኖርም በተግባር ላይ ካልዋለ ሰማይ ላይ ያለ ዳመና ነው:: ተጨባጭ ውጤት የሌለው ከንቱ ነገር ነው የሚሆነው:: ፖሊሲዎችንና ስትራተጅዎችን ለማስፈፀም ብቃት ያለው አፈፃፀም፣ ብቃት ያለው አመራር ያስፈልጋል:: በመሆኑም የገጠር ልማት ዞሮ ዞሮ መቋጫው የአመራር ብቃት ላይ ነው:: ብቃት ያለው አመራር ካለ የአላማ፣ የስትራተጅና የፖሊሲ ጉዳይ የተሟላ በመሆኑ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የገጠር ልማት ይኖራል:: ብቃት ያለው አመራር ከሌለ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የገጠር ልማት ብሎ ነገር የለም:: ከዚህ በመነሳት ነው ፅሁፉን የነገሩ መቋጫ የሆነውን የአመራር ጥያቄ በመዳሰስ የምንቋጨው::

### 1. የህዝብ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎና የገጠር ልማት፣

#### 1.1. የህዝብ ተሳትፎ አስፈላጊነት፣

የህዝብ ተሳትፎ በራሱ ተፈላጊና ጥሩ ነገር ነው:: ለበጎውም ለክፉውም ህዝቡ ራሱ በጉዳዮቹ ላይ ተመካክሮ



መወሰኑ ተገቢ ነው:: ይሁንና የህዝቡ ተሳትፎ በገጠር ልማት ስራ ላይ የላቀ መሆን አለበት ስንል ራሱን መሳተፉን የመጨረሻ አላማ አድርጎ በመውሰድ አይደለም:: ህዝቡ በገጠር ልማት ስራ ላይ በሰፊው መሳተፍ አለበት ስንል ከዚህ ውጭ የገጠር ልማት ስራ በፍፁም ሊንቀሳቀስ ስለማይችልና አማራጭ የሌለው ጉዳይ ስለሆነ ነው::

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የገጠር ልማት እንቅስቃሴያችን ማዕከሉ ግብርና ነው:: ግብርናችን ደግሞ በአርሶ አደሩ አማካኝነት በተበጣጠሰ ማሳ ላይ በሚካሄደው የግብርና ስራ ላይ የተመሰረተ ነው:: በሌላ አነጋገር የገጠር ልማት እንቅስቃሴያችን አርሶ አደሩ በየማሳው በሚያደርገው እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተ ነው:: የምናስቀምጣቸው ፖሊሲዎችና ስትራተጅዎች፣ የምናቀርባቸው የቴክኖሎጂ ፓኬጆች የምናካሂዳቸው ስልጠናዎች ወዘተ. ሄደው ሄደው የሚያርፉት በአርሶ አደሩ ትከሻ፣ በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ነው:: የነገሩ ማሳረጊያ በማሳው ላይ እነዚህ ፖሊሲዎችና አቅርቦቶች ወዘተ. መፍሰሳቸውና በሚፈለገው አኳኋን ተግባራዊ መሆናቸው ነው:: አርሶ አደሩ የቀረቡለትን አማራጮች በራሱ ማሳ ላይ በራሱ ጉልበት ተግባራዊ ሊያደርጋቸው ካልቻለ፣ አርሶ አደሩ የነዚህን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት አምኖ ተቀብሎ እነሱን ተግባራዊ ለማድረግ ሌት ተቀን ካልሰራ የሚመጣ የገጠር ልማት የለም::

የአርሶ አደሩ ተሳትፎ ወሳኝ ነው ስንል በቅድሚያ አርሶ አደሩ የቀረቡለትን የልማት ስራ አማራጮች መርምሮና አምኖ ተቀብሎ በማሳው ላይ ሌት ተቀን በመስራት ተግባራዊ ካላደረጋቸው በስተቀር ፈጣን የግብርና ልማት ብሎም ፈጣን

www.abyssinialaw.com

የገጠር ልማት አይኖርም ማለታችን ነው፡፡ የአርሶ አደሩ ዋናው የተሳትፎ መልክ በራሱ ማሳ ላይ በራሱ ጊዜና በሚመቸው አኳኋን የሚያካሂደው የልማት እንቅስቃሴ ነው፡፡ በርግጥ አርሶ አደሩ ከማሳው ውጭም በገጠር ልማት ስራ ላይ መሳተፍ አለበት፡፡ ነገር ግን ወሳኙ ተሳትፎ ከማሳው ውጭ ያለው አይደለም፡፡ ወሳኙ ተሳትፎ በማሳው ላይ ያለው፣ የግብርና ልማት እንቅስቃሴዎቹ ሁሉ ማሳረጊያ የሆነው ይኸው በማሳው ላይ የሚያደርገው ተሳትፎ ነው፡፡

አርሶ አደሩ በገጠር ልማት ስራ ላይ የሚያደርገው ወሳኙ ተሳትፎ በማሳው ላይ የሚያካሂደው የልማት እንቅስቃሴ ነው ሲባል ከዚህ ውጭ የሚኖረው ተሳትፎ ቀላል ግምት የሚሰጠው ነው ማለት አይደለም፡፡ በአርሶ አደሩ ማሳና ቤት ዙሪያ የፈለገው አይነት እድገት ቢመጣ በአካባቢው የመሰረተ-ልማት አገልግሎት፣ የግብይት ስርአት ወዘተ. ከሌለ የትም ሊደርስ አይችልም፡፡ ከዚህም በላይ እነዚህ አገልግሎቶች በሌሉበት ሁኔታ አርሶ አደሩ በማሳውና በቤቱ የሚያደርገው የልማት ስራ ረጅም ርቀት ሊሄድ የሚችል አይሆንም፡፡ ስለሆነም አርሶ አደሩ ከማሳውና ከቤቱ ውጭ በገጠር ልማት ላይ በሰፊው መሳተፉ አማራጭ የሌለው ነገር ነው፡፡

የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን በገጠርም ሆነ በከተማ የማሟላት ሃላፊነት በመሰረቱ የመንግስት ነው፡፡ ይሁንና መንግስት ያለው የገንዘብ አቅም በጣም ውሱን ነው፡፡ በመንግስት ባጀትና ገንዘብ የገጠር መሰረተ-ልማት እናስፋፋለን ብለን ከተነሳን ፈጣን የገጠር ልማት የምንለው ጉዳይ ከመሞት ውጭ ሌላ ዕድል አይኖረውም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚታየው አብዛኛው የገጠር የመሰረተ-ልማት ስራ በባህሪው በአብዛኛው በሰው



ጉልበትና የአካባቢውን ሃብት በማንቀሳቀስ ሊፈፀም የሚችል ነው፡፡ ጉልበቱና የተፈጥሮ ሃብቱ ያለውም በአካባቢው ህዝብ እጅ ነው፡፡ ይህንን በማስተባበርና በማንቀሳቀስ የመሰረተ-ልማት አገልግሎቱ በከፍተኛ ደረጃ ሊፋጠን ይችላል፡፡ ይልቁንም ግብርናንና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራተጅ መከተል አለብን የምንለው ያለ ብዙ የገንዘብ ወጭ የህዝቡን ጉልበት በማስተባበርና በማሳተፍ የላቀ ልማት ማግኘት የሚቻለው በገጠርና በግብርና ስራ በመሆኑ ነው፡፡ ህዝቡ በጉልበቱና በተፈጥሮ ሃብቱ በግብርና ስራና የመሰረተ-ልማት አገልግሎትን በማስፋፋት ረገድ በሰፊው ካልተሳተፈ በስተቀር ስትራተጅውም ሊሰራ አይችልም፣ የገጠር ልማትም ሊፋጠን አይችልም፡፡

የተፈለገው ልማት ሊመጣ የሚችለው አርሶ አደሩ በማሳውና በጓሮው የግብርና ልማትን ለማቀላጠፍና ኑሮውን ለማሻሻል ሲረባረብ ነው፡፡ የተፈለገው ልማት ሊረጋገጥ የሚችለው ከዚህ በተጨማሪ አርሶ አደሩ ጉልበቱንና የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት አስተባብሮ ለአካባቢው ልማት በሰፊው ማዋል ሲችል ነው፡፡ መንግስት ያለውን ውሱን የገንዘብ አቅም በገጠር ልማትን በሚያረጋግጥ አኳኋን ሊያውለው የሚችለው ይህን በህዝቡ መሰራት ያለበትን ስራ በመተካት አይደለም፡፡ መንግስት ልማቱን ከማፋጠን አኳያ ባለው ውሱን ገንዘብ የላቀ አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችለው ይህንኑ የህዝቡን ጥረት የበለጠ ውጤት በሚያመጣ አኳኋን ሲደግፍ ነው፡፡ ለአርሶ አደሩ የተሟላ የቴክኒክና ምክር አገልግሎት ሲሰጥ፣ ይህን ለማድረግ የሚያስችል ብቃት ያለው መዋቅር ሲዘረጋና ገንዘቡን በዚህ ስራ ላይ ሲያውል ነው፡፡ ህዝብን ለልማት በብቃት ሲያስተባብር፣ ይህን ማድረግ የሚችል መዋቅር ሲዘረጋና ውሱን ገንዘቡን በዚህ ስራ ላይ ሲያውል ነው፡፡ በህዝቡ አቅም ሊሰሩ የማይችሉትን ነገር ግን የገጠሩን

ልማት ለማቀላጠፍ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱትን ስራዎች ሲሰራ፣ ቀዳዳዎችን ሲደፍንና ያለውን ውሱን የገንዘብ አቅም ለዚሁ ስራ ሲያውል ነው::

የገጠር መንገድ የመቀየስ፣ ስራውን የሚያስተባብር ብቃት ያለው አቅም የመፍጠርና የማሰማራት ስራ የመንግስት ነው:: ለገጠር መንገድ ስራ የሚያስፈልጉ ከአርሶ አደሩ አቅም በላይ የሆኑ ቁሳቁሶችን የማቅረብ ስራ የመንግስት ነው:: ስራውን ለመስራት የሚያስፈልግ ጉልበት የማቅረብ፣ ከተሰራ በኋላ መንገዱን የመጠገንና የመንከባከብ ስራ ግን የህዝቡ መሆን አለበት:: የትምህርት ቤት አስተማሪዎችን ማሰልጠንና መመደብ የመንግስት ስራ ነው:: የትምህርት ቁሳቁሶችን ማቅረብም የመንግስት ሃላፊነት ነው:: ትምህርት ቤቶችን በመገንባት፣ በመጠገንና በመሳሳሉት ግን ህዝቡም በጉልበቱና በሌላ መልኩ መሳተፍ መቻል አለበት:: አንዳንድ አካባቢዎች እንጨት ለቅመው ሰብስበው በመሸጥ የሚያገኙትን ገንዘብ ጉልበታቸውን ጨምረው፣ መንግስት ቆርቆሮ ገዝቶላቸው ትምህርት ቤት የሰሩበት ሁኔታ አለ:: ህዝቡ በስራው ልሳተፍ ካለ ባለው ከፍተኛ የፈጠራ ችሎታ ከተጠቀሰው ምሳሌ የሚበልጡ ብዙ የተለያዩ አማራጮችን ማምጣት ይችላል:: ዋናው ነገር መሰረተ-ልማት የሚለማው ህዝቡ በሰፊው ሲሳተፍና መንግስት በህዝቡ ሊሸፈኑ የማችይሉ ቀዳዳዎችን በመድፈን ሲንቀሳቀስ፣ በሁለቱ የተቀናጀ እንቅስቃሴ ብቻ መሆኑን መገንዘቡ ላይ ነው::

ህዝቡ በዋነኛነት በማሳውና በጓሮው ከዚያ ቀጥሎ በአካባቢው በሚካሄዱ የልማት ስራዎች ላይ በሰፊው ካልተሳተፈ በስተቀር ፈጣን የገጠር ልማት ብሎ ነገር የለም ማለት አንድ ጉዳይ ነው:: ተሳትፎውን ለማረጋገጥ ምን መደረግ አለበት



የሚለውን በትክክል መመለስ ደግሞ ሌላው ጉዳይ ነው:: አርሶ አደሩ በማሳው፣ በጓሮው ሌት ተቀን እንዲሰራ፣ የሚቀርቡለትን የልማት ፖኬጆች እንዲፈፅም ነው እየተፈለገ ያለው:: ይህንኑ ስራ አርሶ አደሩ አምኖበት ካልሰራው በስተቀር ተቆጣጥሮና በትእዛዝ ማሰራት በፍፁም የሚታሰብ አይደለም:: ቁጥጥሩ ይሞከር እንኳ ቢባል የአርሶ አደሩን ያህል ቁጥር ያለው ተቆጣጣሪ መመደብ ሊጠይቅ የሚችልና በፍፁም የማይሆን ነገር ነው:: ብቸኛው አማራጭ አርሶ አደሩ ራሱ አምኖ በራሱ ተነሳሽነት እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ነው:: በአካባቢው በሚካሄዱ ስራዎች ላይ አርሶ አደሩ እንዲሳተፍ ለማድረግ በትእዛዝና በመመሪያ መሞከር ይቻላል:: በዚህ መልኩ ሊሰራ የሚችል አንዳችም ነገር የለም ማለትም አይቻልም:: ይሁንና ይህ የምንፈልገውን ፈጣን ልማት ሊያረጋግጥ አይችልም:: አርሶ አደሩ የፈጠራ ችሎታውን በሰፊው በመጠቀም ነው መስራት ያለበት:: አርሶ አደሩ ያለውን ጉልበትና የአካባቢ ሃብት አሟጦ መጠቀም ነው ያለበት:: ይህ ደግሞ በእምነትና በፍላጎት ካልሆነ በስተቀር በሌላ በማንኛውም መንገድ ሊረጋገጥ አይችልም::

የህዝብ ተሳትፎ በምንልበት ወቅት በእምነትና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ተሳትፎን ማለታችን ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው:: ህዝቡ በእምነት እንዲሳተፍ ከተፈለገ በቀረቡለት አማራጮች ላይ በሰፊው መወያየትና መከራከር መቻል አለበት:: ግልፅ ባልሆኑለት ጉዳዮች ላይ አሳማኝ ማብራሪያዎች ማግኘት አለበት:: የተሻሉ የሚላቸው አማራጮች ካሉም ማቅረብ መከራከር መቻል አለበት:: ከዚህ በኋላም ይጠቅመኛል ብሎ የሚያምንበትን ብቻ መርጦ የመወሰንና የመፈፀም መብት ማግኘት አለበት:: በሌላ አነጋገር በተሟላ ዴሞክራሲያዊ አሰራር ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ መሆን አለበት:: ዴሞክራሲ በሌለበት

ፈጣን የገጠር ልማትን ሊያረጋግጥ የሚችል የህዝብ ተሳትፎ አይኖርም። ስለሆነም ነው ዴሞክራሲ በኛ ሁኔታ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ለመዋጋት የሚያስችለን ቁልፍ መሳሪያ ነው የምንለው። ስለሆነም ነው የህዝብ ተሳትፎ ስንል ዴሞክራሲያዊ የህዝብ ተሳትፎ ማለታችን ብቻ የሚሆነው።

ፈጣን የገጠር ልማትን ለማረጋገጥ ወሳኙ ነገር ህዝቡን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን አሳምኖ በዚሁ የልማት ስራ ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ ነው፣ የመንግስት ሚና በዚህ የማይሸፈኑትን ቀዳዳዎች መሸፈን ብቻ ይሆናል ስንል በገጠር ልማት አመራር ላይ የሚኖረውን ወሳኝ ሚናም ማስቀመጣችን ጭምር ነው። በአካባቢው ያሉ የመንግስት አመራር አካላት በህዝቡ የማይፈሸኑት ቀዳዳዎችን ለመድፈን የሚያስችል ስራ የመስራት ብቃት፣ ይህን ለማድረግ የሚያስችል መዋቅር ወዘተ. ሊኖራቸው ይገባል። ነገር ግን እነዚህ ስራዎች ትርጉም የሚኖራቸው በህዝቡ ሰፊ ተሳትፎ ላይ የተመሰረቱ እንደሆነ ነው። ህዝቡ በሰፊው በማይሳተፍበት ሁኔታ ቀዳዳዎችን ልድፈን ብሎ መንቀሳቀስ ቀዳዳ በርሜልን ለመሙላት ከመሞከር የተለየ አይሆንም። ስለሆነም ቀዳዳዎችን ለመድፈን ከመንቀሳቀስ በፊትና ከዚያ በላይ ህዝቡን በዴሞክራያዊ አኳኋን ለልማት ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል። የገጠር ልማት አመራር ዋነኛው ስራና የብቃቱ ዋነኛው መመዘኛም ይኸው ነው። ይህን ለማድረግ የሚችል አመራር ባለበት ፈጣን የገጠር ልማት ይኖራል፣ እንደዚህ አይነት አመራር በሌለበት የፈለገው ነገር ቢቀርብ የተሳካ ፈጣን የገጠር ልማት ፕሮግራም ሊኖር አይችልም።

አርሶ አደሩ አምኖ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ በቅድሚያ መሟላት የሚገባው ነገር የአርሶ አደሩን ጥቅም በላቀ ደረጃ



ሊያስከብር የሚችል የልማት አማራጭ ማቅረብ ነው። የአርሶ አደሩን ጥቅም በላቀ ደረጃ የማያስከብር አማራጭ ይዞ አርሶ አደሩን ማሳመን በፍፁም የሚታሰብ አይደለም። ነገር ግን የአርሶ አደሩን ጥቅም የሚያስጠብቅ አማራጭ ይዞ መቅረብ ብቻውን በቂ አይደለም። የቀረበው አማራጭ ከሌሎች አማራጮች ሁሉ በላቀ ደረጃ የአርሶ አደሩን ጥቅም የሚያስከብር እንደሆነ በዝርዝር ማስረዳት ያስፈልጋል። አርሶ አደሩ ጥሩ አማራጭ መሆኑን ተቀብሎም ቢሆን ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነገር መሆኑን ከተጠራጠረ ተግባራዊ ሊያደርገው አይችልም። ስለሆነም የአርሶ አደሩን ጥቅም የሚያስጠብቅ ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ ሊሆን የሚችል አማራጭ መሆኑንና ይህንኑ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል በዝርዝር ማስረዳት ያስፈልጋል። ይህንኑ የማስረዳት እንቅስቃሴ በተለያዩ አማራጮች በተለያዩ መንገዶች አንዴ ሳይሆን ደጋግሞ መስራት ይጠይቃል። የገጠር ልማት አመራር ብቃት አንዱ መመዘኛ ይህን የመስለውን ብቃት ያለው ተከታታይና ተደጋጋሚ የማስረዳት ስራ በብቃት ለመስራት መቻል ነው።

የማስረዳቱን ስራ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ማስፈፀም የህዝብ ተሳትፎን ለማረጋገጥ አንድ ቁልፍ ስራ ነው። ነገር ግን ይህ የስራው መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ አይደለም። አርሶ አደሩ የህይወቱን አቅጣጫ በመሰረቱ በሚቀይር ስራ ላይ በውይይትና በማብራሪያ በሚያገኘው ሃሳብ ላይ ብቻ ተመስርቶ በብቃት አይሳተፍበትም። ያን አማራጭ በተግባር መፈተሽ መቻል አለበት። በተግባር ፈትሾ የሚሰራና የሚጠቅም መሆኑን ማረጋገጥ መቻል አለበት። የህዝብ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን በሚመለከት ያለው ዋነኛ ችግርና የአመራር ብቃት የሚጠይቀውም ነገር ይኸው ነው። አርሶ አደሩ በተግባር

ካላረጋገጠ በስተቀር ወደአዲስ አቅጣጫ አይገባም። አርሶ አደሩ በተግባር ካልተመለከተ በስተቀር የሚፈለገው አቅጣጫ የማይፈፀም ከሆነ የመጀመሪያውን ተግባር ማን ይግባበት የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል። አርሶ አደሩን ለማሳመን የሚያስፈልገው የአርሶ አደሩ ተጨባጭ ልምድ ከየት ይምጣ ነው ወሳኙ ጥያቄ።

ይህንን ቋጠሮ ለመፍታት የተለያዩ ስልቶች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ዞሮ ዞሮ ግን ጀማሪ የሚሆኑ ግንባር ቀደም አርሶ አደሮችን መፍጠር፣ እነዚህ ስራውን በተሳካ መልኩ እንዲፈፅሙት ማድረግ፣ ይህን የተሳካ ፍፃሜ አርሶ አደሩ በሰፊው እንዲያየው፣ እንዲፈትሸው፣ እንዲረዳውና ከዚህም ተነስቶ ራሱም እንዲከተለው የማድረግ ጉዳይ ነው። ጀማሪ የሆኑ አርሶ አደሮች በውይይት ሂደት ነገሩን በሚገባ በመገንዘባቸውና ለመሞከር ዝግጁ በመሆናቸው የሚለዩ አርሶ አደሮች ሲሆኑ በጅመራ ስራው ላይ ለመሳተፍ የተለያዩ ማትጊያ ተሰጥቷቸው ነገሩን በሞዴልነት ለመጀመር ዝግጁ የሆኑ አርሶ አደሮች ወይም መንደሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ለመንግስት ካላቸው ፖለቲካዊ ድጋፍና ቅርበት የሚነሱም ሊሆኑ ይችላሉ። መነሻቸው ምንም ይሁን ምን እነዚህን በጥንቃቄ መርጦ የተሟላ ድጋፍ ሰጥቶ ስራውን በጠራ መልኩ እንዲፈፅሙ ማድረግ፣ አርሶ አደሩን በተሻለ አዲስ አቅጣጫ ለመምራት የሚያስችለን ቁልፍ ርምጃ ነው።

እንደነዚህ አይነት ሰዎችን ወይም መንደሮችን አፈላልጎ፣ ማትጊያዎችን ሰጥቶ አንቅሳቅሶ የተሳካ ስራ እንዲሰሩ ከተደረገ በኋላ የሚሰራው ስራ ህዝቡን ለማሳመን የመጨረሻው ወሳኙ ርምጃ ነው። ህዝቡ ግንባር ቀደም የሆኑት ሰዎች ስራ ምን



እንደሆነ፣ ምን ውጤት እንዳስገኘ፣ ስራው እንዴት እንደተሰራ፣ ለምን የተሳካ ውጤት እንዳስገኘ በአይኑ ተመልክቶ፣ በማብራሪያዎችና በመግለጫዎች አረጋግጦ አምኖ ለስራ መሰማራት እንዲችል ጥረት መደረግ አለበት። ይህን ለማድረግ ህዝቡ በአይኑ የሚያይበት፣ ስራውን ከሰሩት ሰዎች መንደሮች ወዘተ. ማብራሪያና መግለጫ የሚያገኝበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት። በነዚህ ላይ ተመስርቶ የተቀመጠውን አማራጭ ትክክለኛነትና ተግባራዊ ለመሆን የመቻሉን ዕድል በድጋሚ ለማስረዳት ሰፊ ጥረት መደረግ አለበት።

በዚህ ሂደት ከታለፈ በኋላም ሁሉም አርሶ አደሮች በስራው ላይ እኩል እምነትና ቁርጠኛነት ላይኖራቸው ይችላል። ቀላል ቁጥር የሌላቸው አርሶ አደሮች እስከነጥርጣሪያቸው ሊገቡበት ይችላሉ፣ ሌሎቹ አሁንም ከዳር ሆነው ማረጋገጥ ሊፈልጉ ይችላሉ። ህዝቡን መሄድ ከሚፈልገው ርቀት በላይ መግፋት ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ሁሉም መራመድ በሚችልበት ፍጥነት እንዲራመድ እድል መስጠት ያስፈልጋል። በየራሱ ፍጥነት ከተራመደ በኋላ የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ ፈጥነው የተራመዱና አቅጣጫውን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ያደረጉቱ በይበልጥ እንደተጠቀሙ ማሳየት፣ ይህንኑ መሰረት በማድረግ በድጋሚ የማሳመኑን ስራ መስራት ያስፈልጋል። አርሶ አደሮቹ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በዚህ መልኩ እምነት ከያዙ ከነዚህ በመነሳት መሰራት ባለባቸው ዝርዝር ጉዳዮች ላይ በቀላሉ ማሳመን ይቻላል። አመራር በሰጣቸው ክፍል ላይ ባላቸው እምነት ብቻም ረጅም ርቀት ሊሄዱ ይችላሉ። ዋናው ነገር የሚሆነው ከላይ በተዘረዘረው አኳኋን በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አመለካከታቸውን እንዲያስተካክሉ በመሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ እምነት

www.abyssinialaw.com

እንዲኖራቸው የማድረግ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የአመራር ብቃት የማረጋገጥ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የአርሶ አደሩ የመሳተፍ ፍላጎት የተረጋገጠበት ሁኔታ ስለሚፈጠር የሚቀረው ጉዳይ ይህንኑ በማስተባበር በውሱን አቅም የላቀ የስራ ውጤት የማስገኘት ብቃት ያለው የአመራር ብቃት የማረጋገጥ ጉዳይ ነው፡፡

እንደሌላው የልማት ስራ ሁሉ በገጠር ልማትም የወጣቱ ትውልድ ሚና ወሳኝ ነው፡፡ የገጠር ልማት ስራችን በአብዛኛው የሰው ጉልበትን በመጠቀም የሚፈፀም ነው፡፡ የወጣት ትውልድ ከፍተኛ የስራ ጉልበት በገጠር ልማት ላይ በበቂ ሁኔታ መሰማራቱ ወሳኝ ነው፡፡ ዋናው ሃይል የወጣት ጉልበት ስለሆነም ይህን አቅም ማንቀሳቀስ ወሳኝ መሆኑ የግድ ነው፡፡ የግብርና ቴክኖሎጂያችን በማያቋርጥ የእድገት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገባ የተማረ አርሶ አደር ያስፈልጋል፡፡ ሰፊ የትምህርት ዕድል ያለው ወጣቱ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የቀጣይ ቴክኖሎጂ እድገትና ገጠር ልማት መሰረትም ይኸው ክፍል ከመሆን ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ የግል፣ የቤትና የአካባቢ ንፀህናን ከማሻሻል፣ የአርሶ አደሩን አኗኗር ለመለወጥና ዘመናዊ ለማድረግ፣ መላውን ህብረተሰብ ማንቀሳቀስ የሚያስፈልግ ቢሆንም ለለወጡ ቅርብ የሚሆነው ወጣቱ በተለይም የትምህርት ዕድል ያገኘው ወጣት ነው፡፡ በጥቅሉ ወጣቱን በሰፊው የማያሳትፍና የማያንቀሳቅስ የገጠር ልማት ስራ ቀጣይነት ያለውና ፈጣን ሊሆን አይችልም፡፡

ወጣቱ የገጠር ልማት፣ የአርሶ አደሩ ባህልና አኗኗር የማሻሻል እንቅስቃሴው ግንባር ቀደም ተዋናይና ወሳኝ ሃይል መሆን ይችላል፣ መሆንም አለበት ማለትና ወጣቱን ይህንን



ሚና በብቃት እንዲጫወት ማስቻል ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ወጣቱ በገጠር ልማት ላይ መጫወት የሚገባውን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ የተቀናጀ ጥረት መደረግ አለበት፡፡ በአርሶ አደሩ አቅም ግንባታ ዙሪያ ያነሳናቸው ነጥቦች ይህን ስራ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ወጣቱ የገጠር ትውልድ ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲያገኝ፣ በዚህ ደረጃ የሚጠሰው ትምህርት በገጠርና በግብርና ልማት ስራ ላይ ለመሰማራት የሚችልና የሚፈልግ መልካም አምራች ዜጋን የሚፈጥር እንዲሆን፣ በዚህ ላይ ተመስርቶ በተለያዩ የሞያ ዘርፎች በተለይም በግብርና ዘርፍ እንዲሰለጥን፣ ከስልናው ጋር የሚሄድ የቴክኖሎጂ ፖኬጅ እንዲቀርብለት፣ በዚሁ ለመጠቀም የሚያስችለው የፋይናንስ አገልግሎት እንዲያገኝ ወዘተ. እነዚህ ተሟልተውና ተቀናጅተው እንዲቀርቡ ማድረግ ወጣቱ ሚናውን በአግባቡ እንዲወጣ ለማድረግ የሚያስችሉን ርምጃዎች ናቸው፡፡

ወጣቱ በግብርናና በገጠር ልማት ላይ መጫወት የሚገባውን ሚና እንዲጫወት የሚያስችሉት ስራዎች በአጠቃላይ የገጠር ልማት ስራ ስር ሲፈፀሙና፣ እነዚህ ስራዎች መላውን አርሶ አደር የሚሸፍኑ ቢሆኑም ትኩረታቸው በወጣቱ ላይ እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጎ ወጣቱን ከማብቃትና ከማንቀሳቀስ አኳያ እንዲቃኙ ሲደረግ ውጤቱ ሊለያይ ይችላል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ስራዎች ከአጠቃላይ የገጠር ልማት ስራ አኳያ ብቻ ሳይሆን በዋናነት ወጣቱ በገጠር ልማት ላይ መጫወት የሚገባውን ሚና እንዲጫወት ከማስቻልና ከማብቃት አኳያ እየታዩ የሚፈፀሙ መሆን አለባቸው፡፡

ወጣቱ በገጠር ልማት ላይ መጫወት የሚገባውን ሚና እንዲጫወት የሚያስችለውን አቅም መገንባት ቁልፍ ስራ

www.abyssinialaw.com

ቢሆንም ይህ ብቻ ወጣቱን በብቃት ማንቀሳቀስ የሚያስችል አይሆንም፡፡ ወጣቱ በተደራጀ አኳኋን ለመብትና ለጥቅሙ መንቀሳቀስ የሚያስችለው ድርጅት ያስፈልገዋል፡፡ የወጣቶች ማህበራት መፍጠር፣ መጠናከርና ወጣቱን በገጠር ልማት ላይ በብቃት ማሳተፍን በሚመለከት የላቀ ሚና የሚኖራቸውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ወጣቱ በገጠር ልማት ላይ የመወሰን እቅድ የማፅደቅና የማስፈፀም ስልጣን ባላቸው የመንግስት አካላት በተለይም በቀበሌ ምክር ቤቶች በብቃት የሚወከልበት ስርአት መኖሩም በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የወጣቶች ማህበራት እንደሌሎች የብዙሃን ማህበራት ሁሉ መደራጀትና መጠናከር ያለባቸው የአባላቸውን መብትና ጥቅም ለማስከበር ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሚደራጅ ማህበር ጥንካሬም ሆነ ቀጣይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ የወጣቱ መብትና ጥቅም የሚከበረው ቀደም ሲል የገጠር ልማት ስትራተጅ ተግባራዊ ሲሆን ነው፡፡ ይህ በሌለበት የወጣቱ መብትም ሆነ ጥቅም ሊከበር ስለማይችል የወጣት ማህበራት ወጣቱ በዚሁ ስራ ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ማደራጀትና ማንቀሳቀስ መቻል አለባቸው፡፡ ወጣቱ በገጠር ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ከማምጣትም ባሻገር፣ በዚሁ ላይ ተመስርቶ ከልማቱ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ማህበራቱ ወጣቱ በልማት ስራ ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ከማድረግ ጎን በጎን ከሚመጣው ልማት በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ወጣቱን አስተባብረው መታገል መቻል አለባቸው፡፡

ይህን ለማድረግ የወጣት ማህበራት በሁሉም ደረጃዎች በተለይም በቀበሌ ደረጃ መፈጠርና መጠናከር አለባቸው፡፡ እንደሌሎች የብዙሃን ማህበራት ሁሉ ድርጅታዊ ነፃነታቸው



መጠበቅ አለበት፡፡ ወጣቱ የልማት አቅሙን ለማሻሻል በትምህርትና ስልጠና፣ በጤና አጠባበቅ፣ በቴክኖሎጂና የፋይናንስ አገልግሎት ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ አስተባብረው ማንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ወጣቱ የሚያጋጥሙት ችግሮችና እንቅፋቶች ላይ በሰፊው እየተወያዩ ወጣቱ ተባብሮ ራሱ ሊፈታ የሚችለውን አስተባብሮ እንዲፈታ በማድረግ፣ በወጣቱ ሊፈቱ የማይችሉትን ለሚመለከተው አካል ቀርበው እንዲፈቱ ወጣቱን አስተባብረው መታገል ይገባቸዋል፡፡ የወጣቱን የመሬት ችግር መፍታትም ላይ የላቀና ገንቢ ሚና መጫወት አለባቸው፡፡ ወጣቱ በቀበሌ ምክር ቤቶችና በአመራር አካላት በብቃት እንዲወከልና ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወት ማስተባብርም ይገባቸዋል፡፡

የገጠር ልማትን ለማፋጠን፣ የህዝቡን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚደረገው እንቅስቃሴ የመላውን የገጠር ህዝብ መብትና ጥቅም የሚያረጋግጥ እንደሚሆን እሙን ነው፡፡ ከገጠሩ ህዝብ ግማሽ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡ ሴቶችም ከዚሁ እንቅስቃሴ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ይልቁንም የገጠር ሴቶችን መብትና ጥቅም በላቀ ደረጃ ማረጋገጥ የሚቻለው ከላይ የተጠቀሰው አቅጣጫና የህዝብ ተሳትፎ እውን ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ይህ አቅጣጫ ተግባራዊ ባልሆነበት ሁኔታ የገጠር ሴቶችን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚደረግ ሙከራ አንድም ፋይዳ የሌለው የዋህነት፣ አለያም በገጠር ሴቶች መብትና ጥቅም መነገድ ነው የሚሆነው፡፡ ይሁንና የገጠር ሴቶች መብትና ጥቅም የሚረጋገጠው መላው የገጠር ህዝብ በተጠቀሰው አቅጣጫ ሲንቀሳቀስ ነው በሚል ሴቶች በዚሁ ክልል ተሳትፏቸውን እንዲያጠናክሩ፣ ከሚገኘው የገጠር ልማት የላቀ ጥቅም እንዲያገኙ ለማድረግ በሴቶች ላይ ያተኮረ ለየት ያለ እንቅስቃሴ

www.abyssinialaw.com

አያስፈልግም ወይም መደረግ የለበትም ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም በተቀመጠው አቅጣጫና የመላው ህዝብ ተሳትፎ ተግባር ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎና ጥቅም ለማረጋገጥ በሴቶች ላይ ያተኮረ ለየት ያለ እንቅስቃሴ ካልተደረገ በስተቀር ሴቶች ከተቀመጠው አቅጣጫ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ሊያገኙ አይችሉም፡፡ ስለሆነም በሴቶች ተሳትፎ ላይ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን የተስተካከለ ራዕይ ይዞ በሰፊው መንቀሳቀስ በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ሴቶች በገጠር ልማት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማጠናከር የሚደረገው እንቅስቃሴ የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ወገኖች መብትና ጥቅም በይበልጥ ለማረጋገጥ ሲባል መደረግ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን የሴቶችን ተሳትፎ ለማጎልበት የሚደረገው እንቅስቃሴ ብቸኛው ምክንያቱ ይህ አይደለም፡፡ ሴቶች በሚካሄደው የገጠር ልማት እንቅስቃሴ በሰፊው ካልተሳተፉና ከዚሁም በላቀ ደረጃ እንዲጠቀሙ ካልተደረገ በስተቀር የገጠር ልማት አቅማችን ቢያንስ ግማሹ ከጥቅም ውጭ ይሆናል፣ በአንዳንድ የልማት ዘርፎችም ከግማሽ እጅግ የላቀው የልማት አቅማችን ከጥቅም ውጭ ይሆናል፡፡ ከግማሽ የሚበልጠውን የልማት አቅም ከጥቅም ውጭ በማድረግ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የገጠር ልማት ማረጋገጥ ሊታሰብ እንደማይችል መገመት አዳጋች አይደለም፡፡

ሴቶች በገጠር ልማቱ ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የነሱም የልማት አቅም በከፍተኛ ደረጃ መጨመር አለበት፡፡ በትምህርት ከወንዶች ጋር እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ለየት ያለ ጥረት መደረግ አለበት፡፡ ይህን በተመለከተ በበርካታ የአገራችን አካባቢዎች የሴቶችን



የትምህርት ተሳትፎ የሚገቱ ስር የሰደዱ ኋላ ቀር ባህሎች እንዳሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ለየት ያለ እንቅስቃሴ ካልተደረገ በስተቀር የሚፈለገው ውጤት ሊገኝ አይችልም፡፡ በርግጥ ሴቶች በትምህርት እንደወንዶች በእኩልነት መሳተፍ አለባቸው ስንል ተምረው፣ ሰልጥነው በግብርናም ሆነ በሌሎች ስራዎች እንደወንዶች ሁሉ ተሰማርተው ራሳቸውን ጠቅመው የአገራችንን ልማት በከፍተኛ ደረጃ ያጠናክራሉ፣ እንደወንዶች ሁሉ የዜግነት መብታቸውን በአግባቡ ሊጠቀሙበት ይችላሉ በሚል ነው፡፡ ይሁንና የሴቶች ትምህርት ከዚህ በተጨማሪም ጥቅም አለው፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ ወንዶችና ሴቶች እኩል የመማር መብት ሊኖራቸው ይገባል ማለቱ ትክክለኛና ተገቢ ቢሆንም ቢያንስ በአንደኛ ደረጃ ከወንዶች ትምህርት ይልቅ የሴቶች ትምህርት ለልማት የላቀ ተፈላጊነት አለው ማለት ይቻላል፡፡

ሴቶች ተምረውና ሰልጥነው ወንዶች በተሰማሩባቸው የስራ መስኮች ሁሉ ሊሰማሩ ስለሚችሉና ስለሚገባቸው በእኩልነት መሳተፋቸው ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ሴቶች ቢያንስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ማድረግ ያለእድሜ ጋብቻን በመቀነስ፣ የቤተሰብ ምጣኔን በማሻሻል የወንዶች ትምህርት ለህብረተሰቡ ከሚያስገኘው በላይ ጥቅም ያስገኛል፡፡ በተጨማሪም በተለይም በኛ ህብረተሰብና ባለንበት የእድገት ደረጃ ሴቶች ዋነኛ የቤት ውስጥ ስራ ተሸካሚዎችና የልጆች አሳዳጊዎች መሆናቸው አይቀርም፡፡ ይህ ሁኔታ ተገቢ አይደለም ብሎ መከራከር የሚቻል ቢሆንም ነባራዊ እውነታው ይህ መሆኑ የማይታበል ሃቅ ነው፡፡ የተማሩ እናቶች የቤተሰብ ንፅህናንና ጤናን በመንከባከብ፣ የህፃናት ትምህርትን በከፍተኛ ደረጃና በቤት ውስጥ በመደገፍ የወንዶች ትምህርት የማያስገኘውን ተጨማሪ ጥቅም ያስገኛሉ፡፡

www.abyssinialaw.com

የሴቶች ትምህርት ቢያንስ በአንደኛ ደረጃ ከወንዶች ትምህርትም የላቀ ልማታዊ ጠቀሜታና ተፈላጊነት አለው ሲባልና ለዚህም ምክንያት የሆኑት ነገሮች ሲቀመጡ ዋናው ነጥብ ሴቶች ቢያንስ በእኩልነት የመማር ዕድል ማግኘት እንዳለባቸው ማስመር ነው:: አሁን ያለው የተዛባ ተሳትፎ በእኩልነት መተካቱ ለሴቶች ሲባል ብቻ ሳይሆን ለፈጣን የአገሪቱ ልማት ሲባልም በአፋጣኝ መስተካከል መደረግ እንዳለበት፣ ለዚሁ ሲባል ኋላ ቀር ባህሎችን ጠንክረን በመቋቋም የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ከወንዶች ጋር እኩል ወደሚሆንበት ደረጃ ማድረስ እንዳለብን ለማመልከት ነው:: በቤት ውስጥ የተማሩ ሴቶች የመኖራቸው ተጨማሪ ጠቀሜታ ሲሰመርበት ሴቶች ተምረው ለቤት ስራ ብቻ መታጨት አለባቸው ማለትም አይደለም:: ይልቁንም ይህንኑ ኋላ ቀር አመለካከት ተዋግተን ሴቶች በግብርናም ሆነ በሌላ የልማት ዘርፍ እኩል ተሿትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ካልቻልን በስተቀር የትምህርቱ ውጤት ዝቅተኛ እንደሚሆን ግልፅ ነው:: በዚህ ዘርፍ የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ከወንዶች እኩል እያበረከቱ በዚህ ላይ ተጨማሪ አስተዋፅኦ በቤት ውስጥ ያበረክታሉ ማለት ነው::

ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የትምህርት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ አንዱ ጉዳይ ሆኖ የሚሰጠው ትምህርት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በሽታን የመከላከል፣ የአካባቢ፣ የቤትና የግል ንፅህናን መጠበቅም የሚጨምር ሲሆን በዚህ ትምህርት ወንዶቹም ተጠቃሚ ይሆናሉ፣ ሴቶቹ በራሳቸው ተጠቃሚ ከመሆን አልፈው በጠቅላላ ቤተሰብን መጥቀም ይችላሉ:: የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንደጨረሱም ሴቶቹ በግብርናም ሆነ ከግብርና ውጭ ባሉ ሙያዎች የማሰልጠንም ሆነ ወደሚቀጥለው የትምህርት እርከን የመተላለፍ እኩል እድል



ሊሰጣቸው ይገባል:: በተለይም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ በሚሰጡ የሙያ ስልጠናዎች ውስጥ ከግብርና ውጭ በሚሰጡት ስልጠናዎች ቅድሚያ ለሴቶች መስጠት ትክክለኛና ተገቢ ይሆናል::

በገጠር የሚስፋፋው የጤና ጥበቃ አገልግሎት በመከላከልና በመሰረተ-ጤና አገልግሎት ላይ ያተኮረ እንደሚሆን ቀደም ሲል ተገልፇል:: የመከላከልና የመሰረተ-ጤና አገልግሎት በቤተሰብና ቤት ንፅህናና እንክብካቤ ላይ ማተኮሩም የማይቀር ይሆናል:: ይህ ስራ ወንዶችን የሚሸፍን ቢሆንም በዋነኛነት በእናቶችና በህፃናት ላይ ማተኮር ይኖርበታል:: የመከላከልና የመሰረተ-ጤና አገልግሎት በእናቶችና ህፃናት ጤንነት ላይ ማተኮር አለበት የምንለው የሌላው ሰው ህይወትና ጤንነት ከነሱ ያነሰ ዋጋ አለው ማለት አይደለም:: የእናቶችና የህፃናት ጤና እንክብካቤ ሲሻሻል፣ እናቶች ከዚህ አኳያ መጫወት የሚችሉትን ሚና በተሟላ መንገድ ሲጫወቱ የመላውን ቤተሰብ ብሎም የመላውን ህብረተሰብ ጤንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል ወሳኝ ርምጃ እንደሚወሰድ ለማስቀመጥ ነው:: በመሆኑም የመሰረተ ጤናና የመከላከል ስራችን እናቶችንና ህፃናትን ማዕከል ያደረገና እነሱን በሰፊው የሚያሳትፍ ቅኝት ይዞ መጓዝ ይኖርበታል:: የሴቶች መማር ከዚህም አኳያ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል::

የሴቶችን የማምረት አቅም የማጎልበት ስራ ተሰርቶ በምርትና ልማት ተግባር ላይ በሰፊው የሚሳተፉበት ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር የሚፈለገውን ውጤት አያስገኝም:: ስለሆነም ሴቶች በልማት ተግባር ላይ በሰፊው እንዲሳተፉ ለማድረግ ከዚህ አኳያ ያሉትን ኋላቀር አስተሳሰቦች በቀጣይነት መታገል ያስፈልጋል:: ከዚህ በተጨማሪ የቤት ውስጥ ስራን

www.abyssinialaw.com

ለማቃለል የሚያስችሉ ርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። ወንዶች ቢያንስ በተወሰኑት የቤት ውስጥ ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ይሁንና ባለን ኢኮኖሚያዊ ኋላ ቀርነትና የባህል ተፅእኖ ይህ ጥረት ሊሄድ የሚችልበት ርቀት የራሱ ውሱንነት አለው። ስራው በአብዛኛው በሴቶች ጫንቃ ላይ ማረፉ አይቀርም። ስለሆነም ስራውን ለማቃለል ሰፊ ጥረት መደረግ አለበት። የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ለቤት ቅርብ እንዲሆን በማድረግ፣ የማገዶ እንጨት አቅርቦትና አጠቃቀምን በማሻሻል፣ ወፍጮ ቤቶችን በማስፋፋትና በነዚህ ስራዎች ሌሎች የቤተሰብ አባላትም እንዲሳተፉ በማበረታታት የሴቶችን ሸክም ከማቃለል አኳያ ረጅም ርቀት መሄድ ይቻላል። ይህንን የቤት ስራዎችን ሸክም የማቃለል መሰረታዊ አቅጣጫ በመከተል ሌሎች በርካታ ስራዎችን መስራትና እነዚህን በቀጣይነት እያሻሻሉ መሄድ ይቻላል፣ ይገባልም።

የሴቶችን ልማታዊ አስተዋፅኦ ለማጠናከር ሴቶችን በሞያ ስልጠናዎች ላይ ማሳተፍ በተለይም ከግብርና ውጭ በሚደረጉ ስልጠናዎች ቅድሚያ ከመስጠት ባሻገር በሰለጠኑበት ሙያ ለመሰማራት የሚያስችላቸው የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠርም ያስፈልጋል። በግብርና ዘርፍ ካላቸው የቤት ስራ ሸክም ጋር በተያያዘ በላቀ ደረጃ ሊሳተፉ የሚችሉት በጓሮ ዙሪያ፣ በእንሰሳት ሃብት ልማት (ለምሳሌ የዶሮ፣ የንብ ርቢ) ዘርፍ ስለሆነ በዚህ ላይ ትኩረት መስጠት የብድር አገልግሎት ላይ በተቻለ መጠን ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። ከግብርና ውጭ በሚደረጉት ስልጠናዎች ለሰለጠኑት ሴቶች ቢያንስ በመንግስት ስራ ቅድሚያ መስጠትም ተገቢ ነው። ራሳቸውን ችለው በሚያቋቁሟቸው ተቋሞች የብድርና የምክር አገልግሎት መስጠትም በጣም አስፈላጊ ይሆናል።



ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ ንብረት የማፍራት መብትን የሚመለከተው ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች የገጠር ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል በመሬት የመጠቀም መብት ያላቸው ሲሆን በሌሎች አካባቢዎች ግን ካለው ከፍተኛ የባህል ተፅእኖ ጋር ተያይዞ ይህ ተግባራዊ አልሆነም። ይህን ለማድረግ መሬትን እንደገና ማከፋፈል አይጠይቅም። አርሶ አደሩ እየተጠቀመበት ያለው መሬት የወንድየው ብቻ ሳይሆን የሴቶችም ጭምር መሆኑን በህግ በማረጋገጥ መሬት ሳይከፋፈል ሊረጋገጥ የሚችል የእኩልነት መብት ነው። ይሁንና ይህ በትእዛዝና በመመሪያ ሊፈፀም የሚችል ወይም መፈፀም ያለበት ነገር አይደለም። ከአካባቢው ባህል መለወጥ ጋር ተያይዞ ማህበራዊ ቀውስ በማይፈጥር አኳኋን ህዝቡ ተቀብሎት መፈፀም ያለበት ነው። ህዝቡ እዚህ ደረጃ ላይ ሳይደርስ በስመ እኩልነት በቀላጤ ለመፈፀም ቢሞከር ለልማትም ሆነ ለሴቶች እኩልነት የሚያስገኘው አንዳችም ተጨባጭ ፋይዳ የለም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሴቶች ብድር በሚያገኙበት፣ በሙያቸውና በተሰጣቸው ብድር በተጨባጭ የልማት እንቅስቃሴ በሚሳተፉበት ወቅት የባለቤትነት መብታቸውን በተሟላ ሁኔታ ማረጋገጥ እጅግ ተፈላጊ ይሆናል። ከዚህ ውጭ ሴቶች ከልማቱ መጠቀም በሚገባቸው ደረጃ ሊጠቀሙ አይችሉም።

ሴቶች በገጠር ልማት ውስጥ በሰፊው እንዲሳተፉ ለማድረግ ፖለቲካዊ ተሳትፏቸውን ማጠናከር ያስፈልጋል። በቀበሌ ምክር ቤቶች በተለያዩ ኮሚቴዎች (ለምሳሌ በውሃ ኮሚቴዎች) በበቂ ሁኔታ እንዲሳተፉ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም መንቀሳቀስ ይገባል። ነገር ግን እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባ አንድ ጉዳይ አለ። ወንዶች በዚህ ጉዳይ ላይ ደረጃ በደረጃ አመለካከታቸው እንዲስተካከል ለማድረግ ሰፊ ጥረት

www.abyssinialaw.com

ካልተደረገ በስተቀር አስተዳደራዊ ስልቶችን በመጠቀም የሴቶችን ተሳትፎ ለማጠናከር ሊኬድ የሚችለው ርቀት በጣም ውሱን ነው፡፡ ስለሆነም በዋነኛነት ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ስለሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያለውን አመለካከት ለማሻሻል በመረባረብ ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ የሴቶች ተሳትፎን ሊያጠናክሩ የሚችሉ አስተዳደራዊ ርምጃዎችን በመውሰድ ተሳትፏቸውን ለማጎልበት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡

ሴቶች በልማትም ሆነ በፖለቲካ በላቀ ደረጃ እንዲሳተፉ፣ ከዚሁም በላቀ ደረጃ እንዲጠቀሙ ለማድረግ በየቀበሌው የሚደራጁ የሴቶች ማህበራት ልዩና የላቀ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡ በነዚህ ማህበራት አማካኝነት ሴቶች በልማት ስራ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችላቸው ምክር፣ ብድርና የልምድ ልውውጥ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ በነዚህ ማህበራት አማካኝነት የቤት ስራዎችን በማቃለል፣ የቤተሰብ እንክብካቤንና ጤንነትን ለማሻሻል ቀጣይ ትምህርትና የምክር አገልግሎት፣ ሰፊ የልምድ ልውውጥ እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል፡፡ በነዚህ ማህበራት አማካኝነት ሴቶች በልማቱም ሆነ በፖለቲካዊ ተሳትፎ ረገድ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በሰፊው መወያየትና ተደጋግፈው እንዲፈቷቸው ማድረግ ይቻላል፡፡

በገጠር የሚኖሩ የብዙሃን ማህበራት፣ በተለይም ተምሮ የቀጣይ የገጠር ልማታችን ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሞተር ይሆናል ብለን የምንገምተውን ወጣት የሚያቅፉት የወጣቶች ማህበራት ልዩ ግምት ሊሰጣቸው የሚገባ ናቸው፡፡ ይሁንና አሁን ያሉበትን የእድገት ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባትና ሴቶች በገጠር ልማት ላይ ያላቸውን ልዩ ሚና መሰረት በማድረግ የሴቶች ማህበራትን፣ በተለይም ለገጠር ሴቶች ቅርብ የሆኑትን የቀበሌ



የሴቶች ማህበራትን ማጠናከር ከሌሎች የብዙሃን ማህበራት ማጠናከር ስራም በላይ ትኩረት የሚሻ ነገር ነው፡፡ ህዝቡ የሚሳተፍባቸው መድረኮች በአጠቃላይ መጠናከራቸው ልዩ ግምት የሚጠይቅ ስለሆነ ይህንን ጉዳይ እንደሚከተለው ዘርዘር አድርጎ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

## 1.2. የህዝብን የተሳትፎ መድረኮች በአግባቡ መጠቀም፣

ህዝቡን በላቀ ደረጃ አስተባብሮ ለማንቀሳቀስ የሚቻለው በተደራጀ አኳኋን መስራት ከተቻለ ብቻ ነው፡፡ ህዝቡ በብዙሃን ማህበራት ከተደራጀ፣ በነዚህ ማህበራት መድረክነት ለአርሶ አደሩ ማብራሪያዎች ገለፃዎች ወዘተ. መስጠት ይቻላል፡፡ በነዚህ መድረኮች አማካይነት ህዝቡ በነፃ መወያየት፣ መከራከር፣ የሚመስለውን ተቀብሎ፣ የማይመስለውን የሚጥልበት ሁኔታ መፍጠር ይቻላል፡፡ ሰፋፊ የልምድ ልውውጥ መድረኮች እንዲሆኑ በማድረግ ህዝቡ ከተጨባጭ ልምድ ተነስቶ የተቀመጠውን አቅጣጫ ትክክለኛነት በሙሉ ልብ እንዲያምንበት መስተካከል ያለባቸው ሆነው የተገኙ ካሉም እነሱን ለማስተካከል ይችላል፡፡ በነዚህ መድረኮች አማካኝነት ህዝቡ ለዚሁ አላማ ተባብሮ እንዲነሳ ማድረግና ይህን የሚመለከቱ ውሳኔዎች እንዲወስን ማድረግ ይቻላል፡፡ እነዚህን መድረኮች በአስተባባሪነት በመጠቀም ህዝቡ ጉልበቱን አቀናጅቶ በልማት እንዲሳተፍ ወይም በየማሳው በጓሮው የሚሰራውን ስራ እንዲያስተባብር ማድረግ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ህዝቡን የማሳመንና ካመነም በኋላ የማስተባበር ስራ በአንድ መልኩ ብዙሃን ማህበራትን የማጠናከር፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ የህዝብ መድረኮች እንዲሆኑ የማድረግ፣ የአመራራቸውን ነፃነትና ብቃት የማሳደግና ነፃነታቸውን

www.abyssinialaw.com

ጠብቀው ህዝቡን በማስተባበር ስራ ላይ እንዲሳተፉ የማበረታታት የማስተባበር ስራ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ነገር ግን የብዙሃን ማህበራት የህዝቡ ብቸኛ መድረኮች አይደሉም፣ ሊሆኑም አይችሉም፡፡ የቀበሌ ምክር ቤቶችና አስተዳደሮችም የህዝቡ ቀጥተኛ መድረኮች ናቸው፣ መሆንም ይገባቸዋል፡፡ በተለይም የቀበሌ ምክር ቤቶች በተቻለ መጠን የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚያረጋግጡ መሆን አለባቸው፡፡ ለዚህም ሲባል የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር በርካታ እንዲሆን ማድረግ የመጀመሪያው ርምጃ ነው፡፡ በዚህ መልኩ በቀበሌው ካሉት አባወራዎች ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ቁጥር በቀጥታ በምክር ቤቱ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡ ውክልናውን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተገቢው መጠን እንዲሳተፉ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን መቅረፅም ይቻላል፡፡ የቀበሌ ምክር ቤቶች በቀበሌው ውስጥ የሚሰራውን የልማት ስራ በመወሰን ረገድ የላቀ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ዞሮ ዞሮ የልማቱ ዋነኛ ሃይል የቀበሌው የሰው ጉልበት ነው፡፡ መንግስት የሚሰጠው ድጋፍ ይህንኑ መሰረት በማድረግ ቀዳዳዎችን የመድፈን ስራ ነው፡፡ ስለሆነም የቀበሌ ምክር ቤት በልማት ስራዎች ላይ የመወሰን ስልጣን ይሰጠው ሲባል ዞሮ ዞሮ በዋነኛነት በራሱ ጉልበት አጠቃቀም ላይ ይወስን ማለት ነው፡፡ ይህንን ውሳኔ ከቀበሌው ህዝብና ቀጥተኛ ተወካዮቹ ውጭ ማንኛውም ሌላ አካል ሊወስነው አይገባም፣ ልወስን ቢልም በተሳካ አኳኋን ሊፈፅመው የሚችል አይሆንም፡፡

ቀበሌው እነዚህን የቀበሌ ልማት ውሳኔዎች በሚወስንበት ወቅት የተስተካከለውን የገጠር ልማት አቅጣጫ መሰረት ያደረገ፣ ይህንኑ ከቀበሌው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ተግባራዊ



ለማድረግ የሚያስችል መንገድ የተከተለ መሆን አለበት፡፡ ይህን ለማድረግ የሚቻለው የቀበሌው ምክር ቤት አባላት በተሟላ መንገድ ያመኑበትና የተገነዘቡት እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ አባላት ካመኑበት ህዝቡ የሚቀበላቸውና የሚያከብራቸው መሪዎች ስለሆኑ ውሳኔ ከመወሰን አልፈው ግንባር ቀደም ሆነው ለመፈፀም፣ ህዝቡን ለማስተባበርና ምሳሌ በመሆን ለመምራት ይችላሉ፡፡ ስለሆነም የቀበሌ ምክር ቤት የስብሰባ መድረኮች እነዚህ ነገሮች በሰፊውና በቀጣይነት የሚመከርባቸው መሆን ይገባቸዋል፡፡ ውሳኔዎችም በተሟላ ዴሞክራሲያዊ አኳኋን የሚወሰኑ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የምክር ቤቱ አባላት፣ በተለይ ደግሞ በህብረተሰቡ ዘንድ የላቀ ተሰሚነት ያላቸው የምክር ቤት አባላት አቅጣጫውን በደንብ ያወቁት፣ ያመኑበት፣ በማሳቸውና በጓሮቸው ግንባር ቀደም ሆነው የሚፈፅሙት እንዲሆኑና ህዝቡን በማስተባበር በሚሰራው ስራ ላይ ግንባር ቀደም ተዋናይ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት መደረግ አለበት፡፡

የቀበሌ ምክር ቤት መድረኮች ከሌላውም የላቀ ግምት ሊሰጣቸው የሚገባው በቀበሌው ህዝብ ተቀባይነት ያላቸው ብዙ ሰዎች የሚሰባሰቡበት መድረክ በመሆኑ ብቻ አይደለም፡፡ ህዝቡን ወክለው የመወሰን ስልጣን ያላቸው ሰዎች የተሰባሰቡበት መድረክ ስለሆነ ጭምር እንጂ፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን የብዙሃን ማህበራት መድረኮችንም እንደ ትልቅ መድረክ መውሰድ የሚገባ ቢሆንም መንግስት ከሚያካሄደው የገጠር ልማት ስራ አኳያ ህዝቡን በማሳመንና አስተባብሮ በማንቀሳቀስ ረገድ ወሳኞቹ መድረኮች የቀበሌ ምክር ቤት መድረኮች ናቸው፡፡ የማሳመኑ ስራም በምክር ቤት አባላት ላይ ያነጣጠረ መሆን አለበት፡፡ የምክር ቤቱ አባላት ካመኑበት በኋላም በራሳቸው

www.abyssinialaw.com

ህጋዊ ውሳኔ እንዲያጠናክሩት ብቻ ሳይሆን፣ የህዝቡ አስተባባሪዎች ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ከዚያም ባሻገርና በወሳኝነት ራሳቸው በየጓሯቸውም ሆነ በጋራ ስራዎች ግንባር ቀደም ፈፃሚ ሆነ እንዲሰለፉ ማድረግ ላይ ነው ማተኮር ያለበት:: ህዝቡን በዋነኛነት በቀበሌ ምክር ቤቶች አማካኝነት ማሳመን፣ ማስተባበርና መምራት ሲባልም ይህ ነው::

የቀበሌ ምክር ቤቶች ቁጥር ምንም ያህል ቢጨምር መላውን የቀበሌውን አባወራ የሚያሳትፍ አይሆንም:: ከቀበሌ ምክር ቤት በመለስ በየመንደሩ በየጎጡ ወዘተ. ያሉ አባወራዎች የሚሰባሰቡበት መድረክም ሊኖር ይችላል:: እነዚህ ስብስቦች በቀበሌው ምክር ቤት ስር ሆነውና የቀበሌውን ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት በማድረግ የልማት ስራውን በየጎጡ በየመንደሩ በማስተባበር ስራ ላይ ከፍተኛ አስተዋፀኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ:: ከቀበሌ ምክር ቤቶች ቀጥሎ እነዚህን በመድረክነት መጠቀምና አሰራራቸውን በየጊዜው ማሻሻል ይቻላል፣ ይገባልም::

የቀበሌ ምክር ቤቶች የአካባቢውን ልማት በሚመለከት የመወሰን ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል ሲባል በዋነኛነት የአካባቢውን ህዝብ ጉልበትና የተፈጥሮ ሃብት የሚመለከት ውሳኔ መሆኑ አይቀርም:: ይሁንና መንግስት ቀዳዳዎችን ከመሸፈን የማያልፍም ቢሆን በየቀበሌው ለሚሰራው የልማት ስራ የተወሰነ ገንዘብ መመደቡ አይቀርም:: አገልግሎቶች ለመስጠት ከሚወጣው መደበኛ ወጭ በተጨማሪ የተወሰነ የልማት ወጭ መኖሩ አይቀርም:: ይህ ውሱን የገንዘብ አቅም መቼና በምን ስራ ላይ እንደሚውል የመወሰን ስልጣን እንኳን ቀበሌዎች ወረዳዎችም የላቸውም:: ይህ አካሄድ ተገቢ አይደለም:: በሂደት መንግስት ለየወረዳው ልማት የሚውለውን



ባጀት ለወረዳዎቹ ሰጥቶ፣ በአጠቃላይ መመሪያ ስር ሆነው ወረዳዎች አጠቃቀሙን እንዲወስኑ፣ ወረዳዎች በፈንታቸው ለቀበሌዎች የሚመደበውን የልማት ገንዝበ በጥቅሉ ከአጠቃላይ መመሪያ ጋር ለቀበሌ ምክር ቤቶች ሰጥተው የቀበሌ ምክር ቤቶቹ የቀበሌውን ጉልበት፣ ንብረትና ከመንግስት የተሰጠውን ገንዘብ በማጣመር በምን ስራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው እንዲወስኑ ማድረግ ይገባል:: የአብዛኛው የልማት ሃይል ባለቤት የሆነው የቀበሌ ምክር ቤት ቀዳዳ መሸፈኛ የሆነውን ገንዘብ ሊያዝበት አይችልም ማለት ተገቢ አይሆንም:: ስለሆነም ደረጃ በደረጃ አሁን ካለው አሰራር መሆን ወደሚገባው አሰራር መሸጋገር መቻል አለብን::

ለማጠቃለል ያህል ህዝቡን በዴሞክራሲያዊ መንገድ አሳምኖና አስተባብሮ በሰፊው በገጠር ልማት ስራ ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ ዋናው የአፈፃፀም አቅጣጫችን ይሆናል:: የገጠር ልማት አመራር ብቃት ዋነኛው መመዘኛም ይኸው ነው:: ህዝቡን ለማሳመንና አስተባብሮ ለመምራት ሰፊ የውይይትና የማስረዳት ስራ መስራት፣ ህዝቡ ከተጨባጭ ልምድ እየተነሳ የአቅጣጫውን ትክክለኛነት እንዲረዳ ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶችና ማትጊያዎችን መጠቀም በቀበሌ ነዋሪዎች መካከል፣ በወረዳ ነዋሪዎች መካከልና ከዚያም በላይ ሰፊ የልምድ ልውውጥና የመማማር መድረኮች እንዲኖሩ ማድረግ ያስፈልጋል::

ህዝቡን አሳምኖና አስተባብሮ ለመምራት ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ ብቃት ያላቸው የውይይት የውሳኔና ሰውን የማስተባበር ስራ የሚሰራባቸው መድረኮች መኖር ይኖርባቸዋል:: ከነዚህ መድረኮች ውስጥ ከገጠር ልማት አኳያ ዋናው ተደርጎ መወሰድ ያለበት የቀበሌ ምክር ቤትና አስተዳደር

ነው:: በመሆኑም ይህን ሃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት የሚያስችለው ባህሪ፣ አሰራርና ስልጣን እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል:: ከዚህ በተጨማሪ ብዙሃን ማህበራትም ነፃነታቸውና ዴሞክራሲያዊ ባህሪያቸው ተጠብቆ ለዚህ ስራ ከቀበሌ ምክር ቤት ቀጥሎ በዋና መድረክነት ማገልገል ይችላሉ::

## 2. ቁልፍ የገጠር ልማት ተቋሞችን ማጠናከርና በአግባቡ መጠቀም፣

የገጠር ልማት ስራን ለመምራት፣ ፖለቲካዊ አመራር ለመስጠት የሚመደቡት ሰዎች ጥቂቶች መሆናቸው አይቀርም:: ሁሉንም ነገር ራሳችን እንስራ ብለው ቢነሱ ምንም አይነት ጠቃሚ ስራ ሊሰሩ አይችሉም:: ይህ አካሄድ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚያስችልም አይሆንም:: ከዚህ በላይ መሪዎቹ በሁሉም የገጠር ልማት ስራዎች ላይ ሙያዊ ብቃት ሊኖራቸው አይችልም:: ስራዎችን ሙያዊ ብቃቱ ባላቸው ሰዎች አማካኝነት ለመስራትና ለማስተባበር ካልቻሉ አጥጋቢ ስራ ሊሰራም አይችልም:: በመሆኑም መሪዎቹ ቁልፍ የገጠር ልማት ተቋሞችን በመፍጠር፣ በማጠናከርና አቅጣጫ አስይዞ በማንቀሳቀስ ላይ ያተኮረ ስራ በመስራት ብቻ ነው ብቃት ያለው አመራር መስጠት የሚችሉት::

በገጠር ልማት ስራ ቁልፍ ሚና ያላቸው የፖለቲካ መድረኮች አሉ:: በዚህ ረገድ የቀበሌና የወረዳ ምክር ቤቶች፣ የብዙሃን ማህበራት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው:: እንደ የህብረት ስራ ማህበራት፣ የገጠር ባንኮች የመሳሰሉ ቁልፍ የኢኮኖሚ ተቋሞችም አሉ:: የገጠር ትምህርት ቤቶችና የስልጠናና ኤክስቴንሽን ማዕከሎች፣ የጤና ኬላዎችና የጤና



ጣቢያዎች ከማህበራዊ አገልግሎት አኳያ በቅድሚያ የሚጠቀሱ ናቸው:: የገጠር መንገድ፣ የመጠጥ ውሃና ሌሎችም ተቋሞች ይኖራሉ:: የገጠር ልማት ስራ በመሰረቱ በነዚህ አማካኝነት ነው የሚሰራው፣ በነዚህ አማካኝነት ነው ውሳኔው የሚወሰነውና የሚፈፀመው::

በመጀመሪያ ደረጃ የገጠር ልማት መሪዎች እነዚህ ተቋሞች እንዲፈጠሩና የተዋጣለት አሰራርና አደረጃጀት እንዲኖራቸው ለማድረግ እንደተቋሞቹ ባህሪ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ መስራት አለባቸው:: ከዚያ በኋላ በነዚህ ተቋሞች የሚሰሩ ሙያተኞች የተቋሞቹ ሃላፊዎች ዋነኛ የስራ አጋሮቻቸው መሆናቸውን ተገንዝበው እነዚህ በልማት አቅጣጫው ላይ የተሟላ ግልፅነት እንዲኖራቸው በጉዳዩ ላይ የተሟላ እምነት ይዘው በራስ ተነሳሽነት እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ቀጣይ የማሳመን ስራ መስራት አለባቸው:: በዚህ ላይ ተመስርተው ተቋሞቹ እንደባህሪያቸው በራሳቸው አሰራር የልማት እቅድ እንዲያወጡ መደረግ አለበት:: እቅዶቹ በተቻለ መጠን የሚደጋገፉ እንጂ እርስ በርሳቸው የማይጋጩ እንዲሆኑ ለማስተባበር ጥረት መደረግ አለበት:: በስራ አፈፃፀም ሂደት ችግር ሲያጋጥም በመገምገም ወይም ነፃ አካላት ከሆኑ እንዲገመግሙ በማበረታታት ጉድለቶችን ለማወቅ ጥረት ማድረግ አለባቸው:: ዋናው ነገር አመራር ማለት እነዚህን ተቋሞች ፈጥሮ፣ አጠናክሮ ስራዎችን በነሱ አማካኝነት መፈፀምና ማስተባበር እንደሆነ ተገንዝቦ ይህንኑ በጥብቅ ተግባራዊ ማድረግ ነው::

www.abyssinialaw.com

## 3. በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላትን ሚና መለየት ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ፣

የገጠር ልማት ስራ ከፌዴራል መንግስት ጀምሮ እስከቀበሌ መስተዳድር ድረስ ያሉት አካላት የሚሳተፉበት ሰፊ ስራ ነው፡፡ ይህን ስራ በሚፈለገው ደረጃ መፈፀም የሚቻለው በየደረጃው ያሉ የአስተዳደር አካላት ከገጠር ልማት አኳያ ሚናቸው ምን እንደሆነ በግልፅ ተለይቶ ሲቀመጥ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ በአንድ በኩል የስራ መደራረብ እየተጠፈረ ገንዘብና ጊዜ ይባክናል፡፡ አንዱ በሌላው ስራ ላይ ጣልቃ እየገባ፣ የሌላውን ስራ ለመስራት እየሞከረ የተዘበራረቀና ቅልጥፍና የሌለው ነገር ይሆናል፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ እርከን ሚናው ምን እንደሆነ አውቆ ስራውን በመስራት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ብቻ በቂ አይሆንም፡፡ ሁሉም የየራሱን ስራ ይስራ ሲባል ሁሉም የራሱ ስራ ምን እንደሆነ ያውቃል ማለት ብቻ ሳይሆን የሚያውቀውን የራሱን ስራ ለመስራት የሚያስችል አቅም ይኖረዋል ማለት ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም የገጠር ልማት አመራርን ለማሻሻል መደረግ ከሚገባቸው ለውጦች አንዱ እያንዳንዱ እርከን ምን እንደሚሰራ ተለየቶ እንዲቀመጥለት፣ ይህንን ለመስራት የሚያስችል አቅም እንዲኖረውና ይህንን መሰረት አድርጎ ሁሉም የየራሱን ስራ እንዲሰራ ማድረግ ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ እያንዳንዱ ወረዳ ባለው በፍጥነት ለምቶ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የተፈጥሮና ሰብአዊ ሃብት ደረጃ ላይ የተመሰረተ የአመራር አቅም ሊመደብለትና ይህም አቅም አካባቢውን በአፋጣኝ ለማልማት በሚያስችል ደረጃ ብቃት እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡



በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት የየራሳቸውን ስራ በብቃት በመስራት ላይ ያተኩሩ ስንል ተነጣጥለው ይስሩ ማለታችን አይደለም፡፡ የሁሉም አላማ አንድ ነው፡፡ ይኸውም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የገጠር ልማትን ማረጋገጥ ነው፡፡ እርስ በርሳቸው ተደጋግፈውና ተቀናጅተው ካልሰሩ በስተቀር የሚፈለገው ውጤት ሊገኝ አይችልም፡፡ በመሆኑም የገጠር ልማት ስራችን አመራር እንዲሻሻል ለማድረግ በየእርከኑ ያሉት የመንግስት አካላት በመደጋገፍና በቅንጅት የሚሰሩበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

እያንዳንዱ አካል የየራሱን ስራ ይስራ ብለን ስናበቃ ተመልሰን ሁሉም አካላት በመደጋገፍና በቅንጅት ይስሩ ስንል ሁለቱ አባባሎች የሚጋጩ ሊመስሉ ይችላሉ፡፡ በርግጥም በሁለቱ አባባሎች መካከል ያለው ትስስር በሚገባ ካልተጨበጠ በስተቀር ግጭት የማይቀር ነው፡፡ ይሁንና እነዚህ ሁለት መሰረታዊ የአሰራር መርሆዎች የግድ የሚጋጩ ሳይሆኑ ተሳስረው የሚሄዱ ናቸው፡፡ የአንደኛው አካል ስራ ምን እንደሆነ ተለይቶ በሚቀመጥበት ወቅት የራሱን ስራ በመስራት ሌላውን የሚደግፍበት ስርአት መፍጠር ይቻላል፡፡ ተፈላጊው መደጋገፍ የሚረጋገጠው አንዱ በሌላው ስራ እየገባ ሳይዘበራረቅ የራሱን ስራ በመስራት አማካኝነት እንዲደግፍ በማድረግ ነው፡፡ ቅንጅትን በተመለከተም አንዱ አካል የሚያስቀምጠው እቅድ ቀጥሎ ላለው አካል የእቅድ መሰረታዊ መነሻ እየሆነ በማገልገል የሚፈጠር ቅንጅት ነው መሆን ያለበት፡፡

እነዚህን መሰረታዊ መርሆዎች መነሻ በማድረግና የገጠር ልማት እንቅስቃሴ የመጨረሻው ፈፃሚ በሆነው የቀበሌ መዋቅር በመጀመር አፈፃፀሙ ምን መምሰል እንዳለበት ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ በየቀበሌው የሚሰሩ የልማት ስራዎችን በሙሉ እነዚህን

www.abyssinialaw.com

ስራዎች ለማስፈፀም ህዝቡ በጉልበትም ሆነ በሌላ መንገድ ምን አይነት አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ የመወሰን፣ ህዝቡን የማሳመንና የማስተባበር ስራ በመሰረቱ የቀበሌው ምክር ቤትና የቀበሌው አስተዳደር ስራ ነው መሆን ያለበት። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰውም በሂደት ለቀበሌው ተብሎ የሚመደብ የልማት በጀት ካለም በምን ስራ ላይ መዋል እንዳለበት የመንግስትን አጠቃላይ መመሪያ መሰረት በማድረግ መወሰን ያለበት ቀበሌው ስለሆነ በሂደት ወደዚህ አሰራር መግባት መቻል ይኖርብናል። ህዝቡን ከማነሳሳትና ከማስተባበርም በተጨማሪ በቀበሌው በልማት ስራ ላይ የተሰማሩ ተቋሞች የራሳቸው ነፃነትና አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ ሊያስተባብራቸው የሚገባው የቀበሌው መዋቅር ነው።

በአሁኑ ወቅት በየቀበሌው ያለን አደረጃጀትም ሆነ የሰው ሃይል አቅም ይህንን ስራ ሊሰራ የሚችል አይደለም። በመሆኑም በተቻለ ፍጥነት ሊደረስበት የሚገባ ግብ ነው። የአካባቢው ሁኔታው በፈቀደው ፍጥነትና መጠን ወደዚህኛው አሰራር መሸጋገር አለብን ከማለት አልፈን በአሁኑ ወቅት በሁሉም ቦታዎች በዚህ መልክ ይፈፀም ማለት አይቻልም። ሁኔታው በፈቀደው መጠን ከወዲሁ ለማስተካከል ከሚሰራው ስራ ጎን ለጎንና በዋነኛነትም ይህን ለማድረግ የሚያስችል አቅም የመገንባት ስራን በከፍተኛ ደረጃ ማፋጠን ይኖርብናል።

ቀበሌው ስራውን በሚሰራበት ወቅት የወረዳ አመራር ድጋፍ ማግኘትና በወረዳ ደረጃ ከሚቀመጠው እቅድ ጋር የተያያዘ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ቀበሌው የራሱን ስራ ራሱን ችሎ መስራት ያለበት ቢሆንም በቀበሌ ልማት ላይ እንድምታ ያላቸው ከአቅሙ በላይ የሆኑ ስራዎች መኖራቸው አይቀርም።



ለምሳሌ የገጠር መንገድ ስራን ብናይ መንገዱን የመቀየስ አቅም በየቀበሌው ሊኖር አይችልም። መንገዱ በአንድ ቀበሌ ብቻ የታጠረም አይሆንም። በርካታ ቀበሌዎችን የሚያስተሳስር በቀበሌው ሊቀየስ የማይችል መንገድ ሲሆን ወረዳው ነው የቅየሳ ስራውንና የመንገዱን ይዘት መወሰን ያለበት። ቀበሌው ይህንን መሰረት አድርጎ ቀበሌውን በበለጠ የሚጠቅመው መንገዱ በየት ሲያልፍ እንደሆነ አስተያየቱን ሊሰጥ ይችላል። ከዚያም በላይ መንገዱን በመስራት ረገድ የቀበሌው አስተዋፅኦ ምን እንደሚሆን ሃላፊነቱን እንዴት እንደሚወጣ ማስቀመጥ ይኖርበታል። ሃላፊነቱንም መወጣት ይኖርበታል። ከተሰራ በኋላ የመንከባከብና የመጠገኑን ስራም ራሱን ችሎ ይሰራል፣ ይህን በተመለከተ ከወረዳ የሚቀርብለትን አጠቃላይ መመሪያና ቴክኒካዊ ድጋፍ መሰረት አድርጎ ይንቀሳቀሳል።

ወረዳው ለቀበሌው የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ በመስጠትና ከቀበሌው አቅም በላይ የሆነውን ስራ ራሱ በመስራት ድጋፍ ይሰጣል። ወረዳው የወረዳውን ልማት በተመለከተ አጠቃላይ አቅጣጫዎች ያስቀምጣል፣ ቀበሌው ይህንን መሰረት አደርጎ ይሰራል። የወረዳ አመራሩ በወረዳ ተፈፃሚ የሚሆኑትን የልማት እቅዶች አጠቃላይ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ ብቻ ሳይወሰን ከመንግስት ባጀት በተጨማሪ በወረዳው ውስጥ ከልዩ ልዩ የሃብት ምንጮች የሚገኙ የልማት አቅሞችን ያስተባብራል። በዚህ ረገድ አንዱ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ በወረዳ ውስጥ የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የልማት አቅም አቀናጅቶ ለወረዳው የልማት እቅድ ማስፈፀሚያነት ማዋል ነው። የአገር ውስጥና የውጭ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያላቸውን ሃብትና እውቀት በአግባቡ መጠቀም፣ ይህን ለማሳካት እንዲቻል ደግሞ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በልማት

www.abyssinialaw.com

ስትራተጅው ላይ የተስተካከለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ ከዚህ የልማት ስትራተጅ የሚፈልቀውን የወረዳውን የልማት እቅድ እንዲያውቁትና በነሱ በኩል ለእቅዱ ተፈፃሚነት ሊያበረክቱት የሚችሉትን አስተዋፅኦ ለይተው እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ በመጨረሻም በእቅዱ መሰረት እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታውን ማመቻቸት ይገባል፡፡ በዚህ ብቻ ሳይወሰንም መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ለወረዳው ልማት ከሌሎች ምንጮች ሊያሰባስቡት የሚችሉትን ተጨማሪ ሃብት በቀጣይነት እንዲያሰባስቡ ጥረት ማድረግ ይገባዋል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳ አመራሩ ሌላው መሰረታዊ ስራው ቀበሌን በፋይናንስና በቴክኒክ ማገዝ፣ አጠቃላይ መመሪያዎችን መስጠትና ከቀበሌው አቅም በላይ የሆኑትን ስራዎች መስራት ስለሆነ የራሱ የሆነውን ይህን ስራ ይሰራል፡፡ የራሱ የሆነውን ስራ በመስራት ቀበሌውን ይደግፋል፣ የቀበሌዎች ስራ በወረዳ ደረጃ ከሚሰራው ስራ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ቀበሌውም ይህንን ድጋፍና አጠቃላይ መመሪያ መሰረት አድርጎ ስራውን ይሰራል፡፡ የራሱን ስራ በተቀመጠለት አቅጣጫና ከወረዳ የሚሰጠውን እገዛ መሰረት አድርጎ ሲሰራ ቅንጅቱም ድጋፉም ይሟላል፡፡ የገጠር መንገድ ስራን በምሳሌነት ጠቅሰን ያስቀመጥነው መርህ በሁሉም ስራዎችና እርከኖች ሊሰራ የሚችልና የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም ይህንኑ ከመደጋገም ከቀበሌ በላይ ያሉት መዋቅሮች ስራ ምን መሆን እንዳለበት በመዘርዘር ላይ እንወሰናለን፡፡

የገጠር ልማትን በተመለከተ ዋነኛው የአመራር አካል ወረዳ ነው፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን፣ የግብርና ማሰልጠኛና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተቋሞችን፣ የገጠር



የመጠጥ ውሃና መንገድ ስራዎችን ወዘተ. በበላይነት መምራትና ማስተባበር ያለበት ይኸው መዋቅር ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው መርህ መሰረት ቀበሌዎችን መምራት መደገፍና ማስተባበር ያለበትም ወረዳው ነው፡፡ ከበላይ አካላት በሚደረግለት ድጋፍ የቀበሌ አመራሮችንና መዋቅሮችን አቅም የመገንባት ስራ መስራት ያለበት ይህው የአስተዳደር እርከን ነው፡፡ የወረዳውን ገጠሮች ልማት አጠቃላይ እቅድ የማውጣትና የማስፈፀም ስራም የሱ ነው፡፡

ወረዳው ይህን ስራ በብቃት ለመፈፀም የሚችለው ጠንካራ ተቋሞች መፍጠር ከቻለ ነው፡፡ የገጠር መንገድ፣ የመጠጥ ውሃ፣ የኤክስቴሽን ማስተባበሪያ፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማስተባበሪያ ወዘተ. ተቋሞች በየወረዳው ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ ወረዳው እነዚህን ይዞ ነው ስራውን መስራት የሚችለው፡፡ የገጠር ልማቱን ስራ በበላይነት ለመምራት የሚያስችለው በቂ ስልጣንና አደረጃጀትም ሊኖር ይገባል፡፡ አሁን ያለን አቅም ከዚህ አኳያ በመነሻነት ሊያገለግል ካልሆነ በስተቀር በተሟላ መልኩ የተባለውን ስራ መስራት የሚችል አይደለም፡፡ ባለው አቅም ስራውን በተቀመጠው አቅጣጫ መጀመር ይቻላል፣ ይገባልም፡፡ በሂደት የወረዳው የማስፈፀም አቅም እየጎለበተ ሲሄድ አሰራሩ ይበልጥ እየጠራና እየተስተካከለ ይሄዳል፡፡ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ያለው አመራር ለገጠር ልማት ስኬታማነት ያለውን ቁልፍ ሚና ግምት ውስጥ ያስገባ የነዚህን መዋቅሮች አቅም የመገንባት፣ የመንከባከብና ስራቸውንና አሰራራቸውን በየጊዜው እየገመገሙ የማስተካከል ስራ ልዩ ግምት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

ከወረዳ መዋቅር ቀጥሎ በገጠር ልማት ስራ ላይ የላቀ

www.abyssinialaw.com

ሚና የሚኖረው የክልል መንግስት ነው:: የክልል መንግስት ከገጠር ልማት አኳያ የሚሰራው ዋናው ስራ የቀበሌና የወረዳ አስተዳደሮችን አቅም መገንባት ነው:: በዚህ ደረጃ የፖለቲካ አመራር የሚሰጡ ተቋሞችን የማደራጀትና የአመራር አቅማቸውን በቀጣይነት የማሻሻል ስራ የክልል መስተዳድር ነው:: ዞኖች በክልሉ አስተባባሪነት በዚህ ስራ ላይም ሊሳተፉ ይችላሉ:: በቀበሌና ወረዳ የሚሰሩ ሙያተኞችን የማሰልጠን፣ የማሰማራትና የማሳደግ ሃላፊነት የክልል ነው:: በተለይ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚሰለጥኑትን በተመለከተ የፌዴራል ሃላፊነት ቢሆንም ከሰለጠኑ በኋላ የመመደብና የማብቃት ስራ የክልሉ ነው:: ክልሉ በፌዴራል ተቋሞች የሚቀርቡትን የግብርና እድገት ፖኬጆች መስረት በማድረግና ከክልሉ ልዩ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የክልሉን ፖኬጅ የማዘጋጀትና ለወረዳዎች የመስጠት፣ የማስረዳትና አፈፃፀማቸውን እየተከታተለ የማሻሻል ሃላፊነት አለበት:: የግብርና ግብይት ስርአትና የግብአቶችን አቅርቦት በተመለከተም በፌዴራል መንግስት አጠቃላይ እቅድ መሰረት በክልሉ በተሟላ መልኩ መፈፀሙን የማረጋገጥ ሃላፊነት የሱ ነው:: ለወረዳዎች የፋይናንስ ድጋፍ መስጠት፣ ከዞኖች ጋር በመሆን ከወረዳው አቅም በላይ የሆኑ የመሰረተ-ልማት ስራዎችን የመስራት ሃላፊነትም የሱው ነው::

በፌዴራል መንግስት ደረጃ የሚሰራው ዋናው ስራም የክልሎችን የገጠር ልማት አቅም መገንባት፣ ለዚህ ስራ ዩኒቨርስቲዎችንና የምርምር ተቋሞችን ማዘጋጀት፣ ቴክኒካዊና የፋይናንስ እገዛ መስጠት ነው:: አገር አቀፍ የቴክኖሎጅ ፖኬጆችን የማዘጋጀትና እነዚህን ከክልሎች ጋር በመተባበር ማሻሻልም የራሱ ስራ ነው:: የግብርና ግብይትና የግብአት አቅርቦት ስራዎችን በአገር አቀፍ ደረጃ ማስተባበርም የራሱ



ስራ ነው:: እነዚህን ስራዎች በክልሎች ጉዳይ ላይ ጣልቃ ሳይገባ በመመካከርና በመደጋገፍ ይፈፅማል::

## 4. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚኖር አመራር፣

የገጠር ልማት አመራርን በተመለከተ በአርሶ አደሩና በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች የሚመሳሰሉ ብዙ ነገሮች እንደሚኖሩ እሙን ነው:: ይሁንና አርብቶ አደሩ በተንቀሳቃሽነት የሚኖር ስለሆነ፣ የጎሳ አወቃቀርና ትስስር በዕለት ተዕለት ህይወቱ ውስጥ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳድር ስለሆነ የአመራር ስርአቱ ላይ ለውጥ ማስከተሉ አይቀርም::

ለምሳሌ ትምህርትን ብንወስድ አንድ አማራጭ አዳሪ ትምህር ቤቶች በማቋቋም ቤተሰብ ሲንቀሳቀስ ተማሪው ቋሚ ሆኖ እንዲኖር ማድረግ ነው:: ይህ አሰራር የራሱ ጠንካራ ጎን ቢኖረውም በጣም ውድ ነው:: ሌላው አማራጭ ትምህርት ቤቱም ከህዝቡ ጋር አብሮ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ነው:: ይህም የራሱ ጠንካራ ጎን ቢኖረውም የትምህርት ጥራት ላይ ተፅእኖ ሊያሳርፍ ይችላል፣ በተለይም ከፍ ባሉ የትምህርት ደረጃዎች ለመፈፀም አስቸጋሪ ነው:: ሌላው ህዝቡ በአንድ አካባቢ የሚሰፍርባቸው ወራትን በላቀ ደራጃ በመጠቀም በየሰፈረበት ቦታ ማስተማር፣ አባወራዎች ሲነቃነቁ ተማሪው ሊቀር የሚችልበት ዕድል ካለ መጠቀም ነው:: ሁሉንም በቅንጅት መጠቀምም ያስፈልጋል::

በአጠቃላይ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በተመለከተ የተለያዩ አማራጮችን እያቀናጁ መጠቀም አስፈላጊ ቢሆንም በዋነኛነት ረዘም ላሉ ወራት በሚሰፍርባቸው ቦታዎች ላይ

www.abyssinialaw.com

በማተኮር በነዚህ አካባቢዎች መስጠት፣ ተጠቃሚው በነዚህ ቦታዎች የሚሰፍርባቸውን ጊዜያቶች በላቀ ደረጃ ከመጠቀም በተጨማሪ ጊዜውን ለማራዘም መሞከር፣ ንቅናቄው በተቻለ መጠን በአባወራዎች ላይ የታጠረ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ነው፡፡

የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቱ በከብት ርቢ ላይ ያተኮረ መሆን ስላለበት የኤክስቴንሽን ሰራተኞቹም በዚህ ላይ ያተኮረ ስልጠና ነው ሊሰጣቸው የሚገባው፡፡ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱና ስልጠናው ህዝቡ በሰፈረባቸው ቦታዎችና ወራቶች ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተለይ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ደግሞ በተወሰነ ደረጃ ተንቃናቂ እንዲሆን ማድረግም ይችላል፡፡

የብዙሃን ማህበራትና የቀበሌ አደረጃጀትን በተመለከተም የግድ በአርሶ አደሩ አካባቢ እንዳለው መሆን አለበት ማለት አይደለም፡፡ ዋናው ነገር ህዝቡን በዴሞክራሲያዊ አኳኋን ለልማት ማንሳሳት መቻል ነው፡፡ ይህን ስራ በህዝቡ ጎሳዊ አደረጃጀት ማዕቀፍ ስር መስራት የሚበልጥ ሆኖ ከተገኘ በዚሁ አማካኝነት ሊሰራ ይችላል፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ጉዳይ በወረዳ ሆነ ከዚያ በላይ ባለው የፖለቲካ አመራር አደረጃጀት ላይም የራሱ ተፅእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ እዚህም ላይ እንደአስፈላጊነቱ ከሁኔታው ጋር አብረው የሚሄዱ ለውጦችን ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ከክልል ጀምሮ እስከ ዝቅተኛው እርከን ድረስ ያለው የሲቪል ሰርቪስ አሰራር ግን የተለመደውን የሲቪል ሰርቪስ አሰራር የተከተለና ተመሳሳይ የሙያ ብቃት ያለው ሆኖ መገንባት አለበት፡፡ ማስተካከያው የፖለቲካ አወቃቀሩ ላይ እንጂ የሲቪል ሰርቪሱን



ባህሪና ጥራት የሚነካ ጉዳይ ላይ ሊሆን አይገባም፡፡ እዚህ ላይ በአመራር ጉዳይ ላይ ሊታዩ የሚችሉ አማራጮችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ፅሁፍ ከዚያ በላይ መሄድም አይቻልም፡፡ ይህ ስራ እያንዳንዱ ክልል የየራሱን ሁኔታ ግምት ውስጥ አስገብቶ ሊሰራው የሚገባው ስራ ነው፡፡ እዚህ ላይ መሰመር ያለበት ዋናው ጉዳይ የፖለቲካ አመራሩና አደረጃጀቱ እንደየአካባቢው ሁኔታ ሊለዋወጥ እንደሚችልና መለዋወጥም ያለበት መሆኑ ነው፡፡

*ህዳር 23/1994*